የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የልዩ ልዩ የመንግሥት መ/ቤቶች

የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

ዓመታዊ ሪፖርት

ጥረዝ 1

ሚያዝያ/2006

አዲስ አበባ

ማውጫ

ገጽ

1. መግቢያ……………………………………………………………………1
2. ኦዲት በተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተገኙ

   ዋና ዋና ግኝቶች የተጠቃለለ ሪፖርት /Summery Report/…..……………4
3. የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በዘርፍ የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርት…….40

   3.1 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን……………………..….40

   3.2 የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች……………………………..…101

   3.3 የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች…………………………….………..118

   3.4 የልማትና ማህበራዊ አገልግሎት መ/ቤቶች…………….………...156

   3.5 የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች……………………………….......216

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የልዩ ልዩ የመንግስት መ/ቤቶች

የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

ዓመታዊ ሪፖርት

I. መግቢያ

የዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 101 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

- የፌዴራሉን መንግሥት ዕቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወጡት ሕጎች፣ በአስፈጻሚው አካል በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መሰብሰቡን፣ መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ፣
- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የፋይናንስ፤ የክዋኔ የአካባቢ ጥበቃ፣ የቁጥጥር ኦዲቶች ልዩ ኦዲቶችና ሌሎች ኦዲቶችን ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩ ለክልልና ለፌዴራል መንግሥት ሠራተኞችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ የሚመረመርበትን የኦዲት ደረጃ /ስታንዳርድ/ ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

ናቸው፡፡

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲችል የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግስታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎች ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል ወይም ያስደርጋል፣
- በፌዴራል መንግሥቱ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን ኦዲት ያደርጋል ወይም ያስደርጋል፣
- ማናቸውም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት እና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊው የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ምስክርነት ይሰጣል፣
- ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥትና የክልል መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል አስፈላጊውንም ቁጥጥር ያደርጋል፣
- ከክልል መንግሥታት የኦዲት መ/ቤቶች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፣
- ለግል ኦዲተሮችና የሂሳብ አያያዝ ሥራ ለሚያከናውኑ የሂሳብ አዋቂዎች በሥራው መስክ ለማሰማራት የሚያስችላቸውን የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣

ይህንኑ ስልጣን መሰረት በማድረግ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችን ኦዲት ለማከናወን ለፋይናንስና የህጋዊነት ኦዲት በእንጌጅሜነት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በ4 ዘርፍ በተደረጁ መ/ቤቶች፡- የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች፤ የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች፤ የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች እና የልማትና ማህበራዊ

መ/ቤቶች እና በ2 የክዋኔ ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች፤ እንዲሁም በክልል መንግስታት የተከናወነው የመሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ /PBS/ ተከታታይ ኦዲት ከማከናወን በ1 የድጋፍና ድጎማ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በመደራጀት የኦዲቱ ስራ ተከናውኗል፡፡

ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል እንዲሁም አንዳንዴም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት በዓለም አቀፍ ሂሳብ ኦዲት ደረጃዎች እና ኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሳብ መዛግብት እና ሰነዶች እንዲሁም የሂሳብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው::

በሪፖርቱ ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሃሳቦች፤ ኦዲት የተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን፣ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በመገምገም በተከታታይ ኦዲት በማድረግ የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ ነው::

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተከናወነው የኦዲት ሥራ እንዳለቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊዎች በኦዲት ግኝቶች ላይ የመውጫ ውይይት (Exit Conference) ከመደረጉ ሌላ የኦዲት ሪፖርቱ ለእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ የፌዴራል መ/ቤትና ተቆጣጣሪ መ/ቤት እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ለሥራ አመራር ሪፖርት መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን መልስና አስተያየት ያገናዘበ ነው::

መ/ቤታችን በሚከተለው የኦዲት ጊዜ አቆጣጠር ከጥር 1/2005 እስከ ታህሣሥ 30/2006 ዓ.ም የ132 በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ መደበኛና የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ የኦዲት እና 16 የልዩ ኦዲት ስራዎች በመከናወን የኦዲት ሪፖርቶቹ ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶችና ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል::

II. ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች

ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙት የጥሬ ገንዘብና ሌሎች የአሰራርና የአፈፃፀም ጉድለቶች በርካታ ሲሆኑ፣ እነዚህ ጉዳለቶች በዚሁ ጥራዝ ከገጽ 40 ጀምሮ በየኦዲት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በተደራጁ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አንጻር የታዩት ዋና ዋና ግኝቶችና የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች ተጠቃለው ከዚህ በታች ቀርበዋል።

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ኦዲት

1.1. የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ5 መ/ቤቶች ብር 1,272,093.33 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት እንደሚገኝ ተውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-3 ተመልክቷል/

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል የሚታይ ልዩነት በ3 መ/ቤቶች ቆጠራው በብር 997,412.79 በማነስ ታይቷል። /ዝርዝሩ በአባሪ-4 ተመልክቷል/

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካና የታየው ልዩነት ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.2. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመት የታየባቸው መ/ቤቶች

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፤ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ24

መ/ቤቶች የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር አባሪ- 5/ሀ - ረ ተመልክቷል።/

ከሚታዩት ዋና ዋና የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያየዝ ጉድለቶች፣

- የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከመዝገብ (ሌጀር) ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣
- የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማያደርጉ/የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ተደርጓል ቢሉም ማስረጃ ያላቀረቡ/ መሆኑ፣
- የዋና ገንዘብ ያዥ የጥሬ ገንዘብ መቆጣጠሪያ መዝገብ አለማዘጋጀት፣
- በባንክ ሂሣብ ገቢ ለሆኑ ሂሣቦች የገቢ ደረሰኝ አለማዘጋጀትና አለመመዝገብ፣
- የተሰበሰበውን ገንዘብ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ አለማድረግ፣
- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ የማያዘጋጁ መ/ቤቶች መኖራቸው፣
- ለልዩ ልዩ ጥቃቅን ወጪዎች የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን ያለማስፈቀድ እና ከተፈቀደውም በላይ በሳጥን ማስቀመጥ ወይም በግኸር ሠራተኞች እጅ እንዲያዝ መደረጉ፣
- በካዝና እንዲቀመጥ ከተፈቀደው የጥሬ ገንዘብ በላይ ከፍተኛ ገንዘብ በሳጥን የሚያስቀምጡ መ/ቤቶች መኖራቸው፣
- በ18 መ/ቤቶች ከክፍያ መመሪያ ውጪ በመመሪያው ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ በጥሬ ገንዘብ ወይም በቼክ ወጪ የሚደረግ መሆኑ፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፣ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወቅቱ ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር፣ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በየወሩ እንዲዘጋጅ፣ እንዲሁም በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከቆጠራው ጋር በየወቅቱ ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2. የተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1. በደንቡ መሰረት ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኘባቸው መ/ቤቶች

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ፤ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዢ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጣናቀቅ ያዛል። ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ77 መ/ቤቶች ብር 877,045,264.30 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል። /ዝርዝሩ በአባሪ-6 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	82,677,520.64
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		239,453,035.85
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		295,347,277.92
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		259,567,429.89
ጠ/ድምር	ብር	877,045,264.30

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የግብርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጣና ማስተባበሪያ ብር 173,607,265.52፤ ውጭ ጉዳይ ሚ/ር 149,427,709.65፤ የትምህርት ሚኒስቴር ብር 100,298,362.09፤ የሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 97,146,944.59፤ ግብርና ሚ/ር ብር 77,744,994.72፤ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 32,153,328.69፤ ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ብር 26,671,151.92 እና የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 22,945,234.57 ይገኙበታል።

ይህ የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ ከዓመት ወደ ዓመት እየተንከባለለ በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ሲሆን፤ በተወሰኑ መ/ቤቶች መሻሻል የሚታይ ቢሆንም የአንዳንዶቹ እየጨመረ የሄደና በአብዛኛው ቀደም ባሉት ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ እንዲወራረድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም ሂሳቡ እንዲወራረድ ያልተደረጉ ናቸው።

ስለተሰብሳቢው ሂሳብ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ከሰጡት ምላሽ፤ የሀገር መከላከያ ሚ/ር ስለብር 18,708,030.10 በሰጠው መልስ በመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት በሂሳብ መደብ 4201 በተሰብሳቢ ሂሳብ ተመዝግቦ የሚገኘው ብር 11,593,098.46 ከሽግግር መንግስቱ ጀምሮ በተለያዩ የጦር ክፍሎች በነበሩት አባላት የጠፉና ገንዘቡንም ለማስመለስ ክፍሎቹ በተለያያ ምክንያት የፈረሱ ወይም የታጠፉ ወይም ወደ ሌላ የጦር ክፍል የተቀላቀሉ በመሆናቸውና አባላቱን ይዞ ገንዘቡን ለማስመለስ አብዛኛው በህይወት የሌሉ፣ በተለያየ ምክንያት ከተቋሙ የለቀቁ ወይም የተሰናበቱና አድራሻቸው የማይታወቅ በመሆኑ ለረጅም ጊዜ በዳይሬክቶሬቱ የሂሳብ ምዝገባ ላይ በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ ተመዝግቦ የሚታይና ከመዝገብ ለማሰረዝ በወጣው መመሪያ መሰረት ሂሳቡን ከመዝገብ ለማሰረዝ ደጋፊ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ላይ እንደሆኑ አስፈላጊው ሰነዶች ሲሟሉ ከመዝገብ እንዲሰረዝ ለሚመለከተው አካል የሚያቀርቡ መሆኑን፤

የሂሳብ መደብ 4210 በተመለከተ በማዕከል፣ በዕዞችና በዋና መምሪያዎች በተሰብሳቢ ከሚታየው ገንዘብ ውስጥ ብር 45,000,000.00 በመከላከያ የበላይ አካል ትዕዛዝ ከሰራዊት የደመወዝ ተመላሽ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ላይ ለዝቋላ ስቲል ሮሊን በ2004 በጀት ዓመት የተሰጠና በቀጣይ ድርጅቱ የሚመልሰው መሆኑን፡

የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ከተመለከተው የተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ብር 87,179,420.79 በ2005 በጀት ዓመት ውስጥ ብቻ የተከሰተ የተሰብሳቢ ሂሳብ መሆኑን፤ መ/ቤቱ ካለው የስራ ባህሪ (ዋናው መ/ቤት እና ሚሲዮኖች መካከል ካለው ርቀት አንፃር) እና የ3ኛ ወገን (የሌሎች መ/ቤቶች) ሂሳቦች ጭምር የሚያንቀሳቅስ እንዲሁም ለከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት የህክምና ወጪ ሽፍኖ እስከሚተካለት ድረስ ሰፊ ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ ወደ 2006 በጀት ዓመት የዞረ መሆኑን በ2006 በጀት ዓመት ክትትል ተደርጎ አብዛኛው የተወራረደ መሆኑን፤ ብር 102,430,856.14 ከአሁን በፊት ለረጅም ዓመታት ሲንከባለል የቆየና መ/ቤቱ በሂሳቦቹ ላይ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ባደረገው ከፍተኛ ጥረት ከተጠቀሰው ሂሳብ ውስጥ ብር 45,063,222.52 በ2006 በጀት ዓመት መወራረዱን፤ማስረጃ ከሌለው

ብር 4,674,501.18 ማስረጃወችን አሟልተው ከ3ኛ ወገን እንዲተካ በሂደት ላይ መሆኑን፣ ብር 14,000,691.61 ሊሰበሰብ የማይችል ሂሳብ ተብሎ በመ/ቤቱ በኩል ተለይቶ ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ እና ማስረጃ ከሌለው ቀሪው ብር 35,583,206.29 ረጅም ዓመታት የቆዩ ሰነዶች መሆናቸውን በቀጣይ ሂሳቡን ለማወራረድ በቂ ማስረጃ መኖሩን ለማረጋገጥ መ/ቤቱ ባቋቋመው የተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ አጣሪ ግብረ ሃይል እየተሰራ መሆኑን ገልጿል፡፡

ሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶችን በመጥቀስ ሂሳቡን ለማወራረድ ጥረት እንደሚያደርጉ በመግለጽ ለተላከላቸው የሥራ አመራር ሪፖርት በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቢን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2.2. በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች

- የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የዓለም አቀፍ ግዥ ለማከናወን በንግድ ባንክ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተበት ሂሳብ በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ የነበረበት ብር 84,853,734.49 በሂሳብ መደብ 5516 (በተከፋይ ሂሳብ) ተመዝግቦ በመገኘቱ፣
- በአዳማ ገቢ.ዎችና ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት በሀብት አስተዳደር በኩል(ለባንክ ኮድ 1961) በተዘጋጀዉ የ2005 በጀት አመት ሂሳብ መግለጫ ላይ ሪፖርት ለተደረገዉ በድምሩ ብር 52,385.47 ተሰብሳቢ ምንም አይነት ደጋፊ ሰነድ ሊቀርብላቸዉ አለመቻሉ፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ መሳየት ከሚገበው የሂሳብ ሚዛን ውጭ ያልተለመደ ሚዛን የሚታይባቸው፣ ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ባላንስ (Abnormal balance) የሚታይ ባቸው በ2 መ/ቤቶች ብር 21,996,154.14፣

- ተሳብሳቢ ሂሳቡን በሌላ የሂሳብ መደብ የመመዝገብ ሁኔታ በበርካታ መ/ቤቶች የሚስተወሉ፣በወጪ ተመዝግቦ እያለ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት የተደረገ ሂሳብ የተገኘባቸው በ2 መ/ቤቶች ብር 26,896,921.16 መገኘቱ፣
- በአብዛኛዎቹ መ/ቤቶች ለእቃ ግዥ ሰራተኞችና ሌሎች ሰራተኞች ቅድሚያ ክፍያ በተደጋጋሚ የሚሰጥ በመሆኑና በእያንዳንዱ የእቃ ግዥ ሰራተኛ ወይም ገንዘቡ የተከፈለው አካል ስም ተቀጽላ ሌጀር ባለመኖሩ ማስረጃ ቀርቦለት የተወራረደና ከሰራተኛው የሚፈለግ ቀሪ እዳ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥና ለይቶ ኦዲት ለማድረግ አለመቻሉ፤
- በተሰብሳቢ መያዝ የሚገበውን ሂሳብ አለመመዝገብ ወይም በሌላ ሂሳብ ላይ የመያዝና በታብሳቢ መያዝ የሌለበትን ሂሳብ የመያዝ ችግሮች ናቸው።

በመሆኑም ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ፤ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳቡ ማስረጃ እንዲቀርብለቸውና ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደራግለቸው፤ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. የገቢ ሂሳብ

3.1 በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ ለመሰብሰብ በሚደነግጉ አዋጆች ደንብና መመሪያዎች መሰረት ሳይሰበሰብ የተገኘ ሂሳብ

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ22 መ/ቤቶችና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤትና በስሩ ባሉ ዘጠኝ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 32,139,625.90 በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ

መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 8 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር 28,616,571.03
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	159,489.90
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	3,159,540.92
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	204,024.05
ድምር	ብር 32,139,625.90

በአዋጁ በመሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች፤ በምዕራብ አ. አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 11,583,879.14፣ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,588,619.20፣ በአዲስ አበባ ኤርፖሪት ቅ/ጽ/ቤት ብር 3,469,351.03 እና በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 3,223,745.32 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፤ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S.Code) እና Coustom Procedure Code (CPC Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በትክክለኛው የትራንስፖርት የመጫኛ ማራገፊና ኢንሹራንስ ወጪ ለቀረጥ ማስከፈያነት ባለመወሰዱ ምክንያት ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው ያልተሳበሳበ የንግድ ትርፍ ግብር እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፤ የተጨማሪ

እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች ወሳኝ ስለሆነ፤ ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል።

3.2 ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤትና በስሩ ባሉ አምስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፤ ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው ብር 286,818,836.06 እና በሌሎች 4 መ/ቤቶች ብር 39,856,103.92 በድምሩ ብር 326,674,939.98 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል።/ዝርዝሩ በአባሪ-7 ተመልክቷል/

ገቢን በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት ብር 252,299,705.34፣ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ብር 36,389,175.05፣ አዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 19,512,045.63፤ በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት ብር 13,134,569.83፣ በጅማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 4,850,496.24 እና በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ብር 3,342,102.41 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በመሆኑም ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት ተገቢ እርምጃ በመውሰድ የመንግሥት ገንዘብ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ለየመ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል።

3.3 ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስር ባሉ ሶስት ቅ/ጽ/ቤቶችና በ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 42,942,143.14 እና በሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት/የ5

ዲክለራሲዮን/ና በሌሎች 5 መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ የገቢ ሂሳብ የገቢ ታሪፍ/የማስከፈያ ተመን ባለመኖሩ እና የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያትና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የገቢ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው፤ የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-9/ሀ ተመልክቷል/

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፤ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4 <u>የውስጥ ገቢን ሂሳብ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተቱ መ/ቤቶች</u>

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ5 መ/ቤቶች የሰበሰቡት የውስጥ ገቢ ብር 69,356,951.11 ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ- 10/ሀ ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	20,450,499.51
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		8,478,304.65
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		40,428,146.95
በድምር	ብር	69,356,951.11

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱት መ/ቤቶች አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ፤ በገንዘብ ያልተገለፀ የውስጥ ገቢ ሂሳብ በሪፖርት የማያካትቱ በ7 መ/ቤቶች/ዝርዝራቸው በአባሪ-10/ለ ተመልክቷል/ ከልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮች ገንዘብ የሚሰበስቡና ሪፖርትም የማያደርጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

ይህ አሰራር በመ/ቤቶች የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪም ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስበቸውን ገቢ ሕገዊ በሆነ መንገድ በታተሙ ደረሰኞች ብቻ በመጠቀም እንዲሰበስቡና የገቢን ሂሳብ በሂሳብ መግለጫዎችም በማካተት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.5 በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያልሆነ ወይም ዋስትናው ያልታደሰ መሆኑ

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 54 እና 55 መሰረት እቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸዉ በጊዜያዊነት ሊገቡ እንደሚችሉና በአዋጁ በተደነገገዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ተመልሰዉ ከአገር መዉጣት እንዳለባቸዉ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን እቃዉ አገር ዉስጥ የሚቆይበት ጊዜ ካልተራዘመ በስተቀር በህግ የተወሰነዉ የመቆያ ጊዜ እንደተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ዉስጥ እቃዉ ተመልሶ ካልወጣ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ በሙሉ ለመንግስት ገቢ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ በገቡ እቃዎች ላይ በህግ የተወሰነዉ የመቆያ ጊዜ የተጠናቀቀ ቢሆንም በዋስትና የተያዘዉ ገንዘብ በመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል ብር 2,840,773 እንዲሁም በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል ብር 219,683,687.83 በድምሩ ብር 222,524,461 ዋስትናውን ከሰጠው ድርጅት ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

3.6 ከየመኖሪያ ቤት አበል ግብር የማይቀንሱ መ/ቤቶቹ

በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 12/1 እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነፃ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማንኛውም ክፍያ ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት ደንቡ በሚያዘው መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ9 መ/ቤቶች ብር 1,580,533.99 የመኖሪያ ቤት አበል በጥሬ ገንዘብ ከሚከፈላቸውና መኖሪያ ቤት በአይነት ከተሰጣቸው መምህራንና ሠራተኞች ላይ የገቢ ግብር የማይቀነስ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-12 ቀርቧል/ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጽ/ቤት የመኖሪያ ቤት አበል በጥሬ ገንዘብ የሚከፍል ቢሆን ሊቀነስ የሚገበው ግብር በገንዘብ አልተገለጸም፡፡

መሰብሰብ ያለበት የመንግስት ገንዘብ በወቅቱ ሳይሰበሰብ ሊዘገይ ከመቻሉም በላይ ሳይሰበሰብ ሊቀር የሚችልበትም አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል፡፡

በመሆኑም የመኖሪያ ቤት አበል በጥሬ ገንዘብ ከሚከፈላቸውና መኖሪያ ቤት በአይነት ከተሰጣቸው ሂሳብ በህጉ መሰረት እንዲሰበሰብ ተገቢው ቁጥጥር መደረግ እንዳለበትና ያልተሰበሰበውም ሂሳብ ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.7 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ ተመዝግቦ ስለተገኘው ሂሳብ

የተመዘገበው ሂሳብ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት የሂሳብ መደቡን ጠብቆ መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ:-

በ2 መ/ቤቶች በተገቢው ሂሳብ መደብ ባለመመዝገቡ በተለያዩ በሂሳብ መደብ በድምሩ ብር 8,412,089.37 በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በ2 መ/ቤቶች ብር 255,389,061.56 የገቢን ሂሳብ በተከፋይ ሂሳብ የመዘገቡ መ/ቤቶች መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-11/ሀ እናለ ተመልክቷል/

የገቢ ሂሳብ በተገቢው የሂሳብ መደብ ካልተመዘገበ የሂሣብ ሪፖርት እና የአፈጻጸም ሪፖርት ትክክለኛውን መረጃ እንዳይሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አወቃቀር መሰረት ትክክለኛውን የሂሳብ መደብ ተከትሎ ሊመዘገብ እና የሂሳብ መግለጫውም ትክክለኛውን የገቢ አፈጻጸም በገቢው አይነቱ እንዲያሳይ ተደርጎ ሊስተካከል ይገባል፡፡

3.8 በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር

ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

3.8.1. <u>በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያልሆነ ወይም ዋስትናው ያልታደሰ መሆኑ</u>

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 54 እና 55 መሰረት እቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸዉ በጊዜያዊነት ሊገቡ እንደሚችሉና በአዋጁ በተደነገገዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ተመልሰዉ ከአገር መዉጣት እንዳለባቸዉ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን እቃዉ አገር ዉስጥ የሚቆይበት ጊዜ ካልተራዘመ በስተቀር በህግ የተወሰነዉ የመቆያ ጊዜ እንደተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ዉስጥ እቃዉ ተመልሶ ካልወጣ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ በሙሉ ለመንግስት ገቢ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ በገቡ እቃዎች ላይ በህግ የተወሰነዉ የመቆያ ጊዜ የተጠናቀቀ ቢሆንም በዋስትና የተያዘዉ ገንዘብ በመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል ብር 2,840,773 እንዲሁም በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል ብር 219,683,687.83 በድምሩ ብር 222,524,461 ዋስትናውን ከሰጠው ድርጅት ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 66 መሠረት በእቃዎች አያያዝ፣ በታሪፍ አመዳደብ፣ በዋጋ አተማመን ወይም በሌላ የሂሣብ አሠራር ስህተት ምክንያት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ በስድስት ወራት ውስጥ ለከፋዩ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት፣ በተጨማሪም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 35 መሠረት ለመንግሥት መ/ቤት በስህተት ገቢ የተደረገ ሂሣብ መኖሩ ሲረጋገጥ ገንዘቡ ለባለመብቱ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በናሙና ከታዩት ውስጥ ፡-
    - በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 976,135.67

- በቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ቤት ብር 14,056,107.58

በድምሩ ብር 15,032,243.25 ከሁለቱ ቅ/ጽ/ቤቶች በ2005 በጀት ዓመት ተመላሽ የተደረገው ሂሣብ አስቀድሞ በገቢ የተመዘገበና ለከፋዩ ተመላሽ የተደረገ ሂሣብ ማስተካከያ ሳይደረግበት በዘመኑ የተሰበሰበው ትክክለኛ ገቢ ጋር ተዳምሮ እየተመዘገበ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

➢ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001አንቀጽ17 (1) መሰረት አስመጪዉ ወይም ወኪሉ የጉምርክ ዲክላራስዮን ከቀረበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት ቀን ድረስ ቀጣዩን የጉምርክ ሥነ-ሥርዓት ካልፈፀመ ዲክላራስዮኑ እንዲሰረዝ ያዛል፡፡ ነገር ግን በጅጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ብር **883,692.79** ቀረጥና ታክስ የያዙ ዲክላራሲዮኖች ተመዝግበው ቀጣዩን የጉምሩክ ስነስርዓት ሳይፈጽሙ ወይም ሳይሰረዙ ከአንድ እስከ አራት አመት ቆይተዋል ፡፡

በመሆኑም የመንግስት ገቢ የወጡትን የገቢ ደንብና መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ እንዲከናወንና ለታዩትም ድክመቶች አስፈላጊውን ማስተካከያዎች በማድረግ በገቢው እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

3.8.2. የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች

የገቢ ሂሳብ የገቢ ደረሰኝ ተዘጋጅቶለት በትክክል መሰብሰቡን እና መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ6 መ/ቤቶች ብር 2,164,212.26 የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት ሂሳብ መገኘቱና በሌሎች 3 መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ ሂሳብ የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
ለገቢ ሂሳብ ደረሰኝ አለማዘጋጀት በሂሳቡ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር በማላላት ገንዘብ እንዲጣ ወይም እንዲጎድል መንገድ ይከፍታል፡፡

በመሆኑም ለተመለከተው ሂሳብ የገቢ ደረሰኝ እንዲዘጋጅለትና ሌሎችም ገቢ የሚደረግ ሂሳብ ደረሰኝ ተዘገጅቶለት መመዝገብ እንደሚገባ ለመ/ቤቶቹ አሳስበናል፡፡

3.8.3. የሌሎች የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች

ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ተመን ያላቸው ለመሆኑና ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ሲጣራ፣

- የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ብር 191,790,917.95 በጥሬ ገንዘብ፣ ብር 28,838,307.93 (ተሰብሳቢ) እና ብር 15,198,539.31 የባለድርሻ ተከፋይ በድምሩ ብር 235,827,765.19 ሪፖርት ያደረገ ቢሆንም ለህዝብ ተወካዮች ምክርቤት የባህል ቱሪዝምና መገናኛ ብዙሀን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በተላከው የ2005 ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መሰረት ደግሞ ብር 242,944,263.80 በመሆኑ በሁለቱ ሪፖርቶች መከካከል የብር 7,116,498.61 ልዩነት የሚታይ መሆኑ፣
- በ4 መ/ቤቶች ብር1,410,268.63 /ዝርዝሩ በአባሪ-9/ሐ ተመልክቷል/ ለመንግስት ገቢ መሆን ያለበት የጉዳት ካሳ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በ4 መ/ቤቶች ብር 18,281,997.57 በብድር ከተሰጡ የግንባታ ዕቃዎች ከክፍያቸው ተቀናሽ ያልተደረገ /ያልተሰበሰበ/ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-26 ተመልክቷል/
- አክሱም ዩኒቨርስቲ ቤተመፃህፍትና ኢንፎርሜሽን ማእከል ማባዣ ወረቀት በብር 1,029,940.00 ለህትመት ክፍል ከመደበኛ በጀት ተገዝቶ የተሰጠው ቢሆንም የተለያዩ የህትመት አገልግሎት ሰጥቷል ተብሎ በድምሩ ብር 1,305,483.70 የተከፈለ መሆኑ፣

- የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ለመኪና መጠለያ እና ማቆሚያ እንዲሰራለት ለኢንጂነሪንግ ኮሌጅ ብር 3,449,579.40 እና ተደራራቢ አልጋ እና ችፑድ እንዲሰራለት ለቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ኮሌጅ ብር 12,186,065.56 በጠቅላላው ብር 15,635,644.96 ድርጅቶቹ የራሳቸው የሆነ ህጋዊ ሰውነት ሳይኖራቸው እና እንደ ማንኛውም የንግድ ድርጅት ህጉ የሚጠይቀውን ሁሉ ሳያሟሉ የአገልግሎቱ ክፍያ የተከፈለ መሆኑ-የአርባምንጭ ዩኒቨርስቲ የውስጥ ገቢ የተለያዩ የውስጥ ገቢዎች ቋት ያልተቋቋመላቸው መሆኑ፣ በውስጥ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ላይ የገቢ ምክንያት በትክክል የማይመዘገብና አመዘጋገቡም የተደበላለቀ መሆኑ፣ ከትርፍና ኪሳራ መግለጫ ውጭ/Income Statement/ የውስጥ ገቢ ሂሳብ የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚገልጹና አግባብነት ያላቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ፣ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ማመዛዘኛ እና የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ የማያዘጋጅ መሆኑ እና በድምሩ ብር 97,237.00 ከመደበኛ ሥራ ውጪ ለሆነው የሳምንታዊ መጨረሻ መረሃ-ግብር የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም መምህራን ላስተማሩበት የውሎ አበል ክፍያ እና ለተከታታይ ርቀት ትምህርት ክፍል አገልግሎት የሚውሉ ቋሚ ዕቃ ግዥ ከመደበኛ በጀት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የገቢ አሰባሰብ፤ አፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ፤ እንድሁም በገቢ ደረሰኝ አያያዝ ረገድ የሚደረገው ቁጥጥር ሊጠናከር እንደሚገባ በሰጠነው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

4. የወጪ ሂሳብ

4.1 የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ23 መ/ቤቶች ብር 3,821,243,169.21 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -14 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፡

የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	ብር	1,253,009.52
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		87,524,454.65
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		3,732,485,705.04
ድምር	ብር	3,821,243,169.21

ማስረጃ ሳይኖር በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች ሀገር መከላከያ ሚ/ር 3,242,150,462.37 የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ብር 488,129,584.25፣ ጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 48,055,198.58፣ ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 10,258,169.0 እና አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 6,421,520.70 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለው ሂሳብ ሂሣብ ውስጥ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 3,242,150,462.37፤ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት 477,475,634.45፤ የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ ብር 17,778,644.44፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,258,169.01 እና መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ብር 2.66 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የደመወዝ ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ በበጀት ዓመቱ የተቀጠሩ በዝውውር የመጡ በጡረታ የተገለሉ እና በተለያየ ምክንያት የተሰናበቱ የሠራዊት አባላት ስም ዝርዝር ለኦዲት እንዲቀርብ ተጠይቆ መ/ቤቱ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን የሠራዊት ደመወዝ ወጪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዳልተቻለ፤ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልገሎትና በሥሩ የሚገኙ ዋና መመሪያዎች ለደመወዝ ወጪ ያደረጉት ሂሣብ ፔሮሉ በኮድ በመቅረቡ ኮዱን የሚገልጽ ማስረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው፤ ሌሎቹ የወጪ ሂሣቦች ለምሳሌ የመኪና ጥገና የነዳጅ ለማጣራት የመኪኖች ታርጋ የስልክ ቁጥሮችና የመሳሰሉት ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑት እንዲቀርቡ ተጠይቆ ከሚስጥራዊነት አንጻር ማቅረብ እንደማይቻል በኦዲት ወቅት መገለፁና የሌሎች

መ/ቤቶችም ክፍያ የተፈጸመባቸው ደጋፊ የክፍያ ሰነዶችና ማስረጃዎች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር በላከው መልስ ከመረጃው ሚስጥራዊነት አንጻር የተሰዉ የሰራዊት አባላትና አዲስ የተቀጠሩት ሠራዊት አባላትን ከደህንነት አንጻር ችግር ያለበት በመሆኑ፣ ለወደፊቱም ቢሆን እንደዚህ አይነት ሚስጥራዊ ሰነዶችን አሳልፎ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑ ተገልጿል፡፡

ተገቢውን ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ስለሚችል ባለጥቅሞቹ ገንዘቡ የደረሳቸው ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ለወደፊቱም ማስረጃዎች ወዲያውኑ እንዲቀርቡ ቢደረግ ሊያጋጥም የሚችልን ስጋትና አላስፈላጊ ወጪን ለማስቀረት ስለሚያስችል ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል::

4.2 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ25 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 202,587,739.10 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል:: /ዝርዝሩም በአባሪ -13 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	41,168,557.00
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		16,935,229.26
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		94,846,112.08
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		49,637,840.76
ድምር		202,587,739.10

ሆኖ ተገኝቷል::

ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚየሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፤ በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን የሚገልጽ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጎላ ያሉት ናቸው::

ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና ያልተሟላውም ማስረጃ እንዲሟላ በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልጻዋል፡፡

4.3 ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

ክፍያዎች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ41 መ/ቤቶች ብር 75,992,434.84 ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ - 16 ተመልክቷል/

ሒሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	8,386,094.52
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		39,385,056.45
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		3,343,916.45
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		24,877,367.42
ድምር	ብር	75,992,434.84

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ከተፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤

ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 24,000,000.00፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ 10,196,507.81፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ብር 8,605,050.51፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,190,691.01 ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,062,182.75 እና ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,956,941.47 ሲሆን፤ ከምክንያቶቹም ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በመፈጸም፤ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈልና የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የሃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ለዩኒቨርሲቲ የስራ አመራሮች ክፍያ መፈጸም፣ መ/ቤቱን ለቀቁ ሰራተኞች ክፍያ መፈጸምና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

ከዚሁ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት የቦርዱ ሰብሳቢ ስብሰባ ለመካፈል ላወጡት ወጪ በሚል ከውጭ አገር ከተመለሱ በኋላ ብር 7,744.00 በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ሲሆን ስብሰባው በ2004 የተካሄደና ክፍያው በዚያው በጀት ዓመት ከጉዞው በፊት በቅድሚያ መፈጸም ሲገባው ከበጀት ዓመቱ ውጪ በ2005 በጀት ዓመት በነሀሴ 12,2004 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ወጪውን ጋባዡ እንደሚችል የተገለፀ ሲሆን የ2 ቀን የአልጋና የቁርስ በዶላር 300 አላግባብ ተከፍሏል በወጪ ለተመዘገበውም ሂሳብ ማስረጃ አለመቅረቡ ታውቋል፡፡

በመሆኑም አፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ ስለሆነ፣ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት መመሪያ የተከተለ እንዲሆንና ያለአግባብ የተፈከለውም ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲሆን አሳስበናል፡፡

4.4 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች

የዕቃና አገልግሎት ግዠዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ43 መ/ቤቶች ብር 165,892,637.56 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-15 ተመልክቷል፡፡/ ሒሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር 3,695,461.41
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	133,397,807.60
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	23,025,417.90
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	5,773,950.65
ድምር	ብር 165,892,637.56

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፣ በሀርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 32,061,100.00፣ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 19,117,878.73፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ 18,344,467.23፣ ማዕድን ሚ/ር ብር 16,274,515.25 እና አክሱም ዩኒቨርሲቲ ብር 14,168,410.69 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ካልተከተሏቸው የግዥ ደንብና መመሪያዎች ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ያለጨረታ ማስታወቂያ በመግዛት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ /ኘሮፎርማ/ አማካኝነት መፈጸም ያለበትን

የግዥ ውድድር ሳይደረግ መፈጸም እና የተለያዩ ግዥዎችን ከአንድ አቅራቢ ብቻ መፈጸም የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ከመንግስት መመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቶቹን ጥራቱን ላልጠበቀ ዕቃና ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፣ የመንግስትን አዋጅ በማያከብሩ የመ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ላይም ተገቢው እርምጃ ሊወሳድ ይገባል፡፡

4.5 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆረጠለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ10 መ/ቤቶች በብር 22,557,742.81 የተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 18 እና አባሪ-19 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	ብር	20,934,660.55
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		115,990.87
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		1,507,091.39
ድምር	ብር	22,557,742.81

ከዚህም ውስጥ ትምህርት ሚ/ር ብር 19,231,147.66፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,597,312.92 እና ሀገር መከላከያ ሚ/ር 795,550.00 ለግዥ ወጪ ሆኖ የተገዛው ዕቃና የንብረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልተቆረጡት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ በተጨማሪም በ7 መ/ቤቶች ብር 1,557,178,357.45 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው ከዚህም ውስጥ በቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት ብር 785,919,809.52፣ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 549,166,140.13፣ ትምህርት

ሚኒስቴር ብር 157,971,920.15፣ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 48,756,934.71 ና በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ብር 10.08 ሚሊዮን ይገኙበታል፡፡

ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጠው ገንዘብ ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ መንግስት ለወጠው ወጪ ተመጣጠኝ አገልግሎት ስለመግኘቱ ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን የተገዘው ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡን የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.6 <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ</u>

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ13 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ብር 230,819,512.43 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 17 ተመልክቷል/ ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	ብር	17,913,138.82
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች		2,551,854.90
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		210,354,518.71
ድምር	ብር	230,819,512.43

ቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል የኢንዱስትሪ ሚኒሰቴር ብር 102,872,461.13 ፤ የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ብር 51,883,514.72፤ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ብር 43,983,869.27 እና የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ ብር 13.00 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፤ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ

እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርተችን አሳስበናል፡፡

4.7 በብልጫ የተከፈለ ወጪ

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፤ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ10 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግዢዎች ብር 1,943,820.40 እና በ6 መ/ቤቶች ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 2,527,401.22 በጠቅላላው ብር 4,471,221.62 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 23 ተመልክቷል/

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ዕደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፤ በድገሚ ወጪ በማድረግ ወይም ከተገበው ውል ውጭ በመክፈል፣ ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል እንዲሁም ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳይገኝ የቤት አበል የደመወዝ ጭማሪና ጥቅማ ጥቅሞችን መክፈል የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የግዢ ስርዓቱንና የወጡት ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው በብልጫ የተከፈለውም ወጪ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.8 የወጪ የሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ36 መ/ቤቶች ብር 20,642,389.47 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሣይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 22 ተመልክቷል/ ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	994,949.60
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		8,525,704.05
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		10,100,960.21
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		1,020,775.61
ድምር	ብር	20,642,389.47

የወጪ ሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል በኢንዱስትሪ ሚ/ር ብር 5,094,395.50፣ በአርባምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 3,629,095.64፣ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,110,536.44 እና በብሔራዊ ሜትዎሮሎጂ ኤጀንሲ ብር 2,202,009.47 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.9 <u>የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ</u>

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ13 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 4,397,136.41 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ በ2005 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -21 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	ብር	2,378,792.36
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		2,010,600.05
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		<u>7,744.00</u>
ድምር	ብር	<u>4,397,136.41</u>

ሲሆን ይህም የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት አመቱ የተገኘ አገልግሎት ወጪው በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.10 በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

የውስጥ ገቢ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸውን ያወጡትን ወጪና የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ/ ሁሉም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት የተካተተ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ4 መ/ቤቶች ብቻ ብር 35,562,617.39 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ/ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-20 ተመልክቷል/

ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ ያደርገዋል፤ በተጨማሪም ትክክለኛውን የመ/ቤቶቹን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችላል፡፡

በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.11 በመስክ ላይ ለነበሩ የግንባታ ዕቃዎች (Material on Site) ክፍያ የተፈጸመ ስለመሆኑ፤

በፌዴራል ግዥ አፈጻጸም መመሪያ በሳይት ላይ ያሉ ዕቃዎች በገንዘብ እንዲተካ የማይፈቀድ ቢሆንም በ11 መ/ቤቶች በሳይት ለሚገኙ ዕቃዎች ብር 168,570,095.60 ለተለያዩ ኮንስትራክሽን ድርጅቶች በገንዘብ አላግባብ እንዲተካ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከዚሁ ከግንባታዎች ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ግንባታዎች በሚያከናወኑ መ/ቤቶች በውል በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ግንባታውን በማያጠናቅቁት ተቋራጮች ላይ የጉዳት የካሳ ጥያቄ በውሉ መሰረት መቅረብ መ/ቤቶቹ ይህንን እንደማያደርጉ ተውቋል።

ለግንባታ የቀረቡ ግብዓቶች ስራ ላይ ሳይውሉ ክፍያ መፈጸሙና ተቋራጮች ክፍያ ሲፈጸምላቸው ቀደም ሲል የተሰጠቸው ብድር ሳይቀነስ ክፍያ መፈጸሙ ከውል በላይ ክፍያ እንዲፈጸም፣ የተሰጠ ብድርም እንዳይሰበሰብ ክፍተት ይፈጥራል፡፡

በመሆኑም ያልተሰበሰበው የግንባታ ግብዓቶች እንዲሰበሰብ የወሰዱትን ግንባታ በወቅቱ በመያጠናቅቁ ተቀራጮች ተገቢው የጉዳት ካሳ በውሉ መሰረት እንዲጠየቅና የግንባታ ስራዎት በመመሪያው መሰረት እንዲከናወኑ አስፈላጊ ክትትል እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.12 <u>በባለስልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ</u>

በወጪ ተመዘገበቡት ክፍያዎች ስልጣን በተሰጠው ኃላፊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ3 መ/ቤቶች በኃላፊ ሳይጸድቅ ብር 1,204,219.62 እና በ4 መ/ቤቶች ደግሞ ብር 25,708,880.80 ከተሰጣቸው ውክልና በላይ ወጪ አፅድቀው መገኘታቸው ተረጋግጧል፡፡

በዚህም ውስጥ ስለትክክለኝነቱ ወጪውን ባረጋገጠው ኃላፊ ያልተፈረመ፣ በጀት ስለመፈቀዱ የበጀት ሰራተኛ፣ሂሣቡን ባረጋገጠው ሰው ያልተፈረሙና ከተሰጠው ውክልና ባላይ የተፈረመ ይገኝበታል፡፡

አሰራሩ ከደንብና መመሪያ ውጭ በመሆኑና ለገንዘብ ብክነት ሊያገልጥ ስለሚችል ሊስተካከል እንደሚገበ አሳስበናል፡፡

5. <u>የተከፋይ ሂሣብ</u>

5.1. <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ</u>

በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ46 መ/ቤቶች ብር 471,620,351.75 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-28 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን	ብር	18,437,299.66
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		40,086,773.74
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		377,337,455.67
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		35,758,822.68
ድምር	ብር	471,620,351.75

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች ሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 221,664,033.96፤ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 148,635,332.93፤ በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ብር 21,255,177.05፤ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ብር 16,930,809.30፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,141,502.19 ፣ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,184,429.01 እናመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,995,439.11 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ በሌሎች መ/ቤቶችም የተከፋይ ሂሳቡ የሠራተኞች የጡረታ መዋጮንና በሌሎች የገቢ መሰብሰብ ግዴታዎች ምክንያት ተሰብስበው ለሚመለከተው አካል ያልተከፈሉትን ይጨምራል፡፡

በሀገር መከላከያ ሚ/ር በሰኔ 30/2005 የሂሳብ ሪፖርት በሂሳብ መደብ 5004 የደመወዝ ተከፋይ ብር 198,888,924.20 ደመወዛቸውን ባለመውሰዳቸው ለረጅም አመታት በተከፋይ የተያዘ መገኘቱንና የሂሳቡን ትክክለኛነ ለማረጋገጥ መ/ቤቱ ማስረጃዎቹን ለማቅረብ ፈቃደኛ ሆኖ አልተገኘም ፡፡ ይህ ሂሣብ በመንግሥት የሂሣብ አሠራር መሠረት ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ፈሰስ ተደርጎ ጥያቄው ሲቀርብ የገ/ኢ/ል/ሚኒስቴርን በመጠየቅ መከፈል ሲገባው ሂሣቡ በወጪ ተመዝግቦ ለዓመታት ሳይከፈል መቀመጡ ገንዘቡም ለምን ያህል ጊዜ ሳይከፈል እንደተቀመጠ ለማወቅ የማያስችል በመሆኑና ለብክነት እንዲጋለጥ የሚያደርግ መሆኑን በመጥቀስ ሂሣቡ ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ፈሰስ እንዲደረግ፣ ጥያቄው ሲቀርብ ክፍያ እንዲፈጸም አሳስበናል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚ/ር በዋናው መ/ቤት እና በሚሲዮኖች መካከል ባለው የቦታ ርቀት ሂሳቡን ለማወራረድ ጫና መፈጠሩን እና በ2005 በጀት ዓመት የተከሰቱ ተከፋይ ሂሳቦችን በከፍተኛ ጥረት በ2006 በጀት ዓመት እተወራረደ እንደሚገኝ፣ በ2006 በጀት ዓመት ብር 44,030,007.57 መወራረዱን ቀሪው ማስረጃ የሌለውን ብር 35,305,065.36 በተመለከተ ረጅም ዓመታት የቆዩ ሰነዶች መሆናቸውን በቀጣይ ሂሳቡን ለማወራረድ በቂ ማስረጃ መኖሩን ለማረጋገጥ መ/ቤቱ ባቋቋመው የተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ አጣሪ ግብረ ሃይል እየተሰራ መሆኑንና ሰነዶቹ ከተረጋገጡ በኋላ በግብረሃይሉ በቀረበው አስተያየት መሰረት እርምጃ እንደሚወሰድ ገልጿል፡፡

የሌሎችም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

5.2. <u>በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ድክመቶች</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የየመ/ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በውጭ ጉዳይ ሚ/ር ብር(3,098,228.89) በነገቲቭ (ዴቢት) የተመዘገበ ሂሳብ መኖሩ፣
- የብሄራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ከሚቲዎሮሎጅ መሣሪያ ሽያጭ የሰበሰበውን ገቢ ብር 1,507,619.00 በተገቢው የገቢ ሂሳብ ኮድ መሰብሰብ ሲገባው በልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳብ መደብ 5002 የመዘገበ በመሆኑ፣
- የወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 3,429,889.46 ለማን እንደሚከፈል ማስረጃ ያልቀረበ ሲሆን፣ ብር 203,666.66 ደግሞ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው ያለአግባብ በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ መገኘቱ፣
- የጅማ ዩኒቨርስቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ከተደረገው ውስጥ፣ በሂሳብ መደብ 5001(የችሮታ ጊዜ ተከፋይ) ብር 19,354,879.04፣ በሂሳብ መደብ 5002(ልዩ ልዩ ተከፋይ) ብር 20,693.91 እና በሂሳብ መደብ 5004(የደመወዝ ተከፋይ) ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ምዝገባ /Abnormal Balance/ ብር 187,311.07 ተይዞ መገኘቱ፤
- የትምህርት ሚ/ር በሂሳብ መደብ 5002 (ልዩ ልዩ ተከፋዮች) ብር 1,429,452.00፣ በሂሳብ መደብ 5005 (ሌሎች የደመወዝ ተቀናሾች) ብር 523,662.67 እና በሂሳብ መደብ 5054(ሌሎች የማያገሇ ሂሳቦች) ብር 595,830.20 በድምሩ 2,548,944,.87 ከ1995-1998 እየዞረ የመጣና በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ መገኘቱ፣
- የጎንደር ዩኒቨርስቲ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 2,407,178.29 የሆስፒታል

ማስያዣ ተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት የተደረገው የተከፋዩን ስምና አድራሻ፣ የተያዘው የገንዘብ መጠንና የቆየበት ጊዜ የሚገልጽ ሰነድ ወይም ተቀጽላ ቋት ባለመኖሩ ሂሳቡን በዝርዝር ኦዲት ለማድረግ አለመቻሉ፣

- በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት በሀብት አስተዳደር በኩል(ለባንክ ኮድ 1961) በተዘጋጀዉ የ2005 በጀት አመት ሂሳብ መግለጫ ላይ ሪፖርት ለተደረገዉ በድምሩ ብር 9,733.84 ተከፋይ ሂሳቦች ምንም አይነት ደጋፊ ሰነድ ሊቀርብላቸዉ አልቻለም፡፡

በዚህ አሰራር የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የተከፋይ ሂሳብ ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ምዝገባው ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ከላይ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ ደግሞ ተገቢውን ማጣራት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል።

6. የበጀት አጠቃቀም

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

6.1 ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ30 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ሥራ ላይ የዋለ ሂሳብ ብር 379,901,964.67 ተገኝቷል:: /ዝርዝሩም በአባሪ-29 ተመልክቷል::/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	122,199,033.46
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		232,478,062.87
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		8,601,312.79
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		16,623,555.55
ድምር	ብር	379,901,964.67

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች መካከል ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 96,047, 945.95፣ ሚዛን -ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 48,117,768.20፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 21.80 ሚሊዮን፣ ወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 44,200,479.61፤ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 40,633,615.89 እና አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 19,712,828.14 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም 9 መ/ቤቶች ብር 49,594,003.86 በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ሳይፈቀድ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ላይ ወጪ ያደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ ከመሆኑ በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክንና በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱም መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙም የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

6.2 ያልተሰራበት በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% ላይ የሆነውን ብቻ በመውሰድ በ96 መ/ቤቶች ብር 2,259,197,962.73 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-29 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	207,480,182.28
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		369,682,962.83
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		550,550,707.53
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶ		1,131,484,110.09
ድምር	ብር	2,259,197,962.73

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ብር 213,835,430.84፣ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 119,943,791.03፣ ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር 110,533,882.82፣ ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ብር 86,413,575.05 ፣ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ብር 68,490,363.94 የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ብር 62,189,884.33፣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር 66,166,058.74 እና ኢንዱስትሪ ሚ/ር ብር 53,393,010.81 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም ሌሎች መ/ቤቶች በመንግስት ተፈቅዶላቸው ሊጠቀሙበት የሚችሉትን በጀት እንዳይጠቀሙ ከማድረጉም በላይ የብቃት ማነስን (inefficiency) የሚያመለክት በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

7.1 የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች

ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	28 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	13 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	17 መ/ቤቶች
ቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ	32 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	23 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	47 መ/ቤቶች
ተያያዥነት ያለቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	16 መ/ቤቶች

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር

ድክመቶች፡ እንደሚገኙ በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-30 ተመልክቷል፡፡/

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው፡፡ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለአገልግሎት በየንብረት ክፍሉ ተከመችተው እያለ የተመሳሳይ ንብረቶች ግዥ የሚፈጽሙ መ/ቤቶችም መኖራቸው በኦዲታችን ወቅት ታይተል፡፡

ሌሎች የተለያዩ የንብረት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው መ/ቤቶች 34 መ/ቤቶች ዝርዝራቸው በአባሪ- 30/ሸ የተመለከተ ሲሆን፣ ችግሮቹ በየዘርፍ በንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ ሌሎች የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች በሚል ተገልጿል ፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፤አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንም በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7.2 ተሽከርካሪ

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ16 መ/ቤቶች	177 ተሽከርካሪዎች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ33 መ/ቤቶች	298 ተሽከርካሪዎች
በተለያዩ ድርጅቶች ሥም ሊቢሬ ያላቸው ወደ መ/ቤቱ ስም ያልተቀየረላቸው	በ7 መ/ቤት	25 ተሽከርካሪዎች
የሻንሲና ሞተር ቁጥር ከሊብሬው የማይገጥም፣	በ2 መ/ቤቶች	6 ተሽከርካሪዎች
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣	በ2 መ/ቤቶች	5 ተሽከርካሪዎች

መኖራቸው ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -31 ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ፤ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ/እንዲወገዱ፤ሊብሬ ያሌላቸው እንዲወጣለቸውና በሊብሬው ላይ የተገለጸው ቁጥር በሞተር ላይ ካለው የተለያየው ጉዳዩ ተጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

7.3 ነዳጅና የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የታዩ ችግሮች

የፋይናንስ ደኅንነት መረጃ ማዕከል:

- የማዕከሉ ተሽከርካሪ መኪናዎች ላልሆኑ በተለያዩ ቀናት ለሥራ አገልግሎት የዋለ የናፍጣና ቤንዝን ግዥ ተከናውኖ ተገኝቷል፡፡ ተሽከርካሪ መኪናዎቹም እንዴት እንደመጡና አገልግሎት ሊሰጡ እንደቻሉ ማስረጃ ሊቀርብ አለመቻሉ ታውቋል፡

- የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-12464 በቀን 30/10/04 ብቻ 326 ሊትር ነዳጅ የቀዳ መሆኑ፣

- ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ የነዳጅ መቆጣጠሪያ ጌጃቸው የሚሠሩ የዩኒቨርሲቲው መኪናዎች ወጥነት ባለው አሰራር የተጓዙበት ርቀት /ኪሎ ሜትር/ እየተሰላ እና እየተቀናነሰ በአግባቡ ነዳጅ መስጠት እንዲያስችል አንድ መኪና በሊትር ስንት ኪሎ ሜትር መሄድ እንሚችል የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

- የሠመራ ዩኒቨርስቲ በቅድሚያ ክፍያ እየተገዛ የሚመጣው የነዳጅ ኩፖን፤ ቅባትና ዘይት የገቢና ወጪ መከታተያ ካለመኖሩም በተጨማሪ በየወሩ ወይም በአንድ በተወሰነ ወቅት ሪፖርት የሚቀርብበት አሠራር የሌለ መሆኑ፡

- የጅማ ዩኒቨርስቲ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተሽከርካሪዎች የተሽከርካሪው ሰልቫትዮ /ታንከር/ ከሚይዘው በላይ በቀን ከ600-700 ሊትር ነዳጅ በድምሩ 4411.16 ሊትር እና ለጀነሬተር 15 ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ 1000 ሊትር የቀዳ መሆኑ፤

የአዲግራት ዩኒቨርስቲ፣ የአክሱም ዩኒቨርስቲ፣ የመቀሌ ዩኒቨርስቲ፣ የዋቻሞ ዩኒቨርስቲ፣ የወላይታ ዩኒቨርስቲ የነዳጅ መቆጣጠሪያ ጌጃቸው የሚሠሩ መኪናዎች አንድ መኪና በሊትር ስንት ኪሎ ሜትር መሄድ እንደሚችል የሚያሳይ በባለሙያ የተረጋገጠ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፣

የነዳጅ አጠቃቀምን ትክለኛነት ማረጋገጥ እንዲቻል የመንግሥት ተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያ ቅጅ መጠቀምና የነዳጅ ፍጆታ መቆጣጠር የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

8. ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ

ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ:–

በ22 መ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰዱ ሲሆን /ዝርዝሩ በአባሪ-32 ተመልክቷል/ እርምጃ ያልተወሰዱባቸው ነጥቦች በየመ/ቤቶቹና በየዘርፉ ዝርዝር ሪፖርት መጨረሻ ላይ ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ እርምጃ እንዲወሰድ ለሁሉም መ/ቤቶች በድጋሚ አሳስበናል።

9. ልዩ ልዩ

9.1. የ2005 በጀት ዓመት የቅርንጫፍ መ/ቤቶች በሂሳብ መግለጫ የታየው ጠቅላላ ሂሳብ ከተጠቃለለው የሂሳብ መግለጫ ጋር ሲነጻጸር ልዩነት መኖሩ

ግኝት

በ2005 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያሳወቀው የተጠቃለለ ሂሳብ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች ባቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች መሰረት የተዘጋጀ ለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተላከው የተጠቃለለ ሂሳብ መግለጫ

በተለያዩ የገቢ ሂሳብ መደቦች በማነስ ብር 38,761,015.97 የታየ መሆኑ ፤

- በተለያዩ የወጪ ሂሳብ መደቦች በመብለጥ ብር 3,001,218.85 ተመዝግቦ መገኘቱ፣
- በተለያዩ የተሰብሳቢ ሂሳብ መደቦች በመብለጥ ብር 2,051.31 የታየ መሆኑ ፤
- በተለያየ የተከፋይ ሂሳብ መደቦች ብር 1,149.70 በመብለጥ የታየ መሆኑ ፤
- በተለያየ የዝውውር የሂሳብ መደቦች በዴቢት ብር 11,958,683,009.62 በማነስ ብር 14,755,252,948.39 በመብለጥ እንዲሁም በክሬዲት ብር 35,671,892.76 በማነስ ብር 681,968.89 በመብለጥ የታየ መሆኑ ፤
- በ4101 እና 4103 ሂሳብ መደቦች የጥሬ ገንዘብ በመብለጥ በድምር ብር 149,668,608.49

የታየ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

ዋናው መ/ቤት ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ያቀረበው የተጠቃለለው የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን የተቋሙን የሂሳብ እንቅስቃሴ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

የባለስልጣን መ/ቤቱ ከየቅርንጫፍ መ/ቤቶች እና በዋናው መ/ቤት በቀረበው የሂሳብ መግለጫዎች መሰረት ትክክለኛ የሂሳብ ሪፖርት በማዘጋጀት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡አሁንም ለተገኙት ግኝቶች ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግ ይገባል፡፡

9.2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

- የሂሳብ ምዝገባ ከመ/ቤቱ ውጭ ባለ ሰራተኛ ምዝገባ የሚከናወን መሆኑ፤

- የሂሳብ ስራውን በሃላፊነት የሚሰራ ሰው ባለመኖሩ የተሰራውን የሂሳብ ስራ በአግባቡ ለኦዲት ስራ የሚያስረዳ ባለሙያ አለመኖሩ፤
- በአብዛኛው የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ(JV)ላይ ማዘዣው በሚጠይቀው መሰረት የሚመለከታቸው ሰዎች የማይፈርሙ መሆኑ::
- የሂሳብ ሠነዶች የፋይል አያያዝ ስርአቱን በጠበቀ ሁኔታ ባለመደራጀታቸው መረጃዎችን ለማግኘት በጣም አስቸጋሪ ሆኖ መገኘቱ፤
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በርካታ አላቂ እቃዎች ከንብረት ክፍል ወጪ ተደረገው በሐምሌ ወር/2005 መጀመሪያ ላይ ተመልሰው ገቢ ተደርጎ መገኘቱ፤

ታውቋል፡፡

በመሆኑም በከፍተኛ ፍ/ቤቱ ማስተካከያ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

9.3. በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸውን ያልተወጡ ሠራተኞችን በሚመለከት፤

- የጎንደር ዩኒቨርስቲ አፄ ቴዎድሮስ ግቢ በውጭ ሀገር ለትምህርትና ስልጠና ለተላኩ ብዛታቸው 32 የሚሆኑ መምህራን ለደሞዝና ጥቅማ ጥቅም እንዲሁም ለትምህርት ድጋፍ ብር 1,167,853.00 የተከፈለ ሲሆን መምህራኖቹ ትምህርታቸውን አጠናቀው በገቡት ውል መሰረት የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ባለመፈጸማቸው በዩኒቨርሰቲው ላይ ያደረሱት ጉዳትና ኪሳራ ተረጋግጦ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

- የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት ባልደረባ ሁለተኛና ሶስተኛ ድግሪያቸውን ኢንስቲትዩቱ በሰጣቸው የትምህርት ዕድል ውጭ ሀገር ካጠናቀቁ በኋላ በውሉ መሠረት ኢንስቲትዩቱን ባለማገልገላቸው የወጣባቸው 8,055.00 ብር የደመወዝ እና 21,827.00 ዶላር የትምህርት ወጪ ለኢንስቲትዩቱ ገቢ እንዲደረግ ለተወካያቸው ደብዳቤ የተጻፈ ቢሆንም ክፍያው ያልተፈጸመ /ያልተጀመረ/ መሆኑ፣

- **በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ በዩኒቨርሲቲው ወጪ ትምህርታቸውን የተከታተሉና ግዴጃቸውን ሳይወጡ ዩኒቨርሲቲውን የለቀቁ 63 ሰራተኞች ላይ እርምጃ ያልተወሰደ በመሆኑ፣**

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በውሉ መሰረት በተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል።

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
የ2005 በጀት ዓመት የሂሳብ መግለጫ ኦዲት
የስራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 669/2002 መሰረት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የ2005 በጀት ዓመት ሂሣብ በተጠቃለለ ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዋና መ/ቤት፣ የስምንት ቅ/ጽ/ቤቶችንና የማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

የሪፖርቱ አላማ

የዚህ ሪፖርት አላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ለማድረግ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI/ISA) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት የባለስልጣን መ/ቤቱ ባዘጋጃቸው የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ /የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

በዚህም መሰረት የባለስልጣን መስሪያ ቤቱን፣ 8 ቅ/ጽ/ቤቶችን (ማለትም የከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ የአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች፣ የምስራቅ አዲስ አበባ፣ የአዲስ አበባ ኤርፖርት፣ የድሬዳዋ፣ የሀዋሳ፣ የአዳማ፣ እና የአዲስ አበባ ወጪና ሌሎች እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤትን) እንዲሁም የተጠቃለለ የ2005 በጀት አመት የሂሳብ እንቅስቃሴ ኦዲት ተደርጓል፡፡

በኦዲቱም መሰረት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ቀጥለው ቀርበዋል::

የኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የዋና መ/ቤት የ2005 በጀት ዓመት የማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. <u>የገቢ ሂሳብ</u>

1.1 <u>የጉምሩክ ቀረጥና ታክስን በተመለከተ</u>

ሀ) <u>ድርጅቶች በትክክለኛው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መሰረት ባለመስተናገዳቸው ምክንያት በድምሩ ብር 2,626,409.47 ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ሂሳብ መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት አዘገጃጀትና ስርጭት አጠቃቀምን አስመልክቶ በወጣዉ መመሪያ ቁጥር 10/1996 መሰረት የገቢ ዕቃዎች ዋጋ ከጉምሩክ ሪከርድ መነሻ ዋጋ እና ማነጻጸሪያ ዋጋ አንፃር መመሳከር እንዳለበት እንዲሁም የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት፣አዘገጃጀት፣ስርጭትና አጠቃቀም አስመልክቶ የወጣዉን መመሪያ ለማስፈጸም በወጣዉ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 2/1996 አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡-

- በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ብር 2,230,019.58
- በአዲስ አበባ ኤርፖሪት ቅ/ጽ/ቤት ብር 307,286.4
- በሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ብር 89,103.49

በድምሩ ብር 2,626,409.4 ያልተሰበሰበ መኖሩን አረጋግጠናል፡፡

<u>ስጋት</u>

መንግስት ከገቢ እቃዎች መሰብሰብ ያለበትን ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበሰብ ያደርገዋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በትክክለኛዉ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክሱ ባለመሰብሰቡ ምክንያት ያልተሰበሰበው ሂሣብ ብር 2,626,409.4 ከሚመለከታቸው ድርጅቶች መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ገቢ እቃዎች ስራ ላይ ባለው የዋጋ ሲዲ መሰረት ቀረጥና ታክሱ የተሰላ

ለመሆኑ ችግሩ የታየባቸው ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

የሥራ አመራር አስተያየት

- አስያየቱን በመቀበል ያልተሰበሰበውም ገንዘብ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ለመሰብሰብ የሚያስችለውን መርህ ግብር ማዘጋጀቱንና ክትተል እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

ለ) ገቢ እቃዎች በትክክለኛው ታሪፍ ቁጥርና በትክክለኛው የጉምሩክ ስነስርአት ኮድ (cpc) ባለመስተናገዳቸው ምክንያት ብር 3,835,704.22 ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ

ግኝት

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2009 አንቀጽ 45/1 መሠረት ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ ማናቸውም ዕቃዎች ላይ የሚከፈል ቀረጥ በጉምሩክ የታሪፍ ደንብ በተወሠነው ምጣኔ መሠረት እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡

በዚህ መሠረት ገቢ እቃዎች ላይ ትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር ባለመመደባቸው ምክንያት፡-

- በአዲስ አበባ ኤርፖሪት ቅ/ጽ/ቤት ብር 692,367.75
- በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት ብር 3,418.15
- በቃለቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 491,799.21
- በጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 6,895.72
- በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ብር 178,623.93
- እንዲሁም በቃለቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል እቃዎች በትክክለኛው የጉምሩክ ስነስርአት ኮድ(cpc) ባለመስተናገዳቸው ምክንያት ብር 2,462,599.46 በድምሩ ብር **3,835,704.22** ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ተገኝቷል፡፡

ስጋት

እቃዎች በሀርሞናይዝድ ሲስተም ታሪፍ አተረጓጎም አጠቃላይ ደንቦች መሰረት የተመደቡ ለመሆኑ በሚመለከታቸው ሰራተኞች ተገቢው

ትኩረት እየተሰጠዉ ካልተመረመረ መንግስት ከገቢ እቃዎች ማግኘት ያለበትን ገቢ እንዲያጣ ያደርገዋል::

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በገቢ እቃዎች ላይ ትክክለኛው ምጣኔ ባለመጣሉ ምክንያት ያልተሰበሰበው የቀረጥና ታክስ መጠን ብር 3,835,704.22 ከሚመለከታቸው ድርጅቶች መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ የልዩነቱ መንስኤ በአብዛኛው በሚቀርበው የፍተሻ ውጤት መሰረት እቃዎቹ በሚመደቡበት ታሪፍ ቁጥር ላይ የሚያመጣውን ለውጥ በጥንቃቄ አለመመርመር በመሆኑ የሚመለከታቸው የቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ሰራተኞች ተገቢውን ጥንቃቄ ሊወስዱ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራር አስተያየት</u>

የሥራ አመራር የተሰጠውን አስተያየት በመቀበል ያልተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ሂሳብ ለመሰብሰብ የሚያስችለውን መርሀ ግብር ማዘጋጀቱን ገልፀዋል፡፡

ሐ) <u>ብር 2,811,291.73 ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ከጉምሩክ ክልል የወጣ እቃ መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት አዘገጃጀትና ስርጭት አጠቃቀምን አስመልክቶ በወጣው መመሪያ ቁጥር 10/1996 ማንኛውም በጉምሩክ ክልል የሚገቡ እቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ተሰልቶ መከፈል እንዳለበት በሚያዘው መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል በዲክላራሲዮን ቁጥር 24193/13 የተለያዩ የኤርኮንዲሽነር አባሪ እቃዎች ላይ ብር 2,811,291.73 ቀረጥና ታክስ መከፈል ሲገባው ክፍያ ሳይፈፀም ከጉምሩክ ክልል ወጥቶ ተገኝቷል፡፡

<u>ስጋት</u>

መንግስት ከገቢ እቃዎች መሰብሰብ ያለበትን ገቢ ሊያሳጣው ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የአዲስ አበባ ኤርፖሪት ቅ/ፅ/ቤት በመመሪያው መሰረት ሊሰበሰብ የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ብር 2,811,291.73 ከሚመለከተው አካል መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር በዋናው መ/ቤት በኩል በአፋጣኝ እንዲከፍሉ ውይይት እየተደረገበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

መ/ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያልሆነ ወይም ዋስትናው ያልታደሰ መሆኑ

ግኝት

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 54 እና 55 መሰረት እቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸዉ በጊዜያዊነት ሊገቡ እንደሚችሉና በአዋጁ በተደነገገዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ተመልሰዉ ከአገር መዉጣት እንዳለባቸዉ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን እቃዉ አገር ዉስጥ የሚቆይበት ጊዜ ካልተራዘመ በስተቀር በህግ የተወሰነዉ የመቆያ ጊዜ እንደተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ዉስጥ እቃዉ ተመልሶ ካልወጣ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ በሙሉ ለመንግስት ገቢ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ በገቡ እቃዎች ላይ በህግ የተወሰነዉ የመቆያ ጊዜ የተጠናቀቀ ቢሆንም በዋስትና የተያዘዉ ገንዘብ በመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል ብር 7,642,893.09 እንዲሁም በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል ብር 219,683,687.83 በድምሩ ብር 227,326,580.92 ዋስትናውን ከሰጠው ድርጅት ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

እቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው አገር ውስጥ ገብተው ሊቀሩ ይችላሉ፡፡ይህም መንግስት ከገቢ እቃዎች መሰብሰብ ያለበትን ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበስብ ያደርገዋል፡፡ ቀረጥና ታክስ ከፍሎ የሚንቀሳቀሰውን ነጋዴም የሚጎዳው ይሆናል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በአዋጁና በአፈፃፀም መመሪያው መሰረት በዋስትና የተያዘዉ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ መሆን አለበት፡፡ ለወደፊቱም በጊዜያዊነት በሚገቡ እቃዎች ላይ ተገቢዉ ቁጥጥርና እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

በአስተያየቱ መሰረት የዋስትና ጊዜያቸው ከማለቁ በፊት ዕቃዎች ከአገር ውስጥ እንዲወጡ ወይም ታክስ እንዲከፈል የሚያደርጉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ሠ) ትክክለኛው የትራንስፖርት የመጫኛ ማራገፊያና ኢንሹራንስ ወጪ ለቀረጥ ማስከፈያነት ባለመወሰዱ ምክንያት ብር 157,621.15 ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ.

ግኝት

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 39(4) መሰረት የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ሲወሰን ለእቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ላይ እቃዎችን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ ትራንስፖርት፤ የመጫኛ፤ የማራገፊያ፤ የመንከባከቢያና የኢንሹራንስ ወጪ ለእቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ላይ እንደሚደመር ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ትክክለኛው የትራንስፖርት ፣የመጫኛ ማራገፊያና የኢንሹራንስ ወጪ ለቀረጥ ማስከፈያነት ባለመወሰዱ ምክንያት፡-

- በአደማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል ብር 103,141.57
- በቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ብር   1,614.01
- በሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ብር 52,865.57 በድምሩ ብር 157,621.15 ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

መንግስት ከገቢ እቃዎች መሰብሰብ ያለበትን ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበሰብ ያደርገዋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ትክክለኛው የትራንስፖርት ፣የመጫኛ ማራገፊያና የኢንሹራንስ ወጪ ባለመወሰዱ ምክንያት ያልተሰበሰበው ጠቅላላ ቀረጥና ታክስ ብር 157,621.15 ከሚመለከታቸው ድርጅቶች መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ትክክለኛው የትራንስፖርት ፣የመጫኛ ማራገፊያና የኢንሹራንስ ወጪ ለቀረጥ ማስከፈያነት የተወሰደ ለመሆኑ የሚመለከታቸዉ ሰራተኞች ተገቢዉን ጥንቃቄ መዉሰድ ይኖርባቸዋል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ተገቢው ማስተካከያ በቀጣይ እንደሚያደርጉና ከሚመለከታቸው ድርጅቶችም የሚፈለገውም ቀሪ ሂሳብ እንደሚሰበሰብ ገልፀዋል፡፡

ረ) በደንብ መተላለፍ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ እንዲሁም በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ቡድን በኩል የተጠየቀ ተጨማሪ የጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ሂሳብ ብር 21,744,560.89 ሳይሰበሰብ ለረጅም ጊዜ የቆየ መሆኑ

ግኝት

የጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ እዳ የክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ ቁጥር 69/2004 አንቀጽ 7 መሰረት በኦዲት ልዩነት ለተገኘዉ ቀሪ ቀረጥና ታክስ የዉሳኔ ማስታወቂያ የደረሰዉ ባለእዳ በ 30 ቀናት ዉስጥ እዳዉን መክፈል ወይም ለመክፈል ከስምምነት መድረስ እንዳለበት ይህን በማይፈፅም ላይ ግን የንብረት መያዝ ስርአት ተፈጻሚ እንደሚሆንበት ይደነግጋል ፡፡

ከዚህ አንጻር የቀሪ ቀረጥና ታክስ የክፍያ ማስታወቂያ ከወጣ ከስድስት ወር እስከ አራት አመትና ከዚያ በላይ የሆነው ፡-

- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በኩል **ብር** 19,872,045.63
- በጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ብር 1,872,515.26 በድምሩ **ብር** 21,744,560.89 የሆነ ሂሳብ ቢኖርም ቀሪ ሂሳቡን ለመሰብሰብ ግን ምንም አይነት የንብረት መያዝ ስርአት እንቅስቃሴ ያልተካሄደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

በወቅቱ መሰብሰብ ሲኖርበት ያልተሰበሰበው ሂሳብ በቆይታ ብዛት መሰብሰብ የማይችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል መንግስት ማግኘት ያለበትን ገቢ ሊያሳጣው ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በወቅቱ ባልተከፈሉ የጉምሩክ ቀሪ ሂሳብ ላይ በመመሪያዉ መሰረት የንብረት መያዝ ስርአቱን ተፈጻሚ በማድረግ የመንግስት ገቢ እንዲሰበሰብ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል ፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

የንብረት የመያዝ ሂደት ግን በተቋም ደረጃ አቅጣጫ ያልተሰጠው እና በቅርንጫፍ ፅ/ቤትም ከዚህ በፊት ያልተጀመረ በመሆኑ በቀጣይ ንብረት ያዥ ኮሚቴ እንዲቋቋም እና ባልተከፈሉ ቀሪ ሂሳቦች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ግፊት የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

- ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት በሰጠው ምላሽ ቀሪ ሂሳቡ በመመሪያው መሠረት የሚሰበሰብ መሆኑን በመግለፅ በአሁኑ ጊዜ ኮሚቴዉ ተጠናክሮ እየተሰራ ይገኛል በማለት ገልጸዋል፡፡

ሰ) **<u>በበጀት አመቱ በተለያየ ምክንያት በስህተት ተሰብስቦ የነበረ በድምሩ ብር 15,032,243.25 የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ለባለመብቱ ተመላሽ ቢደረግም በሂሳብ መግለጫ ላይ የገቢ ሂሳቡ ሚዛን ግን የማይስተካከል መሆኑ</u>**

<u>ግኝት</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 66 መሠረት በእቃዎች አያያዝ፣ በታሪፍ አመዳደብ፣ በዋጋ አተማመን ወይም በሌላ የሂሣብ አሠራር ስህተት ምክንያት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ በስድስት ወራት ውስጥ ለከፋዩ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት፣ በተጨማሪም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 35 መሠረት ለመንግሥት መ/ቤት በስህተት ገቢ የተደረገ ሂሣብ መኖሩ ሲረጋገጥ ገንዘቡ ለባለመብቱ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በናሙና ከታዩት ውስጥ ፡-

- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር **976,135.67**
- በቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ቤት ብር 14,056,107.58 በድምሩ ብር 15,032,243.25 ከሁለቱ ቅ/ጽ/ቤቶች በ2005 በጀት ዓመት ተመላሽ የተደረገው ሂሣብ አስቀድሞ በገቢ የተመዘገበና ለከፋዩ ተመላሽ የተደረገ ሂሣብ ማስተካከያ ሳይደረግበት በዘመኑ የተሰበሰበው ትክክለኛ ገቢ ጋር ተዳምሮ እየተመዘገበ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በተለያያ ምክንያት በስህተት ተሰብስቦ የነበረው ገቢ ለባለመብቱ በዚያው በጀት ዓመት ተመላሽ ሲደረግ የገቢ ሂሳቡም በተመሳሳይ መልኩ ማስተካከያ ሊደረግለት ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

- ባለው አሰራር በስድስት ወር ውስጥ ደንበኛው በሚያቀርበው ማመልከቻ መሰረት በሀብት አስተዳደር የስራ ሂደት በኩል ተመላሽ የሚደረግ ስለሆነ የሂሳብ ሚዛኑን ለመስራት የሚያስቸግር በመሆኑ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የአሰራር ስርአት ቢበጅለት የተሻለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ሽ) ቀረጥና ታክሳቸው ብር 883,692.79 የሆነ ዲክላራሲዎች ተመዝግበው ነገር ግን ቀጣዩን የጉምርክ ሥነ-ስርዓት ያልተፈፀመባቸው መሆኑ

ግኝት

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001አንቀጽ17 (1) መሰረት አስመጪዉ ወይም ወኪሉ የጉምርክ ዲክላራስዮን ከቀረበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት ቀን ድረስ ቀጣዩን የጉምርክ ሥነ-ሥርዓት ካልፈፀመ ዲክላራስዮኑ እንዲሰረዝ ያዛል፡፡ ነገር ግን በጅጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ብር 883,692.79 ቀረጥና ታክስ የያዙ ዲክላራሲዮኖች ተመዝግበው ቀጣዩን የጉምሩክ ስነስርዓት ሳይፈጽሙ ወይም ሳይሰረዙ ከአንድ እስከ አራት አመት ቆይተዋል ፡፡

ስጋት

ተገቢው ክትትል ካልተደረገ በተመዘገቡ ዲክሌሬሽኖች ዕቃዎች በህገወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡

የማሻሻያ እርምጃ

ተመዝግበው ቀጣዩን የጉምርክሥነ-ሥርዓት ያልፈጸሙ ዲክላራሲዮኖች ሁኔታው ተጣርቶ እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

ያልተሰረዙት ዲክላራሲዮኖችን በተመለከተ በመመሪያው መሰረት እርምጃ እንደሚወሰድ ገልፀዋል፡፡

ቀ) ወደቀጥታ ገቢ ፈሰስ ያልሆነ የዋስትና ሂሳብ ብር 497,120.37 መኖሩ

ግኝት

የተመላሽ ሥርዓትና የገቢ ሂሳብ አስተዳደር የሥራ ሂደት ማኑዋል መሰረት ለቀረጥና ታክስ ዲፖዚት የተያዘ ሂሳብ ስድስት(6) ወር ከሞላው ወደ ቀጥታ ገቢ እንዲዞር መደረግ እንዳለበት ያዛል፡፡ ነገር ግን በጅጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች መረጃ መሰረት ብር 497,120.37 የዋስትና ሂሳብ ስድስት ወር አልፎት እያለ ወደ ቀጥታ ገቢ ያልዞረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

ወደቀጥታ ገቢ ፈሰስ መሆን ያለበት ገንዘብ በወቅቱ ፈሰስ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ከስድስት ወር በላይ የሆነው የዲፖዚት ሂሳብ የህግ ክርክር እስከሌለው ድረስ ወደ ቀጥታ ገቢ መዞር ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

የተገለፀውን ሂሳብ ፈሰስ እንደሚደረግ በኦዲት መውጫ ውይይት ላይ ገልጸዋል፡፡

በ) ከዋስትና ሂሳብ ብር 2,696,726.64 ለደመወዝ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ

ግኝት

በፌደራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል ስድስት አንቀጽ 34(2) መሰረት በመንግስት ስም የተሰበሰበ ማናቸውም ዓይነት የቀጥታ ገቢ ሂሳብ ወይም ከልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰበሰበው ገቢ በህግ በተለየ ሁኔታ እንዲሠራበት የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር በበጀት ዓመቱ ውስጥ በየጊዜው ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ወይም ተመላሽ መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ እንጻር ማንኛውም የዋስትና ሂሳብ ላይ ምንም ዓይነት ክፍያ የማይፈጸም

መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በጅጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ከዋስትና ሂሳብ (ከባንክ ሂሳብ ቁጥር 2918) ብር 2,696,726.64 ለደሞዝ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ የአመዘጋገብ ሁኔታውም 5051 (ተከፋይ) ዴቢት 4103 (ባንክ) ክሬዲት የተደረገ በመሆኑ ያልተከፈለን ሂሳብ እንደተከፈለ በማድረግ የተመዘገበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ያልተከፈለን የተከፋይ ሂሳብ እንደተከፈለ መመዝገቡ የተከፋይ ሂሳቡን የሚያሳንሰውና የተከፈለ የደመወዝ ሂሳብም ዝቅ እንዲል የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ አሰራሩም የፋይናንስ አዋጁን የሚጥስ ነው፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በ2005 በጀት አመት ዲፖዚት ሂሳብ ላይ የተፈጸመው የሥራ ማስከጃ ክፍያ ብር 2,696,726.64 ከመደበኛ በጀት ላይ መተካት የሚኖርበት ሲሆን ለሂሳቡም ማስተካከያ ምዝገባ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ለወደፊቱም ከአዋጅና ከመመሪያ ዉጪ ስራዎች እንዳይሰሩ የሚመለከተው አካል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

የቅ/ጽ/ቤቱ ስራ ባብዛኛው በኮንትሮባንድ መከላከል ላይ ያተኮረ ስለሆነ ይህን ስራ ደግሞ ፋታ የማይሰጥና እንድሁም ዋናው መ/ቤት በጀት በወቅቱ ባለመላኩ ምክንያት እንዳይስተጓጉል በማሰብ በቅ/ጽ/ቤቱ ከተሰበሰበው ሂሳብ ለተለያየ ክፍያ በጊዚያዊነት ወጪ አድርገን የተጠቅምን ቢሆንም በጀት ሲለቀቅ እንዲመለስ እናደርጋለን በማለት በኦዲት መውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

ተ) ለቀረጥ ማስከፈያነት የሚወሰደው የማስጫኛና የኢንሹራንስ ዋጋ በመመሪያ የተደገፈ አለመሆኑ

ግኝት

በአዲስ አበባ ኤርፖሪት ቅ/ጽ/ቤት በኩል የማስጫኛ (Airway bill) እና የኢንሹራንስ ሰነድ ሳይቀርብ ሲቀር ለማስጫኛ ዋጋ የዕቃውን ዋጋ 10 ፐርሰንት እና ለኢንሹራንስ ዋጋ የዕቃውን ዋጋናየማስጫኛ ድምር 5 ፐርሰንት ስሌት እየተሰላ ለቀረጥ ማስከፈያ እንደሚጠቀሙ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ይህን ስሌት ለመጠቀም የሚያስችል መመሪያ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

ስጋት

ያለመመሪያ መስራት ለብልሹ አሰራር ሊዳርግ ይችላል::

የማሻሻያ ሃሳብ

ስራዎች ሲከናወኑ መመሪያን መሰረት ያደረጉ ሊሆኑ ስለሚገባቸው መመሪያ ሊኖረው ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

ከዋናው መ/ቤትም ሆነ ከቅ/ጽ/ቤት ተፈልጎ እንዳልተገኘ አስረድተው በቀጣይ አዲስ በሚወጣው የመ/ቤቱ አዋጅ ውስጥ እንዲካተት ለሚመለከተው ክፍል እንዳስታወቁ ገልፀዋል፡፡

ቸ) አምራች ድርጅቶች እና የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅቶች /AEO/ ዲክሌር አድርገዉ በሚያቀርቡት ዋጋ መሰረት ከተስተናገዱ በኋላ ሰነዶቹ በድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ቡድን በኩል የማይመረመሩ መሆኑ

ግኝት

ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት በቁጥር 3.1.0/218/8 በቀን 27 ህዳር 2004 በተፃፈ ደብዳቤ መሰረት ፡-

1. አምራች ድርጅቶች ለምርት አገልግሎት የሚያዉሏቸውን ጥሬ እቃዎች እንዲሁም ማሽነሪዎች እና መለዋወጫዎች ወደ ሀገር

ዉስጥ ሲያስገቡ ዲክሌር አድርገዉ በሚያቀርቡት ዋጋ መሰረት እንዲስተናገዱ፤

2. የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅቶች /AEO/ እና የሁለተኛ መደብ ተጠቃሚ ድርጅቶች ወደ ሀገር ዉስጥ ለሚያስገቧቸዉ ማንኛውም አይነት እቃዎች ዲክሌር አድርገዉ በሚያቀርቡት ዋጋ እንዲስተናገዱ፤

3. ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 መሰረት መስተንግዶ ከተፈፀመ በኋላ የእቃ አወጣጥ ቡድን ለድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ማስተላለፍ እንዳለበትና ድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት አስፈላጊዉን ምርመራ በማድረግ ልዩነት ካገኘበት ቀሪ ሂሳብ እንዲሰበሰብ ማድረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ከዚህ አንፃር በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ፈጣን አገልግሎት ከመስጠት አንጻር የገቢ እቃ ቡድን ባቀረቡት ኢንቮይስ መሰረት መስተንግዶ ለሰጣቸዉ አምራች ድርጅቶች፤የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾችና ሁለተኛ መደብ ተጠቃሚዎች መረጃዉን ለድህረ እቃ አወጣጥ ቡድን የሚያስተላልፍ ቢሆንም በድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ቡድን በኩል በሰነዶቹ ላይ ተገቢዉ የዋጋ ማጣራት የማይደረግ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም ድርጅቶቹ በወቅቱ ስራ ላይ ባለዉ የሲዲ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ የከፈሉ መሆኑን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

ስጋት

ድርጅቶቹ በወቅቱ ስራ ላይ ባለዉ የሲዲ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ላይከፍሉ ይችላል፡፡ በመሆኑም መንግስት ከገቢ እቃዎች መሰብሰብ ያለበትን ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበስብ ያደርገዋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ፈጣን አገልግሎት ከመስጠት አንጻር የገቢ እቃ ቡድን ባቀረቡት ኢንቮይስ መሰረት መስተንግዶ ለሰጣቸዉ አምራች ድርጅቶች፤ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾችና ሁለተኛ መደብ ተጠቃሚዎች ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በተላለፈዉ ደብዳቤ መሰረት ድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ቡድን ድርጅቶቹ በወቅቱ ስራ ላይ ባለዉ የዋጋ ሲዲ መሰረት

ዲክሌር ለማድረጋቸዉ በሰነዶቹ ላይ ተገቢዉ የዋጋ ማጣራት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

ዝርዝር የአሰራር ስርአት ባለመኖሩ ምክንያት እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በድርጅቶቹ ላይ የተደረገ ምርመራ የሌለ ቢሆንም በተገለፀው መሰረት ዋጋ ይጣራ ቢባል እንኳን ድርጅቶቹ የሚያስመጧቸው የፋብሪካ ጥሬ እቃዎች በመሆናቸው ዋጋቸው በአብዛኛው ሲዲ ላይ የማይገኝና ለመስራት ውስብስብ ስለሆነ ግልፅ የሆነ የአሰራር መመሪያ ወጥቶ እንዲተገበር ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር መፍትሄ እንዲሰጥበት ግፊት የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

1.2 የአገር ውስጥ ገቢ ሂሳብን በተመለከተ

ሀ) በትርፍና ኪሳራ ሂሳብ መግለጫና በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ የተገለፀ ገቢ ልዩነት የሚታይበት በመሆኑ ምክንያት ብር 15,395,685.91 ግብርና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ

ግኝት

ግብር ከፋዮች ባቀረቡት መረጃ መሰረት በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው ጠቅላላ ሽያጭ በትክክል ወደ ትርፍ እና ኪሳራ ማሳወቂያ ላይ ማስተላለፋቸውን እና በዚህም መሰረት ግብርና ታክስ በትክክል ማሳወቃቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በንግድ ትርፍ እና ኪሳራ መግለጫ የተመለከተው የሽያጭ ሂሳብ በተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመለከተው የሽያጭ መጠን ጋር ልዩነት ያለው በመሆኑ ምክንያት፡-

- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በኩል 4 ግብር ከፋዮች ባቀረቡት የንግድ ትርፍ ማሳወቂያ ላይ የተገለጸው የአመቱ ጠቅላላ ሽያጭ/ገቢ/ ካቀረቡት የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያና ከቀረበው የሽያጭ ማጠቃለያ /z- report/ ጋር ሲነፃፀር በትርፍና ኪሳራ ማሳወቂያ ላይ የተመለከተው የአመቱ ጠቅላላ ሽያጭ/ገቢ/ ያነሰ በመሆኑ ምክንያት ያልተከፈለ የንግድ ትርፍ ግብር ብር 3,940,517.20 ተገኝቷል፡፡

- በጅማ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ብር 1,782.00 የንግድ ትርፍ ግብር ያልተሰበሰበ መሆኑ
- በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በኩል ብር 11,453,386.70 የንግድ ትርፍ ግብር ያልተሰበሰበ ሲሆን ባጠቃላይ ፡

ከሶስቱም ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 15,395,685.91 ግብርና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

መሰብሰብ የሚገባው ገቢ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል። ፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ከላይ የታየው ያልተሰበሰበው ግብርና ታክስ ከሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች ሊሰበሰብ ይገባል፡፡ለወደፊቱም ግብር ከፋዮች ያመኑበትን ግብር ከፍለው ከሄዱ በኋላ በግብር ከፋዮች የቀረበውን ማስረጃ ወዲያውኑ እንዲገናዘብ ተደርጎ ትክክለኛነቱ መረጋገጥ ይኖርበታል ።

የሥራ አመራሩ አስተያየት

ጉዳዩን በማጣራት ላይና በተሰጠው አስተያየት መሠረት ሂሳቡ ከድርጅቱ የሚሰበሰብ መሆኑን ገልጸዋል።

ለ) ተሰብስቦ ገቢ ያልተደረገ የተጨማሪ እሴት ታክስ በድምሩ ብር 1,085,205.44 መገኘቱ

ግኝት

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 20/1 መሠረት ግብር ከፋዮች የሰበሰቡትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት በወቅቱ ገቢ ማድረግ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በኩል 3 ድርጅቶች ካከናወኑት ግብይት ላይ በድምሩ ብር 1,085,205.44 የተጨማሪ እሴት ሰብስበው ገቢ ያላደረጉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል ።

ስጋት

በወቅቱ መሰብሰብ የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ ላይሰበስብ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በየወሩ ግብር ከፋይ ድርጅቶች የሚያቀርቡትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ዲክላሬሽን ከሽያጭ ማጠቃለያ (Z- report) ጋር በማመሳከር በማሳወቂያው ላይ ያልተገለጸ የሽያጭ መጠን ካለ ወዲያውኑ ማስተካከያ በማድረግ ግብሩ በወቅቱ እንዲከፈል መደረግ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም ተሰብስቦ ገቢ ያልተደረገውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የግብር ማስታወቂያ በመስጠት ከነመቀጫው መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

- የግብር ከፋዩቹ ለውስጥ ፍጆታ ለተጠቀመባቸው ዕቃዎች የሽያጭ ደረሰኝ አጠቃቀም ጋር ተያዘ ስህተት መሆኑና የተቆረጠ መሆኑ ማስረጃ ከደረሰኝ ህትመት የተፈጠረው ስህተት ማስተካከል /ሪፈንድ/ እንዲፈቀድላቸው የተጠየቀበትና ውሳኔ የሚጠብቅ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ሐ) ገቢ ያልተደረገ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከነመቀጫው ብር 8,246,720.86 መገኘቱ

ግኝት

የተጨማሪ እሴት ታክስ እየተሠላ ያለው በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 በሚደነግገው መሰረት መሆኑን ለማጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት 3 ድርጅቶች በየወሩ መክፈል የሚገባቸውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ያለ ማስረጃ ወይም ማስረጃው ከፋይል ጋር ተያይዞ ባለመቀረቡ ምክንያት ብር 8,246,720.86 የተጨማሪ እሴት ታክስ ከነመቀጫው ሰብስበው ገቢ ያላደረጉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

መንግስት ገቢውን በወቅቱ ማግኘት እንዳይችል ያደርጋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በግብር ከፋዮች የሚሞላውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ በየወሩ ለቅ/ጽ/ቤቱ ገቢ በሚያደርጉበት ጊዜ የተገለጸው የወሩ ተከፋይ ግብር እና የታክስ ተቀናሹ ካለፈው ወር ጋር በማገናዘብ ተከፋይ የተጨማሪ እሴት ታክሱ እና የታክስ ተቀናሹ (tax credit) ትክክል ስለመሆናቸው ማጣራት ወይም የታክስ ተከፋዩ እንዲቀንስ ወይም የታክስ ክሬዲቱ እንዲጨምር የተደረገበትን ትክክለኛ ማስረጃ እንዲያቀርቡ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም በኦዲት ግኝት መሰረት የተገለጸው ተሰብስቦ ገቢ ያልሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ለግብር ከፋዮቹ የግብር ማስታወቂያ በመስጠት ዕዳው እንዲሰበሰብ መደረግ ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

ልዩነቱ ተጣርቶ ግብር ከፋዩ ልዩነቱን እንዲከፍል ውሳኔ እንዲደርሰው መደረጉንና፣ የአዲስ አበባ ፎምና ፕላስቲክ ፋብሪካ በመጣራት ላይ ያለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

መ/ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 57,494.82 መገኘቱ

ግኝት

ግብር ከፋዮች የሰበሰቡትን የተጨማሪ እሴት ታክስ በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ላይ አሳውቀው ገቢ የሚያደርጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

▪ በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	ብር	21,630.32
▪ በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ		
ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት		35,864.50
በድምሩ ብር		57,494.82

ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተገኝቷል፡፡

ስጋት

መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ ሊያጣ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የስራ ክፍሉ ከላይ የተመለከተውን ያልተሰበሰበ ገቢ ከድርጅቶቹ መሰብሰብ እንዳለበትና ወርሃዊ የተ.እ.ታ. ማስታወቂያ በሚያረጋግጥበት ጊዜ በየወሩ በማስታወቂያው ላይ መሞላት ያለበትን የሽያጭ እና የግዢ መጠን ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥና ማጣራት ይኖርበታል ::

የሥራ አመራሩ አስተያየት

በልዩነት የሚታው ሂሳብ ተጣርቶ የሚሰበሰብ መሆኑን በመውጫ ውይይት ወቅት ገልጸዋል ::

ሠ) በወቅቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ ባላሳወቁ ላይ መቀጫና ወለድ ያልታሰበ መሆኑ

ግኝት

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ክፍል 7 ንዑስ አንቀጽ 26 ተራ ቁጥር 1ሀ እና እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 ከ ሀ እስከ ለ መሰረት በአንድ ሂሳብ ጊዜ ውስጥ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ባይሆንም በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ሂሳቡን ለታክስ ባለስልጣኑ ማሳወቅ እንዳለበት ይደነግጋል:: በተጨማሪ ግብር ከፋዮች በወቅቱ ማስታወቂያ ባለማቅረባቸውና አዘግይተው ክፍያ በመፈጸማቸው በአዋጁ 285/94 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 ሀ እና አንቀጽ 47 መሰረት መቀጫና ወለድ መክፈል እንደሚገባቸው ይደነግጋል :: በተጨማሪም መመሪያ ቁጥር 19/1997 አንቀጽ 9 ከ1-2 ለሰባራ ቡና በተወሰነው የብክነት መጠን ታሳቢ መደረግ እንዳለበት ይታወቃል። ስለሆነም ስራው አዋጁና መመሪያውን ተከትሎ መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በጅማ ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ማስታወቂያውን አዘግይተው ክፍያ የፈጸሙ ሁለት ግብር ከፋዮች ዘግይተው ለከፈሉት ተጨማሪ እሴት ታክስ በአዋጁ መሠረት መቀጫና ወለድ ያልከፈሉ መሆኑ ታውቋል ::

ስጋት

መሰብሰብ ያለበት ገቢ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል ።

የማሻሻያ ሃሳብ

በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያው ላይ የሚሰፍሩት መረጃዎች የየትኛው ወር እና ዓመት እንደሆነ በአግባቡ መጣራት ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ግብር ከፋዮች በወቅቱ ግብር የማይከፍሉ ከሆነ በህጉ መሠረት እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

በዓመታዊ ሂሳብ ማጠቃለያ ጊዜ ECX ካከናወነው ንጹህ ቡና ሽያጭ ላይ በተቀመጠው Rate የሰባራ ቡና የተጨማሪ እሴት ታክስ በራሳችን ስሌት (ግምት) ገቢ ሲሆን በኦዲት ወቅት ሽያጩ ከሶስተኛው ወገን ወይም ከግብር ከፋዩ በሚገኝ መረጃ መሠረት በዘገየበት ወለድና መቀጫ የሚታሰብበት መሆኑን ገልጸዋል ::

ረ) በግብር አወሣሠንና አሰባሰብ እንዲሁም በኦዲት የተጣለ ግብርና ቅጣት ብር 4,850,496.24 በወቅቱ ያልተሰበሰበ መሆኑ

ግኝት

በአጠቃላይ ኦዲት (Comprehensive Audit) ውሳኔ መሰረት ውሳኔ የተሰጣቸው ግብር ከፋዮች (ድርጅቶች) በውሳኔው መሰረት የግብር ዕዳቸውን በተሠጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ባልከፈሉት ድርጅቶች ላይ በገቢ ግብር አዋጅ 286/94 አንቀጽ 77 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት እርምጃ እየተወሰደባቸው መሆኑ ኦዲት ሲደረግ በጅማ ቅ/ጽ/ቤት 12 ድርጅቶች ብር 4,850,496.24 የተወሰነባቸውን ግብር ባለመክፈላቸው በአዋጁ መሠረት ህጋዊ እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

መሰብሰብ ያለበት ገቢ ወቅቱን ጠብቆ ካልተሰበሰበ ከቆይታ ብዛት የመንግሰት ገቢ መሰብሰብ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል::

የማሻሻያ ሃሳብ

በአጠቃላይ ኦዲቱ (Comprehensive Audit) ውሳኔ መሰረት የግብር ዕዳ ያለባቸው መሆኑ ከተረጋገጠና የውሳኔው ማስታወቂያ በደረሳቸው በ 10

ቀናት ውስጥ ቅሬታ ያላቀረቡ ከሆነ በህጉ መሰረት ውሳኔ በደረሳቸው በ 30 ቀናት ውስጥ ዕዳቸውን ካልከፈሉ ከላይ በተገለጸው አዋጁ መሰረት በድርጅቱ ላይ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

ድርጅቶቹ ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም በፋይላቸው ላይ ይህን የሚገልጽ ደብዳቤ ያልታሰረ መሆኑን ጠቅሰው ለወደፊቱ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ከፋይላቸው ጋር የቅሬታ ደብዳቤው እንደሚያያዝ ገልጸዋል ።

ሰ) የተጨማሪ እሴት ታክስን በወቅቱ ባለማሳወቃቸው ምክንያት ብር 123,260.00 ወለድና ቅጣት ያልታሰበ መሆኑ

ግኝት

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 ሀ እና አንቀጽ 47 መሰረት በወቅቱ በማያሳዉቁ ላይ መቀጫና ወለድ መከፈል እንደሚገባው ይደነግጋል። ነገር ግን በጅማ ቅ/ጽ/ቤት ስድስት ድርጅቶች የታክስ ማስታወቂያውን አዘግይተው ክፍያ የፈጸሙ በመሆኑ በአዋጁ መሠረት ብር 123,260.00 መቀጫና ወለድ ያልከፈሉ መሆኑ ታውቋል።

ስጋት

መሰብሰብ ያለበት ገቢ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል ።

የማሻሻያ ሃሳብ

ግብር ከፋዮች በወቅቱ ማስታወቂያ ባለማቅረባቸውና አዘግይተው ክፍያ በመፈጸማቸው በአዋጅ 285/94 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 ሀ እና አንቀጽ 47 መሰረት ያልተሰበሰበው መቀጫና ወለድ ሊሰበሰብ ይገባል። እንዲሁም ግብር ከፋዮች ወቅቱን ጠብቀው የታክስ ማስታወቂያ ስለማቅረባቸው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል።

የሥራ አመራሩ አስተያየት

- የኤች ኤዲ ኳየሪንግ ኃ/የተ/የግ ማህበር የህዳር እና የታህሳስ ማስታወቂያ በግብር አወሳሰን እንዲጣራ እና ተገቢው መፍትሄ እንደሚፈለግለት፣
- የራብዕ ወሊን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የውሳኔ ማስታወቂያ እንዲወጣለት እና እንዲከፍሉ በህጉ መሠረት እንዲፈጸም እንደሚያደርጉ እንዲሁም በወለጋ ዩኒቨርሲቲ ኢንጅ/ኢንተርፕራይዝ በተመለከተ የተገኘው ልዩነት ተገቢውን መመሪያ እና አዋጅ በተከተለው መሠረት እንዲስተካከል እንደሚያደርጉ ገልጸዋል።በመውጫ ውይይት ወቅትም የታክስ መሰብሰቢያ ጣቢያ ኃላፊ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ሂሳቡ ከየድርጅቶቹ የሚሰበሰብ መሆኑን ገልጸዋል።

ሸ) **አዋጅንና መመሪያን ያልተከተለ የመቀጫ አነሳስና አጣጣል በተመለከተ**

ግኝት

ማንኛውም ግብር ከፋይ አዘግይቶ በማሳወቁና ግብሩንም አዘግይቶ በመከፈሉ ምክንያት በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 4/ሀ እና አንቀጽ 47 ሀ እና ለ እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 17 መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በጅማ ቅ/ጽ/ቤት አዋጅና መመሪያ ባልተከተለ የመቀጫ አነሳስና አጣጣል ምክንያት ከ 3 ግብር ከፋዮች ብር 27,523.09 ሳይሰበሰብ የተገኘ መሆኑ፤

ስጋት

መሰብሰብ ያለበት ትክክለኛ ገቢ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡ እንዲሁም የመመሪያ ጥሰትን ያስከትላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የተጠቀሱት ድርጅቶች አዘግይተው በማሳወቃቸው ከላይ በተጠቀሱት አዋጆችና መመሪያዎች መሰረት በአጠቃላይ መሰበሰብ የነበረት ገቢ ከድርጅቶቹ እንዲሰበሰብ መደረግ ይኖርበታል።

የሥራ አመራሩ አስተያየት

በተሰጠው አስተያየት መሠረት ሂሳቡ ከድርጅቱ የሚሰበሰብ መሆኑን በመውጫ ውይይት ገልጸዋል።

ቀ) ትክክለኛው የቋሚ እቃዎች የእርጅና ቅናሽ ባለመወሰዱ ምክንያት ብር 94,627.94 የገቢ ግብር ያልተሰበሰበ መሆኑ

ግኝት

ከትርፍ ገቢ ግብር ማስታወቂያ ላይ ከጠቅላላ ትርፍ ላይ እንደወጪ የተቀነሰው የእርጅና ቅናሽ (depreciation) የተሰላው በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 ምዕራፍ1 ክፍል 4 አንቀጽ 23 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት በትርፍ ገቢ ግብር ማስታወቂያ ላይ በተቀመጠው የቋሚ እቃዎች መረጃ መሰረት የእርጅና ቅናሽ (depreciation) መቀነስ ሲገባ በምን ስሌት እንደተሰላ በማይታወቅ መልኩ የእርጅና ቅናሽ በወጪ ተቀንሶ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የበጀት አመቱን ትርፍ በብር 315426.47 አሳንሶታል እንዲሁም መሰብሰብ የነበረበትን የመንግስት የግብር ገቢ ብር 94,627.94 እንዳይሰበሰብ ከማድረጉም በላይ በአንዳንድ ድርጅቶች ማስታወቂያ ላይ ያለውን የበጀት አመቱን ኪሳራ በብር 54,983.43 ከፍ እንዲል አድርጎታል፡፡

ስጋት

መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ ሊያስቀር ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ወጪን በማጋነን ምክንያት ያልተሰበሰበውን የትርፍ ገቢ ግብር ገንዘብ መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

ድርጅቶች የሂሳብ መግለጫ ላይ አምነው ባሳወቁት መሰረት ተቀብለን በቀጣይ በኦዲት ወቅት በሚያቀርቧቸው መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የሚወሰን መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በ) <u>ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ብር 37,389.94 ገቢ ያልተደረገ ሂሳብ (ዊዝሆልዲንግ ታክስ) መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

በገቢ ግብር በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 53 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ግብር ከፋይ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ሁለት በመቶ/2%/ ቀንሶ ለግብር አስገቢው አካል ገቢ መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን ጠቅላላ ታክስ ከሚታሰብበት ገንዘብ ብር 3,476,398.27 ሁለት ፐርሰንት (2%) ብር 69,527.97 ተቀንሶ ገቢ መደረግ ሲገባ ብር 32,138.03 ብቻ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ በዚህም ምክንያት በአዋጁ መሰረት ለተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ለግብር አስገቢው አካል ገቢ መደረግ የነበረበት ሂሳብ ብር 37,389.94 ተቀንሶ ገቢ ሳይደረግ ቀርቷል፡፡

<u>ስጋት</u>

ሊሰበሰብ የሚገባው የመንግስት ገንዘብ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ሳይሰበሰብ የቀረው የመንግስት የግብር ገቢ ገንዘብ ተሰብስቦ ገቢ ሊደረግ ይገባል።

<u>የሥራ አመራሩ አስተያየት</u>

በኦዲት አስተያየቱ መሰረት ውሳኔ ተወስኖ ለግብር ከፋዮች እንዲደርስ መደረጉንና አቤቱታ ያቀረቡበት ሲሆን አጣሪ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት እንደሚፈጸም በኦዲት መውጫ ስብሰባ ወቅት አስረድተዋል፡፡

ተ) <u>የምዝገባ ማስተካከያ የተደረገበት ምክንያት የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበለት የገቢ ሂሳብ ብር1,469,265.75 መኖሩ ፡</u>

<u>ግኝት</u>

የምዝገባ ማስተካከያ የተደረገባቸው ሂሳቦች በሚመለከተው ሀላፊ እየተፈቀዱ የሚፈጸሙ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በምዕራብ

አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት በናሙና ከተመረጡ የሂሳብ ማስተካከያ የተደረገባቸው የሂሳብ እንቅስቃሴዎች ከምንዳ ደመወዝ የስራ ግብር፣ በዊዝሆልዲንግ/ቀጥ/፣ የዲቪደንድና ሎተሪ ገቢ፣ የከፒል ዕድገት ግብር፣ ሮያሊቲ፣በተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ተርንኦቨር ታክስ፣ እና ቅድመ ገቢ ግብር ውስጥ የብር 1,469,265.75 የማስተካከያ(Reverse) ምዝገባ ለምን እንደተደረገ የሚገልጽ ማስረጃ ሊቀርብ አልቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት በSIGTAS ላይ የማስተካከያ ምዝገባ የተደረገባቸው ሂሳቦች በተገቢው ሃላፊ የተፈቀዱና ተገቢ ማስተካከያዎች ስለመሆናቸው ማረጋገጥ አልታቻለም፡፡

ስጋት

በሲግታስ መረጃ ማስገቢያ ቁጥጥር (Input control) ትክክለኛ ምዝገባ እንዲከናወን ለማድረግ ያለው የመከላከል ብቃት ጠንካራ አለመሆኑን የሚያመላክት በመሆኑ ተመሳሳይ የምዝገባ ስህተት ሊፈጸም ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በምዝገባ ላይ ማስተካከያ በሚደረግበት ወቅት በተገቢው ሃላፊ መፈቀድና የማስተካከል ሃላፊነት በተሰጠው ሰራተኛ መከናወን ያለበት ሲሆን ምዝገባውን ለማስተካከል የተፈለገበት ምክንያትና ማስረጃ በአግባቡ ተደራጅቶ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

የሂሳብ ማስተካከያ ሲሰራ መነሻው ስህተት ስለመፈጠሩ ወይም ማስተካከያ እንደሚያስፈልገው ጉዳዩን ከሚመለከተው ቡድን /ሠራተኛ በቅጽ ተፈርሞ ማስተካከያው ከተደረገ በኋላ ገቢ ሂሳብ ቡድን ክፍል ይቀመጣል፡፡ ከአሁን በኋላ ግን ተመዝግቦ በማህደር ለማደራጀት በሂደት ላይ እንደሆኑና የስራ ሂደቶችም አጣሪ ኦፊሰር አረጋግጦ ከፈረመ በኋላ በቡድን/ኃላፊ ተፈርሞ ለማስተካከል በገቢ ሂሳብ ቡድን ማስተካከያ እንደሚደረግ፡፡ ሆኖም ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉትን ማስረጃዎች በ2 ቀን እንደሚያቀርቡ በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅት የገለጹ ቢሆንም ሊያቀርቡ አልቻሉም፡፡

ቸ) በመመሪያው መሰረት በግብር (ታክስ) እና በቀሪ የገቢ ግብር ላይ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ

ግኝት

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 77፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 31፣በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/95 አንቀጽ 10 እና በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308 አንቀጽ 13 መሰረት ግብር ከፋዩ የሚፈለግበትን ግብር/ታክስ ባለመክፈሉ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የግብር አስገቢው ባለስልጣን የግብር ከፋዩን ሀብት በመያዝ ለሚፈለግበት የግብር ታክስ እዳ እና ንብረቱን በመያዝ ለተደረገው ተጨማሪ ወጪ ለመሸፈን እንዲውል ማድረግ እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን በተጨማሪም በጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ እዳ የክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ ቁጥር 69/2004 አንቀጽ 7 (1 እና 2) መሰረት የቀሪ ቀረጥና ታክስ የውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ባለእዳ በ30 ቀናት ውስጥ እዳውን መክፈል ወይም ለመክፈል ከስምምነት መድረስ እንዳለበት የተመለከተ ሲሆን ነገር ግን በውሳኔ ማስታወቂያው ላይ ቅሬታ ያለው ባለእዳ ውሳኔው በደረሰው 15 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለባለስልጣኑ ማቅረብ እንደሚችል ይህንን በማይፈጽም ላይ የንብረት መያዝ ስርአት ተፈጻሚ እንደሚሆንበት ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በቀሪ ሂሳቡ ላይ ቅሬታ ያልቀረበበት እና ቀሪ ሂሳቡን ተመላሽ ለማድረግ የንብረት መያዝ ስርአት ተፈጻሚ ያልሆነበት በድምሩ ብር 15,437,605.67 ተገኝቷል፡፡

ስጋት

መሰብሰብ ያለበት የመንግስት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊቀር ከመቻሉም በላይ በታክስ ኦዲት ውጤት ላይ እርምጃ አለመውሰድ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

ከላይ የተመለከተው ያልተሰበሰበ የመንግስት ሂሳብ ሊሰበሰብ የሚገባ ሲሆን ለወደፊቱ በታክስ ኦዲቱ ውጤት መሰረት ክትትል እየተደረገ በማይከፍሉት ላይ ተገቢው እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል::

የሥራ አመራሩ ምላሽ

በኦዲተሮች አስተያየት ላይ ከተገለጹት መካከል ፡-

- ብር 2,254,845.70 በቴክኒክ ኮሚቴ እጅ በዋናው መ/ቤት የሚገኝ መሆኑ እና
- ቀሪው ብር 13,182,759.97 ደግሞ እርምጃ ተወስዶ ያልተሰበሰበበት ምክንያት በዋና መ/ቤት የተያዙና የተወረሱ ንብረቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በመቋቋሙ ጉዳያቸው ለንብረት መያዝ የደረሱትን እንድናሳውቃቸው እንጅ እንዲይዙ በመከልከሉ ንብረት ሳይዙ እያሳወቁ በመቆየታቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ነ) ብር 306,246.41 ያልተሰበሰበ የኤክሳይዝ ታክስ መገኘቱ

ግኝት

በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/95 አንቀጽ 6/2 መሰረት ለኤክሳይዝ ታክስ ግብር ከፋይነት የተመዘገቡት ግብር ከፋዮች ታክሳቸውን እየከፈሉ ስለመሆናቸው ኦዲት በሚደረግበት ወቅት በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በኩል፡-

- ከኬኬ ኃ/የተ/የግ/ማህበር (የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000011292 የሆነ) ብር 301,972.87 ያልተሰበሰበ መሆኑ
- ከኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ (የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000015706 የሆነ) ብር 4,273.54 በድምሩ ብር 306,246.41 ሳይሰበሰብ ቀርቷል ፡፡

ስጋት

መንግስት በወቅቱ ማግኘት የሚገባውን ገቢ እንዳያገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ግብራቸዉን በወቅቱ ማሳወቅ ሲኖርባቸዉ ባላሳወቁት ግብር ከፋዮች ላይ አስፈላጊዉን ማጣራት እና ክትትል በማድረግ በአዋጁ መሰረት ሊሰበሰብ የሚገባውን ገቢም ሆነ ሂሳባቸውን በወቅቱ ባለማሳወቃቸዉ ሊከፍሉ የሚገባቸዉን መቀጫና ወለድ እንዲከፍሉ ማድረግ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

በኬኬ ኃ/የተ/የግ ማህበር የታየውን ያልተከፈለ ዕዳ እንዲከፍል በቁጥር 0.2/2.5/10225/06 በቀን 18/04/2006 ደብዳቤ የደርሰው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ በተመለከተ በልዩነት የሚታው ሂሳብ ተጣርቶ የሚሰበሰብ መሆኑን በመውጫ ውይይት ወቅት ገልጸዋል::

ኘ) በተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ

ግኝት

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/2002 ክፍል ሦስት 13/9/ለ እንደተመለከተው ለታክስ ክሬዲት ሰነድ አግባብነት ያለውና ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ለይቶ የሚያሳይ በቂ መረጃ መቅረብ እንዳለበት ያዛል፡፡ ነገር ግን

- በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000047426 የቀረበው የሀምሌ/2004 ዓ.ም ብር 114,971.89 እና የነሐሴ/2004 ዓ.ም ብር 665,538.09 በድምሩ ብር 780,509.98 የተጨማሪ እሴት ታክስ የገቢ ማሳወቂያ ላይ ተቀናሽ የተደረጉ ግዥዎች የዕቃው ዓይነት በትክክል ስላልተገለፀ ግዥዎቹ ከድርጅቱ የሥራ ባህሪ ጋር ቀጥታ ግንኙነት እንዳላቸው ለማረጋገጥ ስላልተቻለ የተደረገውን ተቀናሽ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት አይ ቢኤም (የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0002607441) የሆነ ድርጅት ከሐምሌ /2004 ለተከታዩ ወር የሚታሰብ ተቀናሽ ሂሣብ ብር 342,377.47 ተቀናሽ እንዲደረግ የተገለጸ ቢሆንም በግብዓት ዋጋ ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደጋፊ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም ፡፡

ስጋት

ማስረጃ በግልጽ የማይቀርብ ከሆነ ከድርጅቶቹ ስራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው ወጪዎች ሊቀነሱ ይችላሉ፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሣብ</u>

ግዥዎች ተቀናሽ ከመደረጋቸው በፊት ግብር ከፋዮች በአዋጁ መሰረት ማቅረብ ያለባቸውን ማስረጃ በግልጽ ሞልተው ማቅረባቸው መረጋገጥ ያለበት ሲሆን ከላይ በዝር ዝር ያልቀረበውን የግዥ ሂሳብ በተመለከተ ጉዳዩ ተጣርቶ በውጤቱ መሰረት ተገቢ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

በአስተያየቱ መሰረት መረጃው በሰንጠረዥ ተያይዞ እንዲቀርብና ለሦስተኛ ወገን ግልፅነት ያለው መረጃ እንዲኖር የእርምት እርምጃ ይወሰዳል ብለዋል፡፡

ከ) <u>በግብር ማሳወቂያ አሞላል ስህተት ምክንያት ብር 31,361.85 የተጨማሪ እሴት ታክስ .ያልተሰበሰበ መሆኑ</u>

<u>ግኝት</u>

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ተመላሽ ሂሳቦች ትክክለኛ ስለመሆናቸው ኦዲት በምናደርግበት ጊዜ በጅማ ቅ/ጽ/ቤት ዱሮስ ጀነራል ኃ/የተ. የግል ማህበር (የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0020562350 የሆነ) ያለአግባብ ተመላሽ በተያዙ ሂሳቦች ምክንያት የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር **31,361.85** ያልተሰበሰበ መሆኑ

<u>ስጋት</u>

ግብር ከፋዮች በግብር ክፍያ ወቅት የሚያቀርቡት መረጃ ስለትክክለኛነቱ በሚመለከታቸዉ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሰራተኞች በአግባቡ የማይፈተሽ ከሆነ የመንግስት ገቢ በአግባቡ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሣብ</u>

በቅ/ጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያዎች በትክክል በሚመለከታቸው ሠራተኞች በየወሩ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶአቸው እንዲታዩ እና በተጨማሪ እሴት ታክሱ ማሳወቂያ ቅጽ መሰረት በትክክል እየተሞሉ መከፈል ያለበት ግብር በወቅቱ እንዲከፈልና ተቀናሽ መሆን ያለበትም በትክክለኛው መጠን ለሚቀጥሉት ወራት እንዲዞር መደረግ ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

ድርጅቱ በ2004 የግብር ዘመን በአዲስ አበባ ምዕራብ ቅ/ጽ/ቤት ሲስተናገድ የቆየ ድርጅት ስለሆነ በአጠቃላይ ኦዲት ተሰርቶ ቀሪውን ግብር ከየድርጅቱ የሚሰበስቡ መሆኑን በመውጫ ውይይት ወቅት ገልጸዋል ።

1.3 ሌሎች ገቢዎችን በተመለከተ

ሀ) በውርስ ከተያዙ ንብረቶች ሽያጭ ብር 252,299,705.34 ያልተሰበሰበ ሂሳብ መገኘቱ

ግኝት

የተወረሱ ንብረቶች ማስወገድ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 56/2003 መሰረት ባለስልጣኑ ከሸቀጥ ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት ጋር ጥር 1/ 2005 ዓ.ም በተደረገው የውል ስምምነት አንቀጽ 3 ተራ ቁጥር 3.4 ላይ በተጠቀሰው መሰረት ሽያጩ በ120 ቀናት ውስጥ ካልተሰበሰበ መደበኛ ወለድን ጨምሮ እንደሚከፍል በውል በስምምነቱ ላይ ተጠቅሷል፡፡ በዚህ መሰረት በዋናው መስሪያ ቤት በኩል ለጅንአድ ብር 290,525,709.83 በዱቤ ሽያጭ የተደረገ ሲሆን የተሰበሰበው ሂሳብ ግን ብር 38,296,004.49 በመሆኑ ቀሪ ወለድን ሳይጨምር ብር 252,299,705.34 ያልተሰበሰበ ሂሳብ መኖሩ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም ያልተሰበሰበው ሂሳብ ትክክለኛነት የሚያሳይ መከታተያ መዘክር የሌለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ስጋት

ወደ ጅንአድ በዱቤ ሽያጭ የተላለፉት ንብረቶች ሂሳብ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

መ/ቤቱ ለሸቀጥ ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት የሚያስተላልፋቸው ንብረቶች ሽያጭ ለመሰብሰብና ቀሪውን ሂሳብ ለመከታተል እንዲቻል ለጅንአድ የሚተላለፉት ሂሳቦች መከታተያ መዘክር ሊቋቋምለት ይገባል ፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

የባለስልጣን መ/ቤቱ በዱቤ ሽያጭ ለጅንአድ ያስተላለፋቸውን ዕቃዎችና ድርጅቱ ያስገባው ገንዘብ በተመለከተ ስላልተጣጣመ ከሁለቱ መ/ቤቶች የተወጣጣ የግልግል ኮሚቴ እንዲቋቋም የተጠየቀና በዚያ ልክ የሚከናውን መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ሂሳቡ በተሰብሳቢነት መከታተያ መዝክር አለመኖርን በተመለከተ በቀጣይ በተሰጠን አሰተያየት መሠረት አሠራራችንን ፈትሸን እናስተካክላለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

2. የወጪ ሂሳብን በተመለከተ

ሀ) በትክክለኛው የወጪ አርእስት ያልተመዘገበ ብር 359,427.88 ሂሳብ መገኘቱ

ግኝት

የሂሳብ እንቅስቃሴ ምዝገባ የሚካሂደው በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት የሂሳብ መደቡን ጠብቆ የተመዘገበ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በጅጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ ብር 359,427.88 የተገኘ መሆኑ ፡፡

ስጋት

የሂሳብ መደቡ በትክክል ካልተገለጸ ሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ሁኔታ ላያሳይ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በትክክለኛዉ ሂሳብ መደብ ያልተመዘገበዉ የሂሳብ እንቅስቃሴ ማስተካከያ ሊደረግለትና የመንግሥት የሂሳብ አወቃቀር ሥርአት / Chart of account / መሰረት ሂሳቦች በአይነት ተለይተው በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ለመመዝገባቸዉ የሚመለከተዉ ሠራተኛ አስፈላጊዉን ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

ከኮንትሮባንድ ሥራ ጋር የተያያዘ በመሆኑና ስራዉ ፋታ የማይሰጥ በመሆኑ ቀሪ ሂሳብ ካለበት መደብ በመመዝገቡ መሆኑን ገልጸዋል ፡፡

ለ) ፕሮፎርማ ሳይሰበሰብ ብር 806,048.39 ግዥ የተፈፀመ መሆኑ

ግኝት

በፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 አንቀጽ 24 ከብር 1500.00 በላይ ግዥ ሲካሄድ ከሶስት ካላነሱ አቅራቢዎች ፕሮፎርማ ተሰብስቦና የዋጋ ማወዳደሪያ ተደርጎ ግዥ መፈጸም እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን በጅጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ከመመሪያ ውጪ ብር 390,250.00 እንዲሁም በዋና መ/ቤት በኩል ብር 415,798.39 በድምሩ ብር 806,048.39 የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይደረግ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ስጋት

በግዥ መመሪያዉ መሰረት ስራዉ ካልተሰራ መንግስት ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ማንኛውም ግዥ በመመሪያዉ መሰረት ለመፈጸሙ አስፈላጊው ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

የጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት ከአካባቢው በቂ ተወዳዳሪ ባለመገኘቱ ምክንያት ግዥው ከአንድ አቅራቢ የተፈጸመ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ሐ) ከመመሪያ ውጪ የትርፍ ሰዓት ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በቁጥር መ30/ጠ13/37/820 ቀን 5/13/2001 ዓ.ም ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ ከውጤት ተኮር ሥርዓት ጋር የሚኖረው ግንኙነት በትክክል መልስ እስኪያገኝ ድረስና ተለዋጭ መመሪያ እስኪደርሳችሁ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተግባራዊ ሳይደረግ እንዲቆይ የተወሰነ መሆኑን አሳውቋል፡፡ ነገር ግን በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በኩል ብር 65,668.07 እንዲሁም በዋናው መ/ቤት በኩል ብር 1,129,307.57 በድምሩ ብር 1,194,975.64 በ2005 በጀት ዓመት ለትርፍ ሰዓት ወጪ ሆኖ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

ስጋት

ስራዎች በመደበኛ የስራ ሰዓት እንዳይሰሩ የሚገፋፋ እና መ/ቤቱንም ለተጨማሪ ወጪ የሚዳርግ ነው፡፡ አሰራሩ ያልተፈቀዱ ክፍያዎችን ለመፈፀም የሚያበረታታ ነው፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ለወደፊቱም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ማስፈቀድ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በቁጥር መ30/ጠ/ጠ13/5/13/37/820 በቁን 5/13/2001 የተጻፈ ቢሆንም በጠቅላይ ሚ/ር ፅ/ቤት በ01/5/1990 በቁጥር ጠ80-ሐ2/01/17 በተጻፈ ደብዳቤ የመ/ቤታችን ስራዎች ካላቸው ለየት ያለ የስራ ባህሪ አኳያ የ24 ሰዓት አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ ፤ እንዲፈቀድልን ለጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት ጥያቄ አቅርበን ምላሹን እየተጠባበቅን የምንገኝ መሆኑን እንገልጻለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

መ) ያለአግባብ የደመወዝ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ

ግኝት

በበጀት ዓመቱ መ/ቤቱ ያወጣው የደመወዝ ክፍያ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በዋናው መ/ቤት በJV ቁጥር 0057129 ቀን 23/05/2005 ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች ለወ/ሮ ሩት አሻግሬ ብር 1,153.17 እንዲሁም ለወ/ሮ ማህሌት ዘለቀ ብር 406.34 የጥር ወር ደመወዝ በድምሩ ብር 1,559.51 የተከፈለ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

ስጋት

ሰራተኞች በስራ ላይ የነበሩበት መረጃ በአግባቡ የማይረጋገጥ ከሆነ በስራ ላይ ላልተገኙ ሰራተኞች ክፍያ ሊፈጸም ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ማንኛውም ሰራተኛ ስራ ላይ በተገኘበት ቀን ብቻ ክፍያ ሊከፈለው ስለሚገባ ያለአግባብ የተከፈለው ክፍያም ከሚመለከታቸው አካላት መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

ሁኔታውን በተመለከተ ለወ/ሮ ማህሌት ዘለቀ በቀን 15/05/05 የለቀቀች መሆኑ ሲታወቅ የሁለት ቀን ተጨማሪ 406.34 ብር በስህተት የተከፈለ መሆኑን አውቀን በተሰብሳቢ መዝግበን ቀጣዩን እርምጃ እንወስዳለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ሠ) የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 18,557 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ

ግኝት

በበጀት ዓመቱ መ/ቤቱ ያወጣው ወጪ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በዋናው መ/ቤት በኩል በPV ቁጥር 24064 በቀን 10/08/05 ብር 18,557 የመስተንግዶ ወጪ በሚል ከመጋቢት 25- መጋቢት 30/ 2005 ለወጣው ወጪ በትክክል ስለመውጣቱ የሚያረጋግጥ የተሰብሳቢዎች ዝርዝርም ሆነ ሰአት ፊርማ እንዲሁም የመስተንግዶው አቅርቦት ያወራረዱበት ምንም ማረጋገጫ የሌለ እና በአንድ ደብዳቤ ብቻ ወጪው የፀደቀ መሆኑን አረጋግጠናል፡፡

ስጋት

ባልተሟላ ማስረጃ ክፍያ ሊፈጸም ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት የወጪ መረጃዎች በአግባቡ መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

አስተያየቱን ተቀብለዋል፡፡

ረ) መሰብሰብ የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስና የቅድመ ግብር ክፍያ ያልተሰበሰበ መሆኑ

ግኝት

በግዥ ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ የአፈጻፀም መመሪያ ቁጥር 27/2002 አንቀጽ5 ንዑስ አንቀጽ አንድ መሰረት ባለመከናወኑ በዋናው መ/ቤት

በኩል በደረሰኝ ቁጥር 24388 እና በደረሰኝ ቁጥር 24406 ለተሽከርካሪ ጥገና ከወጣው ወጪ እንዲሁም በደረሰኝ ቁጥር 25892 በአዲስ ዘመን እና በሄራልድ ላይ ለወጣው ማስታወቂያ መሰብሰብ የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 17,113.39 ሳይሰበሰብ ቀርቷል፡፡ በተመሳሳይ በደረሰኝ ቁጥር 24388 እና በደረሰኝ ቁጥር 24406 ለተሽከርካሪ ጥገና ለወጣ ወጪ የቅድመ ግብር ክፍያ ብር 244.53 ያልተሰበሰበ መሆኑን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡በአጠቃላይ በድምሩ ብር 17,357.92 መሰብሰብ የነበረበት የመንግስት ገቢ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

<u>ስጋት</u>

መሰብሰብ የሚገባው የታክስ ገቢ በአግባቡ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መመሪያው በሚያዘው መሰረት ያልተሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ሆነ ቅድመ ግብር ክፍያ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ጋራዡ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰብስቦ ሪፖርት የማድረግ ስልጣን ስለሌለው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የተጠቀሰውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ሲከፍል የተገዛበት ድርጅት ደግሞ የሽያጩን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለሚመለከተው ያቀርባል በማለት ምላሽ የሰጡ ቢሆንም ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ከብር 5,000 በላይ ግዥ ስፈፅም ቆርጦ ማስቀረት እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡

3. <u>በጀት</u>

ሀ. <u>በገቢ ዕቅድ ላይ ያልተካተተ የገቢ ሂሳብ</u>

<u>ግኝት</u>

በበጀት ዓመቱ እንዲሰበሰብ ተብሎ በየገቢ አርዕስቱ በዕቅድ የተያዘው ገቢ በዕቅዱ መሰረት እየተሰበሰበ ወይም እየተከናወነ መሆኑን ኦዲት በምናደርግበት ጊዜ በዓመቱ የገቢ ዕቅድ ላይ ያልተያዙ የገቢ አርዕስቶች

በዓመቱ የገቢ ክንውን ላይ ብር 1,590,367,407.79 በተለያየ የገቢ ሂሳብ አርዕስቶች ተሰብስቦ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

ይህ የገቢ አርዕስት በገቢ ዕቅድ ውስጥ ባለመካተቱ ምክንያት ትኩረት ላይሰጠውና በተሻለ መልኩ ገቢው ላይሰበሰብ ይችላል፡፡የገቢ እቅዱንም ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ከላይ የተመለከተው የገቢ አርዕስት ዕቅዱ በሚታቀድበት ወቅት በገቢ ዕቅድ ላይ እንዲካተት በማድረግ በተሻለ መልኩ ገቢው እንዲሰበሰብ መደረግ ይኖርበታል፡፡

ለ.የተጠቃለለ በጀት አፈጻጸም በተመለከተ

ግኝት

በ2005 በጀት ዓመት የታወጀው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለማጣራት በተደረገው ኦዲት በልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ውስጥ በ19 የወጪ ሂሳብ መደቦች (ከ10% በላይልዩነት ያላቸው) ብር 56,449,623.75 በሥራ ላይ ሳይውል ተገኝቷል ፡፡

ስጋት

ባለስልጣኑ ሊጠቀምበት የማይችለውን በጀት አስፈቅዶ ሊሆን ይችላል፡፡ መንግስት ለሌላ ስራ ሊያውል የሚችለውን በጀት ያለአግባብ ሊሊያዝ ይችላል፡፡

የማሻሻያ እርምጃ

ያልተሰራበትን በጀትን በተመለከተ ቅ/ጽ/ቤቱ በተጨባጭ ሊሰራ ካቀደው ተግባር ጋር በማገናዘብ እና ያለፉትን ዓመታት አፈፃፀም በመገምገም

የበጀት ዝግጅቱ የሚሻሻልበትን ሁኔታ ማመቻቸትና መከታተል እንዳለበት እናሳስባለን፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

ከበጀት በታች በኦዲት ግኝቱ እንደተጠቀሰው ብር 56,449,623.75 በስራ ላይ ሳይውል የተገኘው፡ ከሰራተኛ ቅጥር ጋር ተያያዙና ሌሎች ምክንያቶችጠቅሶ ስራላ አለመዋሉን አብራርቷል፡፡

ሐ.በቅርንጫፍ ጽቤቶች ከተመደበላቸው በጀት በላይ መጠቀም በተመለከተ ግኝት

በፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ክፍያ የሚፈፀመው ወይም ወጪ የሚደረገው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ነገር ግን በቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደው በጀት በላይ በ6200 ብር 3,135,057.95 በ6400 ብር 92,912,888.00 እንዲሁም የጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት ከበጀት በላይ ብር 9,346,460.16 እና በዋናው መ/ቤት በልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች በድምሩ ብር 2,503,995.64 ከበጀት በላይ የተጠቀሙ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

አሰራሩ የመንግስት የፋይናንስ ህግን የጣሰ ከመሆኑም በላይ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊያጋልጣ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቱ በበጀት አጠቃቀም ላይ ተገቢውን ጥንቃቄ ሊያደርግና የበጀት እጥረት ሲያጋጥም የበጀት ዝውውር በመጠየቅ ሊሰራ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

- የቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በተመለከተ የበጀት ዝውውር ስለመደረጉ ማስረጃ ማቅረብ ባይቻልም ለተጨማሪ በጀት ዋናው መስሪያ ቤትን ጠይቀው ክፍያው የተፈጸመውም ከዋናው መስሪያ ቤት ገንዘብ ስለተላከ ነው በማለት አስረድተዋል፡፡

- የጅጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤትን በተመለከተ በብልጫ የታየው በጀት የያዥ አበል፤የጠቋሚ አበል ፤የቀረጥ ተመላሽ፤ ለስልጠና ወጪዎች ከዋና መ/ቤት በኩል በጀት የተያዘ ሲሆን ከቅ/ጽ/ቤቱ ጥያቄ ሲቀርብ ገንዘብ እየተላከ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑንና በ2006 በጀት ዓመት በጀት የሚቆጣጠር ሠራተኛ በመመደብ የበጀት ቁጥጥር እንደሚደረግ ና በተጨማሪ በአይቤክስ በመጠቀም የበጀት እጥረት ካጋጠመ ከዋና መ/ቤት ተጨማሪ በጀት በመጠየቅ የሚጠቀሙ መሆኑን ገልጸው አሁን የተፈጠረው ስህተት የበጀት ክፍል ባለመኖሩ መሆኑን በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅት ገልጸዋል፡፡

ዋናው መ/ቤት በተመለከተ:-

- በወጪ መደብ 6251 የተደለደለው በጀት 19,925,235.00 ሲሆን በስራ ላይ የዋለ በጀት 21,899,773.95 ሲሆን የበጀት ዝውውር ከተደረገ በኋላ በአለም ባንክ እርዳታ ተቀጥረው በመሰራት ላይ ያሉት ሁለት የውጪ ሀገር አማካሪና አንድ አትዮጵያዊ የስራ ግብር ከሀገር ውስጥ በጀት የሚሸፈን በመሆኑ በአመቱ መጨረሻ ለዚሁ አገልግሎት ክፍያ የተከፈለ በመሆኑ ከበጀት በላይ ሊታይ ችሏል፣

- በወጪ መደብ 6257 የተደለደለው በጀት 512,000.00 ሲሆን በስራ ላይ የዋለ በጀት 1,418,873.81 ሲሆን ለዋናው መ/ቤትና ለምሰራቅ አ/አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኘው የመብራት መስመር እየተቆራረጠ በማስቸገሩ ምክንያት ለኢትዮጵያ መብራት ሀይል ተጠይቆ በተፈቀደው መሠረት የመብራት መቆራረጥ እንዳይከሰት በሦስት አቅጣጫ የሚመጣ መስመር ወደ አንድ መስመር ለማስገባት ለዚሁ አገልግሎት ከ830ሺ ብር በላይ የተከፈለ በመሆኑ ምክንያት ለዚሁ አገልግሎት ሌሎች ቅርንጫፎች ከማይጠቀሙበት በበጀት በዝውውር ሊስተናገድ ይችላል በሚል ታሳቢ ከበጀት በላይ መጠቀማቸውን

- በወጪ መደብ 6259 የተደለደለው በጀት 732,000.00 ሲሆን በስራ ላይ የዋለ በጀት 354,582.88 ሲሆን ከቀድሞ ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት ሜክስኮ የሚገኘው የቴክኖሎጅ መረጃ ዳይረክቶሬትና ዋና መስሪያ ቤት

የውሃ ውዝፍ እንዲሁም አስቸኳይ ደብዳቤዎችና የተለያዩ ዶክሜንቶችን በኢ.ኤም.ኤስ ስለሚላኩ ከበጀት በላይ ሊውል መቻሉን ገልጸዋል፡፡

መ) በቅ/ጽ/ቤቶች ብር 88,829,770.25 ስራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ

ግኝት

በ2005 በጀት ዓመት ለዋናው መ/ቤት የተደለደለው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለማጣራት በተደረገው ኦዲት በልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ውስጥ ከ10% በላይ ስራ ላይ ያልዋለባቸው ከተለያዩ አርእስቶች በድምሩ ብር 88,829,770.25 (53%) በሥራ ላይ ሳይውል የተገኘ መሆኑ ታውቋል ፡፡

ስጋት

ለሌሎች መ/ቤቶች ወይም መርሃ ግብሮች ሊደለደል የሚችለውን በጀት ሥራ ላይ እንዳይውል ያደርጋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

መ/ቤቱ በበጀት ጥያቄ ወቅት ሥራ ላይ ሊያውል የሚችለውን በጀት ብቻ ሊጠይቅ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የ2005 በጀት ዓመት ለተቋሙ ተፈቅዶ የመጣውን በጀት ለቅርንጫፍችና ለዋናው መ/ቤት ዕቅድና ክትትል ዳይሬክቶሬት ለደመወዝና ሥራ ማስኬጃ እንዲውል ከተደለደለው ከበጀት በታች በጥቅም ላይ ያልዋለ በጀት የሚያሳየው ከተጠባበቂ በጀት ላይ ለቅርንጫፎች የበጀት እጥረት በሚያጋጥማቸው ወቅት የተስተናገዱ በመሆኑና እንደዚሁም እንደተቋም 97% ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት

አብዛኛው ተራፊ በጀት ለቅርንጫፎች የተላለፈ ነው ቢሎም ለቅርንጫፎች የተላለፈ ስለመሆኑ የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ በተጨማሪም የዋናው መስሪያ ቤት በጀት ክትትል አጥጋቢ አለመሆኑን ያመለክታል፡፡

4. ተሰብሳቢ

ግኝት

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት፡-

የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ እንዳለበት እንዲሁም በተጨማሪ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማናቸውንም በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በጊዜ ገደቡ የማይወራረድ ከሆነ ሂሳቡ በተሰብሳቢነት መያዝ እንዳለበትና የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት መመሪያው ይገልጻል፡፡ ከዚህ አንፃር የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነቱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት በሀብት አስተዳደር በኩል(ለባንክ ኮድ 1961) በተዘጋጀዉ የ2005 በጀት አመት ሂሳብ መግለጫ ላይ ሪፖርት ለተደረገዉ በድምሩ ብር 52385.47 ተሰብሳቢ ምንም አይነት ደጋፊ ሰነድ ሊቀርብላቸዉ አልቻለም፡፡
- በጅማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ሰኔ 30/2005 ሪፖርት ላይ ብር 10,052.76 ሳይወራረድ በተሰብሳቢነት ያለ ሂሳብ መሆኑ
- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ሰኔ 30/2005 ሪፖርት ላይ ብር 3,423.23 ሳይወራረድ በተሰብሳቢነት ያለ ሂሳብ መሆኑ
- በዋናው መ/ቤት በኩል ብር 3,052,114.94 ከ2001 ጀምሮ ሳይሰበሰቡ የቆዩ ሂሳቦች መኖራቸውን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

መሰብሰብ ያለበት የመንግሥት ገንዘብ ሳይሰበሰብ እንዲቀር ሊያደርግ ይችላል፡፡ ሂሳብ መግለጫውም ትክክለኛውን ሁኔታ እ ንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

መሰብሰብ ያለበት ገንዘብና መወራረድ ያለበት ሂሳብ ላይ አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

- መ/ቤቱን ከለቀቁ ሰራተኞች ጋር ተያያዘና ከ2001 ጀምሮ ሲንከባለል የመጣ ተጣርቶ የሚወራረድ፤ ለግኾ፤ለአቅራቢዎች፤ለመንግስት መ/ቤቶች በልዩ ልዩ ተሰብሳቢነት የተያዘ እና ለግለሰብና ለግል ድርጅት ቅድመ ክፍያ ሂሳብ ከ2001 ጀምሮ ሲንከባለል የመጣ ሲሆን ከሦስቱ መ/ቤቶች ውህደት ጀምሮ የተመዘገቡ በመሆኑ እና በጊዜው ኦዲት ተደርጎ ርክክብ ባለመከናወኑ የሦስቱም መ/ቤቶች ሰነዶች መለየት በማይቻል መልክ በአንድ ቢሮ የታጨቁ ስለሆነ በቀጣይ በዋና መ/ቤት የሰነድ ማደራጃ ሲደራጅ ተጠርቶ የሚወራርድ ይሆናል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

5. ተከፋይ

ግኝት

ማናቸዉም ወደፊት ክፍያ የሚፈጽምባቸዉ ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸዉን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለዉ አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ከዚህ አንፃር የተከፋይ ሂሳብ ትክክለኛነቱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት በሀብት አስተዳደር በኩል(ለባንክ ኮድ 1961) በተዘጋጀዉ የ2005 በጀት አመት ሂሳብ መግለጫ ላይ ሪፖርት ለተደረገዉ በድምሩ ብር 9733.84 ተከፋይ ሂሳቦች ምንም አይነት ደጋፊ ሰነድ ሊቀርብላቸዉ አልቻለም፡፡
- በዋናው መ/ቤት በኩል በተለያዩ ተከፋይ ሂሳብ መደቦች በድምሩ ብር 6,484,195.75 ከ2001 በጀት አመት ጀምሮ ሳይወራረድ የቆየ ሂሳብ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

መወራረድ ያለበት ሂሳብ ላይ አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

የዋናው መስሪያ ቤት ፡-

- በሂሳብ መደብ 5002 ብር 356,850.12 ከ2004 ጀምሮ ሲንከባለል የመጣና በ2006 ዓ.ም ለሚመለከተው የሚከፈል፤ሌሎችም ተጣርቶ ሰነድ ተሟልቶ የሚከፈል፤ ከውህደት ጀምሮ ሲንከባለል የመጣ ባለቤቱ ባለመታወቁ ሊከፈል ያልቻለ መሆኑን በመግለፅ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

6. የተጣራ ሀብት

ግኝት

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 (2ለ) መሰረት የእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን/ዴቢት ወይም ክሬዲት/ጠብቆ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡

ነገር ግን ፡-

- በአዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል የተጣራ ሀብት (Equity Account) በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበት ሚዛን ክሬዲት ቢሆንም ሰኔ 30/2005 በአገር ዉስጥ ገቢ በኩል በተጠቃለለው ሂሳብ መግለጫ ላይ የተጣራ ሀብት በብር 9,982,934.16 ዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የተጣራ ሂሳብ (Equity Account) በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበት ሚዛን ክሬዲት መሆን ሲገባው የሰኔ 30,2005 ዓ.ም በመደበኛ ሂሳብ ወይም በሀብት አስተዳደር በኩል በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ የተጣራ ሀብት በብር 101,487.22 ዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

ሂሳቡ ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሣይ ያደርገዋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ከላይ የተገለጸዉ ሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን ያልጠበቀበት ሁኔታ ሊጣራና አስፈላጊው ማስተካከያ ለሰራ ይገባል ፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

- በተለያዩ መረጃ ክፍተት የተፈጠሩ ስለሆነ ሲሆን ሁኔታውን በማጣራት አሰፈላጊውን እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን በኦዲት መውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

7. የተጠቃለለ ሂሳብ

ሀ. የ2005 በጀት ዓመት የቅርንጫፍ መ/ቤቶች በሂሳብ መግለጫ የታየው ጠቅላላ ሂሳብ ከተጠቃለለው የሂሳብ መግለጫ ጋር ሲነጻጸር ልዩነት መኖሩ

ግኝት

በ2005 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያሳወቀው የተጠቃለለ ሂሳብ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች ባቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች መሰረት የተዘጋጀ ለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተላከው የተጠቃለለ ሂሳብ መግለጫ

በተለያዩ የገቢ ሂሳብ መደቦች በማነስ ብር 38,761,015.97 የታየ መሆኑ

- በተለያዩ የወጪ ሂሳብ መደቦች በመብለጥ ብር 3,001,218.85 ተመዝግቦ መገኘቱ፣
- በተለያዩ የተሰብሳቢ ሂሳብ መደቦች በመብለጥ ብር 2,051.31 የታየ መሆኑ

- በተለያየ የተከፋይ ሂሳብ መደቦች ብር 1,149.70 በመብለጥ የታየ መሆኑ
- በተለያየ የዝውውር የሂሳብ መደቦች በዴቢት ብር 11,958,683,009.62 በማነስ ብር 14,755,252,948.39 በመብለጥ እንዲሁም በክሬዲት ብር 35,671,892.76 በማነስ ብር 681,968.89 በመብለጥ የታየ መሆኑ @/
- በ4101 እና 4103 ሂሳብ መደቦች የጥሬ ገንዘብ በመብለጥ በድምር ብር 149,668,608.49

የታየ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

ዋናው መ/ቤት ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ያቀረበው የተጠቃለለው የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን የተቋሙን የሂሳብ እንቅስቃሴ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

የባለስልጣን መ/ቤቱ ከየቅርንጫፍ መ/ቤቶች እና በዋናው መ/ቤት በቀረበው የሂሳብ መግለጫዎች መሰረት ትክክለኛ የሂሳብ ሪፖርት በማዘጋጀት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

አሁንም ለተገኙት ግኝቶች ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግ ይገባል፡፡

ለ. በባንክ ስለመኖሩ ማረጋገጫ መረጃ ያልተገኘለት ገንዘብ፡

ግኝት

በምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት በ2005 በጀት ዓመት የሂሳብ ማመዛዘኛ ላይ የሚታየው በባንክ ያለ ገንዘብ ብር 90,263,075.78 በባንክ ስለመኖሩ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በበጀት አመቱ መጨረሻ ወር(የሰኔ ወር) የባንክ

መግለጫ መሰረት በባንክ የሚታየው ቀሪ ገንዘብ ብር 32,237,402.55 ብቻ መሆኑ ተረጋግጧል በዚህም ምክንያት ብር 58,025,673.23 የት እንዳለ ለማወቅ አልተቻለም፡፡ይህም ሂሳብ በተጠቃለለው ሂሳብ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

ስጋት

ገንዘቡ ጎሎ ወይም ባክኖ ሊሆን ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በባንክ መግለጫ ላይ የማይታየው ቀሪ ገንዘብ ሁኔታ ተጣርቶ ለሚመለከተው አካል ፊሰስ ሊደረግ ወይም አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

በህዳር እና ታህሳስ 2004 ዓ.ም ቀደም ሲልስንጠቀምበት የነበረው የባንክ አካውንት ሂሳብ ሲዘጋ በምትኩ የተከፈቱት፡-

1ኛ.የአዲስ አበባ መስተዳድር የሥራ ግብር የሂሳብ አካውንት
2ኛ. የማህበራዊ ጡረታ የመንግስትና የግሉ ለብቻቸው አካውንቱ ሲከፈት
3ኛ.የፌደራል መንግስት የሂሳብ አካውንት እንደ አዲስ ሲከፈት ገንዘቡ በሶስቱም አካውንቶች እንዲገባ ሲደረግ የሂሳብ መዝገቡ ምዝገባ ግን የሁሉንም በአንድ መዝገብ በመመዝገብ በገቢ ኮድ ለመለየት ጥረት በወቅቱ ቢደረግም በዚያ ወቅት ሂሳቡ በአግባቡ ተመዝግቡ ባለመያዙ የባላንስ ስህተት ያመጣ ሲሆን በወቅቱ የሚሰበበሰብ ገንዘብ በቀን ሁለት ግዜ ባንክ ይግባ የሚል ትዕዛዝ ከበላይ ኃላፊዎች የመጣ በመሆኑ የሂሳብ ሥራው ላይ ጥራት ኖሮት ከመስራት ይልቅ በየዕለቱ የሚሰበሰበው ገንዘብ በዕለቱ ወደ ባንክ እንዲገባ ለማድረግ ሲባል ሁሉም ሂሳብ ሠራተኞች ገንዘብ እንዲሰበሰቡ እና ይኸው ገንዘብ በወቅቱ ወደ ባንክ እንዲገባ ብቻ ቁጥጥር እና ክትትሉ በዚሁ ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ ሲሆን የጉዳዩን አሳሳቢነት ለሚመለከታቸው ሁሉ አሳስበን ባለሙያዎች ተመድበው እንዲያጣሩት እየተደረገ እንዳለና የምዝገባ ችግር እንጂ የገንዘብ ጉድለት አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

8. ልዩ ልዩ

ሀ) ለሚመለከተው አካል ቀርቦ ያልተፈቀደ የጥቃቅን ወጪ የገንዘብ መጠን

ግኝት

የፌዴራል መንግስት ጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 24 (2) መሰረት በመ/ቤቱ የስራ ባህሪይ ምክንያት የተፈቀደ የጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ ገንዘብ መጠን ከፍ እንዲል ካስፈለገ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ወይም ለዋናም መስሪያ ቤት ጥያቄ በማቅረብ የተፈቀደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በጅማ ቅ/ጽ/ቤት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳይጠይቅ በሁለት ገንዘብ ያዥዎች በእያንዳንዳቸው ብር 30,000.00 በድምሩ ብር 60,000 በካዝና የሚያዝ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

የጥሬ ገንዘብን ለመቆጣጠር የተዘረጋ የውስጥ ቁጥጥር ስርዐት ተግባራዊ ለማድረግ እንቅፋት ይፈጥራል፡፡እንዲሁም የመንግስት ገንዘብ ለጥፋት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ሁኔታው የተከሰተው መመሪያውን በትክክል ካለመረዳት የመነጨ በመሆኑ ሊስተካከል ይገባል፡፡በጥሬ ገንዘዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ በካዝና እንዳያድር ጥብቅ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

መ/ቤቱ ሁለት የገንዘብ ያዥ ካለው በሁለቱም እጅ የስራ ማስኬጃ ገንዘብ ወጪ አድርጎ መጠቀም የሚቻል ስለመሰላቸው መሆኑን በመግለፅ ክስተቱ ከግንዛቤ ችግርና የገንዘብ እጥረትም ስለገጠማቸው የተፈጠረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ለ) በመረጃ ቴክኖሎጂ (MIS) እና በየቅርንጫፍ ፅ/ቤቶቹ በገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች ቡድን በኩል ያለው የገቢ መረጃ ልዩነት የሚታይበት መሆኑ

ግኝት

በገ/ኢ/ል/ሚ የፌ/መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁ.5 2003 ን.አንቀፅ 6/ለ/ ማንኛውም ገቢ መመዝገብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ከዚህ አንፃር ማንኛውም የተሰበሰበ ገቢ ተመዝግቦ ሪፖርት የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በናሙና ከታዩት ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ውስጥ፡-

- በአዲስ አበባ ኤርፖሪት እና በቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል በመረጃ ቴክኖሎጂ(MIS or Asycuda) እና በየቅርንጫፍ ፅ/ቤቶቹ በገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች ቡድን በኩል ያለው የገቢ ልዩነት የሚታይበት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በ2005 በጀት ዓመት የሂሳብ ቋት (ledger) ላይ ተመዝግቦ በሂሳብ ማመዛዘኛ(trail balance) የተመዛዘነ ከተለያዩ የግብር ገቢ ምንጮች የተሰበሰበ ሂሳብ ብር 733,457,513.16 በሲስተም (SIGTAS) ላይ ተመዝግቦ የማይታይ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

በአግባቡ ካለመመዝገባቸው የተነሳ የበጀት ዓመቱን ገቢ ሪፖርት በማሳነስ ሊያዛቡት ይችላሉ፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ከሚመለከታቸው አካላት(ከመረጃ ቴክኖሎጂ ባሙያዎች) ጋር በመሆን የልዩነቱን መንስኤ በመመርምር ተገቢው የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

ሥራ አመራር የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ በመቀበል ለመረጃ ቴክኖሎጂ ዳሬክቶሬቱ ክትትል እንዲያደርግ የሚያስችለውን መርሀ ግብር መዘጋጀቱን ገልጸዋል፡፡

ሐ) ከዲክላራሲዮን ጋር መቅረብ ያለባቸው ሰነዶች ተሟልተው ያልቀረቡ መሆኑ

ግኝት

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የጉምሩክ ዲክላራሲዮን በሚቀርብበት ጊዜ አስፈላጊ የሆኑ የሰነዶቹ ዋና ቅጂ

ከዲክላራሲዮኑ ጋር አብሮ መቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን በሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል አምስት ዲክላራሲዮኖች ደጋፊ ማስረጃዎች ያልተያያዙላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

ስጋት

ሰነዶች ተሟልተው ካልቀረቡ የተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ትክክለኛነት ለማጣራት አያስችልም።

የማሻሻያ ሃሳብ

ማንኛውም የጉምሩክ ዲክላራሲዮን በሚቀርብበት ጊዜ ከዲክላራሲዮኑ ጋር አባሪ ሆነው የሚቀርቡ የደጋፊ ሠነድ ዋና ቅጂዎች በሚፈለገው ብዛት ተዘጋጅተው መቅረባቸውን ማረጋገጥ እና ያልቀረቡ ሠነዶች ተሟልተው እንዲቀርቡ ማድረግ እንዲሁም ሠነዶቹም ለሶስተኛ ወገን ግልጽ ሊሆን በሚችል መልኩ በጥንቃቄ መቀመጥ ይኖርባቸውዋል፡፡ አሁን ባልቀረቡት ደጋፊ ማስረጃዎች ላይም ክትትል ተደርጎ ሰነዶቹ ሊያያዙ ይገባል።

የሥራ አመራሩ ምላሽ

በመውጫ ውይይት ወቅት ያልተያያዙ ሰነዶችን ተከታትለው በአስቸኳይ እንደሚያቀርቡ የገለጹ ቢሆንም ምላሽ ያልተሰጠ በመሆኑ ስለተወሰደው የማሻሻያ ርምጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡

መ) በውርስ መጋዘን ውስጥ ለሚገኙ ንብረቶችና በመደበኛ በጀት በተገዙ ንብረቶች ላይ አንዳንድ የአሰራር ክፍተቶች የሚታዩ መሆኑ

ግኝት

በፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት በውርስ መጋዘን ውስጥ በሚገኙ ንብረቶችና በመደበኛ በጀት በተገዙ ንብረቶች ላይ ተገቢው ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች የተገለጹት ክፍተቶች የሚታዩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል፡-

- የ2005 በጀት አመት የውርስ መጋዘን ንብረት ቆጠራ የተከናወነ ቢሆንም የቆጠራ ዉጤቱ ግን ከመዝገብ ወጪ ቀሪ ጋር ያልተመዛዘነ በመሆኑ በቆጠራዉና በንብረት መዝገብ መካከል ልዩነት ይኑር አይኑር ያልታወቀ መሆኑ፡፡
- ውርስ መጋዘኑ መደርደሪያ የሌለው በመሆኑ ንብረቶቹን በእቃዎቹ ባህሪና አይነት ለያይቶ ለማስቀመጥ የማያመች በመሆኑና ንብረቶቹ መሬት ላይ ስለተቀመጡ ለብልሽት የሚዳረጉበት ሁኔታ ያለ መሆኑ
- ከጥቅምት 2003 በፊት የነበሩት የመጋዘን ንበረት ጠባቂዎች በአዲስ ሰራተኛ የተተኩ ቢሆንም ቀደም ብለው ንብረቱን ሲቆጣጠሩ የነበሩት ሰራተኞች ሲቀየሩ ንብረቱ ኦዲት ያልተደረገ በመሆኑ ጉድለት ይኑር አይኑር እስከአሁን ያልተረጋገጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በውርስ መጋዘኑ ውስጥ ሳይወገዱ ረዘም ላለ ጊዜ በመጋዘን የቆዩ ንበረቶች የሚገኙ መሆኑ
- ከዚህ በታች በተገጸው ዝርዝር መሰረት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በተለያየ ምክንያት የወረሳቸውን እንዲሁም ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ክርክር ላይ ባሉ ተሽከርካሪዎች ላይ መሰረታዊ ክፍተቶች የሚታዩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡-
- ጉዳያቸው ያላለቀ (በክርክር ላይ) ላሉ ተሽከርካሪዎች ጊዜያዊ እቃ መረከቢያ ደረሰኝ (ሞዴል270) እንዲሁም ለተወረሱት ደግሞ የውርስ ወይም የኮትሮባንድ መቀበያ ደረሰኝ (ሞዴል 265) ሊቆረጥላቸው ሲገባ ምንም የገቢ ሞዴል 270ም ሆነ ሞዴል 265 የማይቆረጥላቸው መሆኑ
- ለንብረቶቹ ለብቻው የተከለለ ቦታ የሌለ በመሆኑና ለሰው እንቅስቃሴ ክፍት በመሆኑ ለተለያየ ችግር የተጋለጡ መሆኑ
- ንብረቶቹን በባለቤትነት የተረከበ ክፍል (ቡድን) የሌለ መሆኑ
- ተሽከርካሪዎቹ ያሉበት ቦታ ለአቧራና ለፀሀይ የተጋለጠ በመሆኑ ተሽከርካሪዎቹ እየተበላሹና ከጥቅም ውጪ እየሆኑ መሆኑ
- ሶስት ተሽከርካሪዎች ታርጋቸው የሌለ መሆኑ ፡፡

እንዲሁም በሞያሌ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል ረጅም ጊዜ የሆናቸው የተወረሱ ተሽከርካሪዎች በወቅቱ ባለመወገዳቸው ምክንያት ለብልሽት

እየተጋለጡ መሆኑ እንዲሁም ተሽከርካሪዎቹ እስኪወገዱ ድረስ ማቆያ የሚሆን በቂ የሆነ መጠለያ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

<u>በቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት:-</u>

- በተለያየ ጊዜ በውርስ የገቡ የኤሌክትሮንክስ ዕቃዎች፣የምግብ አይነቶች ፣ኬሚካል ፣መድሃኒቶች፣እንዲሁም 65 በርሜል ሻምፖ ሳይወገዱ ለረዥም ጊዜ በመጋዘን ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ
- የንብረት ገቢና ወጪ ምዝገባ ፣የንብረት ርክክብ ስራ በአንድ ሰራተኛ ብቻ እየተሰራ መሆኑ
- የተለያዩ በውርስ የተገኙ መኪናዎች በቂ መጠለያ ባለመኖሩ በሜዳ ላይ በመሆናቸው ምክንያት ለከፍተኛ ብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ
- በርካታ በህግ ጉዳይ የተያዙ ንብረቶች ማለትም ጨርቃጨርቅ (ጣቃ) ፣ኤሌክትሮንክስ (ሞባይል፣ዲቪዲ) ዕቃዎች ክትትል በማድረግ መፍትሔ ባላመሰጠቱ ለረዥም ግዜ ተከማችተው በመቀመጣቸው ምክንያት ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት በኩል፡-</u>

- አመታዊ የንብረት ቆጠራ የማይከናወን መሆኑ እና የንብረት ምዝገባና የንብረት ጥበቃ ስራ በተለያየ ሰራተኛ የማይሰራ (በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን) መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>በጅማ ቅ/ጽ/ቤት በኩል፡-</u>

- በቅ/ጽ/ቤቱ ውስጥ ለሠራተኞች ለተሰራጩ ንብረቶች በንብረት ማዋሻ ፎርም /User Card/ ላይ የመለያ ቁጥር ያልተመዘገበ መሆኑ ፤
- የ2005 በጀት ዓመት የቋሚና የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም የቆጠራው ውጤት ከንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ ጋር ያልተመሳከረና ከወጪ ቀሪው ጋር ያልተረጋገጠ መሆኑ፣
- በቅ/ጽ/ቤቱ የንብረት ክፍል ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች /ኮምፒውተሮች ፣ ወንበሮች/፣ አዲስ ተገዝተው የገቡ ዕቃዎች እና በጉምሩክ የተወረሱ ሞባይሎች፣ልባሽ ጨርቆች በአንድ ላይ ተከማችተው የተገኙ መሆኑ ፣እንዲሁም አዲስ ተገዝቶ የመጣ ፎቶ ኮፒ ማሽን እና

ወንበሮች ወደ ግምጃ ቤት ሳይገቡ በበረንዳ ላይ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ ታውቋል ፡፡

<u>በጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል፡-</u>

- አመታዊ የንብረት ቆጠራ የማይካሄድ መሆኑ
- ስቶክ ካርድ ያልተቋቋመ መሆኑና የንብረት ምዝገባ አለመከናወኑ
- በቅርንጫፍ ፅ/ቤቱና በቶጎ ውጫሌ መቆጣጠሪያ ጣቢያ መጋዘኖቹ በጣም አነስተኛና የእቃ መደርደሪያ የሌለው ከመሆኑ የተነሳ እቃዎቹ በአይነት ተለይተው ያልተቀመጡና ለብልሽት በሚዳርግ ሁኔታ በወለል ላይ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ.
- በቶጎ ውጫሌ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ስቶክ ካርድ ያልተቋቋመ መሆኑ
- የጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤትና በቶጎ ውጫሌ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ዉስጥ ረጅም ጊዜ የሆናቸው የተወረሱ ተሽከርካሪዎች በወቅቱ ባለመወገዳቸው ምክንያት ለብልሽት እየተጋለጡ መሆኑ፡፡
- በጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ተይዘው የቆሙ ተሽከርካሪዎች ሻንሲ ቁጥር፣ ሞተር ቁጥር የሌላቸው በመዝገብ ያልተመዘገቡ መሆኑ አሁን ያሉበትን ደረጃ የሚያስረዳ ማስረጃ ያለመኖሩ የተወረሱ ንብረቶች በሞደል270 ወይም 265 ላይ መመዝገባቸውን የሚያስረዳ ማስረጃ የሌለ መሆኑ

<u>ስጋት</u>

- በውርስ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች በአግባቡ የተጠበቁ ለመሆኑ ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ከላይ ለተገለፁት ክፍተቶች ተገቢው የእርምት እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡ ለወደፊቱም የሚመለከተው አካል በመመሪያው መሰረት ንብረቶች የተጠበቁ ለመሆኑ ተገቢውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ አስተያየት</u>

የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቀጣይ የእርምት እርምጃ የሚወሰድ መሆኑንና የአሰራር ክፍተቱም የሚዘጋ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተለያዩ ዕቃዎች በመጋዘን ተከማችተው የሚገኙበት ምክንያት በተመለከተ፣-

- የኤሌክትሮንክስ ዕቃዎች የህግ ጉዳያቸው ያላለቀና በፍርድ ቤት ውሳኔ ሳይሠጥበት ማስወገድ የማይቻል በመሆኑ፤
- ኬሚካልን በተመለከተ በአገር ውስጥ ለማስወገድ የሚቻልበት ሁኔታና ኃላፊነት ወስዶ የሚያስወግድ የመንግስት መ/ቤት አለመኖሩ
- መድኃኒቶችንና ሻሞፖዎችን ለማስወገድ የመድኃኒት አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ስለሆነ በተደጋጋሚ በደብዳቤ ተጠይቀው ምላሽ ባለመስጠቱ ሊወገዱ አለመቻሉ፣፡፡
- የንብረት ገቢና ወጪ ምዝገባና ርክክብ ሥራ በአንድ ሰው የሚሠራው በተቋሙ የአደረጃጀትና አወቃቀር የሥራ መደብ የሌለው በመሆኑ ፡፡
- በውርስ መጋዘን ለሚገኙ ተሽከርካሪዎች በቂ መጠለያ ለማዘጋጀት ግቢው የኮሜት ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር በመሆኑና ለተሽከሪካሪዎች የተመደበ ቋሚ መጋዘን ባለመኖሩ ከ267 በላይ ተሽከሪካሪዎች መጠለያ ለማሠራትና ለአቀማመጥ ምቹ ለማድረግ ያልተቻለ ከመሆኑም በተጨማሪን ከ196 ተሽከርካሪዎች በላይ የህግ ጉዳይ ያለባቸው በመሆኑ ፡
- በህግ የተያዙ ጣቃ ጨርቆች በዋና መ/ቤት አቃቤ ህግ የተያዘ በመሆኑና ውሳኔ ሳያገኝ ማስወገድ የማይቻል መሆኑ፤በኦዲት መዉጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

የመቀሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፡-

ንብረት ቆጠራን በተመለከተ በሌሎች ንብረቶች ላይ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ስራ እየተሰራ ቢሆንም በውርስ መጋዘን ያልተሰራ ስለሆነ በቀረበው የኦዲት አስተያየት መሰረት የንብረት ቆጠራ ስራ እንዲከናወን የሚደረግ መሆኑን ገልፀው ንብረት ምዝገባን በተመለከተ ግን ምንም እንኳን በቅ/ፅ/ቤቱ መዋቅር ላይ የንብረት መዝጋቢ ሰራተኛ ያልተፈቀደና የተመደበ ሰራተኛ የሌለ ቢሆንም የንብረት ጥበቃና የንብረት ምዝገባ ስራዎች በተለያየ አካል መሰራት እንዳለበት ከቀረበው አስተያየት የተረዳን በመሆኑ መዋቅሩ ተጠይቆ እስኪፈቀድ ድረስ ካለው የሰው ኃይል ጊዚያዊ ምደባ ተሰጥቶ ተለያይቶ እንዲሰራ ይደረጋል ብለዋል፡፡

የጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፡-

- በመጋዘናቸው አመታዊ የእቃ ቆጠራ ማድረግ ያልተቻለበት ዋነኛ ምክንያት የመጋዘን ጥበት፤ የእቃዎች ተደራርቦ መቀመጥ ፣ወደ መጋዘን የሚገቡ እቃዎች ፋታ የማይሰጥና በአማካኝ በቀን ሁለት መኪና እቃ የሚገባ በመሆኑ እቃን ለይቶ ማስቀመጥ አለመቻላቸውን ገልፀዋል፡፡
- የንብረት ምዝገባ ለማድረግና የተሟላ የመጋዘን ቁጥጥር ስርዓት ለማድረግም በሞዴል 265 እና 266 ገቢ ወጪ እያደረጉ የሚቆጣጠሩ ቢሆንም እስቶክ ካርድ ለመጠቀም የዕቃዉ አይነትና ብዛት፤ የመጋዘን ጥበት እና ፋታ የማይሠጥ ሁኔታዎች በመሆናቸው ለአፈፃፀም አስቸጋሪ እንደሆነባቸው ገልፀዋል፡፡
- በሕገ-ወጥና በኮንትሮባንድ ምክንያት ተይዘው የቆሙት ተሸካሪካሪዎች አመታዊ ቆጠራ ያልተካሄደበት ምክንያት የርክክብ ስርዓት ስላልነበረና የተሽከርካሪዎቹ የተሟላ ቻንሲና ፣ሞተር ቁጥር ባለመኖሩና ከደርግ ዘመነ መንግስት ጀምሮ የነበሩ መሆኑን ገልጸው በአሁኑ ሰዓት ግን ሰው ተመድቦ የማጣራት ሥራ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡
- በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር የታዩ ክፍተቶች በቀጣይ የሚስተካከሉበት እና የንብረቶቹ አያያዝና ክትትል ስርአት የሚስተካከል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፡-

- ንብረቶቹን ለማስወገድ የመረጃ ችግር በመኖሩ ለማስወገድ መቸገራቸውን በመግለፅ ተሽከርካሪዎቹ እስኪወገዱ ድረስ ባለው መጠለያ ላይ ተጨማሪ በመስራት ደህንነታቸው የሚጠበቅበት ሁኔታ ለማመቻቸት እንደታሰበ በመውጫ ውይይቱ ወቅት ተገልጿል።

የጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፡-

ቅ/ጽ/ቤቱ ያለውን የቢሮ ጥበት መፍታት ከተቻለ የሚስተካከል መሆኑን እንዲሁም የሚወገዱ ዕቃዎችን በተመለከተ ጉዳዩ በቅ/ጽ/ቤቱ ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ በኮሚቴ የሚታይ መሆኑን በመግለፅ የማሻሻያ ሃሳቡን ተቀብለውታል።

ሠ. የደረሰኝ አመዘጋገብ በተመለከተ

ግኝት

የደረሰኝ አጠባበቅና አመዘጋገብ ሁኔታ ለማጣራት በተሞከረበት ወቅት በዋናው መ/ቤት የንብት ገቢ ደረሰኝ በሞ/22 ወጪ በሚደረግበት ወቅት ከ-እስከ ቁጥር ሳይመዘገብ ወጭ የሆኑ መኖራቸው ታውቋል፡፡

ስጋት

ከ-እስከ ሳይጠቀስ ወጪ የሚደረጉ ደረሰኞች ቢጠፉ ወይም ቢጎድል ለመቆጣጠርና ለመከታተል አያስችልም፡፡ ደረሰኞች በድጋሚ ሊታተሙ የሚችሉበት ሁኔታ የተፈጠረ በመሆኑም ለብልሹ አሰራር ክፍተት ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

በደረሰኞች ስርጭት ላይ ጥንቃቄ ሊደረግ የሚገባ ሲሆን ከ -እስከ ሳይጠቀስ ወጭ የሚሆኑ ደረሰኞች ቢጠፋና ቢጎል ለቁጥጥር ስለማይመች ማስተካከያ እርምጃ መወሰድ አለበት ፡፡በሚታተሙ ደረሰኞች ላይ የጥንቃቄ እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡ በድጋሚ የታተሙ ደረሰኞችም ዝርዝራቸው ተገልጾ ሊወገዱ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

ረ) የእርምት እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2004 በጀት አመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች መኖራቸው

ግኝት

በፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 17(3)መሰረት ተመርማሪ መስሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገኙ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦችና አስተያየቶች መሰረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ከዚህ አንጻር የ2004 በጀት አመት ሂሳብ ኦዲት ግኝት መሰረት፡-

በአዳማ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል :-

- ዋስትና በመግባት በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡት እቃዎች ውስጥ በ17 ዲክላራሲዎኖች የገቡት እቃዎች የዋስትና ገዜ ገደባቸው ያለፈ በመሆኑ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ብር 23,557,440.14 እንዲሰበሰብ አስተያየት የተሠጠ ቢሆንም ገንዘቡ ዋስትናውን ከሰጠው ድርጅት ያልተሰበሰበ መሆኑ፡፡
- በአራት ዲክላራሲዎኖች ላይ በተለያየ ስህተት ምክንያት በወቅቱ ሊሰበሰብ ሲገባው ትክክለኛው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ብር 75,951.41 ባለመሰብሰቡ ምክንያት እንዲሰበሰብ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እስከአሁን ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል፡-

- በዲክላራሲዮን ቁጥር C-11016/11 ከገቡት እቃዎች ዉስጥ በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር ባለመመደባቸው ምክንያት በወቅቱ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር10,536.31 እስከአሁን ገቢ አለመሆኑ
- የረጅም ጊዜ የደሞዝ ብድር ብር 2,213.54 ያልተሰበሰበ መሆኑ
- ከተቀጽላ ሌጀር ኮድ 71 እና 81 ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቅ ገንዘብ ብር 664.58 ላይ እስካሁን ማጣራት አለመደረጉን
- በባለፈው ኦዲት ብር 571,408,135.94 ያልተሰበሰበ ቀሪ ሂሳብ መኖሩ የተገለጸ ቢሆንም ከዚህ ዉስጥ ግን ብር 350,520,714.28 እስካሁን ያልተሰበሰበ መሆኑ ፡፡

ስጋት

በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ወቅታዊ እርምጃ ካልተወሰደ ችግሮች ከአመት አመት እንዲከባለሉ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ የመንግስት ገቢ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ያደርገዋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ተገቢው የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ለሚሰጡ የኦዲት አስተያየቶች ወቅታዊ የእርምት

እርምጃ በመውሰድ ስህተቶች እንዳይደጋገሙና የመንግስት ገቢም ሳይሰበሰብ እንዳይቀር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

<u>የስራ አመራሩ አስተያየት</u>

በአዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በተሠጠው አስተያየት መሰረት በቀጣይ የእርምት እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

<u>የቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ፦</u>

- የዲክላራሲዮን ቁጥር C-11016/11 ያልተሰበሰበውን ሂሳብ ብር10,536.31 በተመለከተ ክትትል እየተደረገ መሆኑ፣
- በቀሩት የኦዲት ግኝቶች ላይ ተገቢው የእርምት እርምጃ እንደሚወሰድ በኦዲት መውጫ ስብሰባ ወቅት ገልፀዋል፡፡

<u>ሰ) ለኦዲት ያልቀረቡ መረጃዎችን በተመለከተ</u>

<u>ግኝት</u>

የፋይናንስ አሰተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀፅ 69 መሰረት ማናቸውም የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት ለመስሪያ ቤቱ ወይም ለውጪ ኦዲተሮች ለማናቸውም ጉዳይ በመረጃነት የሚያስፈልጉትን የፋይናንስ መረጃዎችና መዛግብት ቢያንስ ለአስር አመታት ማቆየት እንዳለበት ያዛል፡፡ ከዚህ አንፃር ሰነዶች በአግባቡ የተያዙ መሆኑንና በሰነዶቹም የተሰበሰበው ገቢ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ፅ/ቤት በኩል ለኦዲት እንዲቀርቡ ከተጠየቁት ዲክላራሲዮኖች መካከል ከ2005 በጀት ዓመት 34 ዲክላራሲዮኖች እንዲሁም ከ2004 በጀት ዓመት 3 ዲክላራሲዮኖች በድጋሚ ተጠይቀው ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- በጅማ ቅ/ጽ/ቤት የነቀምት ታክስ የ 8 ግብር ከፋዮች የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ያልቀረበ መሆኑ
- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች 1 ድርጅት የንግድ ትርፍ በአዋጁ መሰረት ስለማሳወቃቸው የቀረበ ማስረጃ የሌለ መሆኑ ተረጋግጧል።

* በምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት በ SIGTAS ላይ ለብር 79,565,218.42 የገቢ ሂሳብ ማስተካከያ (reverse) በሌላ የገቢ ደረሰኝ የተሰራ ሲሆን ከዚህ መካከል በናሙና ከተመረጡት ውስጥ ለብር 659,534.18 መጀመሪያ ገቢ ተሰብስቦበት የነበረውና የተሰረዘው የገቢ ደረሰኝ ግን ለኦዲት ሊቀርብ አልቻለም፡፡በመሆኑም ገቢው በትክክል የተሰረዘና ማስተካከያ የተሰራለት ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስጋት

በሰነዶቹ የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ለኦዲት ያልቀረቡ ፋይሎች በቀላሉ ለማግኘት በሚያስችል መልኩ በአግባቡ ተደራጅተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ አሁንም ለኦዲት ያልቀረቡት ዲክላራሲዮኖች ተፈልገው ሂሳባቸው በውስጥ ኦዲት ተጣርቶ ውጤቱ ሊገለጽልን ይገባል፡፡ የዚህ አይነት አሰራር በየጊዜው የሚከሰት በመሆኑ ቅ/ጽ/ቤቱ የሁኔታውን አሳሳቢነት በመገንዘብ አስቸኳይ መፍትሄ ሊፈልግለት ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ በመቀበል ያልቀረቡት ዲክላራሲዮኖች ተፈልገው ለኦዲት እንዲዘጋጁ የሚያስችለውን መርሀ ግብር መዘጋጀቱን ገልጸዋል፡፡

የጅማ ቅ/ፅ/ቤት ስራ አመራር፡-

* የሂና ፋርም በፋክስ ስለሚያሳውቁ በጣቢያቸው መረጃቸውን በቀጥታ ማግኘት ስለማይችሉ አለማሳወቃቸውን ማወቅ አለመቻላቸውን ገልፀው ወደፊት ወደ ጣቢያችን ሙሉ በሙሉ እንዲመጣ እና ለመከታተል እንዲያመች የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፣
* የሳት ካርተር አግሮ ኢንዱስትሪ እንዲያሣውቁ በተደጋጋሚ ቢጠየቁም ድርጅቱ ሊያሳውቅ አልቻለም ለወደፊቱ ለሚመለከተው ክፍል በማስተላለፍ መፍትሄ እንዲያገኝ የሚደረግ መሆኑ፣

- ኩሚ ፋርም ኃ/የተ/የግ/ማህበር በተጠቀሰው ወር በጣቢያችን ስላላሳወቁ ውሳኔ እንዲደርሳቸውና መቀጫውን እንዲከፍሉ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

ሸ) ዕቃ ወደ ውጪ ሲላክ በሲል ሳይታሸግ የሚላክ መሆኑ

ግኝት

የወጪ እቃ አላላክን በተመለከተ የተሸከርካሪዉን መረጃ ትራንዚት ኢንስፔክተሩ ሞልቶ እና በሲል አሽጎ ባቀረበለት መሰረት T1 በማዘጋጀት በማህተምና ፊርማ አረጋግጦ ለላኪው/ወኪሉ መስጠት እንዳለበት ማኑዋሉ ላይ ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን በጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ዕቃ ወደ ውጪ ሲላክ በሲል ሳይታሸግ የሚላክ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ስራው ላይ በአካል በመገኘት ባደረግነው ማጣራት አረጋግጠናል፡

ስጋት

እቃዎች ወደ ውጭ ሲላኩ በፕሎምፕ መታሸግ እዳለበት እየታወቀ ሳይታሸግ መላካቸው ዕቃዎቹ በመሀል እንዲጨመር ወይም እንዲቀነስ በማድረግ ለምዝበራ በር ይከፍታል ፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

አሰራሩ ከመመሪያ ውጪ በመሆኑ የሁኔታውን አሳሳቢነት በመገንዘብ በአስቸኳይ ሊስተካከል ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

ሳይታሸግ መላኩ ስህተትና የሚያስጠይቅ በመሆኑ ከዋናው መ/በት ጋር በመሆን የማስተካክያ እርምጃ እንደሚወሰድ ገልፀዋል፡፡

ቀ) <u>የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ተደርጎ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመዛዘን መሆኑ</u>

<u>ግኝት</u>

በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት ቁጥር 5.ሀ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ቆጠራ በማድረግ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር መመዛዘን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን በጅማ ቅ/ጽ/ቤት በኩል የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ቆጠራ የማይደረግና ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋርም የማይመዛዘን መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

የመንግሥት ገንዘብ ለጉድለትና ለብክነት ቢጋለጥ በወቅቱ ላይደረስበት ይችላል።

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በመመሪያው መሠረት የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ በሂሣብ ክፍሉ በኩል ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር መመሳከር ይኖርበታል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ አስተያየት</u>

ከላይ በተገለጸው መመሪያ በየወሩ ዘግቶ መቁጠር የሚል ዝርዝር ሁኔታዎች የሌሉበት ስለሆነ እንደ ሂሳብ ክፍል 4101 ባላንስን በተለያየ መልኩ ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ገልፀው ከላይ የተገለጸውን ገንዘብ ትክክለኛነት ማወቅ አልተቻለም ተብሎ በኦዲተሮች የተገለጸው የሰኔ 30 ሂሳብ ስንዘጋ በገንዘብ ያዥ እጅ ያለውን ገንዘብ በትክክል ሂሳቡን ተሰርቶ ወደ ባንክ እንዲመለስ የተደረገና በቅ/ጽ/ቤቱ በኩል ቆጠራ እነዲያደርጉ የተመረጡት ኮሚቴዎች ገንዘብ መቁጠር ሲገባቸው ንብረት ብቻ በመቁጠር ከገንዘብ ያዥ በቃል የሰሙትን የገንዘብ መጠን በቆጠራ ሰነድ ላይ በማስፈራቸው ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል። የገቢ ሂሳብን በተመለከተ ደግሞ በሐምሌ 1/2005 የኦዲት ቆጠራ ወቅት በጅማ ቅ/ጽ/ቤት በገቢ ሂሳብ ካዝና ውስጥ ስንት ብር

እንዳለ ተጠይቆ እንደነበርና በወቅቱ በጂማ የገቢ ሂሳብ ገንዘብ ያዥ እጅ ወይም ካዝና ውስጥ ምንም ዓይነት ገንዘብ እንደሌለ ነገር ግን በሪፖረት ላይ 4101 ላይ 22,755.37 ተብሎ የተገለጸው ሰኔ 30 ላይ የባንክ ኔትወርክ ባለመስራቱና ወረፋ በመብዛቱ ደንበኞቻችን የሰኔ 30ን ገቢ ሐምሌ 1/2005 አስገብተዋል ፡፡ይህም Bank Statement ላይ እስከ ሰኔ 30 ያሉት ገቢዎች ውስጥ ስለማይታይና ሐምሌ 1/2005 ላይ የገባ በመሆኑ የባንክ ማስታረቂያ ለመስራትን ለማመጣጠን ከሰኔ በኋላ የገቡትን ገቢዎች እንደ 4101 ስለተያዘ ነው ብለዋል።በተጨማሪምበመውጫ ውይይት ወቅት የውስጥ ኦዲት ስለሌለ ቆጠራው በትክክል ያልተቆጠረና የቆጠራው ሪፖርት ያልደረሰኝ በመሆኑ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

በ) በየእለቱ የሚሰበሰበው ገቢ በተሰበሰበበት እለት ወይም በማግስቱ ወደ መስሪያ ቤቱ የባንክ ሂሳብ ገቢ የማይሆን መሆኑ

ግኝት

በፌዴራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 መሰረት በመንግስት ስም የተሰበሰበና ቀጥታ ወደ መስሪያ ቤቱ ወይም ለማእከላዊ ግምጃ ቤት ገቢ መደረግ ያለበት የመንግስት ገንዘብ በተሰበሰበበት እለት እንደአግባብነቱ ወደ መስሪያ ቤቱ ወይም የማእከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ ገቢ መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ነገር ግን በመቀሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በናሙና ከታዩጥ ውስጥ ከተሰበሰበው ገቢ በድምሩ ብር 4,754,726.22 ከ 5 ቀን አስከ 25 ቀን በመዘግየት ገንዘቡ ባንክ ገቢ የተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

በየዕለቱ የሚሰበሰበው ገቢ በወቅቱ ባንክ ገቢ የማይደረግ ከሆነ መንግስት ገንዘቡን በወቅቱ እንዳይጠቀምበት ያደርገዋል፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በፌዴራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 መሰረት በመንግስት ስም የተሰበሰበና ቀጥታ ወደ መስሪያ ቤቱ ወይም ለማእከላዊ ግምጃ ቤት ገቢ መደረግ ያለበት የመንግስት ገንዘብ በተሰበሰበበት እለት እንደአግባብነቱ

ወደ መስሪያ ቤቱ ወይም የማእከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡

<u>*የሥራ አመራሩ ምላሽ*</u>

በየቀኑ የሚሰበሰብ ገቢ ወደ መ/ቤቱ የባንክ ሂሳብ በዛው ዕለት ወይም በነጋታው ገቢ መደረግ ያለበት መሆኑ አጠያያቂ አለመሆኑን በመግለፅ በኦዲተሮች አስተያየት ላይ የተገለፀው ገቢ በጥሬ ገንዘብ የተሰበሰበ ገቢ ሳይሆን በሲፒኦ የተሰበሰበ ገቢ በመሆኑና ሲፒኦ ከግል ባንኮች የሚመጣ በመሆኑ በግል ባንኮችና በንግድ ባንኮች ባለ የገንዘብ ልውውጥ ግንኙነት ችግር ሳቢያ በየዕለቱ ወደ ጥሬ ገንዘብ ተቀይሮ ወደ መ/ቤቱ ባንክ ሂሳብ ገቢ ለማድረግ ባለመቻሉ ከንግድ ባንክና ከግል ባንኮች ጋር በተደረገ ውይይት ይህንን ችግር ለመፍታት ጥረት የተደረገ ቢሆንም መሻሻል ባለመታየቱ ችግሩ በዘላቂነት እስኪፈታ ድረስ ከሀምሌ 1/2005 ዓ.ም በኃላ የሚከፍሏቸው የቀረጥ ክፍያዎች ከንግድ ባንክ ብቻ በሲፒኦ እንዲያቀርቡ በማድረግ ችግሩ የተፈታ ቢሆንም የግል ባንኮችን የስራ እንቅስቃሴ የሚጎዳ በመሆኑ ችግሩን ለዘለቄታው ለመፍታት ተጨማሪ ጥረት ይደረጋል ብለዋል፡፡

የፋይናንስና ኮሙዩኒኬሽን መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት
የ2005 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት ማጠቃለያ

የ2005 በጀት ዓመት በፋይናንስና ኮሚኒኬሽን ኦዲት መ/ቤቶች ስር የሚገኙ መ/ቤቶች ዓመታዊ ሪፖርት ማጠቃለያ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የፋይናንሻልና ሕጋዊነት ኦዲት ዕቅድ አፈፃፀም

በፋይናንስና ኮሚኒኬሽን ኦዲት መ/ቤቶች ዳይሬክቶሬት በ2005 በጀት ዓመት 30 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችን ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ አቅዶ የ30 መ/ቤቶችን ኦዲት አከናውኗል፡፡ ይህም 100% እንደተከናወነ ያሳያል፡፡ የኦዲቱ ሥራ የተከናወነው በ1 ዳይሬክቶሬትና በ3 የኦዲት ማናጀሮች ነው፡፡

ዳይሬክቶሬቱ በ2005 በጀት ዓመት በፌዴራል መ/ቤቶች ላይ በመደበኛ ኦዲት ያከናወነው የፋይናንስ ኦዲት የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብን ጨምሮ 30 የኦዲት ሪፖርቶችን ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች የላከ ሲሆን፣ ሪፖርቶቹም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት አንፃር ሲተነተኑ፣

- አልፎ አልፎ ሊጠቀሱ ከሚችሉ ጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Except for Opinion) 15 መ/ቤቶች፣
- የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት (Adverse opinion) የተሰጠው 2 መ/ቤት እና
- አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Clean opinion) የተሰጠባቸው 13 መ/ቤቶች ናቸው፡፡ /ዝርዝራቸው ከአባሪ-2 ቀርቧል/

የዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች

1. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችል የቁጥጥር ስርአት መዘርጋቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1.1 በፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በሂሳብ መደብ 4202 (የጥሬ ገንዘብ ጉድለት) የተከሰተው ብር 12,687.87 የመሰብሰቡ ሂደት መቋረጡ፣

1.2 1በሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማይደረግ እና ከመዝገብ (ከሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመዛዘንመሆኑ፣

1.3 የኢትጵያ ብሔራዊ ቴአትር በ2005 በጀት ዓመት የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ የላዘጋጀና የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ቆጠራ የላደረገ መሆኑ

1.4 በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ሰኔ 30/2004 በውስጥ ኦዲተሮች በጥሬ ገንዘብ እና በሰነድ ተገኝቶ የተቆጠረው ብር 175,262.79 ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ደግሞ ብር 176,987.61 በመሆኑ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራው በብር 1,724.82 በማነስ የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም ከላይ ለተመለከቱት ግኝቶች ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2. ተሰብሳቢ

2.1 በወቅቱ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) የተሰብሳቢ ሂሳብ

በፋይናንስ አስተዳር ደንብ መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱንና ሂሳቡም በወቅቱ መወራረዱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በ20 መ/ቤቶች በተለያዩ የሂሳብ መደቦችና የቆይታ ጊዜያቸው ከ1 ወር እስከ 39 ዓመታት የሆኑ ብር 82,677,520.64 ያልተወራረደ የተሰብሳቢ መኖሩ ታውቋል፡፡/ ዝርዝሩ አባሪ- 6 ተመልክቷል/

በመሆኑም ውዝፍ ሰነዱን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው የስራ አመራር ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2.2 በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች

የሂሳብ ሪፖርት ላይ የተያዘው የግገር ሠራተኞች የተሰብሳቢ ሂሳብ በግገር ሠራተኞች ተቀጽላ ሌጀር ላይ ከተያዘው የተሰብሳቢ ሂሳብ ጋር መግጠሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ሰኔ 30 ባዘጋጀው የተሰብሳቢ ሂሳብ ባላንስ ዴቢት ቢሆንም፣
- በ4 የግገር ሰራተኞች ላይ ብር 1,110,062.67 ክሬዲት ባላንስ (Abnormal balance) የሚታይ መሆኑ ፣
- በ5 የግገር ሠራተኞች ላይ ደግሞ ሂሳቡ ካለፉት አመታት ጀምሮ የመነሻ ሂሳባቸው በብር 1,323,207.45 ያልተለመደ ሚዛን (Abnormal balance) እየታየ እያለ ሌላ ገንዘብ በመጨመር የነበረውን ባላንስ እየተቀናነሰ የሄደበት ሁኔታ መኖሩና
- የኮንትራክተሮች የተሰብሳቢ ሂሳብ በኮንትራክሮች ስም ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀ በመሆኑ የየኮንትራክተሮቹን ተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በመሆኑም ሂሳቡን ወደ ኋላ በማጣራት የማስተካከያ ምዝገባ እንዲደረግ፣ ለየኮንትራክተሮቹም ተቀጽላ የሂሳብ ሌጀር በመክፈት ሂሳቡን መከታተል እንደሚገባ ለመ/ቤቱ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.3 በተሰብሳቢ ሂሳብ ያልተመዘገበ

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የዓለም አቀፍ ግዥ ለማከናወን በንግድ ባንክ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተበት ሂሳብ በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ የነበረበት ብር 84,853,734.49 በሂሳብ መደብ 5516 (በተከፋይ ሂሳብ) ተመዝግቦ በመገኘቱ፣ ለሂሳቡ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራለት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

2.4 ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ምርትና አግልግሎቶቻቸውን ለማስተዋወቅ

በገቡት ውል መሰረት የሚያስከፍለው ክፍያ ከ1999-2005 ዓ.ም ከተላለፈው ማስታወቂያ መሰብሰብ የነበረበት ውዝፍ ሂሳባ ብር 36,389,175.05 መኖሩ፣

- በኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ከደንበኞቹ ብር 25,816.59 ከ2000 ዓ.ም እስከ 2003 ዓ.ም ያልሰበሰበው ዓመታዊ የአገልግሎት ውዝፍ የተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ እና
- በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በዱቤ የተሰጠና ከ1971-2004 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ተሰጥቶበት ሳይሰበሰብ ከ33 ዓመት በላይ የቆየ ብር 2,120,858.84 እና በ2005 በጀት አገልግሎቱ ተሰጥቶ ያልተሰበሰበ ብር 1,221,243.57 በጠቅላላው ብር 3,342,102.41 ያልተሰበሰበ ውዝፍ የዱቤ ሂሳብ የሚገኝ መኖሩ ታውቋል፡፡

ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው የስራ አመራር ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

3. የገቢ ሂሳብ

የገቢ ሂሳብ በትክክል መሰብሰቡን እና መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

3.1 የቤተመንግስት አስተዳደር ባልደራስ ከሚገኘዉ የመዝናኛ ስፍራ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የተሰበሰበው ገቢ በዕለቱ ወይም በማግስቱ ባንክ ገቢ የማይደረግ መሆኑ እና የተሰራባቸው ደረሰኞች ተመላሽ ሳይደረጉ ሌሎች ደረሰኞች ወጪ የሚደረጉ መሆኑ፣

3.2 የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ከተለያዩ ገቢ ማስገኛ የስራ ዘርፎች ለመሰብሰብ ካቀደው ብር 320,000,000.00 ውስጥ ብር በድምሩ ብር 235,827,765.19 (73.69%) (ብር 191,790,917.95 በጥሬ ገንዘብና ብር 28,838,307.93 በተሰብሳቢ እና ብር 15,198,539.31 የባለድርሻ ተከፋይ) ብቻ የሰበሰበ መሆኑ፣

3.3 የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ብር 191,790,917.95 በጥሬ ገንዘብ፣ ብር

28,838,307.93 (ተሰብሳቢ) እና ብር 15,198,539.31 የባለድርሻ ተከፋይ በድምሩ ብር 235,827,765.19 ሪፖርት ያደረገ ቢሆንም ለህዝብ ተወካዮች ምክርቤት የባህል ቱሪዝምና መገናኛ ብዙሀን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በተላከው የ2005 ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መሰረት ደግሞ ብር 242,944,263.80 በመሆኑ በሁለቱ ሪፖርቶች መከካከል የብር 7,116,498.61 ልዩነት የሚታይ መሆኑ፣

3.4 በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በበጀት ዓመቱ ከተለያዩ እርዳታ የተገኘው የገቢ ሂሳብ ብር 745,679.93 ገቢው በሂሳብ መደብ 5002 እና 5054 ክሬዲት (በተከፋይ ሂሳብ መደብ) የተመዘገበ መሆኑ፣

3.5 በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከሉሲ ሌጋሲ አውደ ርዕይ በውሉ መሰረት የተሰበሰበውን (እየተሰበሰበ ያለውን) ገቢ ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣

3.6 የብሔራዊ ስነልክ ኢንስቲትዩት ለሚሰጠው አገልግሎት የአገልግሎት ጥያቄ የቀረበበት መጠየቂያ፤ የሥራ ማዘዣ፣ የደንበኞች ፍላጎት መገምገሚያ እና የተሰጠውን አገልግሎት ማረጋገጫ ፤ ከሚጠቃለልበት የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ (መሂ/9) ጋር ተጠቃቅሶ ባለመገኘቱ ኦዲት ለማድረግ አለመቻሉ እና የአሠራር ችግሩ በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ ሳይወሰድበት መገኘቱ፣

3.7 በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከሰበሰቡት የውስጥ ገቢ ብር 16,943,264.65 እና ከዚሁ ሂሳብ ላይ ወጪ ያደረገውን ብር 20,450,499.51 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያላደረገ መሆኑን እንዲሁም ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመበት ከ1999 ጀምሮ የውስጥ ገቢ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ይህም ጉዳይ በ2003 በጀት ዓመት እና በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ በተደጋጋሚ የማሻሻያ ሃሳብ የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ፣

ከላይ ለተመለከቱት የተለያዩ የገቢ ሂሳብ ድክመቶች መ/በቶቹ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4. ወጪ

4.1 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች

ግዥዎች በመንግስት የግዥ ደንብና መመሪያ መሰረት መፈፀማቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ8 መ/ቤቶች ብር 3,695,461.41 ግዥ ከአዋጅ ደንብና መመሪያ ውጭ ተፈጽሞ ተገኝቷል።/ዝርዝሩ በአበሪ-15 ተመልክቷል/

በመሆኑም ከመመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቱን ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል ለወደፊቱ መመሪያው ተፈፃሚ መሆን እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.2 ያለ ሂሳብ መደባቸው የተመዘገቡ ወጭዎች

ወጪዎች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሂሳብ አወቃቀር ሥረዓት /chart of account/መሰረት በትክክለኛው የሂሳብ መደባቸው መመዝገባቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 መ/ቤቶች ብር 994,949.60 ከሂሳብ መደቡ ውጭ የተመዘገበ ወጪ ተገኝቷል። /ዝርዝሩ በአበሪ-22 ተመልክቷል/

የሂሳብ መደብን ጠብቆ ያለመመዘገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅእኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም ከበጀት በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱንም ያዛባል፡፡ በመሆኑም የበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ትክክለኛ የሂሣብ መደቡን ጠብቆ መመዝገብ ያለበት ሲሆን ሂሣቡም በትክክል ስለመመዝገቡ የሚረጋገጥበት ሥርዓትም መዘርጋት አለበት፡፡

4.3 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች

በበጀት ዓመቱ በወጪ የተመዘገበው ደንብና መመሪያን መሰረት የደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ10 መ/ቤቶች ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ብር 8,386,094.52 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል/ዝርዝሩ በአባሪ-16 ተመልክቷል/

አሰራሩ ስራዎች በመደበኛ የስራ ሰዓት እንዳይሰሩ የሚገፋፋና ያልተፈቀዱ ክፍያዎችን በመፈፀም መንግሥትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል በመመሪያው መሰረት መስራት ወይም የሚመለከተውን ክፍል በማስፈቀድ የትርፍ ስዓት ክፍያ መክፈል እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.4 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- የወለጋ ዩኒቨርስቲ ለመሰረተ ልማት ግንባታና ለቆሻሻ ማስወገጃ በተለያዩ ስድስት (6) ክፍያዎች በድምሩ ብር 41,000,000.00 ለGIZ-IS በደብዳቤ ትእዛዝ ብቻ ክፍያ ተፈፅሞ መገኘቱ እና ከእያንዳንዱ ክፍያ ጋር በክፍያው ልክ የተያያዘ የክፍያ የምስክር ወረቀት ያልቀረበ መሆኑ እና
- በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ለአሶሳ የሼህ ሆጄሌ ችሎት ማስጠገኛ አገልግሎት ለተላከው ብር 150,000.00 ገንዘቡ ለተላከለት አካል (ለባለጥቅሙ) ለመድረሱ ማስረጃ አለመቅረቡ ታውቋል፡፡

ከላይ ለተመለከቱት ሁኔታዎች ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.5 ያለአግባብ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ

የወለጋ ዩኒቨርስቲ የዳቦ ግብይት ከተጨማሪ እሴትታክስ ነፃ ሆኖ ሳለ የዳቦ ግዥ ሲፈጸም ብር 124,750.43 የተጨማሪ እሴትታክስ ከፍሎ በመገኘቱ ሁኔታው ተገቢ አለመሆኑን እና ለወደፊቱ ተመሳሳይ የአሰራር ስህተት እንዳይከሰትና ያለአግባብ የተከፈለው ሂሳብ ተመላሽ እንዲደረግ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.6 ከክፍያ ላይ ያልተቀነሰ የተጨማሪ እሴት ታክስና ቅድመ ታክስ

የወለጋ ዩኒቨርስቲው በሻምቡካምፓስ ለሚገነባው የመማርያ ክፍሎች እና ለቤተሙከራ (ለላብራቶሪ) ህንጻ ግንባታ ከተከፈለ ብር 271,189.85

እናብር 266,254.84 ሃያ (20%) ቅድሚያ ክፍያ ላይ በድምሩ ብር 80,616.79 ተጨማሪ እሴት ታክስ አለመቀነሱ እና ብር 5,423.79 ቅድመ ታክስ (Withholding tax) ከመጀመሪያው ክፍያ ላይ ሳይቀነስ መቅረቱ በመታወቁ ሂሳቦቹን ከሚመለከተው የሥራ ተቋራጭ ላይ እንዲሰበስብ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል።

4.7 ያለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ

የደመወዝ ሂሳብ ሠራተኞች ለሰጡት አገልግሎት ብቻ የተከፈለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ከሥራ ለለቀቁ ሠራተኞች ብር 3,737.55 ደመወዝ ተከፍሎ መገኘቱ እና በቤተመንግስት አስተዳደር ለአንድ የመ/ቤቱ ሠራተኛ የመጋቢት /2005 ደመወዝ በድጋሚ ብር 1,557.07 መከፈሉ ታውቋል።

ለየመ/ቤቶቹ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል።

4.8 በወጪ ሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ ከእርዳታ የተገኘ ሂሳብ

በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ከተለያዩ እርዳታ ከተገኘው ገቢ ወጪ የተደረገው ብር 710,319.10 በወጪ ሂሰብ መመዝገብ ሲኖርበት በተከፋይ ተመዝግቦ በመገኘቱ ለሂሳቡ ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል።

4.9 የውሎ አበል ፎርም በትክክል ያልተሞላለት

በብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ የውሎ አበልቅፅ (ፎርም) በትክክል ሳይሞላ ብር 26,586.00 ተከፍሎ መገኘቱ እና በፕሬዚዳንት ጽ/ቤት የውሎ አበል መክፈያ ቅጽ(የሀገር ውስጥ) በትክክል የማይሞላ የነበረ መሆኑ በመታወቁ ለወደፊቱ የውሎ አበል ክፍያ የውሎ አበል ቅጽ የሚጠይቀው መረጃ ሁሉ እንዲሞላ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል።

4.10 የሂሳብ ማስተካከያን በተመለከተ

ማስተካከያ ለተሰራላቸው ሂሳቦች ተገቢው ደጋፊ ማስረጃ መሟላቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን ብር 18,603.36 ሁለት የሂሳብ ማስተካከያ በሚሰራበት ወቅት ማጠቃቀሻ (መነሻ ሰነድ) የሌለው በመሆኑ የማስተካከያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ እና
- በባህልና ቱሪዝ ሚኒስቴር የሂሳብ ማስተካከያ ለተሰራላቸው የማስተካከያ ምዝገባው ከመጀመርያ ምዝገባው የማይጠቃቀስ በመሆኑ የማስተካከያ ምዝገባው መጀመርያ በወጪ በትክክል የተመዘገበ መሆኑን ማረጋገጥ አለመቻሉ

በመታወቁ ለወደፊቱ ተመሳሳይ አሰራር ግድፈት እንዳይከሰት በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል።

4.11 በብልጫ የተከፈለ ወጪ

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፤ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡

- በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ 275 ኩንታል ጤፍገቢ ሆኖ ሳለ 305 ኩነታል ጤፍ ገቢ እንደተደረገ በማስመሰል ብር 41,670.00 በብልጫ እንዲሁም
- በመድን ፈንድ ጽ/ቤት ብር 2,106.00

በድምሩ ብር 43,786.00 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ በመሆኑ በብልጫ የተከፈለው ሂሳብ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድበት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.12 ግብር ያልተቀነሰበት የቤት አበል ክፍያ

- የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጽ/ቤት በ2005 በጀት ዓመት ለምክር ቤቱ አባላት ከሚከፍለው የቤት አበል ላይ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ፤

- የብሄራዊ ስነልክ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር የቤት አበል ላይ ብር 6,300.00 የሥራ ግብር ተቀናሽ አለመደረጉ ታውቋል።

ይህም አዋጅና መመሪያን ተግባራዊ አለማድረግ በህግ ሊያስጠይቅ ከመቻሉም በላይ ሁኔታው በመንግስት ገቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ በመሆኑም በገቢ ግብር አዋጁ እና ደንቡ መሰረት ሊሰበሰብ የሚገባውን የመንግስት የገቢ ግብር ከባለጥቅሞች ላይ መሰብሰብ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.13 ያላግባብ የተከፈለ ክፍያ

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ሁሉ ማስረጃ ቀርቦላቸው የተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በግቢው ለሚያሰራው የስፖርት ሜዳ ግንባታ ከኢትዮጵያ መንገድ ኮንስትራክሽን ጋር በገባው ውል መሠረት (20%) ቅድመ ክፍያ ብር 510,330.98 በመክፈል ስራውን እንዲጀምር ቢሆንም ሙሉ ክፍያውን ብር 2,551,854.90 (100%) እንዲከፈለው ከመደረጉ በተጨማሪ ላልተከናወነ ሥራ የተፈፀመ ክፍያ እንዲሁም ሂሳቡ በቅድመ ክፍያ መመዝገብ ሲገባው በቀጥታ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ አሰራሩ የወጪና የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርትን ከማዛባቱ በተጨማሪ ሥራው ሳይሠራ 100 ፐርሰንት ክፍያ መፈጸም መንግስት ያልተገባ ወጪ እንዲያወጣ ስለሚዳርገው ሂሳቡን በቅድመ ክፍያ አርእስት በመመዝገብ ክትትል ሊደረግበት እንደሚገባ ለወደፊቱም ክፍያ በውሉ መሰረት ሊፈጸም እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.14 ሳይፈቀድ የተከፈለ የበረሃ አበል ክፍያ

የድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ ለመምህራንና ሰራተኞች 20% የበረሃ አበል እንዲፈቀድለት በቁጥር ድ/ደ/ዮ/101/734/2004 በተፃፈ ደብዳቤ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር መ/ቤትን ጠይቆ በቀን 02/13/04 ዓ.ም በቁጥር ሲ.ስ.ሚ30/ጠ13/41/920 በተፃፈ ደብዳቤ መ/ቤቱ ገና በጥናት ላይ በመሆኑ ክፍያው ያለመፈቀዱን የገለፀ ቢሆንም በዩኒቨርሲቲው ከሃምሌ 1/2004 ጀምሮ 20% የበረሃ አበል ክፍያ ብር 6,062,182.75 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

ያልተፈቀደን ክፍያ መፈፀም የመንግስት ገንዘብ እንዲባክን ከማድረጉ በተጨማሪ አሰራሩ የህግ ጥሰትን ስለሚያስከትል የተፈፀመው ክፍያ ለመንግስት ተመላሽ መሆን እንደሚኖርበት ለወደፊቱም ያልተፈቀደ ክፍያ እንዳይከፈል ጥንቃቄ እንዲደረግ ለመ/ቤቱ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.15 <u>ጥራቱ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ገቢ የተደረገ እቃን እና የአገልግሎት ግዥ</u>

የተፈፀሙት ግዢዎች በተቀመጠው እስፔስፊኬሽን እና የተጠቃሚን ፍላጎት ባሟላ መልኩ ገቢ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ ብር 669,084.99 የተገዛው L shape imported table, shelf, የደንብ ልብስ እንዲሁም ለተማሪዎች አገልግሎት ከተለያዩ አቅራቢዎች የሚቀርበው የእንጀራና የስጋ አቅርቦት ስለጥራቱ በተማሪዎች ተወካይ ወይም በኮሚቴዎች እንዲሁም በባለሙያ ሳይረጋገጥ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የሚደረግ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ እንዲሁም የመድን ፈንድ ጽ/ቤት በብር 81,180.74 ለከፈለው የጥገና አገልግሎት በትክክል ስለመጠገኑ በሚመለከተው ክፍል ሳይረጋገጥ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ይህም ጥራቱን ያልጠበቀ እቃ ወይም አገልግሎት እንዲያገኙ ስለሚዳርግ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የእቃው ጥራት ወይም የሚፈለገው አገልግሎት መገኘቱን በቴክኒክ ኮሚቴ ወይም በሚመለከተው ኃላፊ መረጋገጥ እንደሚኖርበት ለመ/ቤቶቹ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.16 <u>አላግባብ የተከፈለ በግንባታ ስራ ቦታ ላይ ስለሚገኝ የግንባታ ግብዓት ክፍያ</u>

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ግንባታ ፕሮጀክት ብር 2,317,337.60 ለግንባታ ስራው ቦታ ላይ የሚገኙ የግንባታ ግብዓቶች (material on site) ክፍያ ተፈፅሟል፡፡ ይህም የግንባታ ወጪውን ሊያሳድገው ከመቻሉ በተጨማሪ ዩኒቨርሲቲው በህጉ ላይ

የተቀመጠውን ተግባራዊ አለማድረጉን የሚያሳይ በመሆኑ ህግን መሠረት በማድረግ መስራት እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.17 ከሚመለከተው ክፍል ስለአልተቀነሰ ሂሳብ

ለሚገነቡት ግንባታዎች መቀነስ የሚገባቸው ተቀናናሾች በአግባቡ ስለመቀነሳቸው እንዲሁም የሂሳብ ምዝገባው በትክክል ስለመመዝገቡ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከሚገነቡ ግንባታዎች ክፍያ ላይ መቀነስ የሚገባው የመያዣ ሂሳብ ብር 1,996,652.25፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 2,262,094.94 እንዲሁም የቅድሚያ ግብር ተቀናሽ ብር 329,872.01 በድምሩ ብር 4,588,619.20 GIZ-IS በተባለው ድርጅት ተቀናሽ ለመደረጉ ከክፍያ ሰርቲፊኬት ላይ ማረጋገጥ የተቻለ ቢሆንም ተቀናሽ የተደረገው ገንዘብ ለባለጥቅሙ መ/ቤት የተላለፈ ለመሆኑ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ከሥራ ተቋራጮች ላይ ተቀናሽ የተደረገው ገንዘብ ለባለጥቅሙ መተላለፉን አለማረጋገጥ ገንዘቡ ለታቀደለት ዓላማ በማዋል ረገድ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ በተጨማሪም የስራ ተቋራጮች የሚፈለግባቸውን የመንግስት ግብርና ታክስ ለመክፈላቸው ማረጋገጥ ስለማይቻል ከሥራ ተቋራጮች ላይ ተቀናሽ የተደረገው ገንዘብ ለባለጥቅሙ ለመተላለፉ በአፋጣኝ መረጋገጥ እንዳለበት ለመ/ቤቱ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.18 ያለፕሮግራሙ የተመዘገበ ወጪ

ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤቱ አገልግሎት የሚውል ፕሪንተር የተገዛበት ብር 113,649.90 ወጪው የፕሮግራም አንድ ሆኖ ሳለ የተመዘገበው በፕሮግራም ሁለት ላይ መሆኑ እንዲሁም የፎቶ ኮፒ ወረቀት የተገዛበት ብር 328,187.60 ወጪው የፕሮገራም ሶስት ሆኖ ሳለ የተመዘገበው ግን በፕሮግራም አራት ሆኖ ተገኝቷል፡፡የየፕሮግራሞቹን የወጪ አፈፃፀም እንዲዛባ ስለሚያደርግ የሂሳብ ማስተካከያ ሊሰራለትና ለወደፊቱም ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5. ተከፋይ ሂሳብ

5.1 በወቅቱ ያልተከፈሉ ተከፋዮች

በሂሳብ መግለጫው ላይ የተመለከተው የተከፋይ ሂሳብ የመ/ቤቱ ትክክለኛ እዳ መሆኑንና ሂሳቡም ትክክለኛ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ8 መ/ቤቶች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ ብር 18,437,299.66 ተገኝቷል።/ዝርዝሩ በአበሪ-28 ተመክቷል/

ለየመ/ቤቶቹ በተከፋይ ሂሳብ ላይ ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግና በመክፈያ ጊዜያቸው ክፍያ በመፈፀም ተገቢው ምዝገባ እና ማስተካከያ ሊሠራ እንደሚገባ በላክናቸው የስራ አመራር ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

5.2 በተከፋይ ሂሳብ የተመዘገበ የእርዳታ ሂሳብ

በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በበጀት ዓመቱ ከተለያዩ እርዳታ ከተገኘው ገቢ ከወጭ ቀሪ ሆኖ የዞረው ብር 35,360.83 በተከፋይ ሂሳብ (5054) ሪፖርት የተደረገ በመሆኑ ለሂሳቡ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራለት አሳስበናል።

6. የበጀት አጠቃቀም

6.1 ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪና ያልተሰረበት በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ኦዲት ሲደረግ በ5 መ/ቤቶች ከበጀት ብር 122,199,033.46 ከበጀት በላይ ወጭ የሆነና በ13 መ/ቤቶች ብር 207,480,182.28 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል። /ዝርዝሩ በአባሪ-29 ተመልክቷል/

በመሆኑም ለየመ/ቤቶቹ ለወደፊቱ ተመሳሳይ የበጀት አጠቃቀም ግድፈት እንዳይደርስ ጥንቃቄ እንዲያደርጉና መንግስት ለሌሎች መሠረታዊ ለሆኑ ሥራዎች ሊያውል የሚችለውን ገንዘብ በበጀት ዓመቱ ስራ ላይ እንዳይውል ሊያደርግ ስለሚችል የበጀት ዝግጅት ጥያቄ መ/ቤቶች ሲያቀርቡ በተጨባጭ ሊሰራ ከታቀደው ተግባር ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ያለፉትን ዓመታት የዕቅድ አፈፃፀም በመገምገም ሊከናወን የሚገባ ሲሆን ለወደፊቱም የበጀት ጥያቄ ሲቀርብ ከእቅድ ጋር እየተገናዘበ

የሚቀርብበት ሁኔታ እንዲመቻች ለኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አሳስበናል::

7. የዕቃና ንብረት አስተዳደርና አጠባበቅ ሁኔታ

7.1 የዕቃዎች ምዝገባና ቆጠራ በተመለከተ

ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	6 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	2 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	4 መ/ቤቶች
ቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም ምዝገባ ያላከናወኑ	2 መ/ቤቶች
ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረት የተገኙባቸው	5 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	14 መ/ቤቶች
ተያያዥነት ያለቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	3 መ/ቤቶች

ሌሎች የንብረት አያያዝ ችግሮች

- በቤተ መንግስት አስተዳር ውስጥ ለሚገኙት ውድ ለሆኑ ጌጣጌጦች እና ቅርሳቅርሶች ምዝገባ የተደረገ ለመሆኑ እና በየዓመቱ ቆጠራ እየተደረገ በሚገኘው ውጤት መሰረት እርምጃ የሚወሰድ ለመሆኑ ማስረጃ ባለመቅረቡ ውድ ለሆኑት ጌጣጌጦች እና ቅርሳቅርሶች ምዝገባ ያላቸው ስለመሆኑም ሆነ በአካል ስለመኖራቸውም ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በአሁኑ ወቅት የሚገኙት የዋናው መድሃኒት ክፍል ባለሙያ ስራ የጀመሩት ከቀድሞው ሰራተኛ ርክክብ ሳይፈፀም መሆኑ፤

- በድሬድዋ ዩኒቨርሲቲ 11 መምህራን የተሰጣቸውን ላፕቶፕ ኮምፒውተሮችና 1 LCD projector ሳያስረክቡ ከዩኒቨርሲቲው የለቀቁ መሆኑን፤

በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

በንብረት ክፍል

- ብዛታቸው 74 የሆኑ የሆቴሎችና ሬስቶራንቶች የደረጃ መለያ የወርቅ እና የብር ቅብ የሚገኙ መሆኑ፣
- በጀርመንኛ፣ጣልያንኛእና ስፓንሽኛ ቋንቋ ታትመው የተዘጋጁ መጽሄቶች ለተጠቃሚዎች ሳይሰራጩ ከአራት ዓመት በላይ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣
- የቱሪዝም ልማት ፖሊሲ በሚል በመጽሐፍ እና በሲዲ መልክ ተዘጋጅቶ በወቅቱ ለተጠቃሚ ሳይሰራጭ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣
- የባህል ፖሊሲ በሚል የተዘጋጀ በርካታ መጽሐፍ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ያለጥቅም በዕቃ ግምጃ ቤቱ የሚገኙ መሆኑ፣
- የቱሪስት መስህብ ቦታዎች የሚያመላክት በኢትዮጵያ ካርታ ስራ ኤጀንሲ የታተመ ካርታ ለተጠቃሚዎች ሳይሰራጭ ያለ ጥቅም ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፣

በኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል

- የቆዩ ኬሚካሎችና የተለያዩ የሕክምና ቁሳቁሶች በንብረት ክፍል ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

በደብር ብርሃን ዩኒቨርስቲ

- በዩኒቨርስቲው አገልግሎት መስጠት የማይችሉ በርካታ ዕቃዎች በንብረት ክፍል ተከማችተው የሚገኙ ከመሆኑ በተጨማሪ ለተለያዩ ድርጅቶች ኮምፒውተሮች በስጦታ የተወገዱ ሲሆን ስጦታውን ከተረከበው አካል ኮምፒዉተሮቹን ስለመረከቡ ማረጋገጫ ሊቀርብ አለመቻሉ፤
- በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶች ላይ የማስወገድ እርምጃ ሳይወሰድ በመድሃኒት ክፍል

ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ እና የተማሪዎች የህክምና አገልግሎት ክሊኒክ መድሃኒት ክፍል ውስጥ ዋጋቸው የማይታወቅና በአሁኑ ወቅት ያሉት የፋርማሲ ባለሙያ ያልተረከቡዋቸው የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው የተለያዩ መድኃኒቶች የሚገኙ መሆኑ፤

- በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ብዛት ያላቸው መወገድ ያለባቸው እቃዎችና መድሃኒቶች መኖራቸው፤
- በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በዓይነትና በቁጥር በርካታ ዕቃዎች በንብረት ክፍል ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

ከላይ ለተመለከቱት የንበረት ሂሳብ አስተዳደር ድክመቶች ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል።

7.2 የተሽከርካሪዎች ሁኔታ

በየመሥሪያ ቤቶቹ ውስጥ ያለው የተሽከርካሪዎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓትና መረጃ አያያዝ በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ5 መ/ቤቶች	120 ተሽከርካሪዎች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ6 መ/ቤቶች	122 ተሽከርካሪዎች
በተለያዩ ድርጅቶች ሥም ሊቢሬ ያላቸው ወደ መ/ቤቱ ስም ያልተቀየረላቸው	በ2 መ/ቤት	3 ተሽከርካሪዎች

ከላይ በተመለከቱት የተሽከርካሪዎች ሁኔታ ላይ ተገቢው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል።

8. ልዩ ልዩ

8.1 በመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ከተሸጡ ድርጅቶች የተጠቃለለ የሂሳብ ሪፖርት (consolidated financial statement) የማይዘጋጅ በመሆኑ የድርጅቶችን የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤መ/ቤቱ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ በባለፉት በጀት ዓመታት በተከታታይ የኦዲት አስተያየት

የተሰጠ ቢሆንም በ2005 በጀት ዓመትም እርምጃ ያልተወሰደ በመሆኑ የባላደራ ቦርዱን ልዩ ፈንድ ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ ሳይቻል በመቅረቱ ለሂሳቡ ተገቢው የእርምት እርመጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ በዩኒቨርሲቲው ወጪ ትምህርታቸውን የተከታተሉና ግዳጃቸውን ሳይወጡ ዩኒቨርሲቲውን የለቀቁ 63 ሰራተኞች ላይ እርምጃ ያልተወሰደ በመሆኑ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት

የ2005 በጀት ዓመት ዕቅድና ክንውን ሪፖርት

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዕቅድና ክንውን በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና በበጀት አንጻርና በእቅዱ መሰረት (በእቅዱ መሰረት ያልተከናወነ የኦዲት ሥራ የለም) በማከናወን ይህ ሪፖርት ከጥር 2005 ዓ.ም.እስከ ከታህሳስ 2006 ዓ.ም.ድረስ ያለውን የአንድ ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ለማመላከት የተዘጋጀ ሪፖርት ነው፡፡

ሪፖርቱም ከተዘጋጀው ዕቅድ አንፃር የተከናወኑትን የኦዲት ሥራዎች ከማመላከቱም ባሻገር፣ የተገኙትን ዋና ዋና ግኝቶች አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡

በዚህም መሰረት የ2005 በጀት ዓመት ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

I. ዕቅድና ክንውን፣

የተሰጠው የኦዲት አስተያየት፣

ኦዲት በተደረገት መ/ቤቶች የተሰጠው አስተያየት ሲጠቃለል ነቀፌታ የሌለበት 3 መ/ቤቶች፣ ከጥቂት ስህተቶች በስተቀር አጥጋቢ በመሆኑ ነቀፌታ ያለበት (Except for opinion) 18 መ/ቤቶች የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ (Adverse opinion) 7 መ/ቤቶችና አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች 5 መ/ቤቶች ናቸው፡፡

II. ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣

1. የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሣብ፣

1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣-

የጅማ ዩኒቨርስቲ	ብር	548,422.10
ሠመራ ዩኒቨርስቲ		340,682.87
የወሎ ዩኒቨርስቲ		319,103.36
ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ		44,761.00
ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ		19,124.00
በድምሩ	ብር	1,272,093.33

በጉድለት የሚታይ ለመሆኑ ተረጋጧል፡፡ በጉድለት ከታየው ሂሳብ ውስጥ የጅማ ዩኒቨርስቲ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ገንዘቡን ካጎደለው ሠራተኛ ሊሰበሰብ ሲገባ፣ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ወደ መደበኛ ሂሳብ ተመላሽ በማድረግ የጥሬ ገንዘብ ጉድለቱ ተሸፋፍኖ ከሪፖርት እንዲወጣ የተደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች፣

የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ በደንብና መመሪያ መሠረት መያዙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች፣ የሚታይባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር በአባሪ-5 ተመልክቷል፡፡

2. ተሰብሳቢ ሂሳብ፣

2.1 ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ፣

የሰነድ ሂሳብ በወቅቱ መወራረዱ ሲጣራ በ23 መ/ቤቶች ብር 239,453,035.85 የሰነድ ሂሳብ በደንቡ መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

በተጨማሪም

- መቀሌ ዩኒቨርስቲ በድምሩ ብር 6,032,845.00 በኮሌጆቹ ገንዘቡ ስለመከፈሉ የተሟላ ማስረጃ ቀርቦ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑና በማጠቃለያ ሪፖርት ላይ በተሰብሳቢ ሂሳብ የተያዘ መሆኑ፣
- መቀሌ ዩኒቨርስቲ ብር 20,849,272.61 በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4210 በመንግስት መ/ቤት ውስጥ ሌሎች ቅድመ ክፍያዎች ተሰብሳቢ ሂሳብ ተብሎ የተያዘ ሲሆን ሂሳቡ ለምግብ፣ ለነዳጅ እና የትርፍ ሰዓት የተከፈሉ ክፍያዎች ቀጥታ ወጪ መሆኑ፣
- አዲግራት ዩኒቨርስቲ ብር 14,803.55 ለኢትዮ ቴሌኮም ክፍያ ተፈፅሞ ያለአግባብ በተሰብሳቢ ሂሳብ የተመዘገበ መሆኑ፣፣

ተረጋግጧል፡፡

3. የገቢ ሂሳብ፣

3.1. በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ ህግ መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ፣

• የጅማ ዩኒቨርስቲ	ብር	1,494,517.99
• የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ		389,197.78
• አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ		275,670.06
• አዲግራት ዩኒቨርስቲ		29,540.00
• አክሱም ዩኒቨርስቲ		47,158.80
• መቀሌ ዩኒቨርስቲ		138,834.74
በድምሩ	ብር	2,374,919.37

የገቢ ግብርና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 1,494,517.99 ለሠራተኞች እና መምህራን የቤት አበል ከሚከፈላቸው ላይ ታክስ ቆርጦ ማስቀረትና ለግብር ሰብሳቢ መ/ቤት መክፈል ሲገባው፣ ዩኒቨርስቲው ታክሱን ከውስጥ ገቢው በመሸፈን ክፍያ የፈጸመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

3.2 በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ የገቢ ሂሳብ፣

- የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ፣ የመደወላቡ ዩኒቨርስቲ፣ የሠመራ ዩኒቨርስቲ፣ የወሎ ዩኒቨርስቲ፣ የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ የዩኒቨርስቲው የውስጥ ገቢ ማስገኛ ምንጮች በዝርዝር የሚያሳይ ማስረጃና የጸደቀ ተመን የሌለውና ሂሳቡም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ሪፖርት የማይደረጉ መሆኑ እና የመቱ ዩኒቨርስቲ ብር 1,178,906.78 የውስጥ ገቢ በባንክ ሂሳብ የሚታይ ቢሆንም የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠ፣ ያለተመዘገበና ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- የጅማ ዩኒቨርስቲ በዩኒቨርስቲው የሚገኙ የገቢ ማመንጫዎች የአደረጃጀት፣ የአወቃቀር፣ የመተዳደሪያ ደንብ፣ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት፣ የገቢ፣ የወጪና የንብረት ደረሰኞች እና የሪፖርት አዘገጃጀት በተሟላ መልኩ የሌላቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

3.3 ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ያልተደረገ ገቢ፣

የሠመራ ዩኒቨርስቲ ከተፈጸሙ ግዢዎች ላይ የሰበሰበው (ቀንሶ ያስቀረው) ከተከፋይ ተቀናሽ ታክስ ብር 202,139.96፣ የተጨማሪ እሴት

ታክስ ብር 1,447,139.96 እና ለሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ጭምር በጋራ ከፈጸማቸው ግዢዎች ቀንሶ ላስቀረው ደረሰኝ ከመቅረቡ በስተቀር በተቋሙ የሂሳብ ስርዓቱን ተከትሎ በተከፋይ ያልተያዙና ድርጅቱም ለሚመለከተው አካል ገቢ ለማድረጉ ማረጋገጫ ያልቀረበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

3.4 ማስረጃ ባለመሟላቱ የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ፣

- የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ የባንክ ሂሳብ የውስጥ ገቢ እና የተለያዩ ሂሳብ ማስቀመጫ በየወሩ መጨረሻ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ የማይዘጋጅ በመሆኑ የባንክ ሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- አዳማ ዩኒቨርሲቲ የውስጥ ሂሳብ የገቢ ማስገኛ ምንጮች ዓይነት (Internally Generated Revenue Items/Chargeable Services) እንዲሁም የእያንዳንዱ የገቢ ማስገኛ ምንጭ የማስከፈያ ዋጋ ተመን/ታሪፍ (Charge Rates) በዝርዝር የሚገልጽና በሚመለከተው አካል የጸደቀ ዶክመንት ለኦዲት ሊቀርብ ባለመቻሉ፡ ከፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት በተገኘው መረጃ መሰረት ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበ ብር 26,730,773.12 ከውስጥ ሂሳብ ወጪ የተደረገ ብር 7,515,257.06 በተቋሙ የ2005 በጀት ዓመት የሂሳብ መግለጫዎች ባለማካተቱ ሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የዩኒቨርሲቲ፣የውስጥ ሂሳብ የገቢ ማስገኛ ምንጮች ዓይነት (Internally Generated Revenue Items/Chargeable Services) እንዲሁም የእያንዳንዱ የገቢ ማስገኛ ምንጭ የማስከፈያ ዋጋ ተመን/ታሪፍ (Charge Rates) በዝርዝር የሚገልጽና በሚመለከተው አካል የጸደቀ ዶክመንት ለኦዲት ሊቀርብ ባለመቻሉ፡ ከውስጥ ገቢ ማመንጫ የሰበሰበውን ብር 12,518,467.05 ከውስጥ ገቢው ላይ ብር 13,297,366.17 ወጪ ማድረጉን ይሁን እንጂ የውስጥ ገቢና ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት አለማድረጉን እንዲሁም በተቋሙ የሂሳብ መግለጫዎች ባለማካተቱ ሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ዩኒቨርስቲው ከተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች እና በተለያዩ ዲፓርትመንቶች በማስተማር አገልግሎት የሚያገኘውን ገቢ ባግባቡ መዝግቦ መያዙን ማጣራት ሲደረግ ለእያንዳንዱ ኮርስ በ/credit hour/ የተተመነ የማስከፈያ ዋጋ ተመን /ታሪፍ የሚገልጽና በሚመለከተው አካል የጸደቀ ሠነድ የሌለ በመሆኑ ሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

3.5 <u>በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ ሌሎች የአሠራር ድክመቶች፣</u>

- የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ በባንክ ሂሳብ መግለጫ መሰረት በውስጥ ገቢ በድምሩ ብር 2,085,354.01 የሚታይ ሲሆን፣ በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ ግን ብር 4,329,030.23 በባንክ እንዳለ ተደርጎ ሪፖርት በመደረጉ በብልጫ ብር 2,243,676.22 ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣
- አክሱም ዩኒቨርስቲ ቤተመፃህፍትና ኢንፎርሜሽን ማእከል ማባዣ ወረቀት በብር 1,029,940.00 ለህትመት ክፍል ከመደበኛ በጀት ተገዝቶ የተሰጠው ቢሆንም የተለያዩ የህትመት አገልግሎት ሰጥቷል ተብሎ በድምሩ ብር 1,305,483.70 የተከፈለ መሆኑ፣
- የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ለመኪና መጠለያ እና ማቆሚያ እንዲሰራለት ለኢንጂነሪንግ ኮሌጅ ብር 3,449,579.40 እና ተደራራቢ አልጋ እና ችፑድ እንዲሰራለት ለቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ኮሌጅ ብር 12,186,065.56 በጠቅላላው ብር 15,635,644.96 ድርጅቶቹ የራሳቸው የሆነ ህጋዊ ሰውነት ሳይኖራቸው እና እንደ ማንኛውም የንግድ ድርጅት ህጉ የሚጠይቀውን ሁሉ ሳያሟሉ የአገልግሎቱ ክፍያ የተከፈለ መሆኑ፣
- የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ተጠቃሚዎች የአገልግሎት ክፍያ በዩኒቨርሲቲው ባንክ ሂሳብ ገቢ በማድረግ የባንክ አድቫይስ ቢያቀርቡም የሚሰበሰበው ገቢ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ ተጠቃሎ የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠ ሲሆን፣
- የአርባምንጭ ዩኒቨርስቲ የውስጥ ገቢ የተለያዩ የውስጥ ገቢዎች ቋት ያልተቋቋመላቸው መሆኑ፣ በውስጥ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ላይ የገቢ ምክንያት በትክክል የማይመዘገብና አመዘጋገቡም

የተደበላለቀ መሆኑ፣ ከትርፍና ኪሳራ መግለጫ ውጭ/Income Statement/ የውስጥ ገቢ ሂሳብ የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚገልጹና አግባብነት ያላቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ፣ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ማመዛዘኛ እና የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ የማያዘጋጅ መሆኑ፣ ተረጋግጧል፡፡

4. <u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

4.1. <u>ምንም ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ፣</u>

በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ ለመመዝገቡ ኦዲት ሲደረግ፣ በ5 መ/ቤቶች ብር 65,228,001.96 ምንም ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል:: /ዝርዝሩ በአባሪ-14 ተመልክቷል/ ከዚህም ውስጥ ፣

የጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 48,055,198.58 ለተከፈለበት ክፍያ ህጋዊ የወጪ ደረሰኝ /ማስረጃ/ ሳይቀርብ በዱቤ ደረሰኝ ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦና ተወራርዶ መገኘቱ፤

የሚዛን-ቴፒ ብር 10,258,169.01 የተጨማሪ ሥራ እና የዋጋ ማስተካከያ የተደረገበት ማስረጃዎች ሳይቀርቡ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኙት ዋናዋናዎቹ ናቸው፡፡

4.2 <u>የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፣</u>

በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ የተሟላ የወጪ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ11 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 94,846,112.08 የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበላቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-13 ተመልክቷል/

ከዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፣ በአርባምንጭ ዩኒቨርስቲ በድምሩ ብር 47,738,302.12 ሲሆን ብር 11,124,979.56 የክፍያ ምስክር ወረቀት ሳይቀርብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣ በድምሩ ብር 10,004,743.70 የኮንስትራክሽን የዋጋ ማስተካከያ (Price Adjustment) ክፍያ በወቅቱ ግዢ ለተፈጸመበት የተገኘ የዋጋ ማስረጃ ከክፍያ ሰነዱ ጋር

አለመቅረቡ፣ በድምሩ ብር 26,608,578.86 ተከፋይ ሂሳብ የተሟላ መረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

አዳማ ዩኒቨርሲቲ ለዩኒቨርሲቲው መምህራን የጋራ መኖሪያ ቤቶች ሕንፃ ግዥ ለአዳማ ከተማ መስተዳድር ብር 3,781,139.31 በባንክ የተከፈለ ቢሆንም የግዥ የውል ስምምነት ሠነድ፣ እንዲሁም የይዞታ ካርታና የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አለመቅረቡ፡ ዛምና ኤክስፕረስ ኢንተርናሽናል ለተባለው ድርጅት በቁጥር 4,000 ባለ ክፍልፋይ ትሪ ግዥ ብር 363,400.00 የተከፈለ ቢሆንም ለሂሳብ ማወራረጃነት የቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ፤

የጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 2,428,878.90 ለሞዴል ፋርማሲ ከታህሣሥ 2004 እስከ ሰኔ 2004 ዓ/ም ለተማሪዎች ለህክምና አገልግሎት የሚውል መድሐኒት ለማን እንደተሰጠና መጠኑ ሳይገለጽ በዱቤ የሰጠበት በሚል ያለበቂ ማስረጃ ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

የመቱ ዩኒቨርስቲ ብር 1,572,385.27 ለሚያወጣ ግዥ የቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ፤ በብር 806,799.40 ዕቃዎች ሲገዙ የቀረበው ደረሰኝ ተከታታይ ቁጥር፤ የድርጅቱ ስምና አድራሻ የማይገልጽ ሲሆን፤ ድምራቸው በብር 691,583.82 ግዥ ሲፈጸም ደግሞ ድርጅቶቹ ገንዘቡን ለመቀበላቸው ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ እና ተቋራጮች የተጠቀሙበት ሲሚንቶና የአርማታ ብረት ወጪ የሆነበት የንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞ/22) ከክፍያ ሠነዱ ጋር ተያይዞ አለመቅረቡን፤

የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ በብር 1,650,155.10 የተለያዩ ዕቃዎች ተገዝተው የቀረበው ደረሰኝ የተሟላ ማስረጃ የሌለውና ተራ ደረሰኝ ሲሆን፣ ብር 40,000.00 ዓመታዊ የፀረ ኤድስ አባልነት መዋጮ ደግሞ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑንና በድምሩ 1,690,155.10 የተሟላ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልቀረበለት መሆኑ፣

በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 1,122,533.26 ቀረጥ የተከፈለባቸው ንብረቶች ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ለኦዲት አለመቅረቡ እና ብር 5,700,000.00 የቤት ኪራይ ወጪ

የተሟላ የጨረታ ሠነድ ያልቀረበለት እና እስከ ብር 20,000.00 ወጪ የማጽደቅ ውክልና በተሰጠው ኃላፊ የጸደቀ መሆኑ፣

ተረጋግጧል፡፡

4.3 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች፣

ኦዲት በተደረገት መ/ቤቶች ደንብና መመሪያ ተጠብቆ ክፍያ መፈጸሙ ሲጣራ በ12 መ/ቤቶች ብር 39,385,056.45 ሚሊዮን ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-16 ተመልክቷል/ ከዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ

- መመሪያው ከሚፈቅደው ውጭ የቤት አበል መክፈል፣ መጨመር፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈጸም፣
- የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት እና ም/ፕሬዚዳንቶች ከሶዶ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ በትብብር የመኖሪያ ቤት ተሰጥቷቸው ሳለ የቤት አበል በጥሬ ገንዘብ የሚከፈላቸው መሆኑ፣
- ማበረታቻ (ቶፕ አፕ) በሚል ከውስጥ ገቢ ክፍያ የሚከፈላቸው መሆኑ፣
- መቀሌ ዩኒቨርስቲ ለተለያዩ ኮሚቴዎች በድምሩ ብር 129,983.76 ፣ ለቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ፕሮዳክሽን ማዕከል ለ105 ሠራተኞች ማዕከሉ ለሰራቸው ስራዎች የትርፍ ክፍፍል በጠቅላላ ድምር ብር 2,255,088.48 ከደንብና መመሪያ ውጭ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣
- ስለመኖሪያ ቤት አበል ክፍያ የተላለፈውን የአፈጻጸም መመሪያ ውጭ ለመኖሪያ ቤት አበል ብልጫ ተከፍሎ መገኘቱ እና የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህርን የወር ደመወዝ ላይ 50% (በሙቶ) እየታሰበ ብር 1,464,649.50 ለክሊኒካል አልዋንስ ከደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑ፣

ተረጋግጧል፡

4.4 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች፣

የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይከተል፡- በ15 መ/ቤቶች ብር 133,397,807.60 ግዥውን በመከፋፈል፣ በቀጥታ ግዥ፣ ያለበቂ

ተወዳዳሪና በውስን ጨረታ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-15 ተመልክቷል/

4.5 ያለ ሂሳብ መደቡ የተመዘገበና ሪፖርት የተደረገ ወጪ ሂሳብ፣

የተመዘገበው የወጪ ሂሳብ መደቡን ጠብቆ መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ7 መ/ቤቶች ብር 8,525,704.05 (አባሪ 22) ትክክለኛ የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ ተመዝግቦና ሪፖርት ተደርጎ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

4.6 የተለያዩ የመሰረተ ልማት ግንባታ ወጪዎችን በተመለከተ፣

4.6.1 ለተለያዩ ለግንባታ የቀረቡ ዕቃዎች /በሥራ ላይ ላልዋሉ Materials on site ተብሎ የተከፈለ፣

የሠመራ ዩኒቨርስቲ ብር 9,145,211.05፣ የጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 49,725,743.31፣ የመቱ ዩኒቨርስቲ ብር 2,642,230.59፣ የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 1,328,846.70 እና አዲግራት ዩኒቨርስቲ ብር 1,390,357.18 በጠቅላላው ብር 64,232,388.83 በደንብና መመሪያ ያልተደገፈ በግንባታ ላይ ላለ ዕቃ /material on site/ የተከፈለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

4.6.2 ያልተሰበሰበ በብድር የተሰጡ የግንባታ ዕቃዎች ከክፍያቸው ተቀናሽ ያልተደረገ፣

በብድር ከተሰጡ የግንባታ ዕቃዎች ከክፍያቸው ተቀናሽ እየተደረገ የሚሰበሰብ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ4 መ/ቤቶች ብር 18,281,997.57 ከየድርጅቶቹ ገቢ ያልተደረገ/ያልተሰበሰበ ሂሳብ መሆኑ ተረጋግጧል:: /ዝርዝሩ በአባሪ-26 ተመልክቷል/

በተጨማሪም የአዲግራት ዩኒቨርስቲ ብር 499,421.00፣ የአክሱም ዩኒቨርሰቲ ብር 232,962.40፣ እና የወላይታ ዩኒቨርስቲ ብር 219,709.00 ድርጅቶቹ በውላቸው መሠረት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ለመንግስት ገቢ መሆን የነበረበት የጉዳት ካሳ ሳይቀነስ መገኘቱና በእያንዳንዱ ሥራ

ተቋራጭ ስም ቋት (ሌጀር) በማቋቋም ያለበትን እዳ፣ በየክፍያ ሰርተፍኬቱ ላይ የሚታየውን ከሥራ ተቋራጩ ላይ የተቀነሰውን የብረት፣ የሲሚንቶ እና የመስታወት ዋጋ የማይመዘገብ መሆኑ፤ ተረጋግጧል፡፡

4.6.3 በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ቅድሚያ ክፍያ፣

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ3 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ብር 17,913,138.82 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገቦ ተገኝቷል:: (አባሪ 17)

4.6.4 ሌሎች ከግንባታዎች ጋር የተያየዙ ችግሮች፣

- የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ በድምሩ ብር 17,314,128.17 በክፍያው ሰርተፍኬት ላይ አማካሪ መሐንዲሱ ሳያረጋግጥ የምህንድስና ቴክኒክ ቡድን መሪ ባረጋገጠው ብቻ ለደቡብ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ እና በድምሩ ብር 223,475.82 ከክፍያ ሰርተፍኬቱ በላይ የተከፈለ መሆኑ ፣
- የሠመራ ዩኒቨርስቲ ብር 4,934,260.08 ለተለያዩ የመሠረተ ልማት አገልግሎት የሚውሉ ብረቶችና የኤሌክትሪክ ዕቃዎች በGIZ ተገዝቶ በዩኒቨርስቲው ክፍያ የተፈጸመባቸው የግንባታ ዕቃዎች ተቋራጮቹ የተረከቡት እንጂ በቀጥታ ለዩኒቨርስቲው አገልግሎት ለመዋሉ ማረጋገጫ ያልቀረበ መሆኑ፤ ብር 98,012,990.05 ዋጋ ያላቸው የግንባታ ሥራዎች Bill of Quantity የማዘጋጀት፤ የጨረታ ዶክሜንት (የቴክኒክ) መገምገም፤ የክትትልና ቁጥጥር ተግባር የማከናወን ፤የክፍያ መጠየቂያ ሰርቲፊኬት ትክክለኛነት በማረጋገጥ እስከ ሰኔ 30/2005

ለግንባታዎቹ ብር 65,583,734.71 ክፍያው እንዲፈጽም የማድረግ ተከታታይነት ያላቸው ሥራዎች በተቋሙ የግንባታ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የሚከናወኑ መሆኑ፤ የተሠራው ሥራ ዓይነትና መጠን የሚገልጽ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 467,762.99 ትረስት ድርጅት ለተባለ እንዲከፈለው በGIZ የታዘዘ መሆኑ፤ ብር 985,921.33 ዕቃው በዩኒቨርስቲው የግንባታ ሥራ የሚያከናውኑ ተቋራጮች ያልተረከቡት የGIZ የሰመራ የግንባታ አካባቢ ግምጃ ቤት የተረከበው ለዩኒቨርስቲው አገልግሎት ለመዋሉ ማረጋገጫ ያልቀረበ መሆኑ፤ ውል ከተሰጠ ሂሳብ ብር 30,551,273.18 ውስጥ ብር 2,389,229.00 (24.18) አማካሪ መሃንዲሱ ከተፈቀደለት የሥራ ለውጥ ትዕዛዝ በላይ ለሰጠው ሥራ የተከፈለ መሆኑ፤ ግንባታዎች መጠናቀቅ ከሚገባቸው ጊዜ በላይ የሚቆዩ መሆኑ፣ ከተፈቀደው 30% የቅድሚያ ክፍያ በላይ የሚሰጥ መሆኑ፣ በተገባው ውል መሠረት ግዴታቸውን በማይወጡ ተቋራጮች ላይ እርምጃ አለመወሰዱ እና አንዳንድ ተቋራጮች የሲሚንቶና የብረት እዳ የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡ፣

- የወልድያ ዩኒቨርስቲ ከዩኒቨርስቲው ግቢ የሚገኝ የተመረጠ አፈር የግንባታ አፈር ግብዓት(Selected Material) ተቋራጮቹ በነፃ እየተጠቀሙ በድጋሚ ክፍያ የሚፈጸምበት መሆኑንና ለሌላ የግንባታ ሥራ ላለመዋሉ ቁጥጥር አለመደረጉን፤ ለግንባታ ሥራዎች የተከፈለው የገንዘብ መጠን ከግንባታው የእድገት ደረጃ አፈጻጸም በልጦ መታየቱና ከውለታው በላይ ተፈጽሞ መገኘቱ፣ ግንባታዎች በጊዜው የማይጠናቀቁና የሚዘገዩ መሆኑ እና ውለታቸውን ያልተወጡ የሥራ ተቋራጮች ላይ የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፤
- የወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 6,144,416.64 ከተፈቀደው 30% የቅድሚያ ክፍያ መጠን በላይ ተከፍሎ መገኘቱ፣

የተገዙት የመምህራን መኖርያ ቤቶች ሥራቸው ተጠናቆ አገልግሎት እንዲሰጡ አለመደረጉ፣ የግንባታ ቡድን ተከታታይነት ያላቸውን ሥራዎች የሚሠራ መሆኑ (የጨረታ ሰነድ መገምገም፣ ቢል ኦፍ ኳንቲቲ የማዘጋጀት፣ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ የክፍያ ሠረተፊኬት ትክክለኛነት ማረጋገጥና እንዲከፈል የማድረግ)፣ የፕሮጀክቶች ማጠናቀቂያ ጊዜ ከተገባው ውለታ በላይ የሚዘገዩ መሆኑ፣__ግንባታውን በወቅቱ በማያጠናቅቁና ሥራውን በሚያቋርጡ ተቋራጮች ላይ እርምጃ አለመወሰዱ እና አንዳንድ የግንባታ ሥራዎች በእቅድና በበጀት ያልተደገፉ መሆኑ፣

- የጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 71,127,580.12 ለተጨማሪ የግንባታ ሥራ ትእዛዝ የተከፈለ ሲሆን፣ ለአንድ ሳይት እስከ 17 ጊዜ የተደረገና ተጨማሪ ሥራው ያስፈለገበት ምክንያት ሳይቀርብ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፡
- የመቱ ዩኒቨርስቲ ብር 403,950.63 የውሃ ፍጆታ ሂሳብ በውል ስምምነቱና በክፍያ ሠነድ በዩኒቨርስቲው እንደሚሸፈን ሳይጠቀስ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣ ግንባታዎች በጊዜው የማይጠናቀቁና የሚዘገዩ መሆኑ እና ቅድሚያ ክፍያ ከተሰጣቸው ተቋራጮች መካከል አብዛኛዎቹ ግንባታውን በማቋረጥ ላይ የሚገኙ መሆኑን፤
- የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 867,608.18 የውሃ መኪናና የጀነሬተር ኪራይ ከውል ውጪ ተከፍሎ መገኘቱ እና ከእያንዳንዱ የግንባታ ተቋራጭ የሚፈለገውን የቅድሚያ ክፍያ መጠን፣ ተመላሽ ያደረጉትንና በቀሪ ያለባቸውን እዳ የሚገልጽ ማስረጃ ባለመቅረቡ ሂሳቡን ማጣራት አለመቻሉ፣
- የቡሌ-ሆራ ዩኒቨርስቲ የግንባታ ሥራዎች በውሉ መሠረት አለመጠናቀቃቸው፣
- የመደወላቡ የኒቨርስቲ ብር 6,465,765.88 ለሥራ ተቋራጮች በብድር ከተሰጠው ስሚንቶ ተመላሽ

የተደረገ ቢሆንም ገንዘቡ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ አለመደረጉ፣

- የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ የዋናው ግቢ አጥር ግንባታ አልፊቲህ ኮንስትራክሽን ከተባለው ሥራ ተቋራጭ ጋር በተፈጸመ ውል መሰረት ቅድመ ክፍያ ብር 817,068.62 ተከፍሎት እንደነበር ቢታወቅም፣ የግንባታ ሥራው ጉሌድ ኮንስትራክሽን ከተባለ ሌላ ሥራ ተቋራጭ ጋር ውል በመግባት እየተከናወነ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ለመጀመሪያው ሥራ ተቋራጭ አልፊቲህ ኮንስትራክሽን የተከፈለው ቅድሚያ ገንዘብ ተመላሽ ለመደረጉ ማስረጃ ካለመቅረቡም በተጨማሪ ሥራ ተቋራጩ በውል መሰረት ባለመፈጸሙ እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፤ በ2004 በጀት ዓመት ከሥራ ተቋራጮች የተመለሰው የስሚንቶና የግንባታ ዕቃዎች ዋጋ ብር 4,291,813.46 በወጪ (Expenditure Debit) በማድረግ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተላለፈው ሂሳብ በፈሰስ ለመያዝ ማስተካከያ ሲሠራ የፈሰስ ሂሳብ 4009 ዴቢት የተጣራ ሃብት ክሬዲት ተብሎ መያዝ ሲገባው፣ (Expenditure) ክሬዲት በመደረጉ የካፒታል የወጪ ሂሳብ አላግባብ ዝቅ እንዲል የተደረገ መሆኑ፣
- የወልቂጤ ዩኒቨርስቲ Infrastructure Phase I Lot-B ፕሮጀክት ለሥራ ተቋራጩ ብር 12,791,073.40 የተከፈለው ቢሆንም፣ በመጀመሪያው ምዕራፍ የተገነባው መንገድ ሙሉ በሙሉ ከአገልግሎት ውጭ መሆኑ፤ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ እና በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት በጉራጌ ዞን የወልቂጤ ከተማ ቤቶች ልማት ፕሮጅክት ጽ/ቤት በጅምር ላይ ያሉ አስራ ስድስት ህንጻዎች ግዥ በተፈጸመው ስምምነት መሰረት ብር 13,960,852.38 የተከፈለ ቢሆንም፣ በውሉ መሰረት የይዞታ ካርታ እና

የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ዩኒቨርስቲው ያልተረከበ መሆኑ፣

- ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ A.M.B.Constrcution የሥራ ተቋራጭ ከሚገነቡ ፕሮጀክቶች ውስጥ፡- Agriculture Faculty Lot-2፤ Agriculture Faculty Lot-4 የግንባታው ሥራ ሙሉ በሙሉ የተቋረጠ መሆኑንና ሥራ ተቋራጩ ግንባታውን በማቋረጥ ጥለው መሄዳቸው እየታወቀ ተቋራጩ በውል መሠረት ባለመፈጸማቸው በተቋሙ ላይ ላደረሱት ጉዳት እርምጃ አለመወሰዱ፣ የግንባታ ሥራ ተቋራጭ በውለታ ሰነዱ መሰረት ጥራቱን ጠብቆ ግንባታውን ለማከናወኑና በሥራ ጥራትና ጉድለቶች ለሚደርሱ ጉዳቶች የግንባታው ሥራ ከተጠናቀቀ በኃላ ቢያንስ ለ1 ዓመት የሚቆይ የጉዳት ማካካሻ ዋስትና የፕሮጀክቱን ግምት 20 በመቶ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት ከታወቀ የመድን ድርጅት እንድያቀርብ ደንቡ ቢያዝም ሥራ ተቋራጮች፡-

1. ሳትኮን ኮንስትራክሽን ብር 59,540,789.45
2. ኦርቢት ሥራ ተቋራጭ ብር 29,915,581.44
3. ካሳሁን አበጀ ሥራ ተቋራጭ ብር 8,593,821.14
4. ዮቴክ ሥራ ተቋራጭ ብር 29,908,544.73
5. ጋድ ሥራ ተቋራጭ ብር 39,045,908.84

ቅድሚያ ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም የመድን ዋስትና እንዲያቀርቡ አለመደረጉ እና በዩኒቨርሲቲው ከሚከናወኑት ግንባታዎች ውስጥ በቁጥር ከ 7 በላይ ፕሮጀክቶች በውል ከተወሰነው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና የማስረከቢያ ጊዜ ከ 2 ዓመት በላይ የዘገዩ መሆኑ፣

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ አኪር ኮንስትራክሽን በተባለው ሥራ ተቋራጭ የሚከናወነው የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የሪፈራል ሆስፒታል በውሉ መሰረት በውል ስምምነት የተወሰነው ፕሮጀክት የግንባታው ሥራ ደረጃ /Physical Status/ 39.17 % በመቶ ብቻ የተከናወነ ከመሆኑም በላይ

የሥራ እንቅስቃሴ ባለመኖሩ ግንባታው እየተከናወነ አለመሆኑን ለማየት የተቻለ ሲሆን፤ የአፄ ቴዎድሮስ ግቢ Lot 8 የድህረ ምረቃ ኮምፕሌክስ የግንባታው ሥራ የፊዚካል አፈጻጸሙ 64.52 % በመቶ ብቻ በመሆኑ እና ከ2 ዓመት ከ 6 ወር በላይ ግንባታው በመዘግየቱ በውል መሠረት ባለመፈጸም በዩኒቨርስቲው ላይ የደረሰ ጉዳትና የኪሣራ መጠን በማረጋገጥ በሥራ ተቋራጩ ላይ እርምጃ አለመወሰዱ እና በዩኒቨርሲቲውና ኮንስትራክሽን ሃ/የተ/የግ/ማህበር መካከል በተፈጸመው የግንባታ ውል ስምምነት መሰረት በማራኪ ግቢ የሚከናወነው Lot 11 ዶርሚታሪ ግንባታ የግንባታው የፊዚካል አፈጻጸም 64.52 በመቶ ብቻ ከመሆኑም በተጨማሪ ግንባታው ከ 1 አመት ባለይ በመዘግየቱ ዩኒቨርሲቲው በውሉ መሠረት ባልፈጸሙት ሥራ ተቋራጭ ላይ አፋጣኝ እርምጃ አለመወሰዱ፤ ተረጋግጧል፡፡

4.7 በብልጫ የተከፈለ፤

የሠመራ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች መኝታ ክፍል ግንባታ ከተፈጸመው ብር 332,070.24፣ አዳማ ዩኒቨርሲቲ ለምግብ አቅርቦት ክፍያ ሲፈጸም ብር 11,535.20፣ አሶሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 442,550.15 ለሥራ ተቋራጭ እና በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 12,724.00 ለውሎ አበል ብልጫ ተከፍሎ መገኘቱ፣

የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ በድምሩ ብር 225,862.44 የደሞዝ ሂሳብ መምህራኑ ዩኒቨርሲቲውን ከለቀቁ በኋላ የተከፈላቸው ሲሆን፣

በጠቅላላው ብር 1,024,742.03 በብልጫ ለመከፈሉ ተረጋጧል፡፡

4.8 የወጪውን ትክክለኛነት ማጣራት ያልተቻለ ሂሳብ፣

የወሎ ዩኒቨርስቲ በብር 194,626.00 የተሽከርካሪዎች የጥገና አገልግሎት ግዥ የጨረታ ሠነድ ባለመቅረቡና ድርጅቱም ለተከታታይ ከ3 ዓመታት በላይ በአሸናፊነት የተመረጠ በመሆኑ ድርጅቱ በጨረታ ተወዳድሮ ለማሸነፉ ማረጋገጥ ባለመቻሉ፣

የመቱ ዩኒቨርስቲ እያንዳንዱ ተቋራጭ የሲሚንቶና የብረት አቅርቦት ብድር እና የቅድሚያ ክፍያ የወሰዱትንና ያወራረዱትን የሚያሳይ መረጃ ባለመኖሩ፤

መደወላቡ የኒቨርስቲ ራዳር ኮንስትራክሽን ለተባለው ሥራ ተቋራጭ ብር 2,661,934.35 የተከፈለ ቢሆንም ለኦዲት የቀረቡት ዝርዝር የክፍያ አፈጻጸም ማስረጃዎች ኮፒ ወይም ቅጅ ከመሆናቸው በተጨማሪ ሠነዶቹ ስርዝ ድልዝ የበዛባቸው በመሆኑ፤ GIZ ተብሎ በሚጠራው ድርጅት የሚከናወኑ የመሰረተ ልማት ግንባታ የፕሮጀክት ዶክመንቶችና ደጋፊ የክፍያ ማስረጃዎች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው፣

የአዳማ ዩኒቨርስቲ GIZ/IS and MH.ENGINEERING በተባለው አማካሪ መሃንዲስ ሲከናወኑ የነበሩ ፕሮጀክቶች የርክክብ ሰነዶችና መረጃዎች ለኦዲት ባለመቅረባቸው፣

የአምቦ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,882,963.03 የወጪ ሂሳብ የተወራረደ ቢሆንም፣ በቅድሚያ ወጪ የተደረገው የገንዘብ መጠንና የወጪው ምክንያት የሚገልጹ የወጪ ማስመስከሪያች ለኦዲት ያልቀረቡ በመሆኑ፣

የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ ብር 3,991,655.00 የመሰረተ ልማት ግንባታና የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ፕላንት ግንባታው ለGIZ-IS ክፍያ ሲፈጽም ለተከፈለው ክፍያ የወጪ ማስረጃዎች ከክፍያው ሰነድ ጋር ያልቀረበ መሆኑ፣ ከGIZ-IS ጋር በህንጻ ተቋራጮች ላይ ያለ ተሰብሳቢ ሂሳብ ፣ተከፋይ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የፋይናንስ መረጃዎችንና ሰነዶችን በተመለከተ ምንም አይነት ርክክብ ሳይደረግ ብር 6,264,581.31 የግንባታ ክፍያዎች እና የመያዣ የመጨረሻ ክፍያዎች የተፈጸመ ሲሆን ለግንባታ ተቀንሶ የሚቀረው የመያዣ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የማይተላለፍ መሆኑና ክፍያው በወጪ ሂሳብ የተመዘገበ መሆኑ፣

የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ ብር 1,641,247.90 የያዙ የሂሳብ ሰነዶችና ደጋፊ የክፍያ ማስረጃዎች ለኦዲት ስራ ተጠይቀው ሊቀርቡ

ባለመቻላቸው፤ GIZ-IS ተብሎ በሚጠራው ድርጅት የሚከናወኑ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች /GIZ-IS-Treatment Plant & Inferastructure/ የፕሮጀክት ሠነዶች እና ደጋፊ የክፍያ ማስረጃዎች ለኦዲት ባለመቅረባቸው፣

የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ በመደበኛ በጀት ሂሳብ ብር 389,563,813 የያዙ ከ400 በላይ የሂሳብ እንቅስቃሴዎችን፤ በውስጥ ገቢ ሂሳብ ብር 5,506,085 የያዙ 135 የዴቢትና የክሬዲት የሂሳብ እንቅስቃሴዎች የሂሳብ ማስተካከያ የተደረገ ሲሆን፣ የሂሳብ ማካስተካከያዎቹ ከፍተኛ ገንዘብ የያዙ፤ ተደጋጋሚ የሆኑና ብዛት ያላቸው ከመሆናቸው በተጨማሪ የሂሳብ ማስተካከያ የተሰራበት ምክንያትና አጣቃሽ ቁጥር፣ ማስተካከያ በተሰራባቸው ላይ ያልተገለጸ በመሆኑና ተሰብሳቢው ሂሳብ ለመወራረዱ ወይም ገንዘቡ ለመመለሱ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ፣

ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣ ተረጋጧል፡፡

4.9 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት ወጪ ሂሳብ፣

በ4 መ/ቤቶች ብር 20,934,660.55 እና 1 መ/ቤት በአሜሪካ በዶላር 30,493.00 የተገዘ ንብረት ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበ ሲሆን፣በ3 መ/ቤቶች ብር 207,851,388.12 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው ወይም የንብረት ገቢ ደረሰኝ አለመቅረቡ ተረጋግጧል፡፡(አባሪ 18)

4.10 ከተከፋይ ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ ግብርና ታክስ፣

የአምቦ ዩኒቨርስቲ ለጉድጓድ ውሃ ቁፋሮ ክፍያ ሲፈጸም፣ ብር 1,588.15 ከተከፋይ ተቀናሽ ታክስ ፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የሌላቸው የግብር ቅድመ ክፍያ 30% መክፈል እንዳለባቸው በገቢ ግብር አዋጅ የታዘዘ ቢሆንም ብር 65,911.76 ከተከፋዩ ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ መሆኑ፣

የጎንደር ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን በሀገር ውስጥ የድረ ምረቃ ትምህርት ለሚከታተሉ ተማሪዎች የሚደረግ የቤት አበል፤ የትራንስፖርትና ለጽህፈት መሳሪያ ክፍያ ላይ ግብር እንደሚከፈልበት መመሪያ ያስተላለፈ ቢሆንም፣ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ

የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 120,083.56 በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ማራኪ ግቢ ብር 308,016.50 በጎንደር ዩኒቨርሲቲ አፄ ቴዎድሮስ ግቢ ብር 136,390.30 በድምሩ ብር 564,490.36 ግብር ያልተከፈለ መሆኑ፣

የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ብር 129,060.18 እና የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ ብር 107,480.88 ለተለያዩ ድርጅቶች ያልተከፈለ ሂሳብ መኖሩ፣

የአርባምንጭ ዩኒቨርስቲ በድምሩ ብር 56,518,270.07 ባልተለመደ የሂሳብ መደብ 5511 ሌተር ኦፍ ክሬዲት /letter of Credit/ በተከፋይ ሂሳብ የሚታይ መሆኑ፣ ተረጋግጧል፡፡

4.11 በበጀት ላልተሸፈነ ሂሳብ ወጪ የተደረገ፣

የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ ብር 464,694.42 ከመደበኛ በጀት ይተካል በሚል በብድር ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ወጪ ተደርጎ በበጀት ላልተሸፈኑ ወጪዎች የተጠቀሙ መሆኑን፣

የመቱ ዩኒቨርስቲ ብር 38,500.00 በጀት ላልተያዘለት ወጪ ተከፍሎ መገኘቱ፤

የአዲግራት ዩኒቨርስቲ ብር 2,378,792.36 ከበጀት ዓመቱ ውጪ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ ፣ ተረጋግጧል፡፡

4.12 በማነስ ሪፖርት የተደረገ ወጪ፤

በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 543,938.27 የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ፕሮጀክት ብሔራዊ ጽ/ቤት ወጪ በተጠቃለለው የሚኒስቴር መ/ቤቱ እና የጽ/ቤቱ ሂሳብ ላይ በቀን ሠራተኞች ምንዳ (በሂሳብ መደብ 6114) በብር 210,000.00 በማነስ ሪፖርት መደረጉ፣

የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ በድምሩ ብር 6,271,689.51 በበጀት ዓመቱ ወጪ የሆነው በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ያልተመዘገበ እና ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ ተረጋጧል፡፡

5. የተከፋይ ሂሳብ፣

5.1. ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ፣

በየመ/ቤቶቹ ሪፖርት የተደረጉ ተከፋይ ሂሳብ ሲጣራ በ13 መ/ቤቶች ብር 40,086,773.74 በወቅቱ ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ዝርዝሩ በአባሪ-28 ተመልክቷል/

5.2. በተከፋይ ሂሳብ ዙሪያ የታዩ የአሠራር ድክመቶች፣

የወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 3,429,889.46 ለማን እንደሚከፈል ማስረጃ ያልቀረበ ሲሆን፣ ብር 203,666.66 ደግሞ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው ያለአግባ በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ መገኘቱ፣

የጅማ ዩኒቨርስቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ከተደረገው ውስጥ፣ በሂሳብ መደብ 5001(የችሮታ ጊዜ ተከፋይ) ብር 19,354,879.04፣ በሂሳብ መደብ 5002(ልዩ ልዩ ተከፋይ) ብር 20,693.91 እና በሂሳብ መደብ 5004(የደመወዝ ተከፋይ) ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ምዝገባ /Abnormal Balance/ ብር 187,311.07 ተይዞ መገኘቱ፤

የጎንደር ዩኒቨርስቲ በሰኔ 30 2005 ከተከፋይ ላይ ተቀናሽ ግብር ብር 7,284.38 የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 27,049.90 በድምሩ ብር 34,334.28 ከወጪ ቀሪ የነበረ ቢሆንም በአዋጁ መሰረት በቀጣዩ ወር ለሚመለከተው አካል ያልተላለፈ መሆኑ እና በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ማራኪ ግቢ ብር 99,671.96 የተከፋይ ሂሳብ በዴቢት የሚታይ መሆኑ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን አላግባብ ዝቅ እንዲል መደረጉ፣

በአክሱም ዩኒቨርስቲ የተቋቋመው ሰፍሖ ቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ንግድ ፈቃድ የተሠጣቸው ሲሆን የኢንተርፕራይዞቹ እንቅስቃሴ በሙሉ በመደበኛ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ወጪው እንደ ዩኒቨርስቲው እዳ በተከፋይ ሂሳብ 5002 የሚመዘገብ መሆኑ፣

የጎንደር ዩኒቨርስቲ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 2,407,178.29 የሆስፒታል

ማስያዣ ተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት የተደረገው የተከፋዩን ስምና አድራሻ፣ የተያዘው የገንዘብ መጠንና የቆየበት ጊዜ የሚገልጽ ሰነድ ወይም ተቀጽላ ቋት ባለመኖሩ ሂሳቡን በዝርዝር ኦዲት ለማድረግ አለመቻሉ፣

ተረጋግጧል፡፡

6. የበጀት አጠቃቀም፣

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ኦዲት ሲደረግ በ14 መ/ቤቶች ከበጀት ብር 232,478,062.87 ከበጀት በላይ ወጪና በ6 መ/ቤቶች ብር 45,437,789.07 በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ሳይፈቀድ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ላይ ወጪ ያደረጉ መ/ቤቶች መኖራቸው፣እንዲሁም በ30 መ/ቤቶች ብር 1,131,484,110.09 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል።/ዝርዝሩ በአባሪ-29 እና አባሪ-29/1 ተመልክቷል/

7. የዕቃና ንብረት አስተዳደር

7.1. ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር፣

7.1.1. ለቋሚ ንብረት መዝገብ ያልተቋቋመባቸው /ያልተመዘገቡ/ መቤቶች፣

ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	7 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	3 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	10 መ/ቤቶች
ቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም ምዝገባ ያላከናወኑ	19 መ/ቤቶች

ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረት የተገኙባቸው	9 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	7 መ/ቤቶች
ተያያዥነት ያለቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	7 መ/ቤቶች

7.1.2. ሌሎች የተለያዩ የንብረት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው መ/ቤቶች

የአዲግራት ዩኒቨርስቲ

- ከይርጋ መካኒካል ኃ/የተ/የግ/ማህበር single presidential table ብዛት 150 በብር 202,500.00፣ ከቅድስተ ማርያም ኃ/የተ/የግ/ማ የተማሪዎች ሎከር ብዛት 2110 በብር 4,752,512.49 ግዥ የተፈፀመ ሲሆን በናሙና ያየናቸው በሙሉ የጠረንጴዛው መሳቢያ ቁልፉ የማይሰራ ከሎከሮች ውስጥ አብዛኛዎቹ በአግባቡ የማይገጥሙ፣ቁልፋቸው የማይሰራና በአጠቃላይ ጥራቱን ያልጠበቀ ንብረት መሆኑ፣
- አንድ የቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት በዩኒቨርሲቲው ዳርቻ ወይም አጥር አጠገብ የሚገኝ በውስጡ በርካታ የላብራቶሪ ዕቃዎችና መገጣጠሚያዎች የሚገኙበት ቢሆንም የንብረት ክፍሉ መስኮት ግሪል ባለመሰራቱ ንብረቶቹ ለአደጋ የተጋለጡበት ሁኔታ መኖሩ፣
- የምግብ ቤት አዳራሽ/ኪችን/ እና መመገቢያ አዳራሽ መብራቶችና ሶኬቶች ግንባታውን ባከናወነው ኮንትራክተር ችግር ምክንያት ሙሉ በሙሉ የማይሰሩ መሆኑና በዚህም

ምክንያት አራት ዲፕ ፍሪዝ ማቀዝቀዣ ማሽኖች አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፣

- በዩኒቨርሲቲው ምግብ ቤት ውስጥ hood type dish washer የዕቃ ማጠቢያ በብር 244,000.00 የተገዛ እና በቀን 08/12/04 ወጪ ሆኖ ከተገጠመበት ጊዜ ጀምሮ የማይሰራ መሆኑ፣
- አቶ ሳሙኤል እምብዛ፣አቶ ኢሳያስ ወ/ትንሳኤ እና አቶ ሃይላይ በሪሁ Toshiba Laptop የወሰዱ ሲሆን በመጀመሪያ የወሰዱት ተመላሽ ሳያደርግ በድጋሚ ወጪ ያደረጉ መሆኑ፣

አክሱም ዩኒቨርስቲ ኢንተርፕራይዙ የወተት ላሞች ያሉት ሲሆን የወተት ላሞቹ በቀን ምን ያህል ሊትር እንደሚሰጡ እና የሚጠበቅ ምርት መግለጫ የሌለ መሆኑ ፣የላሞች የወተት መጠን ለማወቅ በየላሞቹ መከታተያ ቅፅ የተከፈተ ቢኖርም በመቼ ቀን ምን ያህል ሊትር እንደታለበ የሚገልፅ ማስረጃ በአግባቡ የማይያዝ መሆኑ፣

የዋቻሞ ዩኒቨርስቲ

- የተለያዩ የሲቪልና ኤሌክትሪካል ኢንጅነሪንግ እና፣ የህክምና እቃዎች ርክክብ ሳይደረገባቸው በአደራ በንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣
- የመድኃኒት ንብረት ክፍል እና ሰራተኛ ባለመኖሩ የተለያዩ መድኃኒቶች በፋርማሲ ቴክኒሻል ክፍል የሚገኝ መሆኑ፣
- የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው አይነታቸው 11 የሚሆኑ የተለያዩ መድኃኒቶች የሚገኙ መሆኑ ፣
- መድኃኒት ክፍል የመድሀኒት መዝገብና መቆጣጠሪያ ባለመኖሩ ከወጪ ቀሪያቸው የማይታወቁ መሆኑ፣

የወላይታ ዩኒቨርስቲ

ብዛታቸው 24 የሚሆን የኤሌክትሪክ ምጣዶች መገዛቱ እና አዲስአበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ማቀዝቀዣ፤ሲንክ ማጠቢያዎች፤የጋዝ ምድጃ፤የዳቦና የእንጀራ መጋገሪያ ማሽኖች፤ዲ ፍሪጅ ፣የፊልም ፕሮጀክተር፣ የማዳበሪያ ጆንያ እና ሲሊንደሮች ተገዝተው ሥራ ላይ ሳይውሉ ተቀምጠው መገኘታቸውና

አገልግሎት ለሚሰጡ ንብረቶች ምንም ማስቀመጫ መጋዘን የሌለው መሆኑ፣

አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፣

- በሞዴል 19ና በሞዴል 22 ገቢና ወጭ ሳይደረጉ ሥራ ላይ የዋሉ ዕቃዎች መኖራቸው፤
- በአመቱ መጨረሻ የንብረት ቆጠራ ተደርጎ ከወጭ ቀሪ ማመዛዘኛ ያልተሰራለት መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተገኝቷል፡፡
- የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃዎች የምዝገባ ሂደት የሚከናወነው በአንድ ሰራተኛ ብቻ መሆኑና ስቶክ ሪከርድ ካርድ የማይጠቀሙ መሆኑ፤

የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ

- በመጻህፍት ግምጃ ቤት መጻህት በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ እየተደረጉ ለንባብ ክፍል በርክክብ ቬርባል ከማስተላለፍ በስተቀር በግምጃ ቤቱ የሚገኘውን ከወጪ ቀሪ የሚያሳይ መከታተያ አለመኖሩ፣
- ቤተ መጻህፍት ለመምህራንና ሠራተኞች አገልግሎት የሚሰጥበትን የአሠራር ሥርዓት የሌለው መሆኑ እና ገንዘብና ንብረት የሚያንቀሳቅሱ ሠራተኞች ሲቀያየሩ ወይም ሲለቁ ርክክብ ቢፈጸምም ያስረከቡት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ መሆኑ

የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ

- የህክምና መድኃኒቶች ከማዕከላዊ ዕቃ ግምጃ ቤት ወጪ ሆነው በየኮሌጁ(ካምፓሱ) በሚገኙት የተማሪዎች ክሊኒክ ሚኒ ስቶር ገቢና ወጪ የሚደረጉ መድሃኒቶች መከታተያና መቆጣጠሪያ መዝገብ (ስቶክ ካርድ) ያልተቋቋመ መሆኑ፤
- እያንዳንዱ ኮሌጅ፤ ካምፓስ ወይም የፋይናንስ አገልግሎት ከማዕከላዊ ንብረት ክፍል ወጪ በማድረግ የወሰዱዋቸውን የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች መዝግበው የማይዙ መሆኑ፤-የባህር ዳር

ዩኒቨርስቲ ከተማሪዎች ክሊኒክ የመድሀኒት መጠበቂያ ሚኒ ስቶር መድሀኒቶች ወጪ የሚደረጉት በማተሚያ ቤት ያልታተመና ተከታታይ ቁጥር በሌለው ነጭ ወረቀት ከመሆኑም በተጨማሪ ሰነዱ በማህደር ሆኖ በክሊኒኮቹ አስተባባሪዎች እጅ በጥንቃቄ የማይቀመጥ መሆኑ እና በህክምና መስጫ (Dispensary Room) መድሃኒቶች ዓይነትና ዋጋ እንዲሁም የታካሚው ተማሪ ስምና ዲፓርትመንት የተሰጠው መድሃኒት ዓይነት የሚገልፅ መረጃ በዝርዝር ተመዝግቦ የማይያዝ መሆኑ፤

የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ

- የንብረት መከታተያና መቆጣጠሪያ መዝገብ የንብረት ምዝገባ የሌለ መሆኑ፣ ከህክምና መስጫ ክፍል ወጪ ሆነው ለታካሚው ተማሪ የተሰጡት መድሀኒቶች እና ከዋናው የንብረት መጋዘን ወደ ምግብ ማዘጋጃ ክፍል የምግብ ጥሬ እቃ ሲሰጥ ዩኒቨርሲቲው ካሳተመው ፎርም ውጭ ገቢና ወጪውን ለመቆጣጠር የሚያስችል መዝገብ (ስቶክ ካርድ) አለመኖሩን፣
- በዕቃ መጋዘን ውስጥ የሚገኙት የቋሚና አላቂ እቃዎች በዓይነት፤ በዋጋ ወይም በሚሰጡት አገልግሎት በመለየት በስርዓት የማይጠበቁ በመሆኑ አብዛኛዎቹ ንብረቶች በመጋዘን ወለል ላይ ተበታትነው ለብልሽት ተጋልጠው የተገኙ መሆኑ፤
- የምግብ ግብዓቶችና ሌሎች እቃዎች በመጋዝን ውስጥ ካለው አቀማመጥ አኳያ ብዙ ንብረቶች በአይጥ የተበሉና እየተበሉ መሆኑ፣ በጥገና መጋዘን አካባቢ በቁጥር በውል የማይታወቁ በርካታ አሮጌ ወንበሮችና ከላሜራ የተሠሩ የብረት መደርደሪዎች ሜዳ (መስክ) ላይ በተበታተነ መልኩ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በዩኒቨርስቲው ውስጥ የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ ያልተቋቋመ መሆኑ እና በምግብ ቤት መጋዝን እና በአዲሱ የምግብ ማብስያ ቤት ውስጥ አገልግሎት ሳይሰጡ ብዙ ዓመታት ያስቆጠሩና አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ዋጋቸው እጅግ ከፍተኛ የሆኑ የዳቦ መጋገሪያ ማሽን፤የድንች መላጫ ማሽኖች፤

በኤሌክትሪክ የሚሰሩ የምግብ ማብሰያ ማሽኖች፣የማቡኪያ ማሽኖች እና ሌሎችም ተመሳሳይ እቃዎች ለረዥም ዓመታት ያለአገልግሎት ተቀምጠው መገኘታቸው፣

የሠመራ ዩኒቨርስቲ

- የዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኞች በተለያየ ምክንያት ሲቀያየሩ ያስረከቡት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ መሆኑና ቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር እየተሰጠ ቢሆንም ያልተጠናቀቀ መሆኑ፤
- ለአገልግሎት ወጪ የተደረጉ ለአስተዳደር አገልግሎት የተገነባ አንድ ህንጻ ሙሉ በሙሉ በንብረት መጋዘንነት /ማከማቻነት/ እንዲያገለግል የተደረገ መሆኑ፤
- ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉና የማይችሉ የተለያዩ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ያለምንም እርምጃ የሚገኙ መሆኑ፤
- የተለያዩ የላብራቶሪ ዕቃዎች 3 ሚክሰር ማሽን፣ 2 ባርክተር፣ 1 ኮምፓክተር ፋክተርስቴት እና የተለያዩ ማሽነሪዎች ያለምንም አገልግሎት ከአንድ ዓመት በላይ በምህንድስና ቤተ-ሙከራ የተቀመጠ መሆኑ፤ ከትምህርት ሚኒስቴር የተላኩ ከተቋሙ ጋር ርክክብ /የዕቃ ገቢ ደረሰኝ/ ያልተፈጸመ የመብራት ጀነሬተር የወጥ ማብሰያ፤ የሻይ ማፍያ እና የዳቦ መጋገርያ ማሽን ያለምንም አገልግሎት በተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ የተቀመጡ መሆኑ እና ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተገዙትና በዕርዳታ የተገኙ የተለያዩ በርካታ መጻህፍት /በቂ የመጽሃፍት መደርደሪያ ባለመኖሩ/ በአብዛኛው ያለምንም ድጋፍ ለብልሽት በሚዳርግ መልኩ አንዱ በአንዱ ላይ ተደራርበው በወለል ላይ የተቀመጡ መሆኑ፤

የወሎ ዩኒቨርስቲ

- ከትምህርት ሚ/ር የተላኩ የተለያዩ ዕቃዎች ያለአገልግሎት በንብረት ክፍል መገኘታቸው እና በምግብ ቤት አካባቢ በጎርፍ

ምክንያት የተበላሹ ዕቃዎች መኖራቸውንና የዘይትና ማርማራታ መያዣዎች ተከማችተው መገኘታቸው፣-

- የዕቃ ምዝገባና ርክክብ የማይደረግ መሆኑ፣

የጅማ ዩኒቨርስቲ

- በሆስፒታሉ የሚገኘው የመድሐኒት ንብረት ክፍል የመድሃኒት አያያዝ፤ ቁጥጥርና የተሟላ ምዝገባ ባለመኖሩ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉና ለምዝበራ የተጋለጠ መሆኑ፣
- አላቂ ዕቃዎች ከምዝገባ ጋር የማይገናዘቡ መሆኑንና በንብረት ክፍሉ ከአምስት ዓመት በላይ የሆናቸው ቀለሞችና የተለያዩ ንብረቶች መገኘታቸው፡
- በቋሚ ዕቃ ንብረት ክፍል የምግብ ማብሰያ ማሽኖች፣ ማቀዝቀዣዎችና የተለያዩ ዕቃዎች ያለአገልግሎት ተከማችተው መገኘታቸው፣ ያገለገሉ ዕቃዎች ንብረት ክፍል ውስጥ የተለያዩ ዕቃዎች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
- በምሕንድስናና ጠቅላላ አገልግሎት ቢሮዎች ውስጥ የተለያዩ ዕቃዎች የተለያዩ ዕቃዎች ያለአገልግሎት ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣ በምሕንድስና ንብረት ክፍል የሚገኙ ዕቃዎች ከወጪ ቀሪያቸው ከምዝገባ ጋር የማይገናዘብና በንብረት ክፍሉ ለረጅም ዓመታት ጥቅም ላይ ያልዋሉ ንብረቶች የሚገኙ መሆኑ፣
- በምሕንድስና የአገለገሉ ዕቃዎች ማከማቻ በርካታ ብረታ ብረት፣ ቆርቆሮዎችና የተለያዩ ዕቃዎች ሜዳ ላይ ተበትነው መገኘታቸው፣
- በሆስፒታሉ ንብረት ክፍሎች የሚገኙ ዕቃዎች ከወጪ ቀሪ የማይታወቅና ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ተደራርበው የተቀመጡ መሆኑ፣ በግብርና ኮሌጅ ሁለት የውሃ መሳቢያ ጀነሬተሮች ያለአገልግሎት ከ10 ዓመት በላይ በንብረት ክፍሉ በረንዳ ላይ የተቀመጡና የተለያዩ ዕቃዎች ሜዳ ላይ ተከማችተው መገኘታቸው እና በብር 8,873,559.44 ከኦሜጻድ

ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ የተገዙ ንብረቶች በሶስቱም ምግብ ቤት ለሁለት ዓመት ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤

የመቱ ዩኒቨርስቲ

ንብረቶች በዓይነታቸው፤ በባህሪያቸውና በሚሰጡት አገልግሎት ተለይተው በሥርአት ባለመቀመጣቸው ከፍተኛ ዋጋና ብዛት ያላቸው ዕቃዎች ለብልሽትና ጉዳት እየተዳረጉ መሆኑ እና የሥጋና ጤፍ አቅርቦት በመረካከቢያ ሠነድና በንብረት ገቢ ደረሰኝ(ሞ/19) የሚታየው በጥቅል በመሆኑ የየቀኑን አቅርቦት ለማወቅ አለመቻሉ፤

የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ

የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ንብረት ክፍል ቢኖርም በየክፍሉ ተደበላልቀው መገኘታቸው እና በምግብ ቤት አካባቢ በጎርፍ ምክንያት የተበላሹ ዕቃዎች መኖራቸውንና የዘይትና ማርማራታ መያዣዎች ተከማችተው መገኘታቸው፣

የቡሌ-ሆራ ዩኒቨርስቲ

የዩኒቨርስቲው ሕንፃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣ በበጀት ዓመቱ በተደረገው ቆጠራ የምህንድስናና የሜካኒካል መሣሪያዎች ያልተካተቱ መሆኑ እና የኢንጂነሪንግ መሣሪያዎች፣ የምግብ ማብሰያ ዕቃዎች እና የተለያዩ ዕቃዎች ያለአገልግሎት ተቀምጠው መገኘታቸው፣

የዲላ ዩኒቨርስቲ

- በተለያዩ የዩኒቨርስቲው ንብረት ክፍልና በቅጥር ግቢ ውስጥ የተለያዩ ዕቃዎች ያለአገልግሎት ተከማችተው መገኘቱ፣
- በተደረገው ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ የምሕንድስና መሣሪያዎች (Engineering Materials) አለመቆጠራቸው፣

የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ

ለጥበቃ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ የመከላከያ መሣሪያዎች ሳይወገዱ መገኘታቸው እና ያልተወገዱ የተለያዩ ንብረቶች በግብርና እና በሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጆች መገኘታቸው፣

የአዳማ ዩኒቨርስቲ

- በጤና ሳይንስ ከዋናው ስቶር ወደ መድሃኒት ማከፋፈያ በሞዴል 22 ወጪ ከተደረገ በኋላ በቀጥታ ወደ ተጠቃሚ በሽያጭ የሚተላለፍ መሆኑና በየ 15 ቀን ያለቁ መደሃኒቶች ሲኖሩ ከዋናው ስቶር እየተጠየቀ ገቢ የሚደረግ መሆኑ ይህ ሂደት የሚከናወነው ከወጪ ቀሪ ባልተናበበ ሁኔታ መሆኑና የንብረት መዛግብቶች (ስቶክ ካርድ ና ቢን ካርድ)የሌለ መሆኑ ወይም መድሃኒቱ በሙሉ ለተጠቃሚ ስለመድረሱ ለማረጋገጥ የሚያስችል የውስጥ ቁጥጥር ያልተዘረጋ መሆኑ፤
- ለተለያዩ ኃላፊዎች የሞባይል ቀፎና ካሜራ የተሰጠ ቢሆንም ዕቃውን ለመለየት እንዲቻል የዕቃውን ዓይነት የሚገልጹ መረጃዎች በዝርዝር ተመዝግቦ የማይያዝ መሆኑ፤ የህክምና መድሃኒቶች ከተማሪዎች ክሊኒክ ወደ ህክምና መስጫ ክፍል /Despensory Room/ የተላለፉና እንዲሁም ከህክምና መስጫ ክፍል ለተጠቃሚዎች የተሰጡ መድሃኒቶች ለመከታተል የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ያልተቀረጸ መሆኑ፤
- ንብረት በመጠበቅ ሥራ ላይ የተመደቡ ሰራተኞች ወደ ሌላ ክፍል ሲዘዋወሩ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ኦዲት እየተደረገና ከወጪ ቀሪው እየተረጋገጠ ማስረከብ በሚገባቸው ልክ ያስረከቡ መሆኑ ቁጥጥር አይደረግም፡፡ በመሆኑም የተማሪዎች ክልኒክ ሃላፊ የነበሩት በትምህርት ምክንያት ክፍሉን ሲለቁ ያንቀሳቀሱት የህክምና መድሃኒቶች ሂሳብ ኦዲት ሳይደረግና የንብረት ቆጠራ እና የንብረት ርክክብ ሳይፈጸም በሌላ ሠራተኛ የተተኩ መሆኑ፤
- በተማሪዎች ክልኒክ የሚገኙ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው የተላለፈ መድሀኒቶች እንዲወገዱ በ2004 በጀት ዓመትና በ 2005 በጀት ዓመት ከክሊኒኩ ሪፖርት ቀርቦ የነበረ ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣
- በሚኒ ስቶር ውስጥ የሚገኙ መድሃኒቶች በካርቶንና በክፍሉ ወለል ላይ ተበታትነው ለብልሽትና ለጉዳት ተዳርገው የተቀመጡ መሆኑ፤ በቋሚ እቃ መጋዘን ውስጥ የተበላሹና ለረዥም ጊዜ

እርምጃ ሳይወሰድባቸው ተከማችተው የተገኙ ንብረቶች መኖራቸው፤

- በአሰላ የጤና ሳይንስ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው የተላለፈ (Expiry date) መድሃኒቶች በተለየ ክፍል እንዲቀመጡና እንዲወገዱ የተጠየቀ ቢሆንም አፋጣኝ እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣ ረዥም ግዜ የሆናቸውና በብልሽት ምክኒያት ተመላሽ የተደረጉ በርካታ ኮምፒውተሮች ፎቶ ኮፒ ማሽኖች በቋሚ እቃ መጋዘን ተከማችተው የተቀመጡና እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ፤
- የጽዳት ወይም ኬሚካል ነክ ያላቸውና በንብረትና በሰው ጤና ላይ አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ ንብረቶች ተለይተው ሊጠበቁ የሚገባ ቢሆንም እንደ በረኪና ያሉ መርዛማ ኬሚካሎች በወለል ላይ ተበታትነው የተቀመጡ መሆኑ፤
- ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ አልያም ተሸጠው እጅግ ከፍተኛ ዋጋ ሊያወጡ የሚችሉ በርካታ የህክምና እቃዎች(x-ray machine, Bed)ና ስማቸው በውል ያልተለዩ ከፍተኛ መጠን ያላቸው የህክምና መሳሪያዎች ብረታ ብረቶችና ሌሎች ትኩረት ተነፍጎአቸው በመጋዘንና በሜዳ ላይ ተጥለው በጸሀይና በዝናብ እየተበላሹ መሆናቸው፤
- ለሆስፒታሉ የልብስ እጥበት አገልግሎት ከሚውሉ 8 ልዩ ልዩ መጠንና አይነት ካላቸው የልብስ ማጠቢያና ማድረቂያ ማሽኖቹ ሁለቱ ብቻ አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን በኦዲት ቅኝት ለመረዳት እንደተቻለው አንዳንዶቹ በቀላሉ ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ቢሆንም ይህ አለመደረጉ እየሰሩ ያሉ ማሽኖችም ከስራ ጫና ብዛት የመበላሸታቸው ሁኔታ የሰፋ መሆኑና በተለይ ለቀዶ ጥገና አገልግሎት የሚውሉ አልባሳት በዚሁ ክፍል የሚጸዱ ሲሆን ከማሽን እጥረት አንጻር ልብሶቹ እንዲደርቁ የሚደረጉት ባህላዊ በሆነ መንገድ መሆኑ እና በርካታ ለቁጥር በሚያዳግት መልኩ ባንድ ከቆርቆሮ የተሠራ መጋዘን ውስጥ ከወለል እስከጣሪያ ጥግ ድረስ ተቆልለው ለብልሽት በተጋለጠ መልኩ የብረት አልጋዎች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

- በአሰላ ግብርና ትምህርት ዘርፍ በተመላሽ እቃ መጋዘን ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ በርካታ ኮምፒውተሮች ታይፕራይተሮችና ሎሎች ዕቃዎች ያገለገሉና ወደፊት ሊያገለግሉ የሚችሉት ተለይተው በሥርዓት ያልተቀመጡ መሆናቸው፤ ወደ ዩኒቨርሲቲ ከመተላለፉ በፊት ለኮሌጁ ከፌደራል ግብርና ሚኒስቴር በእርዳታ የተሰጡና አገልግሎታቸውና ዓይነታቸው በውል ያልታወቀ ማሽን ፤ የውሃ ፓምፕ፤ ፋይል ካብኔት፤ በርካታ የእርሻ መሳሪያዎች ያለአገልግት የተቀመጡ መሆኑ እና የተለያዩ አልባሳቶች የወንድና የሴት የፕላስቲክና የቆዳ ጫማዎች ዩኒቨርሲቲው ኮሌጁን ሲረከብ አብሮ የተረከባቸው ያለአገልግሎት በመጋዘን ውስጥ የተከማቹ መሆኑ፣

የአምቦ ዩኒቨርስቲ

- ለተማሪዎች አገልግሎት በግዥ ወይም በእርዳታ የሚገኙ የህክምና መድኃኒቶች ወደ መድሀኒት መጠበቂያ ክፍል ገቢ ሲደደረጉ እና እንዲሁም ከመድሃኒት መጠበቂያ ክፍል ወደ ህክምና መስጫ ክፍል ሲተላለፉ የመድሀኒቶች መከታተያና መቆጣጠሪያ ስቶክ ካርድ ባለመኖሩ ምዝገባ የማይደረግ መሆኑ እና ወደ ምግብ ጥሬ እቃዎች ማከማቻ መጋዘን ገቢ የሚደረጉ እንዲሁም ለምግብ ዝግጅት ወጪ የሚደረጉ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች መከታተያና መቆጣጠሪያ ስቶክ ካርድ ባለመኖሩ ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ በተጨማሪም በጀት አመት መጨረሻ በምግብ ጥሬ እቃዎች ማከማቻ መጋዘን የተገኙ የምግብ ጥሬ እቃዎች ቆጠራ የማይደረግ መሆኑ፣
- በመድሃኒት መጠበቂያ ግ/ቤት እና በህክምና መስጫ ክፍል /Dispensary Room/የሚገኙት መድሀኒቶች በስርአት ባለመቀመጣቸው በጥንቃቄ የማይጠበቁ መሆኑ፤ የመድሀኒት ማዘዣዎች በቀን፤ በወር ወይም በበጀት ዓመት ተለይተው በስርዓት የማይጠበቁ መሆኑ፤ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው የተላለፈ መድሃኒቶች /Expired Medicine /አገልግሎት ከሚሰጡት ጋር

በመድሃኒት መጠበቂያ ስቶር ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤ ለተቋሙ ሰራተኞች መድሀኒቶች የሚሰጡት በዱቤ መሆኑ ከክሊኒኩ ሰራተኞች ቢገለጽም ተጠቃሚው ሰራተኛ በዱቤ የወሰደውን የመድሃኒት ዋጋ ለመክፈሉ ማረጋገጫ የሌለ መሆኑ፤

የአሶሳ ዩኒቨርስቲ

ለሥራ ማከናወኛ ወጪ የተደረጉ ቋሚ ንብረቶች በአብዛኛው የመለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ እና ከኮድ ኢትዮጵያና ከሌሎች ለጋሽ ድርጅቶች በዕርዳታ የተገኙ መጻህፍቶች ዓይነትና ብዛት በዝርዝር የሚገልጽ ማስረጃ ካለመኖሩ በተጨማሪ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸው መሆኑ፤

የወልቂጤ ዩኒቨርስቲ

- በግዥ ወይም በእርዳታ ተገኝተው ወደ መድሀኒት መጠበቂያ ክፍል ገቢ የሚደረጉ እና እንዲሁም ከመድሀኒት መጠበቂያ ክፍል ወደ ህክምና መስጫ ክፍል የሚተላለፉ መድሀኒቶች እና ወደ ምግብ ጥሬ ዕቃዎች ማከማቻ መጋዘን ገቢ የሚደረጉ እንዲሁም ለምግብ ዝግጅት ወጪ የሚደረጉ የምግብ ጥሬ እቃዎችመከታተያና መቆጣጠሪያ ሰቶክ ካርድ የሌለ መሆኑ፤
- የመድሀኒት መጠበቂያ የተለየ እቃ ግ/ቤት ያልተዘጋጀ መሆኑ፤ በከፍተኛ ዋጋ የተገዙና ለምግብ ማዘጋጃ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ምድጃዎች እና የሻይ ማፍያ ማሽኖች አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ እና ከትምህርት ሚኒስቴር የተላኩ አራት የተለያዩ ማሽኖች በዝናብ እና በፀሃይ ለጉዳትና ለብልሽት ተጋልጠው ሜዳ ላይ የተቀመጡ መሆኑ፤

የመደወላቡ ዩኒቨርስቲ

- የህክምና መድኃኒቶች መከታተያና መቆጣጠሪያ መዝገብ ወይም ስቶክ ካርድ ባለመኖሩ ወደ ተማሪዎች ክሊኒክ ገቢ የተደረጉ መድኃኒቶች እንዲሁም ወደ ህክምና መስጫ የተላለፈ ወይም

ለታካሚው ተማሪ ወጪ የተደረጉ መድኃኒቶች ዓይነት፣ብዛትና ዋጋ እየተዘረዘረ የማይመዘገብ መሆኑ፤

- በበጀት ዓመት መጨረሻ በመድኃኒቶች መጠበቂያ ስቶር እና በህክምና መስጫ /Despensory Room/ የተገኙ መድኃኒቶች ቆጠራ የማይደረግና ዝርዝር መረጃው የማይያዝ መሆኑ፤
- የመደወላቡ ዩኒቨርስቲ በከፍተኛ ገንዘብ የተገኙ የምግብ ማብሰያ የኤለክትሪክና የጋዝ ምድጃዎች ወደ ተቋሙ ገቢ ከተደረጉበት ጊዜ ጀምሮ ምንም ዓይነት አገልግሎት ሳይሰጡ በተማሪዎች ምግብ ማዘጋጃ ክፍሎች ውስጥ የተገኙ መሆኑ እና በህትመትና ማባዣ የስራ ክፍሎች ውስጥ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የህትመት ቋሚ ዕቃዎች በቴክኒክ ዕውቀት ችግር በጥገና እጦትና በመሳሰሉት ምክንያቶች አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች መኖራቸው፤

የጎንደር ዩኒቨርስቲ

- በማዕከል የተገዙት መድኃኒቶች በዩኒቨርሲቲው በሚገኙ አራት የተማሪዎች ክሊኒክ የመድሃኒት መጠበቂያ ክፍል ገቢ የሚደረጉ እንዲሁም ለታካሚው ተማሪ የተሰጡ መድሃኒቶች ዓይነትና ብዛት እና ዋጋ የማይመዘገብ መሆኑ ፡
- ከተማሪዎች ክሊኒክ መድሀኒቶች ወጪ የሚደረጉት በማተሚያ ቤት ያልታተመና ተከታታይ ቁጥር በሌለው ነጭ ወረቀት ከመሆኑም በተጨማሪ ሰነዱ በማህደር ሆኖ በክሊኒኮቹ አስተባባሪዎች እጅ በጥንቃቄ የማይቀመጥ መሆኑ፤ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው መድሃኒቶች በሁሉም ክሊኒኮች በብዛት ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ እና በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በቂ የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘን ባለመኖሩ በርካታ መድሃኒት የያዙ ካርቶኖች በሠራተኞች ቢሮ ውስጥና በየኮሪደሮች ላይ ተደርደርው መቀመጣቸው፣

በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ተጠግነው ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ዓይነታቸው 28 እና ብዛታቸው በቁጥር 2267 የሆኑ የተማሪዎች የጥናት ጠረጴዛዎች፤ የራስጌ ኮመዲኖዎች፤ የእንግዳ ወንበሮች እና ተጠግነው ሥራ ላይ ሊውሉ የማይችሉና የሚወገዱ፡-

- ዓይነታቸው 106 እና ብዛታቸው በቁጥር 2014 የሆኑ ኮምፒዩተር፤ ዩፒኤስ፤ የህትመት ቀለሞች ያሉ የኤሌክትሮኒክስና ተያያዥ ዕቃዎች፤
- ዓይነታቸው 14 እና ብዛታቸው በቁጥር 35111 የሆኑ የተለያዩ መጻህፍት፤ እንጨት ነክ ዕቃዎች፤ የእንግሊዘኛ ቋንቋ መማሪያ ካሴት ቴፕ፤ ተንጠልጣይ/ ሰስፔንሽን/ ፋይሎች፤
- ዓይነታቸው 55 እና ብዛታቸው በቁጥር 1640 የሆነ ስፖንጅ ፍራሾችና ትራሶች፤ ያገለገለ ጋዜጣ፤ ጠርሙሶች፤ ባዶ ፕላስቲክ ዕቃዎች፤ የቢሮ ተሽከርካሪ ወንበሮችና የስም ቲተሮች፣ መኖራቸዉ፤

የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

ከሚገኙት 6 መጋዘኖች ውስጥ፡ በሦስት መጋዘኖች የንብረት ገቢና ወጪ ምዝገባ እና ንብረት የመያዝ ሥራ በአንድ ሰው የሚሠራ መሆኑ፣ በአንድ መጋዘን ውስጥ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ አዳዲስ ተሽከርካሪ ወንበሮች እና ሊወገዱ የሚገባቸው በርካታ ቋሚ ዕቃዎች ሳይመዘገቡና ሥርዓት ሳይዙ አንድ ላይ ተቀምጠው መገኘታቸው፣

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

እንዲወገዱ በኮሚቴ የተለዩ የተለያዩ ንብረቶች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ አመራር ሪፖርት መቅረቡ ቢገለጽም የተወሰደውን እርምጃ የሚመለከት መረጃ ለኦዲት ያልቀረበና፣ በተመሳሳይ ሁኔታ በ2004 በጀት ዓመት የኦዲት ማሻሻያ ሀሳብ የተሰጠበት መሆኑ፣

በኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት

በዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ቋሚ ዕቃዎች፣ የአይ ቲ እና ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች፣ የመኪና ጎማዎች፣ ባትሪዎችና መለዋወጫዎች እንዲሁም የጽህፈት መሳሪያዎች ያለአገልግሎት መቀመጣቸው፣

7.1.3. በነዳጅና የነዳጅ ኩፖን አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮች፣

የሠመራ ዩኒቨርስቲ በቅድሚያ ክፍያ እየተገዛ የሚመጣው የነዳጅ ኩፖን፤ ቅባትና ዘይት የገቢና ወጪ መከታተያ ካለመኖሩም በተጨማሪ በየወሩ ወይም በአንድ በተወሰነ ወቅት ሪፖርት የሚቀርብበት አሠራር የሌለ መሆኑ፡

የጅማ ዩኒቨርስቲ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተሽከርካሪዎች የተሽከርካሪው ሰልቫትዮ /ታንከር/ ከሚይዘው በላይ በቀን ከ600-700 ሊትር ነዳጅ በድምሩ 4411.16 ሊትር እና ለጀነሬተር 15 ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ 1000 ሊትር የቀዳ መሆኑ፤

የአዲግራት ዩኒቨርስቲ፣ የአክሱም ዩኒቨርስቲ፣ የመቀሌ ዩኒቨርስቲ፣ የዋቻሞ ዩኒቨርስቲ፣ የወላይታ ዩኒቨርስቲ የነዳጅ መቆጣጠሪያ ጌጃቸው የሚሠሩ መኪናዎች አንድ መኪና በሊትር ስንት ኪሎ ሜትር መሄድ እንደሚችል የሚያሳይ በባለሙያ የተረጋገጠ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፣

7.1.4. የገቢ ደረሰኝና ሌሎች የሕትመቶች አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው መ/ቤቶች፣

የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለስራ አገልግሎት በሰራተኞች ወጪ ከተደረጉት የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተሰርቶባቸው የተጠናቀቁ ደረሰኞች፤ በከፊል የተሰራባቸው እና ያልተሰራባቸው ጥራዞችና የደረሰኙ ቅጠሎች በትክክል ለመኖራቸው እየተረጋገጠ በውስጥ ኦዲት አገልግሎት እና በፋይናንስ አገልግሎት ቆጠራ የማይደረግ መሆኑ እና እያንዳንዱ ሠራተኛ ለሥራ ወጭ ያደረገውን ደረሰኝ በሥራ ላይ ለማዋሉ እና በእያንዳንዱ ደረሰኝ የተሰበሰበው ገንዘብ ወጭ ካደረገው ደረሰኝ ብዛትና ቅጠል ጋር እየተመሳከረ ገንዘቡ ሙሉበሙሉ ወደባንክ ገቢ ለማድረጉ የማይመዛዘን መሆኑ፤

የመቀሌ ዩኒቨርስቲ የውስጥ ገቢ እና የፕሮጀክት ሂሳብ ገንዘብ መሰብሰቢያ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርን ሳያስፈቅድ ዩኒቨርሲቲው ባሳተመው ደረሰኝ የተጠቀመ መሆኑ፣

7.2. የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም፣

የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም ኦዲት ሲደረግ፣

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ6 መ/ቤቶች	22 ተሽከርካሪዎች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ5 መ/ቤቶች	60 ተሽከርካሪዎች
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣	በ2 መ/ቤቶች	5 ተሽከርካሪዎች
የሻንሲና ሞተር ቁጥር ከሊብሬ ጋር የማይገጥም፣	2 መ/ቤቶች	6 ተሽከርካሪዎች

መኖራቸው ተረጋግጧል።

በተጨማሪም

- የአክሱም ዩኒቨርስቲ እና የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ዩኒቨርሲቲው ለጥቃቅን ጥገናዎች የሚያገለግል የራሱ ጋራዥ ያላቋቋመ መሆኑ፣
- የአዲግራት ዩኒቨርስቲ መኪናዎች ጥገና ከተደረገላቸው በኋላ የተመለሱ የጥገና ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ከክፍያ ሰነዱ ጋር የማይያያዝ መሆኑ፣
- የአዲግራት ዩኒቨርስቲ ታርጋ ቁጥር 4-16100 መኪና በማን ቁጥጥር እና ተረክቦ የሚያሽከረክር ሹፌር ወጪ እንደተደረገ የሚገልፅ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፣
- የሠመራ ዩኒቨርስቲ የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ዓይነት፤ ሞዴል፤ የጭነቱ ልክ፤ የተገኙበት ሁኔታ፤ ዋጋቸው እና ሌሎች የተሽከርካሪው ታሪክ የሚያመለክት የተሟላ ምዝገባ (ማህደር) የሌላቸው መሆኑ፤

8. የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት፣

የወልድያ ዩኒቨርስቲ የመጸዳጃ ማጠራቀሚያ ሞልቶ የአካባቢው ሕብረተሰብ ለመጠጥ፣ ለእንስሳትና ለተለያዩ አገልግሎቶች ወደሚጠቀምበት ምንጭ በመፍሰሱ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ መሆኑ፤

የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ምግብ የሚዘጋጅበት አካባቢ ከፍተኛ የጽዳት (የጥራት) ችግር ያለበት ሲሆን የፍሳሽ ማስወገጃ በአካባቢው ባለመዘርጋቱ ምክንያት በምግብ ቤቱ አካባቢ ለምግብ ብክለት እና በተማሪዎችና በሠራተኞች ጤንነት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ከፍተኛ ሽታ የተፈጠረ መሆኑ፤

ተረጋግጧል፡፡

9. ልዩ ልዩ፣

9.1. ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ፣

የወሎ ዩኒቨርስቲ ባለፈው በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ላይ እርምጃ አለመወሰዱ፣

የጅማ ዩኒቨርስቲ በ2004 በጀት ዓመት የኦዲት አስተያየት መሠረት የእርምት እርምጃ ሰላለመወሰዱ፣

9.2. በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸውን ባልተወጡ ሠራተኞችን በሚመለከት፤

የጎንደር ዩኒቨርስቲ አፄ ቴዎድሮስ ግቢ በውጭ ሀገር ለትምህርትና ስልጠና ለተላኩ ብዛታቸው 32 የሚሆኑ መምህራን ለደሞዝና ጥቅማ ጥቅም እንዲሁም ለትምህርት ድጋፍ ብር 1,167,853.00 የተከፈለ ሲሆን መምህራኖቹ ትምህርታቸውን አጠናቀው በገቡት ውል መሰረት የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ባለመፈጸማቸው በዩኒቨርሰቲው ላይ ያደረሱት ጉዳትና ኪሳራ ተረጋግጦ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት ባልደረባ ሁለተኛና ሶስተኛ ድግሪያቸውን ኢንስቲትዩቱ በሰጣቸው የትምህርት ዕድል ውጭ ሀገር

ካጠናቀቁ በኋላ በውሉ መሠረት ኢንስቲትዩቱን ባለማገልገላቸው የወጣባቸው 8,055.00 ብር የደመወዝ እና 21,827.00 ዶላር የትምህርት ወጪ ለኢንስቲትዩቱ ገቢ እንዲደረግ ለተወካያቸው ደብዳቤ የተጻፈ ቢሆንም ክፍያው ያልተፈጸመ /ያልተጀመረ/ መሆኑ፣

9.3. <u>የሰው ሀብት አስተዳደርን በተመለከተ፣</u>

የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ፣

አራት ዓመት የስራ ልምድ በሚጠይቅ የስራ መደብ ላይ የስራ ልምዱን ሳያሟሉ በሲቪል መሃንዲስነት ብር 5,870.00 እንዲከፈላቸው ተደርጎ የተመደቡ መሆኑ፣

ያለ ማስታወቂያ በማመልከቻ ብቻ ቅጥር የሚፈጸመ መሆኑ

በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ማስታወቂያ ሳይወጣ ሰራተኞች በቀጥታ ከያዙት የሰራ መደብ ከፍ ብለው ያለውድድር የተመደቡ መሆኑን፣

ተቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት ያቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ በጀት	ካፒታል በጀት	ድምር
1	መደወላቡ ዩኒቨርስቲ	7/01/06	127,621,626	122,740,400	250,362,026
2	አምቦ ዩኒቨርስቲ	18/02/06	201,086,250	456,952,867	658,039,117
3	አዳማ ሳ/ቴ ዩኒቨ.	28/02/06	214,112,500	311,831,092	525,943,592
4	ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ	09/03/06	54,798,050	202,718,413	257,516,463
5	አሶሳ ዩኒቨርስቲ	30/03/06			154,054,893
6	ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ	10/02/06	139,650,630	154,448,900	294,099,530
7	ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ	04/02/06	405,984,300	686,555,966	1,092,540,266
8	ጎንደር ዩኒቨርስቲ	04/02/06	320,876,051	645,843,921	966,719,972
9	የከ/ት/ስትራቴጂ ማ.	12/12/05	9,919,050	39,756,000	49,675,050
10	ደብረ ታቦር ዩኒቨ.	03/01/06	50,359,599	212,148,653.45	262,508,252.45
11	ወልድያ ዩኒቨርስቲ	15/02/06	55,058,760	258,564,999.32	313,623,759.32
12	ወሎ ዩኒቨርስቲ	13/03/06	98,440,773	175,384,257	273,825,030

ተቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት ያቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ በጀት	ካፒታል በጀት	ድምር
13	ሠመራ ዩኒቨርስቲ	11/04/06	116,953,606	129,526,700	246,480,306
14	ቡሌ-ሆራ ዩኒቨርስቲ	21/03/06	51,102,070	137,822,512.70	188,924,582.70
15	ዲላ ዩኒቨርስቲ	14/4/06	204,317,199	185,000,000	389,317,199
16	ሐዋሳ ዩኒቨርስቲ	13/02/06	393,767,295	596,156,000	989,923,295
17	ጅማ ዩኒቨርስቲ	08/05/06	398,401,353.28	779,499,488.91	1,177,900,842.19
18	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ	15/02/06	106,996,190	124,967,350	231,963,540
19	መቱ ዩኒቨርስቲ	27/12/05	54,678,989.42	132,458,335.49	187,137,324.91
20	ትምህርት ሚኒስቴር	21/04/06	177,947,397.73	1,374,881,824.75	1,552,829,222.48
21	ወላይታ-ሶዶ ዩኒቨ.	06/02/06	104,576,710.00	146,366,130.00	250,942,840.00
22	አርባ ምንጭ ዩኒቨ.	13/03/06	250,388,868.80	607,485,290.00	857,871,768.80
23	ዋቸሞ ዩኒቨርስቲ	14/01/06	61,469,238.00	159,559,125.50	221,028,363.50
24	መቀሌ ዩኒቨርስቲ	28/01/06	482,868,711.00	675,324,981.00	1,158,193,692.00
25	አክሱም ዩኒቨርስቲ	18/02/06	159,892,528.00	139,280,600.00	299,173,128.00
26	አዲግራት ዩኒቨርስቲ	30/11/05	72,396,976.22	268,437,217.13	340,834,193.35
27	ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨ.	04/03/06	94,118,180.54	107,311,705.81	201,429,886.35
28	ሲቪል ሰርቪስ ሚ/ር	15/11/05	27,987,361.84	27,478,390.00	55,465,751.84
29	አ.አ.ሳይንስና ቴ. ዩ.	17/04/06	94,758,200.00	258,080,306.74	352,838,506.74
30	ሳይንስና ቴክ. ሚ/ር	18/04/06	26,371,950.00	80,250,121.11	106,582,071.11
31	መ/ኛና ኢ. ቴ.ሚ/ር		40,330,613.00	194,758,414.00	235,089,,027.00
32	ከፍ. ትም.ጥና አ. ኤ.	12/04/06	7,481,690.00	-	7,481,690.00
33	የኢ. ልማት ምር. ኢ.	19/03/06	3,358,000.00	-	3,358,000.00
	ጠቅላላ ድምር				14,153,673,181.74

በልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች

ኦዲት ዳይሬክቶሬት ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶች

የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት

መንግሥት ባወጣቸው የፋይናንስ ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያዎችና ሥርዓቶች መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም የመንግስት ንብረቶች በሚገባ መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ፣ የ33 የመንግስት መ/ቤቶች የ2005 በጀት ዓመት ሂሣብን ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ መያዙ ይታወቃል። በዕቅድ የተያዙት መሥሪያ ቤቶች በሙሉ የኦዲት ሥራቸው ተጠናቆ ለመሥሪያ ቤቶች ለሥራ አመራር የተዘጋጀው ሪፖርት የተላከ ሲሆን፣ መሥሪያ ቤቶች በተሰጠው የማሻሻያ ሀሣብ መሠረት የወሰዱትን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ምላሽ ያልሰጠ ሲሆን፣ የሕብረት ሥራ ኤጀንሲ ደግሞ የኦዲት ሪፖርቱ ከተላከ በኋላ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ኦዲት ከተደረጉት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ለግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ የሥራ አመራር ሪፖርት የተላከ ሲሆን፣ ለቀሪዎቹ ሰላሳ ሁለት መሥሪያ ቤቶች የኦዲት አስተያየቱን የያዘ የኦዲት ሪፖርት ተልኳል፡፡

1. የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ የዕቅድ ክንውንን በተመለከተ

1.1 ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ የያዛቸውን ሰላሳ ሶስት መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ሥራ አጠናቋል፡፡ ይህም የዕቅዱን 100% የሸፈነ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

1.2 የተሰጠው የኦዲት አስተያየት

በዳይሬክቶሬቱ ኦዲት ለተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው አጥጋቢ ያልሆነ አስተያየት ለሁለት መሥሪያ ቤቶች፤ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ነቀፌታ ያለበት አስተያየት ለስምንት መሥሪያ ቤቶች ፣ ለአስራ ሰባት መሥሪያ ቤቶች ደግሞ ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት ተሰጥቷቸዋል፡፡/ዝርዝሩ ከአባሪ 2-6 ተመልክቷል።/

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች

በዳይሬክቶሬቱ በ2005 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሒሳብ

1.1 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ የተለያዩ የባንክና የጥሬ ገንዘብ አያያዝና የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ላይ የታዩ ክፍተቶች ያሉባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር በአባሪ- 4 እና 5 ተመልክቷል።

በመሆኑም መሥሪያ ቤቶቹ በጥሬ ገንዘብ አስተዳደሩ መመሪያ ላይ በተቀመጠው መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢ የሆነ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

2 የገቢ ሂሳብ

2.1 በውስጥ ገቢ አሰባሰብ ላይ የታዩ የአሰራር ክፍተቶች፤

2.1.1 ግኝት

በአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ

- በተከታታይ የትምህርት ክፍል ከማታ ትምህርት የሚገኝ ገቢ እና ከገቢው ላይ ወጪ የተደረገው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ ከሬጅስትራር ክፍል በመጣ የምዝገባ እስሊፕ መሰረት በ2005 በጀት ዓመት ከማታ ትምህርት ክፍል ብር 85,050.00 ገቢ የተሰበሰበ ሲሆን፣ ለገቢው የመንግሥት ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ (መሂ1/1)

ያልተቆረጠለት እና ወደ ውስጥ ገቢ የባንክ አካውንት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፣

- ኮሌጁ በ2005 በጀት አመት ለተለያዩ ድርጅቶች ካከራየቻው ቤቶች የሰበሰበውን የቤት ኪራይ ገቢ ብር 188,085.70 ወደ መዝናኛ ክበቡ ገቢ ያደረገ መሆኑ፣
- ከማታ ትምህርት የሚገኝ ገቢዎች በአደራ መልክ ወደ መዝናኛ ክበቡ አካውንት ገቢ የሚደረጉ መሆኑ፤
- ከማታ ትምህርት የሚገኝ ገቢም ሆነ ከገቢው ላይ ወጪ የሚደረገው ሒሳብ በመዝገብ (በሌጀር) የማይመዘገብ፣ ተቀፅላ የሂሳብ ቋት የሌለው፣ የፋይናንስ ሪፖርት የማይዘጋጅለት እና ከወጪ ቀሪው የማይታወቅ መሆኑ፤
- በ2005 በጀት አመት ደመወዝ የተከፈለባቸው ፔይሮሎች በኮሌጁ ሂሳብ ክፍል መጠበቅ ሲኖርባቸው በተከታታይ የትምህርት አስተባባሪው ቤት የሚገኙ መሆኑ፤
- የተከታታይ ትምህርት አስተባባሪው ከማታው ትምህርት ክፍል የሚገኘውን ገቢ የሚሰበስብ፣ ባንክ የሚያስገባ፣ ፔይሮል የሚያዘጋጅ እና ክፍያም የሚፈፀም መሆኑ፤
- ከዕስቶር ወደ ችርቻሮ መሸጫ ሱቅ ገብተው ለሽያጭ የሚውሉ ሸቀጣሸቀጦች በታሪፋቸው መሰረትና ወደ መሸጫ ሱቅ በገባው ሸቀጣሸቀጥ ልክ ተሸጠው ገቢ ስለመደረጋቸው የሚረጋግጥበት ተገቢ የሆነ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤

<u>በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን</u>

- በአብያታ ሻላ እንዲሁም በአዋሽ ብሄራዊ ፓርኮች ከዋናው መሥሪያ ቤት ለስራ ማስኬጃና ለደሞዝ ለሚላከው ገንዘብ የገቢ ደረሰኝ የማይቆረጥለት እና ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፣

- በአብያታ ሻላ እንዲሁም በአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ የእለት ገቢ መሰብሰብ፣ የእለት ገቢ ደረሰኝ ማዘጋጀት እና የእለት ገቢ ምዝገባ የማከናወን ስራ በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፣

- በአብያታ ሻላ እንዲሁም በአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ በዕለት ገቢ ሰብሳቢ የሚሰበሰበው ገቢ በገቢ መዝገብ የሚመዘገብ ቢሆንም ወደ ዋናው መሥሪያ ቤት ሲላክ ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፣

- በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ በመሂ 7/1 የተሰበሰበ ገቢ በመሂ/64 ሳይጠቃለል በቀጥታ ከመሂ 7/1 ወደ ሂሳብ መመዝገቢያ መዝገብ ምዝገባ የሚከናወን መሆኑ፣

- በፌዴራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀፅ 3 "10" የመንግሥት ቀጥተኛ የሆኑ ገቢዎች በህግ ካልተፈቀደ በስተቀር ገቢውን መስሪያ ቤት ሊጠቀምበት እንደማይችል ይገልፃል። ሆኖም በአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ ብር 5,500.00 ከፓርኩ ቀጥታ ገቢ ላይ ወጪ ተደርጎ በተንጠልጣይ ሂሳብ ተይዞ የተገኘ መሆኑ፤

2.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መሥሪያ ቤቶቹ በመመሪያው መሰረት የገቢ አሰባሰብ ሥርዓቱን ማስተካከል እንዳለባቸውና በህግ ካልተፈቀደ በስተቀር የሰበሰቡትን ገቢ በቀጥታ መጠቀም እንደማይችል አሳስበናል።

2.2 <u>በአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ለኦዲት ሥራ ሊቀርቡ ያልቻሉ የገቢ ደረሰኞችን በተመለከተ</u>፤

2.2.1 <u>ግኝት</u>

- ብር 59,560.21 ገቢ የተሰበሰበባቸው አምስት ቅጠል ደረሰኞች (መ/ሂ1 እና ደጋፊ ሰነዶች) ለኦዲት ሥራ

ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

- ብር 407,439.56 ባንክ የገባበት ዲፖዚት እስሊፕ እና ገቢው ተጠቃሎ የገባበት የገቢ ደረሰኝ (መሂ1) ለኦዲት ሥራ የቀረበ ሲሆን፣ የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢዎች ገቢ የሰበሰቡበት የገቢ ደረሰኞች (መሂ 1) ግን ለኦዲት ሥራው ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፤

2.2.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ለኦዲት ያልቀረቡት የገቢ ደረሰኞች ቀርበው ትክክለኛነታቸው እንዲረጋገጥ፣ ያልተገኙት የገቢ ሠነዶችም ተፈልገው እንዲቀርቡ፣ ለወደፊቱም በገቢ ደረሰኞች ላይ ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

2.3 <u>የሂሳብ መደቡን (አርስቱን) ጠብቆ ያልተመዘገበ ገቢ፤</u>

2.3.1 <u>ግኝት</u>

- በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ በበጀት ዓመቱ ከግብርና ምርቶች ማለትም የቢራ ገብስ ፣ ድንች ፣ በርበሬ ፣ የቁም እንስሳት፣ ወተት እና ከመሳሰሉት ሽያጭ የሰበሰበውን ብር 6,768,944.58 በሂሳብ መደብ 1455 መመዝገብ ሲገባው በሂሳብ መደብ 1485 መዝግቦ የተገኘ መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ በበጀት ዓመቱ ከሰበሰበው ገቢ ውስጥ ብር 1,638,664.79 በአደራ ሂሳብ ኮድ (5054) መዝግቦ የተገኘ መሆኑ፣
- የኤሌክትሪክ ኤጀንሲ ከልዩ ልዩ ዕቃዎች የጨረታ ሽያጭ የሰበሰበውን ገቢ ብር 4,480.00 በ1489 ሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲገባው በሥራ ፈቃድ የሂሳብ መደብ 1413 መዝግቦ የተገኘ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

2.3.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በትክክለኛዉ የሂሳብ መደብ ላልተመዘገበው ሒሳብ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራለት፣ ለወደፊቱም ኮሌጁ የገቢ ሂሳብ ምዝገባ ሲያከናውን የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትን ተከትሎ ምዝገውን ማከናወን እንዳለበት አሳስበናል፡፡

2.4 የነዳጅ ተመላሽ ገቢ ሂሳብ፤

2.4.1 ግኝት

የአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ የነዳጅ አጠቃቀም ሁኔታ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ኮሌጁ ከመደበኛ በጀት ገዝቶ በነዳጅ ዴፖ የሚገኘውን ነዳጅ የኮሌጁን የውስጥ ለውስጥ መንገድ ለሚሰራው ጳውሎስ ዘለቀ ጠ/ሥ/ተቋራጭ ወጪ ተደርጎ የተሰጠ መሆኑ ታውቋል፡፡ ሆኖም፡

- ነዳጁን የወሰደው ድርጅት የነዳጁን ዋጋ ብር 113,327.13 መስከረም 14 ቀን 2005 ዓ.ም በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 812250 ገቢ ያደረገ ቢሆንም ገንዘቡ ገቢ የተደረገው ወደ ውስጥ ገቢ የባንክ አካውንት ቁጥር 104 ውስጥ መሆኑ፣
- ኮሌጁ ለመንግሥት ሥራ ጉዳይ በተፈቀደለት የመደበኛ በጀት የተገዛውን ነዳጅ ለሌላ አካል ወጪ አድርጎ መሰጠቱ አግባብ ያለመሆኑ፣

ታውቋል፡፡

2.4.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ለሥራ ማስኬጃ በተፈቀደ በጀት የተገዛን ነዳጅ ለሌላ አካል መስጠት የመንግስትን የፋይናንስ መመሪያን መጣስ ከመሆኑም በላይ ከሽያጩም የተገኘውን ገንዘብ ወደ ወደ መደበኛ ሂሳብ ፈሰስ አለማድረግ አግባብ ባለመሆኑ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

2.5 በታሪፉ መሰረት ያልተሰበሰበና የገቢ ታሪፍ ሳይኖረው የተሰበሰበ ገቢ፤

2.5.1 ግኝት

- የብሄራዊ ሚትዎሮሎጅ ኤጀንሲ ለሚሰበስበው ገቢ ኤጀንሲው በበጀት አመቱ ለሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን የአየር ትንቢያ መረጃ ከሰጠበት አገልግሎት ለሰበሰበው ገቢ ብር 633,750.00 በሚመለከተው አካል የተፈቀደ ታሪፍ ባለመቅረቡ ምክንያት ገቢው በታሪፉ መሰረት ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- በአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን የውሀ ፈቃድ የክፍያ ተመን ብር 87.00 ሆኖ ሳለ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ብር 92.00 እያስከፈለ የሚገኝና በተጨማሪም ለሚያስከፍለው የውሀ ስርጭት አገልግሎት በሄክታር ብር 78.1813 እና ለሰራተኛ ክፍያ በሄክታር ብር 5.9198 ተመን ሳይኖር ገቢ እየሰበሰበ የሚገኝ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

2.5.2 የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቱ ለሚሰበስበው ገቢ በመንግሥት የጸደቀ ታሪፍ እንዲኖረው ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

2.6 ያልተሰበሰበ የገቢ ሂሳብ ፤

2.6.1 ግኝት

የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በወቅቱ የሚሰበሰብ መሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ከወንጂ ስኳር ፋብሪካ ከሀምሌ 1 ቀን 2003 ዓ.ም ሰኔ 30/2004 ድረስ ከውሀ አገልግሎት መሰብሰብ ካለበት ሂሳብ ብር 331,289.87 ውስጥ ብር 232,280.00 የሰበሰበ ሲሆን፣ ብር 99,009.87 ያልሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡

2.6.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ያልተሰበሰበው የውጭ ገቢ ሂሳብ እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

3 ተሰብሳቢ ሂሳብ

3.1 በደንቡ መሰረት ያልተሰበሰበ ወይም ያልተወራረደ ሂሳብ፤

3.1.1 ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል ይሁንና ኦዲት የተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በደንቡና በመመሪያው መሰረት የፈጸሙ መሆኑ ሲጣራ፡ በ23 መ/ቤቶች በድምሩ ብር **295,347,277.92** ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል።

3.1.2 የማሻሻያ ሀሳብ

በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች እንዲወራረዱ መሰብሰብ የማይችሉት ደግሞ ተጣርተው አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4 ተከፋይ ሒሳብ

በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሠረት መሆኑን እና በተከፋይ ሒሳብ መግለጫዎቹ ላይ የተመለከቱት ሒሳቦች በተገቢው ማስረጃ የተደገፉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ12 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 35,758,822.68 ተከፋይ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-28 ተመልክቷል/

በመሆኑም የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ ሪፖርቱን ተአማኒነት ሊያሳጣው ስለሚችል መሥሪያ ቤቱ የተከፋይ ሂሳቦቹ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

4.1 በተከፋይ የተመዘገበ የገቢ ሂሳብ፤

4.1.1 ግኝት

የብሄራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ከሚቲዎሮሎጅ መሣሪያ ሽያጭ የሰበሰበውን ገቢ ብር 1,507,619.00 በተገቢው የገቢ ሂሳብ ኮድ መሰብሰብ ሲገባው በልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳብ መደብ 5002 የመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.1.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በተከፋይ ሂሳብ መደብ የተመዘገበዉ የገቢ ሂሳብ በተገቢው የገቢ ሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ገንዘቡ ለመንግስት ፈሰስ መደረግ እንዳለበት እናሳስበናል፡፡

5 የወጪ ሂሳብ

5.1 ያለ ጨረታና የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ፤

5.1.1 ግኝት

በፌደራል መንግሥት የግዥ መመሪያ መሰረት ከብር 100,000.00 በላይ የሆኑ ግዥዎች ሲፈጸሙ ጨረታ መውጣት እንዳለበት ያዛል፡፡

ይሁን እንጂ፡ በ13 መ/ቤቶች ብር 23,025,417.90 ያለ ጨረታና የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-15 ተመልክቷል/

5.1.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ግዥዎች የግዥ መመሪያውን ተከትለው እንዲፈጸሙ ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት እናሳስበናል፡፡

5.2 በመስክ ላይ ለነበሩ የግንባታ ዕቃዎች (Material on Site) ክፍያ የተፈጸመ ስለመሆኑ፤

5.2.1 ግኝት

የግዥ አዋጁና መመሪያው በሳይት ላይ ያሉ ዕቃዎች በገንዘብ እንዲተካ የማይፈቀድ ቢሆንም የግብርና ሚኒስቴር በሳይት ለሚገኙ ዕቃዎች ዋጋ ብር 9,496,899.70 ለተለያዩ ኮንስትራክሽን ድርጅቶች በገንዘብ እንዲተካ ከመደረጉም በተጨማሪ ገንዘቡ ለኮንስትራክሽን ድርጅቶቹ ሲተካ በተሰብሳቢ ሒሳብ መመዝገብ ሲገባው ሥራው ለመሰራቱ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.2.2 የማሻሻያ ሀሳብ

የግዥ አዋጁም ሆነ መመሪያው በሳይት ላይ የሚገኙ ዕቃዎች በገንዘብ እንዲተካ የማይፈቀድ በመሆኑ ውል ሲፈጸም የግዥ መመሪያውን መሰረት አድርጎ መሆን እንዳለበት እንዲሁም በሳይት ላይ ላሉ ዕቃዎች (Material on Site) የተከፈለው ሂሳብም ቢሆን ሥራው ለመሰራቱ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ አግባብ ስላልሆነ ገንዘቡ እስኪተካ ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሊመዘገብ እንደሚገባ አሳስበናል ፡፡

5.3 ማስተካከያ ያልተሰራለት ያልተከፈለ የደሞዝ ሂሳብ፤

5.3.1 ግኝት

- በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ በተለያዩ ምክንያቶች ለቀን፣ ለኮንትራት፣ ለቋሚና ለጊዜያዊ ሰራተኞች ላልተከፈለው የደሞዝ ሂሳብ ብር 28,627.85 የሂሳብ ማስተካከያ ያልተሰራለት መሆኑ፤
- በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ለሰራተኞች ላልተከፈለው የደሞዝ ጠቅላላ ወጪ፣ የመንግሥት የጡረታ መዋጮና

ተቀናናሽ ሂሳቦች ብር 70,655.28 የሂሳብ ማስተካከያ ያልተሰራለት መሆኑ፤

- በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ በተለያዩ ምክንያቶች ለሰራተኞች ላልተከፈለው የደመወዝ ጠቅላላ የመንግሥት የጡረታ መዋጮ ወጪና ተቀናናሽ ሂሳቦች ብር 73,606.32 የሂሳብ ማስተካከያ ያልተሰራለት መሆኑ፤

በድምሩ ለብር 172,889.45 ለሰራተኞች ላልተከፈለው የደመወዝ ማስተካከያ ያልተሰራለት መሆኑ ታውቋል፡፡

5.3.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በሂሳብ አያያዝ ሥርዓቱ መሰረት ላልተከፈለው የደሞዝ ሂሳብ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራለት፤ ለወደፊቱም ያልተከፈለ የደሞዝ ሂሳብ ሲያጋጥም ወዲያውኑ ተገቢው ማስተካከያ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንዳለበት አሳስባናል፡፡

5.4 <u>ደንብና መመሪያን ሳይከተል የተፈጸመ ክፍያ፤</u>

5.4.1 <u>ግኝት</u>

መሥሪያ ቤቶች የፈጸሟቸው ክፍያዎች ደንብና መመሪያን የተከተሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ በ12 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 3,343,916.45 ደንብና መመሪያን ሳይከተል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-16 ተመልክቷል/

5.4.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ክፍያውን የሚደግፍ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይኖር ክፍያው መፈጸሙ አግባብ ስላልሆነ አሰራሩ መስተካከል እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.5 ለክፍያው የክፍያ ደረሰኝ (ማረጋገጫ ደብዳቤ) ያልቀረበለትን ሂሳብ

5.5.1 ግኝት

የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ የግብርና መካናይዜሽን አገልግሎት ድርጅት ለሰጠው የእርሻ አገልግሎት ሥራ የአግልግሎት ክፍያ ብር 518,737.05 ለድርጅቱ የፈፀመ ቢሆንም ገንዘቡ ለድርጅቱ ለመድረሱ የገቢ ደረሰኝ አልቀረበም ወይም ድርጅቱ ገንዘቡ በአካውንታቸው ለመግባቱ በደብዳቤ ያላሳወቀ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.5.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ከክፍያ ሰነዱ ጋር የግብርና መካናይዜሽን አገልግሎት ድርጅት መስጠት ያለበትን የገቢ ደረሰኝ ወይም ገንዘቡ በድርጅቱ አካውንት ለመግባቱ ደብዳቤ እንዲያያዝ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.6 ያልተቀነሰ የግንባታ ቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ፤

5.6.1 ግኝት

የከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቢሮ ለማስገንባት ከተቋራጩ ጋር በገባው ውል መሰረት እያንዳንዱ የክፍያ ሰርተፍኬት ሲቀርብ 30% የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ ታስቦ ከተቋራጩ ክፍያ ላይ ብር 120,076.68 የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ በአግባቡ ባለመቀነሱ ምክንያት በብልጫ ለተቋራጩ የተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.6.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በብልጫ የተከፈለውን የቅድሚያ ክፍያ በቀጣይ የክፍያ ሰርተፍኬት ላይ ቀንሶ ማስተካከያ ማድረግ እንዳለበት፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ስህተት

እንዳይፈጠር ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.7 <u>በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የወጪ ሒሳብ፤</u>

5.7.1 <u>ግኝት</u>

በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ለመመዝገቡ ኦዲት ሲደረግ በ17 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 10,100,960.21 በተገቢው ሂሳብ መደብ ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡ዝርዝሩ በአባሪ-22 ተመልክቷል/ በተጨማሪም በ9 መ/ቤቶች ብር 210,354,518.71 በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዝ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-17 ተመልክቷል/

5.7.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ክፍያ ከመፈጸሙና ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ለወጪዎቹ በጀት መያዙንና በትክክለኛ የሂሳብ መደብ ለመመዝገባቸው መረጋገጥ እንዳለበትና ለሂሳቡም ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.8 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት የቀረጥ ሒሳብ፤</u>

5.8.1 <u>ግኝት</u>

መሥሪያ ቤቶች ከገቢዎችና ጉምሩክ ባልሥልጣን በተጻፈላቸው ደብዳቤ መሠረት የቀረጥ ሂሣብ ምዝገባ የሚያከናውኑ ሲሆን፣ ቀረጡ የተከፈለላቸው የዕርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች አቃዎቹን ገቢ ለማድረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ኮፒ እንዲልኩ ባለመደረጉ ዕቃዎቹ ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሳብ፤ በ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 1,349,326,969.33 የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ የተከናወነ ቢሆንም ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎቹ ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-19 ተመልክቷል/ በተጨማሪም በ2 መ/ቤቶች ብር 115,990.87 ለተገዙት ዕቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡/ ዝርዝሩ በአባሪ-18 ተመልክቷል/

5.8.2 የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቶቹ የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡ የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

5.9 በጥሬ ገንዘብ የተፈጸመ የደንብ ልብስ ክፍያ፤

5.9.1 ግኝት

የደንብ ልብስ ግዥ በአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ጥናት አፈቃቀድ እና አፈጻጸም መመሪያ መሰረት መፈጸም ሲገባቸው ከደንብ ልብስ አስፈላጊነትና ዓላማ ውጪ በ2005 በጀት አመት ለሰራተኞች የደንብ ልብስ በጥሬ ገንዘብ ክፍያ ፈጽመው የተገኙ መሥሪያ ቤቶች ፤

- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር **196,866.39** ፤
- የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 559,784.28፤
- በኢትዮጵያ የጤናና ሰነምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት ብር 378,151.69፤
- በአለርት ማዕከል ብር 805,130.25፤

በድምሩ ብር 1,939,932.61 ለሰራተኞች ለደንብ ልብስ በጥሬ ገንዘብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

5.9.2 የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቶቹ የደንብ ልብስ አሰጣጥ መመሪያ አዘጋጅቶ በግዥ መመሪያው መሰረት ግዥውን በመፈጸም ለሰራተኞቹ የደንብ ልብሱን እንዲሰጥ፤ የደንብ ልብስ የተፈቀደላቸው ሰራተኞችም በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋላቸው ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.10 <u>በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ፤</u>

5.10.1 <u>ግኝት</u>

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት በ2005 በጀት ዓመት በተፈቀደው የበጀት ድልድል መሰረት ለመሆኑ እና የበጀት ዓመቱ ሂሳብ በበጀት ዓመቱ የሚመዘገብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ 12 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 2,010,600.05 ከበጀት ዓመቱ በፊት የነበሩት ወጪዎች በ2005 በጀት ዓመት ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-21 ተመልክተቷል/

5.10.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የበጀት ዓመቱ ወጪ በበጀት ዓመቱ እንዲመዘገብ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.11 <u>ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፤</u>

5.11.1 <u>ግኝት</u>

በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለወጪ ሒሳቦች ተገቢው የወጪ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ$ በ6 መ/ቤቶች ብር 1,253,009.52 ማስረጃ ሳይቀርብላቸውና በሌሎች በ2 መ/ቤቶች በድምሩ ለብር 16,935,229.26 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብላቸው በወጪ ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-13ና 14 ተመልክቷል/

5.11.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ያልተሟላ ማስረጃው እንዲሟላና ማስረጃ ያላቀረበላቸው ሂሳቦች ማስረጃ እንዲቀርብላቸው፤ ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ገንዘቡ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.12 ሳይፈቀድ የተከፈለ የቤት አበልና ከቤት አበል ላይ ያልተቀነሰ ስራ ግብር፤

5.12.1 ግኝት

- በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በማገልገል ላይ ለሚገኙ የጤና ባለሞያዎች በ2004 በጀት ዓመት በሚመለከተው የመንግሥት አካል ሳይፈቀድ ከመደበኛ በጀት ብር 519,600.00 የቤት አበል ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን፣ በወቅቱ በተደረገው ኦዲት ክፍያው አግባብ አለመሆኑ ተገልጾ ሁኔታው እንዲስተካከል አስተያት የተሰጠ ቢሆንም ለሆስፒታሉ የጤና ባለሙያዎች የቤት አበል እንዲከፈል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከመፈቀዱ በፊት ኮሌጁ በ2005 በጀት ዓመትም ብር 595,936.85 በጠቅላላው ብር 1,115,536.85 የቤት አበል ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤
- በ6 መ/ቤቶች ከተፈቀደው የቤት አበልና ክፍያዎች ላይ ብር 204,024.05 የሥራ ግብር ተቀናሽ ያልተደረገ መሆኑ፣ /ዝርዝሩ በአባሪ-8 ተመልክቷል።/

ታውቋል።

5.12.2 የማሻሻያ ሃሳብ

- በሚመለከተው አካል ከመፈቀዱ በፊት የተፈጸመው የቤት አበል ክፍያ በሙሉ ተመላሽ እንዲደረግ እና ለወደፊቱም መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ እንዳይፈፀም አሳስበናል፡፡
- በገቢ ግብር አዋጁ፣ ደንብና በተላለፈው መመሪያ መሰረት ያልተቀነሰው ያልተቀነሰው የገቢ ግብር ተቀንሶ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.13 አሸናፊ ካልሆነ ድርጅት ጋር ውል የተገባና እና የግንባታ ሥራው እንዲቋረጥ ስለመደረጉ፤

5.13.1 ግኝት

የፌዴራል መንግሥት ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣው የእቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት በግልጽ ጨረታ መከናወን ለሚገባቸው የግንባታ ሥራዎች ጨረታ መውጣቱ፡ እንዲሁም የጨረታ ሂደቱን አካሔድ ተገቢነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የእናቶችና ሕፃናት ሆስፒታል ግንባታ ለማከናወን በኢትዮጵያ ሄራልድ ጥር 2002 ባወጣው ጨረታ ከተሳተፉት ህንፃ ተቋራጮች ውስጥ ማገርኮን ሥራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማህበር ግንባታውን እንዲያከናውን ተመርጦ በብር 146,612,897.51 ውል ገብቷል፡፡ ሆኖም አሸናፊው ድርጅት፡

1. ተቋራጩ ያሉትን ለግንባታ ሥራ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን እንዲያቀርብ በተጠየቀው መሠረት ለግንባታ ሥራው የሚጠቀምበት የአፈር ማንሻ መሣሪያ (Crane) የሌለው በመሆኑ ከቀረቡት ተወዳዳሪዎች ዝቅተኛ ነጥብ የተሰጠው መሆኑ፣

2. በግንባታ ሥራው ላይ የሚሳተፉ ባለሞያዎችን በማቅረብ ረገድ በተደረገው ምዘና ከተወዳዳሪዎች አነስተኛ ነጥብ ያገኘ መሆኑ፣

3. ተገቢ የሥራ ልምድ እና የሞያ ብቃት ያላቸውን ባለሞያዎች እና የታደሰ የሥራ ፈቃድ በማስረጃነት ባለማቅረቡ ምንም ነጥብ ያልተሰጠው መሆኑ፣

4. ከውድድሩ በፊት በነበሩ አምስት ዓመታት በዋና ሥራ ተቋራጭነት ያከናወነው ሥራ እና ቢያንስ በአንድ የግንባታ ሥራ የመስክ እይታ (Work Sited) 70% ያጠናቀቀ መሆኑን የሚገልፅ በቂ ማስረጃ እና የመልካም ሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ከአሰሪው መቅረብ እንደሚገባው

በመመዘኛው ቢገለፅም የተጠቀሰው ተቋራጭ ይህንን ባለማድረጉ ምንም ነጥብ ያልተሰጠው መሆኑ፣

ከላይ በዝርዝር በተገለፁት ሙያዊ ምዘናዎች (Technical Evaluations) መሠረት ተቋራጩ ከተቀመጠው 70% ማለፊያ ነጥብ 52.3% በማግኘቱ ከውድድሩ ወጪ (Disqualified) መሆኑ የተገለፀ ሲሆን፣ የጨረታ ኮሚቴው ሚያዚያ 19/2002 ባደረገው ስብሰባ በፋይናንስ ውድድሩ ላይ በቂ ተወዳዳሪዎች መሣተፍ እንዲችሉ ለማድረግ ቀደም ብሎ በሞያዊ ምዘና ከውድድሩ ውጪ የሆኑትን ማገርኮንን እና ሌሎች ሁለት ተቋራጮችን እንዲካተቱ በማድረግ ማገርኮን ባቀረበው ዝቅተኛ ዋጋ አሸናፊ እንዲሆን መደረጉ ታውቋል፡፡ ይሁንና ከጨረታ ኮሚቴው አባላት መካከል በተሰጠው አስተያየት የተመረጠው የሥራ ተቋራጭ በአማኑኤል የአእምሮ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ባከናወነው የግንባታ ሥራ የአፈፃፀም ድክመት የነበረበት መሆኑን እንዲሁም በወቅቱ ብዙ ጅምር ሥራዎች በእጁ ላይ ያሉት ለመሆኑ ኮሚቴው መረጃ እንዳለውና የግንባታ ሥራው በተጨማሪ ቢሰጠው የሥራ መጓተትና የጥራት ጉድለት እንዳይፈጠር ኮሚቴው ስጋቱን መግለፁን ከቀረበው የኮሚቴ ቃለ ጉባኤ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ሆኖም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተመረጠው ድርጅት፡

1. በአሁኑ ወቅት ያለው የሥራ አፈፃፀም ከ5 ዓመታት በፊት ከነበረው የተሻለ በመሆኑ፣
2. የቴክኒክ ምዘና መስፈርቱን በሚሟላቱ መመረጡን፣
3. ያቀረበው የሥራ ማስፈፀሚያ ዋጋ ከሌሎቹ ተቋራጮች ዝቅተኛ መሆኑን፣
4. ከድርጅቱ ጋር የሚፈፀመው ውለታ በሁኔታ ላይ የተመሠረተ እንደሚሆን በመጥቀስ የግንባታ ሥራው እንዲሰጠው የወሰነ መሆኑን ፣

ለመረዳት ተችሏል፡፡

ድርጅቱ ከ5 ዓመታት በፊት የነበረውን የሥራ አፈፃፀም የሚሳይ ማስረጃ ባለማቅረቡ ነጥብ ያልተሰጠው መሆኑን፤ የተደረገውን የቴክኒክ ምዘና መስፈርት ባለማሟላቱ ውድቅ መደረጉን፤ እና ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በአማኑኤል የአዕምሮ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የግንባታ ሥራ ላይ የታየውን የአሰራር ድክመት ከግምት ውስጥ ሳያስገባ በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ውል በመፈፀም ዝቅተኛ ዋጋ በማቅረቡ ብቻ የግንባታውን ሥራ እንዲያከናውን ማድረጉ የመንግሥትን የግዢ አዋጅና መመሪያ ያልተከተለ ከመሆኑም በላይ በዝርዝር በተገለፁት የተቋራጩ አጠቃላይ የምዘና ውጤት እና የሥራ አፈፃፀም ድክመት ምክንያት የግንባታ ሥራው እንዲቋረጥ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.13.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በግንባታው ሥራ የጨረታ አመራረጥ ላይ ችግር መኖሩ በግልጽ እየታወቀ መስፈርቱን ላላሟላ ተቋራጭ የግንባታው ሥራ እንዲሰጠው በመደረጉ ምክንያት ግንባታው እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ስለሚሆን የተከሰቱ የጥራት ችግሮችን አይነት እና ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቁ እና ተጀምረው ያላለቁ ሥራዎች በዝርዝር እና በመጠናቸው እንዲለዩና ለተቋራጩ የተፈጸመው ክፍያ ተመጣጣኝ መሆኑ እንዲጣራ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.14 በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ፤

5.14.1 ግኝት

- የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በህንድ ሐገር ትምርታቸውን ለሚከታተሉ ለኪስ አበል እንዲሁም ለመላኪያና ለተለያዩ ወጪዎች ክፍያ ሲፈጸም በባንክ ስሌት የምንዛሪ ስሌት ምክንያት በተፈጠረው ስሕተት ምክንያት ብር 18,444.16 በብልጫ ከባንክ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ የተደረገ መሆኑ፤

- የማዕድን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የቢሮ ዕቃዎች እና የደንብ ልብስ ግዥ ለመፈጸም የፋይናንሻል ግምገማ ሲደረግ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡትን ድርጅቶች በመተው ከፍተኛ ዋጋ ያቀረቡት የተመረጡ በመሆኑ ምክንያት በድምሩ ብር 88,245.30 በብልጫ የተከፈለ ከመሆኑም በተጨማሪም የፋይናንሻል ግምገማ የተደረገዉ በአንድ የግዥ ክፍል ሠራተኛ ብቻ መሆኑ፤

ብር 106,689.46 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.14.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በብልጫ ወጪ የተደረገው ክፍያ እንዲስተካከል መሥሪያ ቤቱ ተገቢ የሆነ እርምጃ መውሰድ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.15 የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተመዝጋቢ ካልሆነ ድርጅት የተፈጸመ ግዥ፤

5.15.1 ግኝት

የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 27/2004 አንቀጽ 5 በወጣው መመሪያ መሰረት ከብር ከ50,000.00 በላይ ዋጋ ያላቸው የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ የተፈጸመው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በብር 204,937.20 የተፈጸሙት ግዥዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ካልሆኑ ድርጅቶች መሆኑ ታውቋል፡፡

5.15.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በተጨማሪ እስት ታክስ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 27/2004 አንቀጽ 5 በወጣው መመሪያ መሰረት ብር ከ50,000.00 በላይ ዋጋ ያላቸው የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ መፈጸም የሚቻለው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገበ ታክስ ከፋይ ብቻ መሆን እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.16 የበጀት ዝውውር ሳይፈጸም ከደመወዝ በጀት ለሥልጠና የተከፈለ፤

5.16.1 ግኝት

የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 መሰረት ለደመወዝ የተፈቀደን በጀት ለሥራ ማስኬጃ ለመጠቀም በቅድሚያ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መፈቀድ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለግል ኢኮኖሚ ማስፋፊያ ፕሮጀክት ለኮንትራት ቅጥር ሰራተኞች ከተፈቀደው የደመወዝ በጀት ላይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር የበጀት ዘውውር ሳይጠይቅ በኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ቢሾፍቱ ላካሄደው ስልጠና ብር **1,788,204.80** ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.16.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ለደመወዝ የተፈቀደን በጀት በቅድሚያ የበጀት ዝውውር ሳይጠየቅ ለስራ ማስኬጃ ለማዋል የማይፈቀድ መሆኑ እየታወቀ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለስራ ማስኬጃ መጠቀሙ አግባብ አለመሆኑ ተገልጾ ለወደፊቱ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በቅድሚያ ተገቢ የሆነ ዝውውር መፈጸም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.17 በመመሪያው መሰረት ያልተቀነሰ የህክምና ክፍያ፤

5.17.1 ግኝት

ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚያዝያ 16 ቀን 2004 ዓ.ም በቁጥር መ30-899/4 የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን የሚመሩ ዋና እና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚያገኙትን ጥቅማ ጥቅሞች አሰጣጥ በተመለከተ በተላለፈው መመሪያ መሰረት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተርና ቤተሰቦቻቸው በጦር ሀይሎች ሆስፒታል የነጻ ህክምና አገልግሎት ማግኘት እንደሚችሉ

ለዚሁም ከወር ደሞዝቸው ላይ 1% የህክምና መቀነስ እንዳለበት መመሪያ ተላልፏል፡፡ ሆኖም፡

- በዱር እንስሳ ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ብር 810.00፤
- በመድኃኒት ቁጥጥርና ክብካቤ አስተዳደር ባለሥልጣን ብር 2,554.08፤

በድምሩ ብር 3,364.08 ያልተቀነሰ የህክምና ክፍያ መኖሩ ታውቋል፡፡

5.17.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በተላለፈው መመሪያ መሰረት ያልተቀነሰው የህክምና ክፍያ እንዲቀነስ፤ ለወደፊቱም በተላለፈው መመሪያ መሰረት እንዲፈጸም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ እሳስበናል፡፡

5.18 <u>ያልተቀነሰ የቅድሚያ ገቢ ግብር፤</u>

5.18.1 <u>ግኝት</u>

በገቢ ግብርና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ከፈጸማቸው ክፍያዎች ላይ ተገቢውን ተቀናናሾች ቀንሶ ለሚመለከተው አካል ገቢ የሚያደርግ መሆኑ በናሙና ሲጣራ፣ በ3 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 18,128.52 የቅድሚያ ገቢ ግብር ያልተቀነሰና በአማኑኤል ለአሰልጣኞችና ከተለያዩ ክፍያዎች በድምሩ ለብር 70,727.14 የቅደሚያ ግብርና የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተቀናሽ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-8 ና 9 ተመልክቷል/

5.18.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በገቢ ግብርና በታክስ አዋጁ፣ ደንብና መመሪያው መሰረት ክፍያ ሲፈጸም ተቀናሽ የሚደረጉት ሂሳቦች ተቀንሶ ለገቢ ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ገቢ መደረግ ያለበትና የገቢ ደረሰኝ በመቁረጥ ተገቢውን ምዝገባ በማከናወን ገንዘቡ ለገቢው ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ገቢ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል

5.19 <u>የቀረበው የክፍያ ደረሰኝ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደረሰኝ ያለመሆኑ፣</u>

5.19.1 <u>ግኝት</u>

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት ተገቢ የሆነ የወጪ ማስረጃ (ሕጋዊ ደረሰኝ) ሲቀርብላቸው መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

- በመድሀኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን የፅህፈትና የፅዳት ዕቃዎች ግዥ በብር 78,162.97 የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተመዝጋቢ ከሆነው ከአርት የፅህፈትና የፅዳት ዕቃዎች አቅርቦት ኢንተርፕርይዝ የፈጸመ ሲሆን፣ ለክፍያው የቀረበው ደረሰኝ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደረሰኝ ያለመሆኑ፣
- የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ለደረጀ ሲሳይ ቡና ቤትና ስጋ ቤት. ብር 180,527.00 የፈጸመው ክፍያ የተጨማሪ ዕሴት ታክስን የሚጨምር ሲሆን፣ የቀረበው ደረሰኝ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ያለመሆኑ፣

በድምሩ ብር 258,689.97 ከተጨማሪ ዕሴት ታክስ ከፋዮች ላይ ግዥ ተፈጽሞ የቀረበው የክፍያ ደረሰኝ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደረሰኝ ያለመሆኑ ታውቋል፡፡

5.19.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተመዝጋቢ ከሆነ ድርጅት ግዥ ሲፈጸም በህጉ መሰረት መቅረብ ያለበት የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደረሰኝ ሊሆን እንደሚገባና ለወደፊቱም አሰራሩ እንዲስተካከል አሳስበናል፡፡

5.20 <u>በግዢ አፅዳቂ ኮሚቴ ሳይወሰን የተፈጸመ ግዢ፣</u>

5.20.1 <u>ግኝት</u>

በማዕድን ሚኒስቴር በተለያየ ጊዜ ለተለያዩ እቃዎች ግዢ የተከፈለው ብር **16,238,144.22** በግዢ አጽዳቂ ኮሚቴ ሳይድቅ

በዋጋ ወይም በጥራት እንዲገዛ የወሰነው ወይም በፊርማው ያረጋገጠው በግዥ ክፍል ሠራተኛ ብቻ ከመሆኑም በተጨማሪ ስለሁኔታዉ በ2004 ኦዲት ሪፖርት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ምንም አይነት እርምጃ ሳይወሰድበት አሁንም በድጋሚ ሁኔታው የተከሰተ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.20.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የፌዴራል መንግሥት ሰኔ 2002 ዓ.ም ያወጣዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥ አፈጻጸም መመሪያው ተግባራዊ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.21 <u>በመመሪያው መሰረት ተይዞ ያልተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤</u>

5.21.1 <u>ግኝት</u>

የካቲት 8/2002 ዓ.ም በቁጥር ታክ/ቀ/5/102 በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ መሠረት ታክሱን የመሰብሰብ ኃላፊነት የተሰጣቸው የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ከመጋቢት 1 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ከብር 5,000.00 በላይ ከሚፈፅሙት ግዥ ላይ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ክፍያውን በመቀንስ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ እንዳለባቸው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ፡

- የማዕድን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የቧንቧ እና መብራት ዕቃዎች ግዢ ሲፈፅም ብር 2,913.90 የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ክፍያውን ቀንሶ ለታክስ ሰብሳቢው ባለስልጣን ገቢ ማድረግ ሲገባው ክፍያውን ለሻጩ ድርጅት ፈፅሞ የተገኘ መሆኑ፤

- የአማኑኤል ሆስፒታል የሲሚንቶ ግዢ ሲፈጽም ብር 4,800.00 የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ክፍያዉን ቀንሶ ለታክስ ሰብሳቢዉ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ ሲገባዉ ክፍያውን ለሻጩ ድርጅት ፈፅሞ የተገኘ መሆኑ፤

- የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን የተለያዩ የዕቃና የአገልግሎት ግዥ ከታክሱ ተመዝጋቢዎች ላይ ሲፈጽም ብር 334,176.06 የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ ለገቢዎችና ግምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ ሲገባው ክፍያውን ለድርጅቶቹ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 341,889.96 የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀንሶ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ መደረግ ሲገባው ክፍያውን ለሻጮቹ ድርጅቶች ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

5.21.2 የማሻሻያ ሀሳብ

መስሪያ ቤቶቹ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋዮች ላይ የአገልግሎትና የእቃ ግዥ ሲፈጽሙ በመመሪያው መሰረት ታክሱን እየቀነሱ ለሚመለከተው አካል ገቢ ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

5.22 በተከፋይ ያልተመዘገበ የመያዣ ሂሳብ፤

5.22.1 ግኝት

የገ/ኢ/ል/ሚ ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለህንፃ ተቋራጭ ክፍያ ለመፈጸም የክፍያ የምስክር ወረቀት ሲቀርብ ከክፍያው ላይ የመያዣ ሂሳብ ተቀንሶ በሂሳብ መደብ 5061 (በተከፋይ ሒሳብ) በክሬዲት መመዝገብ እንዳለበትና በውሉ መሰረት የመያዣው ሂሳብ ተመላሽ በሚደረግበት ወቅት የመያዣ ሂሳቡ በዴቢት መመዝገብ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ሆኖም የከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከተለያዩ ኮንትራክተሮች የክፍያ የምስክር ወረቀት ቀርቦ ክፍያ ሲፈጽም ተቀናሽ ለተደረገው ብር 2,664,608.80 የመያዣ ሂሳብ በተከፋይ ሒሳብ (በሂሳብ መደብ ቁጥር 5061) በክሬዲት፣ የወጪ ሒሳቡም (በሂሳብ መደብ ቁጥር 6323) በተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ያልተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.22.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የግንባታ ሂሳብ ምዝገባ የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ተከትሎ እንዲመዘገብ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ፤ ለሒሳቡም ተገቢ የሆነ ማስተካከያ እንዲሰራለት አሳስበናል፡፡

6 <u>የሒሳብ ሪፖርት</u>

6.1 <u>በሒሳብ ሪፖርት ላይ ያልተጠቃለለ ሂሳብ</u>፤

6.1.1 <u>ግኝት</u>

የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ የአላጌ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ የሰበሰበውን የውስጥ ገቢ እንዲሁም ከገቢው ሂሳብ ላይ ወጪ ያደረገውን ሒሳብ ብር 8,478,304.65 ከፕሮጀክት ማስተባበሪያው ሂሳብ ጋር አጠቃሎ ለግብርና ሚኒስቴር ሪፖርት ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

6.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የኮሌጁ የውስጥ ገቢና ከውስጥ ገቢ ላይ የተጠቀመው የወጪ ሒሳብ አጠቃቀም ሁኔታ ከማስተባበሪያው የሂሳብ ሪፖርት ጋር ተጠቃሎ ለግብርና ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

6.2 <u>የተጣራ ሀብት ዴቢት ሚዛን የሚያሳይ ስለመሆኑ፤</u>

6.2.1 <u>ግኝት</u>

በፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት ሰኔ 30 ቀን 2005 ዓ.ም በተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የሀብት (Equity) ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ክሬዲት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ ሲጣራ፡

- በህብረት ሥራ ኤጀንሲ የሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው ሀብት (Equity) ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ብር 78,357.63 የዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ፤
- የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆሰፒታል የሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው ሀብት (Equity) ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ብር 1,540,311.93 የዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ፤
- በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን የሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው ሀብት (Equity) ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ብር 124,286.79 የዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ፤
- በአለርት ማዕከል የሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው ሀብት (Equity) ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ብር 29,488.63 የዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 1,772,444.98 የሀብት (Equity) ከወጪ ቀሪ ሂሳብ የዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ ታውቋል፡፡

6.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ

የሀብት (Equity) ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ብር 1የዴቢት ሚዛን ሊያሳይ የቻለበትን ምክንያት ማጣራት ተደረጎ መንስዔው እንዲታወቅ እና ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

6.3 በሂሳብ መግለጫ ላይ የተደረጉ የሂሳብ ማስተካከያዎች፤

6.3.1 ግኝት

በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚደረጉ የሂሳብ ማስተካከያዎች ትክክለኛነት ሲጣራ፡

- የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆሰፒታል ለብር 755,947.11 የተሰሩት የሂሳብ ማስተካከያዎች በተጨባጭ መረጃ ያልተደገፉ እና ግልጽነት የጎደላቸው ከመሆናቸውም በተጨማሪ ለማስተካከያ ሂሳቦቹ የሂሣብ

ምዝገባ ማዘዣ (ጆርናል ቫውቸር) የተዘጋጀላቸው ቢሆንም፡

- ስህተቱ በየትኛው የገቢና የወጪ ደረሰኞች ላይ እንደተፈፀመ፣
- የሂሣብ ማስተካከያው እንዲሠራ ያስፈለገበት ምክንያት፣

ማስተካከያ በተሰራበት የሂሣብ ምዝገባ ማዘዣ ላይ በአብዛኛው ያልተገለጸ መሆኑ ታውቋል፡፡

6.3.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በፋይናንስ ሥርዓትና መመሪያው መሰረት ለአመዘጋገብ ስህተቶች የተሰሩት የሂሳብ ማስተካከያዎች በተገቢው መረጃ መደገፋቸው እንዲረጋገጥና በተጨማሪም ሂሳብ እንዲገጥም ወይም የተወሰኑ የሒሳብ መደቦች ላይ የሚታዩ ሒሳቦችን ለማጥፋት ተብለው የሚሠሩ ማስተካከያዎች ለጥፋትና ለጉድለት መንገድ የሚከፍቱና የሂሳብ መግለጫውን ተዓማኒነት የሚያሳጡት በመሆኑ ማስተካከያው በተገቢው መረጃ ተደግፎ መሰራት እንደሚገባው አሳስበናል፡፡

7 ከወጪ ቀሪ ሒሳብ

7.1 የካፒታልና የውስጥ ገቢ በጀት ከወጪ ቀሪ ሂሳብ፤

7.1.1 ግኝት

- የአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ከፕሮጀክት ማስተባበሪያው ለደመወዝ እና ለሥራ ማስኬጃ እንዲሆን ከተላከለት ገንዘብ ውስጥ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2005 ብር 58,389,680.99 ከወጪ ቀሪ ሒሳብ የነበረ ሲሆን፣ ገንዘብም ፈሰስ ያልተደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ ከከወጪ ቀሪው ሒሳቡ ውስጥ ብር 9,030,140.31 በጥሬ ገንዘብ፣ በባንክና በተሰብሳቢ ሂሳብ

ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ ቀሪው ብር 49,359,540.68 ለረጅም ዓመታት ሳይወራረድ ሂሳቡ የሚገኝበት ሁኔታ በግልጽ ተጣርቶ የማይታወቅ መሆኑ፤

- የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ከፕሮጀክት ማስተባበሪያው ለደመወዝ እና ለሥራ ማስኬጃ እንዲሆን ከተላከለት ገንዘብ ውስጥ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ብር 6,213,746.12 ከወጪ ቀሪ ሒሳብ የነበረ ሲሆን፣ ገንዘቡም ፈሰስ ያልተደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ ከከወጪ ቀሪ ሂሳቡ ውስጥ 5,830,539.81 በጥሬ ገንዘብ፣ በባንክና በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ ብር 383,206.31 በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ የማይታወቅ መሆኑ፤

- የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ከውስጥ ገቢ የሰበሰበውን ገቢ እንዲጠቀም በተፈቀደለት መሰረት ተጠቅሞ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2005 ብር 7,410,183.05 ከወጪ ቀሪ ሒሳብ የነበረ ሲሆን፣ ገንዘብ ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ ታወቋል፡፡ ከከወጪ ቀሪው ሒሳቡ ውስጥ ብር 2,226,070.80 በጥሬ ገንዘብ፣ በባንክና በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ ቀሪው ብር 5,184,112.25 በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ የማይታወቅ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 54,926,859.24 ከወጪ ቀሪ ሒሳብ በምን ሁኔታ እንደሚገኝ የማይታወቅ መሆኑ ታውቋል፡፡

7.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የሒሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ እንዲሁም በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ የከወጪ ቀሪ ሂሳብ ማመዛዘኛ እንዲሰራና ትክክለኛነቱ መረጋገጥ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

8 ንብረት

8.1 የንብረት አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ፤

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች ያለው የንብረት አስተዳደር ሥርዓቱ መንግሥት ባወጣው የንብረት አሰተዳደር መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	9 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	5 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	3 መ/ቤቶች
ቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም ምዝገባ ያላከናወኑ	10 መ/ቤቶች
ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረት የተገኙባቸው	7 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	20 መ/ቤቶች
ተያያዥነት ያለቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	6 መ/ቤቶች

መኖራቸው ተረጋግጧል።

8.2 ሌሎች የንብረት አያያዝ ችግር የሚታይባቸው መ/ቤቶች

8.2.1 ግኝት

1. በቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት

- ከተለያዩ አካላት በዕርዳታ የሚገቡ ዕቃዎች ምዝገባ ቢካሄድላቸውም ዋጋ ያልተተመነላቸው መሆኑ፤

- በ40 ኮንቴነር ታሽገው የሚገኙ የተለያዩ ጥቅም ሊሰጡ የሚችሉና የማይችሉ የቢሮ ዕቃዎችና የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፤

2. በአላጌ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ

- በአንድ ጊዜ 75,000 የሽክላ ጡብ ማምረት የሚችል የሸክላ ማምረቻ ፋብሪካ ከ1975 ዓ.ም ጀምሮ ለኮሌጁ አገልግሎት እየሰጠ አይደለም፡፡ ንብረቱ አገልግሎት ሊሰጥ የማይችል ከሆነ ሁኔታው ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ ያለበት መሆኑ ፣
- ተቀቅሎ በስራ ላይ ሊውል የሚችል እጅግ ብዙ ያልተቀቀለ የሸክላ ጡብ ግድገዳ በሌለው መጋዘን ውስጥ ተከማችቶ የተገኘ መሆኑ፣
- በ2000 በጀት አመት የተገዛ 1394 ከረጢት ጀሶ አስካሁን ለኮሌጁ አገልግሎት ሳይሰጥ የተገኘና ለብልሽት እየተዳረገ መሆኑ፣
- ኢኒኩቤተር (Incubator) እና ጊሪ (Gree) የሚባል ማሽን ከ1994 ጀምሮ አስካሁን ለኮሌጁ አገልግሎት ሳይሰጥ የተገኘ መሆኑ፣
- የኮሌጁ ቄራ ለረጅም ጊዜ የኤሌትሪክ ሲስተሙ የተተበላሸ በመሆኑ ለኮሌጁ መስጠት ያለበትን አገልግሎት በተገቢው ሁኔታ እየሰጠ ያለመሆኑ፣
- በማረጃው ቄራ ውስጥ የሚገኙ 3 ዲፕ ፍሪጅዎች (የጥሬ ስጋ ማስቀመጫ ትልቁ ፍሪጅ፣ የበሰለ (የተቀቀለ) ስጋ ማስመጫ መካከለኛ ፍሪጅ እና የቢራ ማስቀመጫ ፍሪጅ)፣ የአሳማ ስጋ እና ቅመማ ቅመሞች ማደባለቂያ ማሽን፣ በውሃ የሚሰራ የሞርቴዴላ ማሽጊያ ማሽን እና በእንፋሎት

ማንኛውንም ስጋ የሚቀቅል ማሽን ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ሳይሰጡ የተገኙ መሆኑ፣

- በማረጃው ቁራ እስቶር ውስጥ 270 የስሃንና የፕላስቲክ ትልልቅ የስጋ ማስቀመጫ ሳህኖች፣ጥቅም ላይ ያልዋለ 1 ቬንትሌተር እና 2 ኮንፕረሰር፣ የቢላዋ መቀቀያ ማሽን፣ ከቦታ ቦታ የስጋ መውሰጃ ፍሪጅ፣ የተለያዩ መለዋወጫዎች እና ከማሽኑ ጋር የመጡ ኬሚካሎች ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ሳይሰጡ የተገኙ መሆኑ፣

3. በአጋርፋ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ

- በቋሚና አላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት በርካታ የተለያዩ ዓይነት ሞዴል ያላቸው ጥራዝ ደረሰኞችና መዛግብት፤ የታሸጉ ኬሚካሎች እና በርካታ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- በተማሪዎች የምግብ ሸቀጣሸቀጥ ግምጃ ቤት አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ ሳጥን የለስላሳ እና የቢራ ጠርሙሶች የሚገኙ መሆኑ፤
- በመኪና መለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት አገልገሎት መስጠት ያቆሙ የመለዋወጫ ዕቃዎች (Spareparts) ተከማችተው የሚገኙ ሲሆን ፤ የሚሰሩትም ቢሆን በቦታ ጥበት ምክንያት አንዱን ከአንዱ ለመለየት በማያስችል ሁኔታ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- በሳልቫጅ ግምጃ ቤት ውስጥ ሊወገዱ የሚገባቸውና ተጠግነው አገልገሎት መስጠት የሚችሉ በርካታ አሮጌ ጎማዎች፤ በሮች፤ የውሃ ማሞቂያዎች፤ 2 የስንዴ እና የገብስ መዝሪያ ማሽኖች፤ 25 ትላልቅና ትናንሽ ፍሪጆች፤ 43 ታይፕራይተሮች፤

9 ማባዣ ማሽኖች፣ 5 ቴሌቭዥኖች፣ 8 ፕሪንተሮች፣1 የፋክስ ማሽን፣ 2 ኮምፒውተር፣ 1 የቡና መጭመቂያ ማሽን፣ 2 የፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ 800 የስንዴ ምረጥ ዘር ማዳበሪያ ባለ 50 ኪ.ግ፣ 900 የግብአት ባለፕላስቲክ ከረጢት፣ 8613 የፀረ-አረም ማሸጊያ ፕላስቲክ፣ እና 6492 በኬሚካል የተነከረ ጆንያ የሚገኙ ሲሆን፣ መወገድ ያለባቸውና ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉት በአንድነት ተቀላቅለው የተከማቹ መሆኑ፣

- የእህል ግምጃ ቤት ጣሪያ የሚያፈስ በመሆኑ ለምርት ክምችት አመቺ ያለመሆኑ፣
- በእንስሳት እና እንስሳት ተዋጽኦ ግምጃ ቤት ረዥም ጊዜ ያስቆጠሩ የህክምና መሳሪያዎች መኖራቸው ፣
- በዕርዳታ ለሚገቡ ዕቃዎች ምንም እንኳን ምዝገባ ቢካሄድም የዕቃዎቹ ዋጋ የማይጠቀስ መሆኑ፣
- በተማሪዎች ክሊኒክ ውስጥ የመድሀኒት ስቶክ ካርድ እንደማይጠቀሙ፣ ቢን ካርድ የሚጠቀሙ ቢሆንም በምዝገባውና በግምጃ ቤት ተቀምጦ የሚገኘው መደኃኒቶች ብዛት(ቁጥር) እኩል አለመሆኑ፣ ተገቢው የመረጃ አያያዝ ሥርዓት የሌለው መሆኑ፣
- በተሽከርካሪዎቹ ሁለቱም የፊት በሮች ጎን ላይ የኮሌጁን ስም የሚያመለክት መለያ ወይም አርማ ያልተለጠፈ መሆኑ ፣

4. <u>በብሔራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከልና በሆለታ ጣቢያ</u>

- በግንቦት ወር 1993 በሞ/19 ቁጥር 338606 ገቢ የሆኑ በብሔራዊ የእንስሳት ዘር ማሻሻያ ፕሮጀክት

(National Live Stock Development (NLDP)) **የተገዙ ንብረቶች ፤ ይኸውም :**

- ♦ **የወተት ማቀዝቀዣ ፍሪጅ** (Milk Cooler)
- ♦ **ቅቤ መናጫ መሳሪያ** (Butter Churner)
- ♦ **ክሬም ሰፓሬተር** (Cream Separator)
- ♦ **እርጎ መስሪያ** (Yogurt Maker)

መሳሪያዎች ያለአገልግሎት ከ12 **ዓመት በላይ በንብረት ክፍል ውስጥ ተቀምጠዉ የሚገኙ መሆኑ፤**

- **የሞተር ሳር ማጨጃ፤ ተሽከርካሪ ወንበሮች ጠረጴዛ እና ሌሎች ብዛታቸው** 204 **በአይነታቸው የተለያዩ በርካታ ቋሚ ዕቃዎች አስፈላጊዉ እርምጃ ሳይወሰድባቸዉ በጣቢያዉ ግቢ ዉስጥና በንብረት ክፍል ዉስጥ የሚገኙ መሆኑ፣**
- **በንብረት ክፍል ውስጥ የተገኘ የብርሀን መስጫ ቆርቆሮ ብዛት** 39 **በቆጠራ ላይ ያልተቆጠረ ወይም ያልተገለጸ መሆኑ፣**
- **በንብረት ክፍል** 87 **የሚሆኑ አካፋዎች የሚገኙ ሲሆን ፣ ነገር ግን በንብረት ክፍሉ ያሉት አካፋዎች እያሉ ሌላ ግዥ እየተፈጸም መሆኑ፣**
- **የአንድ ቦንዳ ሳር ማምረቻ ዋጋ** (Production Cost) **የማይታወቅና ንብረት ክፍል ገቢ በሚደረግበት ወቅት ዋጋው የማይገለጽ መሆኑ እና በቆጠራ ሪፖርት ውስጥም ያልተካተተ መሆኑ ፣**

5. <u>**በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፤**</u>

- **ብዛት ያላቸው ባለቀለም የህትመት ቀለሞች (Color Print Tonners)፤ የብዕር ቀለሞች እንዲሁም በእርዳታ የተሰጡ ከፍተኛ ቀጥር ያላቸው ቀይ እስክሪብቶዎች ያለ አገልግሎት ለረጅም ጊዜ እንዲመጡ የተደረጉ መሆኑ፤**

- የተለያዩ የማስተማሪያ ፁሁፎች፤ በራሪ ወረቀቶች የህክምና መፅሀፍት፤ እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ ቀደም ብሎ ይጠቀምባቸው የነበሩ የተለያዩ ፎርሞችና ቅፆች በብዛት ታትመው ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤
- ብዛት ያላቸው የማባዣ እና የፎቶ ኮፒ ማሽኖች መለዋወጫ ዕቃዎች በአሁኑ ወቅት የአገልሎት ጊዜያቸው ያለፈና አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ ቢታወቅም ንብረቶቹን ለማስወገድ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
- በመለዋወጫ መጋዘን ከፍተኛ ዋጋ እና ብዛት ያላቸው በእርዳታ ከገቡ መኪናዎች ጋር የመጡ የኢቬኮ መኪና መለዋወጫዎች መኪናዎቹ ለረዥም አመታት ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- የተሽከርካሪዎች ጋራዥ የሞተር እድሳት አገልግሎት በመቋረጡ የመሥሪያ ቤቱ መኪናዎች በግል ጋራዦች እንዲጠገኑ የሚደረግ መሆኑ፤

6. <u>በውሃ፣ የመስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር</u>

- ቃሊቲ ከሚገኘው የኮንስትራክሽን እቃዎች መጋዘን ውጪ አገልግሎት ላይ የማይውሉና ያረጁ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎችና ብረታ ብረቶች ለፀሀይና ለዝናብ ተጋልጠው የተቀመጡ ከመሆኑም በተጨማሪ አገልግሎት ላይ ሊውሉ የሚችሉ ፓይፖችና የፓምፕ ኬብል ከመጋዘን ውጪ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- አሚቼ በሚገኘው መጋዘን ውስጥ ያሉ ያገለገሉ ንብረቶች፤ ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ፋክሶች፣ ፍሪጆች፣ የመኪና ጎማዎች እና የመሳሰሉት ንብረቶች ሳይወገዱ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

7. በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ

- ብዛት ያላቸው ሸሚዞች በወቅቱ ለሠራተኞች ባለመከፋፈላቸው ለረዥም ጊዜ በኮሌጁ ዋና ግምጃ ቤት እንዲቀመጡ የተደረጉ መሆኑ፤
- ጥቅምት 08 ቀን 2005 ዓ.ም በሞዴል 19 ቁጥር 68919 እና 68920 ገቢ የተደረጉ የህክምና መሣሪያዎችና ካሜራዎች ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኞች በግምጃ ቤት ኃላፊው እና በንብረት አስረካቢው ያልተፈረሙ መሆኑ፤
- በእርዳታ እና በግዢ የሚመጡ የህክምና መሣሪያዎችና መድሃኒቶች ሳይለዩ በአንድ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ሆነው በአንድ የንብረት ወጪ ደረሰኝ ለአገልግሎት ወጪ የሚደረጉ መሆኑ፤
- በመደበኛ በጀት ወጪ የሚገዙ የማደንዘዣ መድሀኒቶች፣ ጓንቶች፣ ስሪንጆች እና የላብራቶሪ ኬሚካሎች በዕቃ ወጪ ማድረጊያ (ሞ/22) ወጪ ተደርገው ለግል ህክምና ዘርፍ (Private Wing) አገልግሎት እንዲውሉ የተደረገ መሆኑ፤
- በህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግምጃ ቤት የሚገኙ የህክምና መሣሪያዎች ለአገልግሎት የተቀመጡ ሲሆን፣ የታሸጉ አልሚ ምግቦችና ግሉኮስች ደግሞ ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፤
- የመድሀኒት እና የህክምና መገልገያ መሣሪዎች ግምጃ ቤት ኃላፊዎች በየስድስት ወራት እንዲቀያየሩ ሲደረግ የንብረት ቆጠራ እንዲሁም ርክክብ ሳይደረግ መሆኑ፤
- በራስ እምሩ የሚገኘው የኮሌጁ ማተሚያ ቤት ለኮሌጁ የህትመት አገልግሎት እንዲሰጥ በበቂ

የሰው ኃይል እና የማተሚያ መሣሪዎች የተደራጀ ቢሆንም ኮሌጁ ለማስተማሪያና ለሆስፒታሉ አገልግሎት የሚያስፈልጉ የህትመት ውጤቶችን በሌሎች ማተሚያ ቤቶች በማሳተም የሚጠቀም በመሆኑ የማተሚያ መሳሪያዎቹ ያለአገልግሎት እንዲሁም የክፍሉ ሠራተኞች ያለሥራ እንዲቀመጡ የተደረጉ ከመሆኑም በተጨማሪም ከረጅም ዓመት በፊት ተገዝተው ገቢ የተደረጉ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ወረቀቶችና ካርዶች ያለአገልግሎት እንዲቀመጡ በመደረጋቸው ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፤

8. <u>በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር</u>

- ለረጅም ጊዜ የቆየ አንድ በርሚል(134.6 ሊትር) የጸረ ተባይ ኬሚካል የሚገኝ መሆኑ፤
- ምግብ ነክ ባልሆኑ ግምጃ ቤት ውስጥ ከ1997 ዓ.ም በፊት እና ከ1998 ጀምሮ በእርዳታ የገቡና ያልተንቀሳቀሱ ንብረቶች (ብርድ ልብስ፣ ሸራ፣ የመመገቢያ እቃዎች፣ ጀኔሬተሮች እና የዉሃ ማጣሪያዎች) እንዲወገዱ ለቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት ያሳወቀ ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ፤

9. <u>በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል</u>

- አገልግሎት የማይሰጡ የተለያዩ የተነቃቀሉ የቢሮ ዕቃዎች፣ የተሰበሩ የብረት ወንበሮች፤ የቁም ሳጥን በሮች፤ ትንንሽ የመርፌ መቀቀያ፤ የተበላሸ ስቶቭ፤15 የተሰባበሩ የመደርደሪያ ጣውላዎች፤ የራጅ ማሽን ብረት ትልልቅ የብረት በሮች፤ እንዲሁም አይነታቸው የማይታወቅ የተለያዩ ብዙ እቃዎች በሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

- በቆርቆሮ በተሰራ መጋዘን ውስጥ፣ አገልግሎት የማይሰጡ 700 አሮጌ የተሰራበት ችብዱ፣ 158 የቤት ካዳንቆርቆሮ፣ የህጻን ማጠቢያ፣ የተሰባበረ ጠረጴዛ፣ የህጻን አልጋ፣ መርፌ መቀቀያ፣ ሚዛን፣ የተሰባበሩ ብረቶች፣ 200 የእንጨት ወንበሮች እንዲሁም በአይነቱ የማይታወቁ በርካታ እቃዎች ሳይወገዱ የሚገኙ መሆኑ፣
- በሆስፒታሉ ግቢ ውስጥ ሶስት የኮንቴነር እና አንድ ቆርቆሮ በቆርቆሮ የተሰራ መጋዘን የሚገኙ ሲሆኑ፣ ኮንቴነሮቹ ለረጅም አመታት ሳይከፈቱ ታሽገው የሚገኙ በመሆኑና ቁልፋቸው ባለመገኘቱ ምክንያት የመጋዘኖቹን ውስጣዊ ሁኔታ ማየት አልተቻለም፡፡ ነገር ግን በውስጣቸው የተለያዩ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ በርካታ ንብረቶች የሚገኙባቸዉ መሆኑ፣

10. በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

- በአሮጌ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ለረጅም ጊዜ የተከማቹ ብዛት ያላቸው ጎማዎች፣ የተለያዩ ብረታ ብረቶች፣ ኮምፒውተሮች፣ ወንበሮች፣ ፋክስ ማሽኖች ካልኩሌተሮች፣ ታይፕራይተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ ዩፒኤሶች (UPS)፣ ምንጣፎች፣ ፕሮጀክተሮች፣ ወንበሮች እና የመሳሰሉት፣ የሚገኙ ሲሆን በደንቡ መሰረት ተጠግነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ መጠገን የማይችሉት ደግሞ እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፣

11. በአባይ ተፋሰስ ባለስልጣን

- የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ እና በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም አስተያየት የተሰጠበት

ቢሆንም አሁንም ማስተካከያ ሳይደረግበት የተገኘ መሆኑ፤

- በዋናው መ/ቤትና በቆጋ ውኃ እንክብካቤ ጽ/ቤት ብዛት ያላቸው አሮጌ ጎማዎች፣ የተለያዩ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች፣ ኮምፒውተሮች፣ ወንበሮች፣ የፋክስ ማሽን፣ የፎቶ ኮፒ ማሽን እና የመሳሰሉት፣ የሚገኙ መሆኑ፤

12. በአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል

- በየንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞችን ከስቶክ ካርድና ከቢን ካርድ ጋር ሲመሳከር ብር 146,773.93 ዋጋ ያላቸው አስራ ሁለት ዓይነት ዕቃዎች ሳይመዘገቡ ተገኝተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በ2005 በጀት ዓመት ለአብዛኛው ንብረቶች ስቶክ ካርድና ቢን ካርድ ያልተከፈተላቸውና ተገቢው ምዝገባ ያልተከናወነላቸው መሆኑ፣
- በመድኃኒትና በፋርማሲ ክፍል ውስጥ የሚገኙ የህክምና መገልገያ መሳሪያ ንብረቶች ሙሉ በሙሉ በ2005 ዓመታዊ ቆጠራ ውስጥ ያለተካተቱ ከመሆኑም በተጨማሪ በስቶክ ካርድ ላይ ያልተመዘገቡ መሆኑ፣
- በ2005 ንብረት ቆጠራ የተካሄደ ቢሆንም በአሮጌ እቃ መጋዘን የሚገኙ ንብረቶች፣ አገልግሎት የማይሰጥ አንድ ቶዮታ (ጃፓን) መኪና በአመታዊ ቆጠራ ውስጥ ያልተካተተ መሆኑ፣
- የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸዉ መድሃኒቶች እና አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የህክምና እቃዎች ላይ የማስወገድ እርምጃ ሳይወሰድባቸው በንብረት ክፍል ተከማችተዉ የሚገኙ መሆኑ፤
- በእርዳታ የሚገቡ መድኃኒቶች እና የህክምና እቃዎች ዋጋ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ላይ የማይጠቀስ መሆኑ፤

- እያንዳንዱ መድኃኒት በቁጥር በአይነት ተለይቶ በስቶክ ካርድ የማይያዝ ሲሆን፣ ቢን ካርድ የተዘጋጀ ቢሆንም ተገቢው ክትትል ተደርጎ የማይመዘገብ መሆኑ ፣
- የመድኃኒት መጋዘኑ የተጨናነቀና አየር ማስገቢያ የሌለው እና መድኃኒቶችን በቀላሉ ለመለየት የማያስችል መሆኑ፣
- የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢዎች የዕለት ገቢ የሚሰበስቡበትን ደረሰኞች በኃላፊነት ከንብረት ክፍል በሞዴል 22 ወጪ እንዲያደርጉ መደረግ ሲገባው ከሰነድ ክፍል ወጪ የሚያደርጉ መሆኑ፣

13. <u>በዱር እንስሳ ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን</u>

♦ <u>በአብያታ ሻላ ብሔራዊ ፓርክ</u>

- በአብያታ ሻላ ብሔራዊ ፓርክ በጊዜያዊነት የተመደቡት የፓርኩ የንብረት ክፍል ሰራተኛ ስራ የጀመሩባቸው የተለያዩ ቅፆች (ሞ/19፣ ሞ/22፣ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች እና የወጪ ማዘዣ ደረሰኞች) ርክክብ ሳይደረግ በፊት የነበሩት የንብረት ክፍል ሰራተኛ ይጠቀሙበት የነበረውን ቅፆች በመጠቀም ሥራ የጀመሩ መሆኑ፣

♦ <u>በአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ</u>

- የቀድሞ ንብረት ክፍል ሰራተኛ ለአዲሷ ንብረት ክፍል ሰራተኛ ሲያስረክቡ ያስረከቡት ንብረት ማስረከብ ባለባቸው ልክ ለመሆኑ ያልተረጋገጠ መሆኑ፣
- በአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ለረጅም ጊዜ የተከማቹ፣ ዲናሞዎች፣ የእንስሳት መንጓንዣ ሳጥኖች፣ የአጥር ሽቦዎች፣ የመብራት

ጄነሬተሮች ፣ የወዳደቁ የተለያዩ ብረታ ብረቶች የመኪና ባትሪዎች ፣ ፍሪጆች ፣ ፍራሾች ፣ የመኝታ ከረጢት(ሲልፒንግ ባግ)፣ ድንኳኖች፣ ወንበሮች፣ ታይፕራይተሮች፣ የውሀ ኮዳዎች፣ ብርድ ልብሶች ፣ አልጋ ልብሶች፣ አልጋዎች ፣ አንሶላዎች፣ የመደመሪያ ማሽኖች፣ ፋኖሶች፣ የውሀ ማጣሪያዎች፣ የመኪና መለዋወጫ እቃዎች፣ የኦክስጂን ሲልንደሮች፣ አጉሊ መነፅሮች፣ የኮምፒውተር ማስቀመጫ ቦርሳዎች፣ እንዲሁም አገልግሎት በማይሰጠው ጋራጅ ውስጥ የሚገኙ የተለዩ የጋራጅ መጠቀምያና መለዋወጫ እቃዎች የሚገኙ መሆኑ፣

14. <u>በመድሀኒት ቁጥጥር ክብካቤና አስተዳደር ባለስልጣን</u>

- በአሮጌ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ለረጅም ጊዜ የተከማቹ ብዛት ያላቸው ኮምፒውተሮች ፣ ላፕቶፖች፣ የተለያዩ ብረታ ብረቶች፣ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ ፋክስ ማሽኖች፣ ካልኩሌተሮች፣ ታይፕራይተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ ዩፒኤሶች (UPS)፣ ፕሮጀክተሮች፣ ደብተሮች፣ የወፍጮ ሚዛን፣ የስልክ ቀፎዎች፣ የእርሳስ መቅረጫዎች ፣ ማህተም መርገጫዎች፣ መቀሶች እና የመሳሰሉት በንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣ እንዲሁም በግቢው ውስጥ በርካታ የማያገለግሉ ጎማዎች፣ ሞተር ሳይክል፣ ቆርቆሮ፣ ብረታብረቶች፣ ፍሪጅ እና የመሳሰሉት በተለያየ ቦታ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

15. በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ

- ለአንድ እቃ ከአንድ በላይ እስቶክ ካርድ የተከፈተለት መሆኑ፤
- አልፎ አልፎ ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ ላይ የእቃዎች ዋጋ ያልተጠቀስ መሆኑ፤
- በድሪሊንግ መጋዘን አዳዲስ ማሽኖች (Center lulher lazth machine Model LLA65X200HS፣ Universal Miling Machene Quantity/SPU-ch/ no with manul፣ Pour operated sharing Machine 74030075 Model Ns 506) ለረጅም ጊዜ ያለስራ ቆመው የሚገኙ መሆኑ፤
- መወገድ ያለባቸው አሮጌ ንብረቶች (ኮምፒውተሮች፣ የቢሮመገልገያ ዕቃዎች፣ የመስክ ዕቃዎች፣ የላቦራቶሪ ዕቃዎች፣ ቶነሮችና የሰርቬይንግ ዕቃዎች) እንዲወገዱ ያልተደረጉ መሆኑ፤
- በድሪሊንግ መጋዘን ውስጥ የሚገኙና መወገድ የሚገባቸው ኬሚካሎች ለመጋዘን ሰራተኛውም ሆነ አካባቢውን በትነት እየበከሉ መሆኑ፤
- በድሪሊንግ ዕቃ መጋዘኖች ውስጥ የድሪልንግ ዕቃዎች ከኬሚካል ጋር በአንድነት የተቀመጡ ሲሆን ዚንክ የተባለ ኬሚካል በወለሉ ላይ ፈሶ የሚገኝ መሆኑ፤
- በመካኒሳ የኬሚካል ማስቀመጫ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ ኬሚካሎች (TALINITE,QUCIK GEL, BENTONITE, LIBONITE እና CMC) አልፎ አልፎ ከረጢቱ ተቀድዶ በወለል ላይ እየፈሰሰ የሚገኝ ሲሆን፤ ሶዳ አሽ (SODA ASH) 4 በርሜል ለረዥም ዓመታት በመጋዘን ውስጥ ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፤

- የድሪልንግ ቁጥር 2 መጋዘን ጣሪያው በስተደቡብ በኩል የሚያፈስ መሆኑ፤
- በድሪሊንግ መጋዘን ውስጥ ዋጋቸው የማይታወቁ አዳዲስ የወርክ ሾፕ ማሽኖች በቬርቫል እና በቢን ካርድ ላይ ባለው መረጃ መሰረት ከ20 ዓመት በላይ ለሚሆን ግዜ ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

16. <u>በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት</u>

- በዕቃ ግምጃ ቤት ጥገና ቢደረግላቸው አገልግሎት መስጠት የሚችሉና የማይችሉ፤ 1 ፕሪንተር እና 1 ኮምፒውተር፤ 2 ዩፒኤስ (UPS)፤ 6 የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ (ዲቫይደር)፤ እንዲሁም 9 የሚሆኑ የመኪና ጎማዎች የሚገኙ መሆኑ፣

17. <u>በአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን</u>

- <u>በላይኛውና ታችኛው አዋሽ</u>

    - የንብረት ሠራተኞች ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነት፣ ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ ላይ የመመዝገብ፣ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 እና የንብረት ወጪ ደረሰኝ ሞ/22 የማዘጋጀት ሥራ ደርበው የሚሰሩ መሆኑ፣

    - ንብረት ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ አሮጌ ጎማዎች፣ የተለያዩ የመኪና መለዋወጫዎች፣ የተለያዩ ብረታ ብረቶች፣ ኮምፒውተሮች፣ ወንበሮች፣ ስካነሮች፣ የመደመርያ ማሽኖች፣ ታይፕራይተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ሌዝ ማሽን፣ ፓውዛዎች፣ ማባዣ ማሽን፣ ፍሪጆች፣ ዩፒኤስ (UPS)፣ ስታፕላይዘሮች፣ መጠረዣ፣ የመኪና ባትሪዎች፣ የውኃ ሞተር፣ የሠነድ መያዣ ቦርሳዎች፣ በርሜሎች፣ የብረትና የእንጨት

አልጋዎች፣ ፍራሾች፣ የአየር ማቀዝቀዣዎች (ኤየር ኮንዲሽነሮች)፣ ካናል ውኃ መጠን መለኪያ፣ የወተት ማስቀመጫ ጋኖች፣ ስሊንደሮች፣ ስቶቮች፣ የእጅ ጋሪዎች፣ የመጽሃፍ መደርደርያዎች፣ የቪድዮ ካሴቶች፣ የፎቶ ኮፒ ማሽን፣ የልብስ ማጠብያ ማሽን፣ የጀልባ ሞተሮች፣ የመገናኛ ሬድዮዎች የሚገኙ ሲሆን በደንቡ መሰረት ተጠግነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ መጠገን የማይችሉት ደግሞ እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፣

18. በአካባቢና ደን ሚኒስቴር

- በ2003 በጀት ዓመት የተገዛ በወቀቱ በነበረዉ ዋጋ መሰረት ብር 19,248.00 የሚወጣ የሚያገለግል የፎቶ ኮፒ ቀለም በመጋዘኑ ዉስጥ ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፣
- በሰራተኛ ስም የሚገኙ ንብረቶች ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ በሚሆኑበት ወቅት የፕሮጀክት እና የመደበኛ ንብረቶች ተብለዉ የማይለዩ መሆኑ፣
- የንብረት ክፍል ሰራተኞቹ ሲቀጠሩ ዋስ የሌላቸዉ መሆኑ፣
- የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 4-10090 መኪና ንብረቱ ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ ሳይሆን በግለሰብ እጅ የሚገኝ መሆኑ፣
- የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 4-28752 መኪና ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ ያልሆነና በማን ስም እንደሚገኝ የማይታወቅ መሆኑ፣

19. የአለርት ማዕከል

- ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የተለያዩ የመኪና መለዋወጫዎች ወደ ግምጃ ቤት ገቢ ሲደረጉ እንዲሁም ለአገልግሎት ወጪ ሲሆኑ በየስማቸው

ስቶክ ካርድ ያልተዘጋጀላቸውና የማይመዘገቡ መሆኑ፤

20. የኢትዮጵያ የጤናና ስነ-ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት

- በኬሚካልና ላብራቶሪ ግምጃ ቤት ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ የላብራቶሪ መሳሪያ ኬሚካሎች ሪኤጀንቶችና የተለያዩ አላቂ ዕቃዎች፤
- በተሽከርካሪ መለዋወጫና ነዳጅ ግምጃ ቤት ውስጥ የሚወገዱና የማይወገዱ የተለያዩ መለዋወጫዎች በአንድነት ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

ስለሁኔታው በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም የተገለጸ ቢሆንም በዚህ በጀት ዓመትም ያልተስተካከለ መሆኑ፣

8.2.2 የማሻሻያ ሀሳብ

የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲስተካከል ተገቢው ጥረት መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

8.3 የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም

8.3.1 ግኝት

በየመሥሪያ ቤቶች ውስጥ ያለው የተሽከርካሪዎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓትና መረጃ አያያዝ በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ3 መ/ቤቶች	27 ተሽከርካሪዎች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ17 መ/ቤቶች	88 ተሽከርካሪዎች
በተለያዩ ድርጅቶች ሥም ሊቢሬ ያላቸው ወደ መ/ቤቱ ስም ያልተቀየረላቸው	በ3 መ/ቤት	7 ተሽከርካሪዎች

8.3.2 የማሻሻያ ሀሳብ

በንብረት አስተዳደሩ መመሪያው መሰረት ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉት ተሽከርካሪዎች እንዲጠገኑ መጠገን የማይችሉት ደግሞ በንብረት አስተዳደሩ መመሪያው መሰረት እንዲወገዱ መደረግ እንዳለባቸው እንዲሁም ሊቢሬ ለሌላቸው ተሽከርካሪዎችም ሊቢሬ እንዲወጣላቸው መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

9 በጀት

9.1 ከመደበኛኛ ከካፒታል በጀት ያልተሰራበት ሂሳብ፤

9.1.1 ግኝት

በልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት ኦዲት ለተደረጉት መስሪያ ቤቶች በ2005 በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሳብ ሲመዛዘን ከመደበኛ በጀት ከ10% በላይ ብር 94,161,183.64 እንዲሁም ከካፒታል በጀት 456,389,523.89 በድምሩ 550,550,707.53 ሥራ ላይ ያልዋለ ሲሆን ከተደለደለው በጀት በላይ ደግሞ ከመደበኛ በጀት ብር **2,689,772.75** ከካፒታል በጀት ደግሞ ብር **5,911,540.04** በድምሩ ብር 8,601,312.79 ወጪ መሆኑ (ለዝርዝሩ አባሪ 29 ተያይዟል) ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በ3 መ/ቤቶች ብር 4,156,214.79 ከውስጥ ገቢ ከተደለደለውና ከተፈቀደው በጀት በላይ የወጣ ሂሳብ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-29/1 ተመልክቷል/

9.1.2 የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቶች በጀትን በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይችሉ ዘንድ በዕቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሠረተ በጀት ሊይዙ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

10 የውስጥ ገቢ ዕቅድ ክንውን

10.1 በዕቅዱ መሰረት ያልተገኘ ገቢ

ግኝት

- የአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ በ2005 በጀት ዓመት ከውስጥ ገቢ ብር 15,655,646.00 ለመሰብሰብ አቅዶ ብር 3,835,441.10 ብቻ የሰበሰበ ሲሆን፣ በዕቅዱ መሰረት ብር 11,820,204.49 ያልተገኘ ገቢ መሆኑ፤

- በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ የ2005 በጀት ዓመት የውስጥ ገቢ ዕቅድ ከክንውኑ ጋር ሲመዛዘን ኮሌጁ በ2005 በጀት ዓመት ብር 10,780,221.00 ለመሰብሰብ አቅዶ ብር 7,043,626.09 የሰበሰበ ሲሆን፤ ብር 3,736,594.31 (35%) በዕቅዱ መሰረት ያልተገኘ ገቢ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 15,556,798.80 በዕቅዱ መሰረት ያልተገኘ ገቢ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ኮሌጆቹ የገቢ ዕቅድ ሲያቅዱ ተጨባጭ መረጃን መሰረት በማድረግ በገቢ አሰባሰቡ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ ፣ ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ አሳስበናል፡፡

11 ልዩ ልዩ

11.1 በ2004 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች፤

ግኝት

1. በግብርና ሚኒስቴር

   - የአገልግሎት ግዜ ያለፈባቸው በርካታ ሲሚንቶዎች፣ ሰብሎች፣ እጅግ ብዛት ባላቸው ኮንቴነሮች የታሸገ የመሬት

ማዳበሪያ እና ሌሎች ቋሚና አላቂ እቃዎች እርምጃ ሳይወሰድባቸው ለረጅም ጊዜ በመጋዘን ውስጥ እና ከመጋዘን ውጭ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

- ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ 28 የቴክኒክ ብልሽት ያለባቸው ተሽከርካሪዎች ያለአገልግሎት ለረጅም ጊዜ ቆመው የሚገኙ መሆኑ፤
- በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ የተጋላጭነት ደረጃ መለየት እና የስጋት ተጋላጭነት ፍተሻ ያልተደረገ መሆኑ፤

2. <u>በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር</u>

- ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ብር 1,500,985.84 ቀረጥ ለተከፈለባቸው እቃዎች የጉምሩክ ዲክላራሲዮን እና ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) እንዲሁም ብር 408,302,049.00 ቀረጥ ለተከፈለባቸው ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ያልቀረበላቸው መሆኑ፤

- የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል መድኃኒት ቤት ላይ ልዮ ኦዲት አከናውኖ ባቀረበው የውስጥ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በሕግ ክፍሉ በኩል ህጋዊ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

3. የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታሉ ለዴንታል ዩኒት ስትሪም ስቴራላዘር ግዥ ለቅድሚያ ክፍያ ከመድሀኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ ጋር በ2003 ዓ.ም ውል መዋዋሉ እና ቅድሚያ ክፍያ ብር 1,141,675.20 ፈጽሞ በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ መመዝገቡ ተገልጾ ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ አስተያየት በተሰጠው መሰረት ማስተካከያው ያልተደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ በውሉ መሰረት ዕቃው እስካሁን ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

4. <u>በዱር እንስሳ ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን</u>

- ♦ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ለተመዘገበው ሂሳብ ብር 3,223.36 ተመዝግቦ ለተገኘው ሂሳብ በዚህ ኦዲት ወቅትም ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፣

- ♦ በ2004 በጀት ዓመት መጨረሻ በመሥሪያ ቤቱ የቆጠራ ኮሚቴ የቋሚና አላቂ እቃ ቆጠራ በተከናወነበት ወቅት፣

- ✓ አንድ ላፕቶፕ ቶሺባ ኮምፒውተር ከነቦርሳው፣

- ✓ አንድ ዲጂታል ካሜራ ከ4ጂቢ ሚሞሪ ካርድ ጋር፣

- ✓ አንድ ድንኳን እና አንድ አጉሊ የሜዳ መነፅር፣ በቆጠራ ወቅት ያልተገኙና ያልተቆጠሩ መሆኑ ተገልጾ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያልተደረገ መሆኑ፣

5. የአካባቢና ደን ሚኒስቴር የሚገለገልባቸው የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶች ስም ለሆኑ ሰባት ተሽከርካሪዎች በመሥሪያ ቤቱ ሥም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር እንዲዘጋጅላቸው አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር እንዲዘጋጅላቸው ያልተደረገ መሆኑ ፣

6. <u>በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ</u>

- ✓ በ2004 በጀት ዓመት የተሰበሰበ ገቢ ብር 21,819,664.39 በአደራ ሂሳብ መደብ (5054) እንዲሰበሰብ የተደረገ መሆኑ፤

- ✓ በ2004 በጀት ዓመት የበጀት አዋጅ መሰረት ከውስጥ ምንጭ ከሚሰበስበው ገቢ ላይ እንዲጠቀም የተፈቀደለት ገንዘቡ ሥራ ላይ ሲውል በተፈቀደው የበጀት ርዕስ መሰረት በወጪ መያዝ ሲገባው በአደራ የሒሳብ መደብ (5054) ብር 11,736,794.08 እንዲያዝ የተደረገ መሆኑ፣

✓ **<u>ከውጪ ተገዝተው ገቢ ያልተደረጉ ዕቃዎች፤</u>**

- በዩኤስ ዶላር 1,620.76 የተገዛው ቢት ብሬከር 17 1/2 እንዲሁም 10,000.00 ዶላር ከሚያወጣው ስታንዳርድ አክሰሰሪስ ፎር ድሪሊንግ ውስጥ ሁለት አዳብተር ቢት ብሬከር ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ፤

- በዩኤስ ዶላር 812,800.04 የተገዛው የውሃ መቆፈሪያ ሪግ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ፤

- በዩኤስዶላር 3,235.00 የተገዛው የድሪሊንግና ሌሎች ተጓዳኝ መሣሪያዎች መለዋወጫ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

- ከተገዙት የመለዋወጫ ዕቃዎች ውስጥ በዩኤስ ዶላር 4,600.00 የተገዙት የመለዋወጫ ዕቃዎች ያልመጡ መሆኑ፤

ተገልጾ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድ ባለበት ሁኔታ የሚገኝ መሆኑ፤

7. <u>የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር</u>

- የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከተቋራጮች የክፍያ የክፍያ የምስክር ወረቀት በቀረበበት ወቅት የቀነሰውን የመያዣ ሂሳብ ብር 41,419,848.07 በተከፋይ ሒሳብ (5061) በክሬዲት ያልመዘገበ መሆኑ ተገልጾ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በድጋሚ አሳስበናል፡፡

11.2 በ2002 እና 2003 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል እርምጃ ያልወሰደባቸው ግኝቶች፤

ግኝት

- የአባለዘርና የፈሳሽ ናይትሮጅና መሸጫ ዋጋው በመመሪያ ያልተደገፈ መሆኑ፤
- በአብዛኛው በእንስሳትን በሌሎች ቋሚ ንብረቶች ቆጠራ ሪፖርት ላይ የንብረቶቹ ዋጋ የማይጠቀስ መሆኑ፤
- ታህሳስ 2000 ዓ.ም በወጣው የመንግሥት ቋሚ ንብረት አስተዳደር ማንዋል መሰረት ለማዕከሉ እና ለሆለታ ጣቢያ ቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ተሚልቶ ያልተሰጠ መሆኑ ፤
- አባለዘር መስጠት የማይችሉ ኮርማዎችና ሌሎች የወተት ዘር ከብቶች ጉዳት ሲደርስባቸውና ሲያረጁ የሚወገዱበት መመሪያ የተዘጋጀ ቢሆንም መመሪያው ያልጸደቀ መሆኑ

የማሻሻያ ሃሳብ

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ እንዲደረግ ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በድጋሚ አሳስበናል፡፡

11.3 በውስጥ ኦዲት ክፍል ላይ የታዩ የአሠራር ክፍተቶች፤

ግኝት

በግብርና ሚኒስቴር

- የውስጥ ኦዲት ክፍሉ 21 የሰው ኃይል የሚያስፈልገው ቢሆንም አሁን 8 የሰው ኃይል ያለው መሆኑ፤
- ሥጋትና ተጋላጭነት ያለባቸውን የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን የሥራ ክፍሎች በመለየት ስራውን የማይሰራ መሆኑ፤
- የውስጥ ኦዲት ክፍሉ በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ሥር ያሉትን ኮሌጆችን፣ በግብርና ሥር የሚገኙ ተጠሪ መሥሪያ ቤቶችን፤ የኳራንቲን ጣቢያዎችን እና ቂራዎችን ዕቅድ አውጥቶ ኦዲት የማያደርግ መሆኑ፤
- በግብርና ማስተባበሪያ ሥር የሚገኙ ኮሌጆች ሥር እንዲሁም ለግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ መሥሪያ ቤቶች በዓመቱ መጨረሻ የሚቆጠሩ የጥሬ ገንዘብና የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የፌሰስ ሪፖርት ጋር የማይጠቃለል መሆኑ፤

በአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ

- የውስጥ ኦዲት አገልግሎቱ በ2005 በጀት አመት እቅዱ መሰረት ሥራውን ያላከናወነ እና በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሰረት የየሩብ ዓመቱ ሂሳብ ኦዲት ያልተደረገና ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ፤
- የውስጥ ኦዲት አገልግሎቱ ለሚመለከተው ክፍል የስራ አፈፃፀም (Progress Report) ሪፖርት የማያቀርብ መሆኑ፤

በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ

የውስጥ ኦዲት ክፍሉ የ2005 በጀት አመት የኦዲት እቅድ ያዘጋጀ እና የ2005 በጀት ዓመት የፊስስ ሪፖርትና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያለቸውን ሥራዎች ከመሥራቱ ውጪ ሌሎቹን ሥራዎችን በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሰረት የየሩብ ዓመቱን ሂሳብ ኦዲት ያላደረገና ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ፤

በዱር እንስሳ ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን

- ለኦዲት ክፍሉ የተፈቀደው የሰዉ ሃይል አስራ ዘጠኝ ሲሆን፣ አሁን በስራ ላይ የሚገኙት ስድስት ብቻ መሆናቸው፣
- በአብያታ ሻላ ሐይቆች ብሄራዊ ፓርክ የውስጥ ኦዲት ክፍል፡
- የ2005 በጀት ዓመት የ4 ወር እቅድ ያቀደ ቢሆንም በፓርኩ ሀላፊ ያልፀደቀ መሆኑ፣
- በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሰረት በዝርዝር የተሰሩ የኦዲት ስራዎችን የሚያሳይ የኦዲት ስራ ወረቀት ወይም መግለጫ ያላዘጋጀ መሆኑ እና ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊም የኦዲት ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ፣

የመድሀኒት ቁጥጥርና አስተዳደር ባለስልጣንና የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ያላደረገ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቶች ለውስጥ ኦዲት ክፍሎች መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች እንዲሟሉ እንዲያደርጉ የውስጥ ኦዲት ክፍሎችም የኦዲት ሥራውን በማከናወን በመመሪያዉ ላይ በተቀመጡት ግዜ ዉስጥ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊና ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት እንዲያቀርቡ አሳስበናል ፡፡

11.4 <u>ዋስትና በሚያስፈልጋቸዉ የስራ መደቦች ላይ የተመደቡ ሰራተኞች ዋስትና (ተያዥ) እንዲያቀርቡ ያልተደረገ ስለመሆኑ</u> ፤

<u>ግኝት</u>

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የፌዴራል መንግሥት ሰራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003 መሠረት በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት ወይም ንብረት ያዥነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሰራተኞች ሁሉ ለተሰጣቸው ኃላፊነት የሚሆን ዋስትና ወይም ተያዥ እንዲሰጡ ወይም እንዲያቀርቡ መደረግ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ሆኖም፡

- በብሔራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል በናሙና ከተመረጡት ሰራተኞች ውስጥ አንድ ገንዘብ ያዥ፣ ሁለት ጥበቃዎች እና አንድ የዕቃ ግምጃ ቤት ሰራተኛ ዋስትና (ተያዥ) እንዲያቀርቡ ያልተደረገ መሆኑ፤
- በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ስድስት የግምጃ ቤት ኃላፊዎች እና ሰላሳ ሰባት የጥበቃ ሠራተኞች ዋስትና ያላስያዙ መሆኑ፤
- በማዕድን ሚኒስቴር መሥሪያ አራት ገንዘብ ያዦች ስድስት የግምጃ ቤት ኃላፊዎች እና ሰላሳ አራት የጥበቃ ሠራተኞች ዋስትና ያላስያዙ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በፌዴራል መንግሥት ሰራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003 መሠረት በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት ወይም ንብረት ያዥነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች ሁሉ ለተሰጣቸው ኃላፊነት የሚሆን ዋስትና ወይም ተያዥ እንዲሰጡ ወይም እንዲያቀርቡ መደረግ እንዳለበት እናሳስበናል፡፡

11.5 በሰራተኛ ያልተሞሉ ክፍት የሥራ መደቦች፤

ግኝት

- የግብርና ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በመዋቅር ከተፈቀደለት 2139 የሰራ መደቦች ውስጥ 983 (46%) የሥራ መደቦች ሰራተኞች ያልተቀጠረባቸው መሆናቸው፤
- የዱር እንስሳ ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን በመዋቅር ከተፈቀደለት 1,876 የሰራ መደቦች ውስጥ 1,057 (56%) የሥራ መደቦች ሰራተኞች ያልተቀጠረባቸው (ክፍት) መሆናቸው፣
- የመድሀኒት ቁጥጥርና አስተዳደር ባለሥልጣን በመዋቅር ከተፈቀደለት 587 የሰራ መደቦች ውስጥ 140 (24%) የሥራ መደቦች ሰራተኞች ያልተቀጠረባቸው (ክፍት) መሆናቸው፣
- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚንስቴር በመዋቅር ከተፈቀደለት 561 የሰራ መደቦች ውስጥ 234 (41.71%) የሥራ መደቦች ሰራተኞች ያልተቀጠረባቸው (ክፍት) መሆናቸው፣
- የኤሌክትሪክ ኤጀንሲ ኤጀንሲው በመዋቅር ከተፈቀደለት 164 የስራ መደቦች ውስጥ 88 (54%) የስራ መደቦች ሰራተኛ ያልተቀጠረባቸው (ክፍት) መሆናቸው፣
- የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በመዋቅር ከተፈቀደለት 414 የሰራ መደቦች ውስጥ 243 (58%) የሥራ መደቦች ሰራተኞች ያልተቀጠረባቸው (ክፍት) መሆናቸው፣
- በማዕድን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በመዋቅር ከተፈቀደለት 498 የሰራ መደቦች ውስጥ 162 (33%) የሥራ መደቦች ሰራተኞች ያልተቀጠረባቸው (ክፍት) መሆናቸው፣

ታውቋል፡

የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቶቹ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ያስችላቸው ዘንድ ክፍት የስራ መደቦችን በቅጥርና በእድገት እንዲሞሉ ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

11.6 በመቋቋሚያ ደንቡ መሰረት ያልተፈጸሙ ሥራዎች፤

ግኝት

የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 198/2003 የተቋቋመ ሲሆን በደንቡ አንቀፅ 12(2ለ) መሰረት የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የኤጀንሲውን ሰራተኞች ቅጥር በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሰረት እንዲሁም እንደተፈለጉ ሊገኙ የማይችሉ ባለሞያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሰረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚፀድቅ መመሪያ መሰረት እንደሚቀጥርና እንደሚያስተዳድር እንዲሁም በደንቡ አንቀፅ 14 መሰረት ደግሞ የኤጀንሲው የሥራ ማስኬጃና የደመወዝ በጀት በመንግሥት እንደሚመደብ ተመልክቷል፡፡ ኤጀንሲው በደንቡ ላይ በተገለፀው መሰረት በመንግሥት የጸደቀ መመሪያ እና የፀደቀ ድርጅታዊ መዋቅር እንዲሁም በመንግሥት ለስራ ማስኬጃ የተፈቀደ በጀት አለመኖሩ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ኤጀንሲው በደንቡ ላይ በተገለፀው መሰረት በመንግሥት የጸደቀ መመሪያ እና የፀደቀ ድርጅታዊ መዋቅር አዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ማስደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

አባሪ 1

ተ.ቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ሥም	መ/ቤቶቹ የተመደቡበት የስጋት ደረጃ	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፓርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
				መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	ግብርና ሚኒስቴር	ከፍተኛ 1	24/04/2006	1,009,418,181.98	627,188,796.19	1,636,606,978.17
2	የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	ከፍተኛ 1	ህዳር 2006	76,631,763.12	552,966,789.10	629,598,552.22
3	የውሃ፣ የመስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር	ከፍተኛ 1	ታኅሳስ 1/ 2006	56,042,855.68	3,006,098,500.00	3,062,141,355.68
4	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	ከፍተኛ 2	ህዳር 2006	74,097,856.27	95,500,000.00	169,597,856.30
5	የብሄራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ	ከፍተኛ 2	24/04/2006	34,200,089.00	33,400,000.00	67,600,089.00
6	የህብረት ስራ ኤጀንሲ	መካከለኛ	11/04/2006	15,032,370.00		15,032,370.00
7	የመጠባበቂያ ምግብ ክምችትአስተዳደር	መካከለኛ	07/02/2006	16,885,400.00		16,885,400.00

ተ.ቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ሥም	መ/ቤቶቹ የተመደቡበት የስጋት ደረጃ	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፓርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
				መደበኛ	ካፒታል	ድምር
8	የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን	ዝቅተኛ	05/13/2005	7,825,000.00		7,825,000.00
9	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	መካከለኛ	27/02/2006	23,399,340.00	63,191,320.00	86,590,660.00
10	የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል	መካከለኛ	29/02/2006	17,931,790.00	13,000,000.00	30,931,790.00
11	የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት	መካከለኛ	04/04/2006	16,490,714.00	10,000,000.00	26,490,714.00
12	የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት	መካከለኛ	21/01/2006	3,581,100.00	50,000,000.00	53,581,100.00
13	የኢትዮጵያሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢኒስቲትዮት	መካከለኛ	14/04/2006	12,313,250.00		12,313,250.00
14	የብሔራዊ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ አስተዳደር	ዝቅተኛ	15/02/2006	1,126,380.00		1,126,380.00
15	የአማኑኤል የአዕምሮ ሰፔሻላይዝድ ሆሰፒታል	መካከለኛ	28/02/2006	29,905,100.00	16,000,000.00	45,905,100.00
16	የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሀኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን	ከፍተኛ 2	10/04/2006	36,015,830.00	62,756,940.00	26,741,110.00

ተ.ቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ሥም	መ/ቤቶቹ የተመደቡበት የስጋት ደረጃ	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፓርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
				መደበኛ	ካፒታል	ድምር
17	የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር	መካከለኛ	23/01/2006	18,729,470.36		18,729,470.36
18	የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	መካከለኛ	02/03/2006	29,232,517.83	13,000,000.00	42,232,517.83
19	የአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን	መካከለኛ	16/03/2006	65,911,608.44		65,911,608.44
20	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	መካከለኛ	07/05/2006	47,431,730.00	28,436,640.00	75,868,370.00
21	የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን	ዝቅተኛ	28/02/2006	10,043,360.00		10,043,360.00
22	የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን	ዝቅተኛ	13/01/2006	21,261,700.00		21,261,700.00
23	የመንገድ ፈንድ ጽሕፈት ቤት	ዝቅተኛ	01/12/2005	5,163,520.00		5,163,520.00
24	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኤጀንሲ	ዝቅተኛ	22/02/2006	6,163,542.82		6,163,542.82
25	የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	ከፍተኛ 2	ህዳር 2006	59,423,994.40	251,737,767.50	311,161,761.90
26	የትራንስፖርት ሚኒስቴር	መካከለኛ	13/01/2006	18,310,900.00		18,310,900.00
27	የኢትዮጵያ ጤናና ሥነ ምግብ ኢኒስቲትዩት	መካከለኛ	01/04/2006	22,447,490.00	12,734,500.00	35,181,990.00

ተ.ቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ሥም	መ/ቤቶቹ የተመደቡበት የስጋት ደረጃ	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
				መደበኛ	ካፒታል	ድምር
28	የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ	መካከለኛ	04/03/2006	9,521,640.00	1,053,950.00	10,575,590.00
29	የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን	መካከለኛ	27/03/2006	25,443,170.00		25,443,170.00
30	የኢፌዲሪ ስፖርት ኮሚሽን	መካከለኛ	24/01/2006	61,033,600.00	106,017,000.00	167,050,600.00
31	ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ	መካከለኛ	14/12/2005	6,048,000.00		6,048,000.00
32	አለርት ሆስፒታል	መካከለኛ	02/02/2006	34,590,151.57	10,000.000.00	44,590,151.57
33	ማዕድን ሚኒስቴር	መካከለኛ	ኅዳር 2006	23,584,320.00	42,726,000.00	66,310,320.00
	ድምር			1,895,237,735.47	4,985,808,202.79	6,819,014,278.29

ንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት
የ2005 በጀት ዓመት የኦዲት ዕቅድ ክንውንና
ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች ሪፖርት

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ

1.1. የጥሬ ገንዘብ የባንክ ሂሣብ አያያዝ ድክመቶች

ከ2004 በጀት አመት በፊት መኪና ለመግዛት ሌተር ኦፍ ክሬዲት ተከፍቶ በፑል የባንክ ሂሣብ ገቢ ከሆነው ተራፊው እና በገ/ኢ/ል/ሚ/ር የታገደ የመኪና ግዥ ለማእከላዊ ግምጃ ቤት ተመላሽ በመመሪያው መሠረት ገቢ ያልሆነ፤

- በፌድራል ማረሚያቤቶች አስተዳደር ብር 1,247,332.17
- በኢትዮጲያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ብር 1,335,963.72

1.2. በሰኔ 30/2005 በባንክ ካለው ገንዘብ በታች በሪፖርት የተደረገ

- በኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ብር 10,437.99
- የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማይደረግና በሂሳብ ክፍል ከሚገኘው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሌጀር ጋር የማይመዛዘን መሆኑ ፡
- በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰኔ 30,2005 በቀረበው የሂሳብ ሚዛን ሪፖርት በሂሳብ መደብ ቁጥር 4114 በዝውውር ላይ ያለ የባንክ ተቀማጭ /Deposit in transit/በሚል የተመለከተው ብር31,663,784.76 ሲሆን እንዲሁም በቀረበው የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ መሠረት የተመለከተ ብር 30,050,597.13 በመሆኑ በልዩነት የታየው ብር 1,613,187.63 ባንክ ገቢ የሆነበት የባንክ ክሬዲት አድቫይስ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

  ኦዲት አስደራጊዎቸ ይህንን ገንዘብ ሰኔ 30 ቀን 2005 ዓ.ም ከገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተሰጠው መመሪያ መሠረት እንዳይንቀሣቀስ (block) የተደረገ ሲሆን፣ ምዝገባው ሊከናወን የሚገባው

በተሰብሳቢ ሂሣብ /4210/ ቢሆንም ገንዘቡ እጅግ የተጋነነና ተዓማኒነት የሚያሣጣ በመሆኑ ለጊዜው በዝውውር ላይ ያለ የባንክ ተቀማጭ /4114/ ተመዝግቦ ሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ.ም ወደትክክለኛው ሂሣብ /4103/ የሚመለስ መሆኑን፡በዚህ ምክንያት የሚቀርብ ማስረጃ እንዳልነበረው ገልጸዋል፡፡በመሆኑምበልዩነት ለታየው ብር 1,613,187.63 በዝውውር ላይ ያለ የባንክ ተቀማጭ /deposit in transit/ ተብሎ የተያዘው ሂሳብ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ደጋፊ ማስረጃዎች (የባንክ ክሬዲት አድቫይስ) ቀርቦለት ስለትክክለኛነቱ በውስጥ ኦዲት ተረጋግጦ መቅረብ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

1.3. የሰኔ 30/2005 የባንክ ማስተረቂያ ያልተሰራለት የባንክ ሂሳብ

- የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የፋይናስ መመሪያ የባንክ ሂሳቦች የየወሩ የባንክ ሂሣብ ማስታወቂያ ከባንክ ሂሣብ ሌጀር ከወጪ ቀሪ ጋር ማስታረቂያ እየተሰራ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መቅረብ እንዳለበት ቢያዝም በሀገር መከላከያ ሚ/ር የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ በስሙ ለተከፈቱት ሁለት የባንክ ሂሳቦች የሰኔ 30/2005 ዓ.ም. የባንክ ማስታረቂያ ያላዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

1.4. ወደ ባለመብቱ የባንክ ሂሣብ በማስተላለፍ ክፍያ እንዲፈጸም የሚያዘውን መመሪያ የተላለፈ ክፍያ

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ቁጥር 6 ንኡስ ቁጥር 5 በጀት ዓመቱ ውስጥ የሚከፈሉ የክፍያ መጠናቸው ከብር 50,000 /ሃምሣ ሺህ ብር በላይ የሆኑ ወጪዎች መከፈል ያለባቸው ወደ ባለመብቱ ባንክ ሂሣብ በማስተላለፍ እንደሆነ ቢያዝም በ9 መ/ቤቶች ብር 281,019,805.18/ዝርዝራቸው በአባሪ-5 ተመልክቷል/ መመሪያውን በመተላለፍ በቼክ ክፍያ ፈጽመው መገኘታቸውን በመግለጽ መንግስት በባንክ ሂሳብ ላይ የዘረጋው ቁጥጥር ተግባረዊ እንዲሆን በመመሪያው መሰረት እንዲፈጽሙና መመሪያውን በመፈጸም በኩል ያሉትን ችግሮች ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር በማሳወቅ መፍትሔ እንዲያገኝ እንዲደረግ እሳስበናል፡፡

መሥሪያ ቤቶቹ በሰጡት መልስ ለአገልግሎት ሰጪና ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች ክፍያዎችን ለመፈጸም በመንግስት የንግድ ባንክ የከፈቱትን

የባንክ ሂሳብ ቁጥር እንዲያሳውቋቸው ሲጠይቋቸው በመንግስት ንግድ ባንክ የተከፈተ የባንክ ሂሳብ ቁጥር የሌላቸውና የድርጅታቸው አካውንት ያለው በግል ባንክ መሆኑን በመግለጽ ክፍያዎችን በቼክ እንዲሰጣቸው የሚጠይቁ መሆኑን፤ ከመንግስት የንግድ ባንኮች ወደግል ባንኮች የመንግስት ገንዘብ ማዘወር ስለማይቻል፣ በተጨማሪም በባንክ ዝውውር ለሚፈጸም ክፍያ የገቢ ደረሰኝ ማግኘትና መሰብሰብ አስቸጋሪ በመሆኑና አንዳንድ ድርጅቶችም በባንክ ዝውውር ለተፈጸመ ክፍያ የገቢ ደረሰኝ አንቆርጥም እንደሚሉአቸው፡ገልጸዋል፡፡

1.5. <u>በሰኔ 30/2005 ለባለጥቅሞቹ ሳይከፈል እንደተከፈለ በመቁጠር ባንክ በወጪ ተከፋይ ሂሳብ በዴቢት የተመዘገበ ሂሳብ</u>

- የፌዴራል ፖሊስ ኮምሽን የአስተዳደር ልማት ዘርፉ ብር 59,128,463.63

ከዚህ ውስጥ የፌዴራል ፖሊስ ኮምሽን ወንጀል መከላከል ዘርፍ ብር 7,722,,206.64 ሲሆን፡ በሰኔ 30ቀን 2005 በባንክ ብሎክ ተደርጎ በሐምሌ 2005 መጀመሪያ ተመልሶ ገቢ የተደረገ ሲሆን ኮሚሽኑ ሂሳቡ ለባለመብቶቹ እንደተከፈለ በመቁጠር ተከፋይን ዴቢት ባንክን ዴቢት በማድረግ ጄቪ በማዘጋጀት በሰኔ 30 ቀን 2005 ምዝገባ አካሂዶ ሀምሌ 2005 መጀመሪያ ገንዘቡ ተመላሽ ተደርጎ የሪቨርሲንግ ምዝገባም ተካሂዶ ተገኝቷል፡፡ የተከፋይ ሂሳቡ ለባለጥቅሞቹ ሳይከፈል እንደተከፈለ በመቁጠር በዴቢት በመመዝገቡ የተከፋይ ሂሣብ ሪፖርቱ እና በባንክ ያለው ገንዘብ በብር 59,128,463.63 ዝቅ ብሎ መገኘቱን፡ የሂሳብ አሰራርን ያልተከተለ መሆኑንና ሪፖርቱ የኮሚሽኑን የሂሳብ እንቅስቃሴ በትክክል የማያሳይ መሆኑን በመግለጽ ምዝገባው እንዲስተካከል አሳስበናል፡፡ ኮሚሽኑ ለተላከለት የሥራ አመራር ሪፖርት መልስ አልሰጠም፡፡

1.6. <u>በባንክ ካለው ገንዘብ በታች ሪፖርት የተደረገ</u>

በውጭ ጉዳይ ሚ/ር በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2005 በሂሳብ ሪፖርት የተመለከተውን በባንክ ያለ ገንዘብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ የብራሰልስ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን በባንክ ያለ ገንዘብ

በብር 159,911.88 በማነስ ሪፖርት ተደርጎ መገኘቱን በመግለጽ ሪፖርቱ እንዲስተካከል አሳስበናል፡፡

2. ተሰብሳቢ ሂሣቦች

2.1. ውዝፍ የሠነድ /ተሰብሳቢ/ ሂሣብ

የውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በ 11 መ/ቤቶች ብር 259,567,429.89 በወቅቱ ያልተወራረደ ሂሳብ ተገኝቷል። (አባሪ 6)

ከነዚህ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ከፍተኛው የሀገር መከላከያ ሲሆን ተሰብሳቢዎቹን የሚገልጽ ዝርዝር ቢቀርብም ደጋፊ ማስረጃዎቹ በአባሪነት አለመቅረባቸውንና ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ እንዲወራረዱም ክትትል ሊደረግባቸው እንደሚገባ፤ እንዲሁም በፋይናንስ ዳይሬክቶሬቱም ሆነ በሌሎች ክፍሎች የሚገኙት ተመሳሳይ ሂሳቦች ማስረጃቸው ተፈልጐ በፋይናንስ ዳይሬክቶሬቱ ሊጠበቁና እንዲሰበሰቡ ክትትል እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር ስለብር 18,708,030.10 በሰጠው መልስ በመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት በሂሳብ መደብ 4201 በተሰብሳቢ ሂሳብ ተመዝግቦ የሚገኘው ብር 11,593,098.46 ከሽግግር መንግስቱ ጀምሮ በተለያዩ የጦር ክፍሎች በነበሩት አባላት የጠፋና ገንዘቡንም ለማስመለስ ክፍሎቹ በተለያያ ምክንያት የፈረሱ ወይም የታጠፉ ወይም ወደ ሌላ የጦር ክፍል የተቀላቀሉ በመሆናቸውና አባላቱን ይዞ ገንዘቡን ለማስመለስ አብዛኛው በህይወት የሌሉ፣ በተለያየ ምክንያት ከተቋሙ የለቀቁ ወይም የተሰናበቱና አድራሻቸው የማይታወቅ በመሆኑ ለረጅም ጊዜ በዳይሬክቶሬቱ የሂሳብ ምዝገባ ላይ በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ ተመዝግቦ የሚታይና ከመዝገብ ለማሰረዝ በወጣው መመሪያ መሰረት ሂሳቡን ከመዝገብ ለማሰረዝ ደጋፊ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ላይ እንደሆኑ አስፈላጊው ሰነዶች ሲሟሉ ከመዝገብ እንዲሰረዝ ለሚመለከተው አካል የሚያቀርቡ መሆኑን፤

የሂሳብ መደብ 4210 በተመለከተ በማዕከል፣ በዕዞችና በዋና መምሪያዎች በተሰብሳቢ ከሚታየው ገንዘብ ውስጥ ብር 45,000,000.00 በመከላከያ የበላይ አካል ትዕዛዝ ከሰራዊት የደመወዝ ተመላሽ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ላይ

ለዝቋላ ስቲል ሮሊን በ2004 በጀት ዓመት የተሰጠና በቀጣይ ድርጅቱ የሚመልሰው መሆኑን፡ ከላይ ከተገለጸው ብር 5,188,285.76 ብር 4,093,372.83 በየጊዜው ለውጪ ጉዞና ልዩ ልዩ ተያያዥ ወጪዎች በቅድሚያ ለአባላት የተከፈለ መሆኑንና ቀሪው በማዕከል፣ በዕዞችና መምሪያዎች ለአባላት የተደረገ የቅድሚያ ክፍያ ወደፊት ሰነዱን በማጣራትን አስፈላጊውን ማስረጃ በማጠናቀር በሰነድ ወይም በጥሬ ገንዘብ እንዲወራረድ የሚጠበቅ ሂሳብ መሆኑን፤

ከላይ ከተመለከተው ብር 29,744,019.00 በአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ብር 2,970,000.00 ለሃንጋር ስራ በቅድሚያ ለተቋራጭ ድርጅት መከፈሉንና ድርጅቱ አስፈላጊውን ስራ ሳይጨርስና ርክክብ ሳይፈጽም ስራው መቋረጡን፣ አሁን ተቋራጭ ድርጅቱ ቀሪ ስራውን በመፈጸም ላይ የሚገኝ መሆኑን በዚህ በጀት ዓመት የቀሪ ስራውን ርክክብ በመፈጸም ሂሳቡ የሚወራረድ መሆኑን፤ በ2003 በጀት ዓመት ለመረጃ መረብና ደህንነት ኤጀንሲ በውል መሰረት በቅድሚያ የተከፈለው ገንዘብ ብር 24,367,855.88 እና ቀሪው ብር 2,227,858.25 ለተለያዩ ድርጅቶች በቅድሚያ ክፍያ ተሰጥቶ እስካሁን ያልተወራረደና ከ1997 ዓ.ም. ጀምር በምዝገባ የሚታይ ሂሳብ መሆኑን ወደፊት አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ በሰነድ ወይም በጥሬ ገንዘብ እንዲወራረድ የሚደረግ መሆኑን፤ መ/ቤቱ ገልጿል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ከተመለከተው የተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ብር 87,179,420.79 በ2005 በጀት ዓመትውስጥ ብቻ የተከሰተ የተሰብሳቢ ሂሳብ መሆኑን፤ መ/ቤቱ ካለው የስራ ባህሪ (ዋናው መ/ቤት እና ሚሲዮኖች መካከል ካለው ርቀት አንፃር) እና የ3ኛ ወገን (የሌሎች መ/ቤቶች) ሂሳቦች ጭምር የሚያንቀሳቅስ እንዲሁም ለከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት የህክምና ወጪ ሸፍኖ እስከሚተካለት ድረስ ሰፊ ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ ወደ 2006 በጀት ዓመት የዞረ መሆኑን በ2006 በጀት ዓመት ክትትል ተደርጎ አብዛኛው የተወራረደ መሆኑን፤ ብር 102,430,856.14 ከአሁን በፊት ለረጅም ዓመታት ሲንከባለል የቆየና መ/ቤቱ በሂሳቦቹ ላይ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ባደረገው ከፍተኛ ጥረት ከተጠቀሰው ሂሳብ ውስጥ ብር 45,063,222.52 በ2006 በጀት ዓመት መወራረዱን፤ማስረጃ ከሌለው ብር 4,674,501.18 ማስረጃወችን አሟልተው ከ3ኛ ወገን እንዲተካ

በሂደት ላይ መሆኑን፣ ብር 14,000,691.61 ሊሰበሰብ የማይችል ሂሳብ ተብሎ በመ/ቤቱ በኩል ተለይቶ ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ እና ማስረጃ ከሌለው ቀሪው ብር 35,583,206.29 ረጅም ዓመታት የቆዩ ሰነዶች መሆናቸውን በቀጣይ ሂሳቡን ለማወራረድ በቂ ማስረጃ መኖሩን ለማረጋገጥ መ/ቤቱ ባቋቋመው የተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ አጣሪ ግብረ ሃይል እየተሰራ መሆኑን ገልጿል፡፡ ፌደራል ፖሊስ መልስ አልሰጠም፡፡

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ የአካባቢ ምርጫ በተካሄደበት ወቅት ለምርጫ አስፈጻሚዎች የሚከፈል የድጎማ አበልና ስራ ማስኬጃ ለዞን የምርጫ አስተባባሪዎች በሰነድ የተሰጠ መሆኑና ከፍተኛውን ሂሳብ በ2006 በጀት አመት መወራረዱን በላኩት መልስ ገልጸዋል፡፡

2.2. በተሰብሳቢ ሂሣብ የታዩ የአሠራር ችግሮች

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት

ኤጀንሲው ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ውል የገቡት መ/ቤቶች ለአገልግሎቱ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ገቢ ሲያደርጉ ሂሳቡን በሂሳብ መደብ 5054 በክሬዲት፣ አገልግሎቱን ከሰጠ በኃላ ወጪ ሲያደርግ በዚሁ የሂሳብ መደብ በዴቢት የሚመዘግብ ሲሆን ኤጀንሲው በበጀት አመቱ ውል የገቡት መ/ቤቶች በቅድሚያ ካስገቡት በላይ ከሌሎች ፕሮጀክቶች ለ34 መ/ቤቶች ብር 83,377,549.17 ወጪ አድረጎ ክፍያ ሲፈጽም በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው 5054 ዴቢት በማድረጉ ተሰብሳቢ ሂሳቡ በተጠቀሰው ገንዘብ ዝቅ ማለቱን እንዲሁም ኤጀንሲው ከባለበጀት የመንግሥት መ/ቤቶች ጋር በሚያደርገው ውል መ/ቤቶቹ በየበጀት ዓመቱ መንግሥት በፈቀደላቸው በጀት የሚተዳደሩና ብድር መውሰድ የማይፈቀድላቸው በመሆኑ፤ መ/ቤቶቹ በቅድሚያ ለኤጀንሲው ገቢ ካደረጉት በላይ ወጪ የሚጠይቅ ከሆነ በበጀት ዓመቱ ገቢ እንዲያደርጉ መጠየቅ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡ በሌላ በኩል መ/ቤቶቹ ካስገቡት በላይ ወጪ ካደረገላቸው መ/ቤቶች ለሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 39,752,723.03 ይገኛል፡፡ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የ2005 በጀት አመት ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ ለኤጀንሲው በ2003 በጀት አመት በቅድሚያ የከፈልኩት አገልግሎት ያላገኘሁት ብሎ በተሰብሳቢ የያዘው

ብር 24,367,855.88 መኖሩን በመግለጽ መ/ቤቶቹ ካስገቡት ገንዘብ በላይ ወጪ የተደረገው ሂሣብ በኤጀንሲው በተሰብሳቢ ተመዝግቦ በበጀት ዓመቱ መጨረሻም በትክክለኛው የሂሣብ መደብ በሪፖርቱ ሊገለጽ እንደሚገባና ከመከላከያ ሚ/ር ጋርም የሂሳብ ማስታረቅ ሥራ ሊሠራ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

<u>በውጭ ጉዳይ ሚ/ር</u>

በኔጋቲቭ (ክሬዲት) የተመዘገበ ብር (1,853,939.53) ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ

<u>የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የሥልጠና ማዕከል፡</u>

- በ2005 በጀት አመት በሚያዝያ ወር የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከD አካውንት መቀነስ ሲገባው ከz አካውንት የቀነሰው ብር 112,226.51

  እንዲሁም ባንኩ ያለማዕከሉ ትዕዛዝ የቀነሰው ›› <u>2,450.00</u>

  በድምሩ ብር 114,676.51 ገንዘቡ ተመላሽ ሳይደረግ በተሰብሳቢ መያዙ የበጀት ሂሳቡንም አላግባብ መጠቀም በመሆኑ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

3. <u>የገቢ ሂሳብ</u>

3.1. <u>በገቢ ግብርና ታክስ አዋጅ፤ህግ መሠረት ያልተሰበሰበ</u>

የገቢ ሂሳብ በትክክል ለመሰብሰቡ ኦዲት ሲደረግ በ5 መ/ቤቶች ብር 159,489.90 በገቢ ግብርና ታክስ አዋጅ፤ህግ መሠረት ያልተሰበሰበ ሂሳብ መኖሩ ተረጋግጧል። (አባሪ 8) ከዚህም በታላቁ የህዳሴ ግድብ ተለያ ግዥዎች ተፈጽመው ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሲሆን በህጉ መሰረት አለመሰብሰቡ አግባብ አለመሆኑን በመግጽ አሰራሩ እንዲታረም አሳስበናል፡፡ ጽ/ቤቱ ስራ የጀመረው በ2005 ዓ.ም በ2ኛው ሩብ አመት መሆኑንና መመሪያዎች እንዳልደረሰው በዚህም ምክንያት ችግሩ መፈጠሩን ገልጿል፡፡

3.2. በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የታዩ የአሰራር ድክመቶች

በፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ

- እስከ 6 ወር ዘግይቶ ፈሰስ ያልተደረገ የገቢ ሂሣብ ብር 343,378.80
- የትራንስፖርት አገልግሎት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የሆነ ግብይቶች ሆኖ እያለ መቆረጥ የማይገባው ተቀንሶ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተከፈለ ብር 6,962.40 ተገኝቷል፡፡
- ጽ/ቤቱ ከሚሰበስበው የገቢ ርዕስ ውጪ በሂሣብ መደብ 1203 (ኤክሳይዝ ታክስ ጨው)፣ 1295 (የቴምብር ሽያጭ)፣ 1419 (የቴሌቭዥን አገልግሎት)፣ 1421 (የቡና ምርመራ) እና 1459 (ከሌሎች ዕቃዎችና አገልግሎቶች) በገቢ መቀበያ ደረሰኝ (RV) እና በገቢ ማጠቃለያ (SRV) ገንዘቡ ገቢ የሆነበት ደረሰኝ ቁጥር በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ሣይጠቀስ ብር 106,416.76 በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ሳይተላለፍ በሌጀር ብቻ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

3.3. የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ

ኤጀንሲው በበጀት ዓመቱ ከልማት ድርጅቶች ሽያጭ ብር 217,121,184.12 እና በሊዝ ከተሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ብር 38,267,877.44 በድምሩ ብር 255,389,061.56 የሰበሰበው ገቢ በተገቢው የሂሳብ መደብ 1504 በገቢ ሂሳብ ከልማት ድርጅቶች ሽያጭ ተመዝግቦ መታየት ሲገባው በተከፋይ ሂሳብ በ5054 ሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ተገኝቷል። በፌዴራል የመንግስት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት እንደተጠቀሰው የአደራ ገንዘብ የተወሰኑ ሁኔታዎች ሲሟሉ ለአስቀማጩ ተመላሽ የሚደረግ መንግስት በጊዜያዊነት በአደራ የያዘውን ገንዘብ የሚታይበት እንደሆነ ተመልክቷል። በመሆኑም ኤጀንሲው ከልማት ድርጅቶች ሽያጭ እንዲሁም በሊዝ ከተሸጡ ድርጅቶች የሚሰበስበው ገቢ ለዚሁ ተብሎ በተሰየመው የገቢ ሂሳብ መደብ 1504 በገቢ መዝግቦ ሪፖርት ሊያደርግ እንደሚገባ። ይህ ካልሆነ ከዘርፉ የተገኘው ገቢም ሆነ ለማስፋፊያ ወጪ የሚደረገው ሂሳብ በትክክል ተለይቶ እንዲያዝ ካለማድረጉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱ የኤጀንሲውን የሂሳብ እንቅስቃሴ እንዳያሳይ እንደሚያደርግ ገልጸናል፡፡

በሥራ አመራሩ ምለሽ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 26 ሐምሌ 26 ቀን 2004 ዓ/ም የፌዴራል መንግስት የ2005 ገቢ በጀት ላይ የተጠቀሰው ቁጥር 1504 በሂሳብ መደብ ገቢ ዝርዝር ውስጥ የሌለ በመሆኑ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተነጋግረው በተቀመጠው አሰራር መሰረት በአደራ ገቢ እንዲያዝ የተደረገ መሆኑን እየገልጸው ከዚህ በተጨማሪ በፌዴራል ለጋሪት ጋዜጣ አስራስምንተኛው እትም ቁጥር 18 አዋጅ ቁጥር 730/2004 ዓ/ም በፊደል ተራ ቁጥር ሀ እና ለ የፕራይቬይታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል አዋጅ ላይ በአገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ቁልፍ ሚና ሊጫወት የሚችል በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 2(1) ለመክፈል ወይም አክሲዮኖች ሙሉ በሙሉ በመንግስት የተያዘ አክስዮን ማህበርን ለማሻሻል ወይም ለማስፋት የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን አንዱ የገንዘብ ምንጭ ከልማት ድርጅቶች ሽያጭ የሚገኝ ገቢ ነው በማለት በዚህ ምክንያት የልማት ድርጅቶች ሽያጭ የሚገኝ ገቢ በ1504 የሚለው ኮድ ከመደበኛ ገቢ የወጣ በመሆኑ በገቢ በጀት አዋጅ ላይ ባልተጠቀሰ የወጪ መደብ ገቢን መመዝገብ አግባብነት የሌለው መሆኑንና እንዲሁም በየወሩ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከሚላከው የሂሳብ ሪፖርት ጋር ሊታረቅ ስለማይችል በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ መውሰድ በኤጀንሲው በኩል የሚቸገሩ መሆኑን ገልጸዋል።

3.4. ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ ያልተደረገ ገቢ

በሀገር መከላከያ መ/ር በበጀት ዓመቱ የሰሜን ዕዝ ጠቅላይ መምሪያና በሁርሶ የመሰረታዊ ውትድርና ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ከልዩ ልዩ ገቢዎች የሰበሰበው ገንዘብ በገቢ ተመዝግቦ ለመንግስት ገቢ የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ከጨረታ ሰነድ ሽያጭ፣ በዕዙ ሆስፒታል ከሚታከሙ የሲቪል ሰራተኞች 50% የህክምና አገልግሎት፣ ከመድሃኒት ሽያጭ፣ የተለያዩ የሰራዊት አባላት በንብረት ላይ ላደረሱት ጥፋት የከፍሉት ምትክ የንብረት ግምትና አቅራቢዎች በጨረታ ውሉ መሰረት ባለመፈጸማቸው የተሰበሰበ ቅጣት በድምሩ ብር 574,242.84 ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈሰስ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ገቢ መደረግ ሲገባው በተከፋይ

ሂሳብ መደብ 5054 ሌሎች መያዣዎች ተመዝግቦ በሀገር መከላከያ ሚ/ር በኩል ለልዩ ገቢ መምሪያ ገቢ የተደረገው አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ፣ ገቢዎች መምሪያ የተቋቋመው ሰራዊቱ በሰላም ጊዜ በልማት ላይ ወይንም ምርት እያመረተ ገቢ እንዲሰበሰብ በመሆኑ መንግስት ከመደበው በጀት የተገዛን መድሃኒት እና ከተሰጡ የህክምና አገልግሎቶች የተሰበሰበን 50%፣ በህጉ መሰረት የተሰበሰበን ቅጣት፣ንብረት በማጥፋት ከአባላቱ የተተካን ገንዘብ እና ሌሎቹም ከበጀት ጋር የተያያዙ ገቢዎች በመሆናቸው አላግባብ ወደ ገቢዎች መምሪያ ፈሰስ በመደረጉ ተመላሽ ሊደረግና ለወደፊቱም አሰራሩ እንዲስተካከል አሳስበናል፡፡

መ/ቤቱ በላከው መልስ የተጠቀሱት ገቢዎች ለመከላከያ ገቢዎች ዳይሬክቶሬት ገቢ መደረጉ ስህተት መሆኑን፣ ተመላሽ የተደረገውን ገንዘብ ማስረጃውን በማረጋገጥ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ እንደሚያደርግና ወደፊትም ግኝቱን መሰረት በማድረግ ስህተቱ እንዳይቀጥል አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ እንደሚወስዱ ገልጿል፡፡

3.5. <u>የተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተቆረጠለት ሂሳብ</u>

በሀገር መከላከያ ሚ/ር የአየር ሀይል ጠቅላይ መምሪያ የመስተንግዶ የወጪ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በተለያዩ ክፍያዎች ብር 157,952.25 የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ያልተቆረጠለትና ያልተመዘገበ ሂሳብ መገኘቱን በመግለጽ ደረሰኝ እንዲቆረጥለት አሰራሩም እንዲስተካከል እንዲሁም መ/ቤቱ በሰጠው መልስ የጠቅላይ መምሪያው አየር ምድብ ነጣላ የሂሳብ ምዝገባ በመፈጠሩ ደረሰኝ አለመቆረጡን ቢገልጽም በሚከተለው የምዝገባ ስርአት ደረሰኝ መቁረጥ እንደሚቻል አሳስበናል፡፡

4. <u>የወጪ ሂሣብ</u>

4.1. <u>ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በ9 መ/ቤቶች ብር 49,637,840.76 እና በ5 መ/ቤቶች ብር 11,891,455.32 ማስረጃ ሳይቀርብ

በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ መኖሩ ተረጋግጧል። /ዝርዝሩ በአባሪ -13 እና 14 ተመልክቷል/

4.2. ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎችና የተሰጠ ብድር

ወጪ ሆነው የተመዘገቡት ወጪዎች በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ7 መ/ቤቶች ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች ብር 877,367.42 እና በ1 መ/ቤት አላግባብ የተሰጠ ብድር ብር 24.00 ሚሊዮን በድምሩ ብር 24,877,367.42 መኖሩ ተረጋግጧል። /ዝርዝሩ በአባሪ -16 ተመልክቷል/

ከዚህ ውስጥ ከፍተኛው የሀገር መከለከያ ሚ/ር ሲሆን መንግስት ካለው ውስን በጀት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ከመደበው በጀት በኮንስትራክሽን በመከላከያ ኮንስትረክሽን ኢንተርፕራይዝ በኩል ለዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ፋብሪካ ብድር መስጠቱ የመንግስትን የገቢ ምንጭ ያላገናዘበና ዘርፉ ከተቋቋመለት ዓላማ ውጪ የተሰጠ ብድር መሆኑን በመግለጽ አሰራሩ እንዲታረም እና ሚ/ር መ/ቤቱ ተገቢውን ቁጥጥር እንዲያደርግ አሳስበናል፡፡

ሚ/ር መ/ቤቱ በላከው መልስ ኢንተርፒራይዙ በወቅቱ በነበረበት የካሽ ፍሎው እጥረት ብድሩ መሰጠቱን ጠቅሶ የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ገንዘቡን ለዘርፉ በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 592596 ብር 11,000,000.00 እና በገቢ ደረሰኝ ቁጥር ብር 13,000,000.00 በድምሩ 24,000,000.00 ብር ከሶስት ወራት ባነሰ ጊዜ ተመላሽ ያደረገ መሆኑን፣ ግኝቱን በአስተማሪነት በመውሰድ ወደፊት ድርጅቱ የስራ ዕቅዱን መነሻ በማድረግ የጥሬ ገንዘብ ፍላጎቱን ከዕቅዱ ጋር የተጣጣመ እንዲሆንና የብድር ጥያቄና አሰራርም እንዳይከሰት ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እንደሚያደርግ ገልጿል፡፡ ሌሎቹ ከመንግስት መመሪያ ውጭ የትርፍ ሰዓት ክፍያ የተከፈለ፣ ከትዕዛዝ ውጪ በብልጫ የተከፈለ የመስተንግዶ ወጪ፣ የደመወዛቸው መጠን ሳይገለጽ የተከፈለ የውሎ አበል ክፍያ፣ያለአገልግሎት ለቆሙ ተሽከርካሪዎች ለኢንሹራንስ ክፍያ ይገኝበታል፡፡ የትርፍ ሰዓት

ክፍያ መፈፀም ያለበት የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ የታገደ መሆኑንና መመሪያው ተጠብቆ እንዲሰራ አሳስበናል፡፡

<u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት</u>

- የቦርዱ ሰብሳቢ ስብሰባ ለመካፈል ላወጡት ወጪ በሚል ከውጭ አገር ከተመለሱ በኋላ ብር 7,744.00 በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ሲሆን ስብሰባው በ2004 የተካሄደና ክፍያው በዚያው በጀት ዓመት ከጉዞው በፊት በቅድሚያ መፈጸም ሲገባው ከበጀት ዓመቱ ውጪ በ2005 በጀት ዓመት በነሀሴ 12,2004 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ወጪውን ጋባዡ እንደሚችል የተገለፀ ሲሆን የ2 ቀን የአልጋና የቁርስ በዶላር 300 አላግባብ ተከፍሏል በወጪ ለተመዘገበውም ሂሳብ ማስረጃ አለመቅረቡ፣

ከጽ/ቤቱ መመሪያ ውጪ አላግባብ ተከፍሎ የተገኘውን ተመላሽ እንዲደርግ ማስረጃዎቹም እንዲቀርቡ አሳስበናል፡፡

4.3. <u>የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተል የተፈጸመ ግዥ</u>

በበጀት ዓመቱ የተፈጸመው ግዢ በመንግሥት የግዢ ህግመሠረት መሆኑ ኦዲት ሲደረግ፣በ7 መ/ቤቶች ብር 5,773,950.65 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተል የተፈጸመ ግዥ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ -15 ተመልክቷል/

ከዚህ ውስጥ ከፍተኛው የሀገር መከላከያ ብር 3,520,593.33 እና የቆዳ ኢንዱስተሪ ልማት ኢኒስቲቲዩት ብር 1,411,317.38 ሲሆን፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የሰሚን ዕዝ ካቋቋመው ምርት ክፍል ብር 2,787,636.00 የቋሚ ዕቃዎች ግዥ መፈጸሙንና ከምርት ክፍሉ ግዥው የተከናወነ መሆኑ ይህም አሰራር፣ ምርት ክፍሉ የፋይናንስ ክፍል የሌለው ለዕዙ ከሸጠው ምርት የሰበሰበውን ገቢ እራሱ ባሳተመው የገንዘብ መሰብሰቢ ደረሰኝ የሰበሰበ መሆኑ፣ ምርት ክፍሉ ለሰራተኛ ደመወዝ፣ የኤሌክትሪክ እና ሌሎች ወጪዎች በዕዙ በጀት የሚሸፈን ሲሆን ከሽያጭ የሚያገኘው ገቢ በዕዙ የፋይናንስ ክፍል ቁጥጥር የማይደረግበትና ገንዘቡ ለመንግስት ፈሰስ የማይደረግ መሆኑንና ምርት ክፍል የስራ ማስኬጃ እና ደመወዝ

ከመንግስት በጀት እየተሸፈነለት ጥሬ ዕቃውንም የሚገዙት ለክፍሉ በጀት እየተሰጠው በመሆኑ ክፍሉ ዕዙ የሚፈልጋቸውን ምርቶች መሰራትና ማስረከብ እንጂ በግዥ መፈፀም እንደሌለበት፤ እንዲሁም የፅህፈት መሳሪያዎች፣ የፅዳት ዕቃዎች፣ ቋሚ የቤት ዕቃዎች እና የግንባታ መሳሪያ ዕቃዎች በብር 732,957.33 ዕዙ ግዥ ሲፈፀም የግልፅ ጨረታ አሰራርን ሳይከተል በቀጥታ ከወታደራዊ መደብሮችና ክበቦች ድርጅት መፈጸሙ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ አሰራሩ እንዲታረም አሳስበናል፡፡

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትም ግዥው የተፈፀመው ከአንድ አቅራቢ ብቻ መሆኑ በባለሙያዎች መረጋገጡን በጣም አስቸኳይ በመሆኑ ግዥው መፈጸሙ ተገልጿል፡፡ አቅራቢው ብቸኛ ለመሆኑ በጽሁፍ ማረጋገጫ በመስጠት በዋና ዳይሬክተሩ ውሳኔ ሲሰጥበት ግዥ ሊፈጸም እንደሚገባ በሪፖርታችን አስገንዝበናል፡፡

4.4. የንብረት ገቢ ደረሰኝ /መ/19/ ያልቀረበ

- የብሔራዊ መረጃንደህንነት አገልግሎት ብር 696,194.64
- የሀገር መከላከያ ሚ/ር 795,550.00
- የፌ/ት/አ/ኢን/ኤጀንሲ 15,346.75

ሶስቱ መ/ቤቶች የዕቃ ግዥ ፈጽመው ሂሣቡ ሲወራረድ ሞ/19 በማሰረጃነት ሳይቀርብ በመወራረዱ ግዥው ለመ/ቤቶቹ አገልግሎት የዋለ መሆኑን ማረጋገጥ አለመቻሉን በመግለጽ ማስረጃዎቹ እንዲቀርቡ አሳስበናል ፡፡

4.5. የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የሠራዊት ደሞዝና አበል ብር 3,242,150,462.37

ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣

- ለደመወዝና ሌሎች ወጪዎች ብር 189,968,177.76
- ከውጭ ለገቡ ዕቃዎች ለጉምሩክ
  ከቀረጥ ነጻ መብት የተከፈለ ብር 287,507,456.69

በድምሩ ብር 477,475,634.45

በፌደራል ፖሊስ ለመረጃ ግዢ ብር 25,000.00

በድምሩ ብር 3,720,594,249.72 ማስረጃው ለኦዲት ባለመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል።

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎትና ለደመወዝ ወጪ ያደረጉት ሂሣብ ፔሮሉ በኮድ በመቅረቡ ኮዱን የሚገልጽ ማስረጃ ለመሰጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው፤ ሌሎቹ የወጪ ሂሣቦች ለምሳሌ የመኪና ጥገና የነዳጅ ለማጣራት የመኪኖች ታርጋ የስልክ ቁጥሮችና የመሳሰሉት ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑት እንዲቀርቡ ተጠይቆ ባለመቅረባቸው ሂሣቡን ኦዲት በማድረግ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ መ/ቤቱ ከሚስጥራዊነት አንጻር ማቅረብ እንደማይቻል ለስራ አመራር ሪፖርት በሰጠው መልስ ገልጿል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የደመወዝ ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ በበጀት ዓመቱ የተቀጠሩ በዝውውር የመጡ በጡረታ የተገለሉ እና በተለያየ ምክንያት የተሰናበቱ የሠራዊት አባላት ስም ዝርዝር ለኦዲት ተጠይቆ መ/ቤቱ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን የሠራዊት ደመወዝ ወጪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዳልተቻለና ሚ/ር መ/ቤቱ በላከው መልስና ቀደም ብሎም በኦዲቱ ወቅት በደብዳቤ ለመ/ቤታችን እንደገለጸው ከወታደራዊ ሚስጥራዊነት አንጻር በሀገር ደህንነት ላይ ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ መረጃዎችንና ዶክመንቶችን ለኦዲት ለማቅረብ እንደሚያስቸግር በአዲሱ የሚ/ር መ/ቤቱ አዋጅ መሠረት ለወደፊቱ ከዚህ አንጻር ለኦዲት የማይቀርቡትን ለይተው እንደሚያሳውቁን ተገልጿል፡፡

4.6. <u>ከመመሪያ ውጪ የተፈጸመ የግንባታ ወጪ</u>

ለተለተለያዩ ግንባታዎች የዋለ ወጪ ኦዲት ሲደረግ በ3 መ/ቤቶች ብር 84,288,481.94 በመስክ ላይ ለነበሩ የግንባታ ዕቃዎች (Material on Site) ከመመሪያ ውጪ የተፈጸመ የግንባታ ወጪ መሆኑ ተረጋግጧል።/ዝርዝሩ በአባሪ-25 ተመልክቷል/

ከዚህ ውስጥ ከፍተኛው የሀገር መከላከያ ሚ/ር ለተቋራጭ መከፈል ያለበት ክፍያ ስራ ተቋራጩ ለሰራው ስራ ብቻ እንጂ በግንባታ ቦታ ለሚገኝ ስራ ላይ ላላዋለ የግንባታ ግብአት (material on site) በማካተት እንዳልሆነ ሀምሌ 2002 የግዢ ኤጀንሲ ባወጣው የፌደራል መንግስት ግዥ አፈጻጸም

መመሪያ አንቀጽ 8.17.2 መከልከሉን ጠቅሰን፤ መ/ቤቱ ለመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ብር 26,562,128.11 እና ለቫርኔሮ ብር 53,297,107.60 በድምሩ ብር 79,859,235.71 በግንባታ ቦታ የግንባታ ግብአቶች (material on site) አሉ በማለት በክፍያ መጠየቂያ ውስጥ በማካተት ከመመሪያ ውጪ ያለአግባብ በየስማቸው የተገለጸው ገንዘብ ክፍያውም በተደጋጋሚ ከ5 እስከ 12 ጊዜ የተፈጸመ መሆኑ በመግለጽ አሰራሩ እንዲስተካከል አሳስበናል፡፡ መ/ቤቱ በሰጠው መልስ ክፍያ መፈጸሙ ስህተት መሆኑንና በኦዲት ግኝቱ የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት ከአሁን በኋላ ከመንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ውጪ ክፍያዎች እንዳይፈጸሙ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑ ተገልጿል፡፡

ከዚሁ ከግንባታ ጋር በተያያዘ በሀገር መከላከያ ሚ/ር በሰባት ግንባታዎች በውሉ መሰረት በጊዜያቸው ያልተጠናቀቁና የጊዜ ገደባቸው ከ242 እስከ 685 ቀናት ያለፈባቸውና የጉዳት ካሳም ሳይጠየቅ ተገኝቷል፡፡

4.7. <u>በባለሥልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ</u>

የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም	ብር	832,699.45
የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	ብር	201,811.15
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ	ብር	60,839.02

ስለትክክለኝነቱ ወጪውን ባረጋገጠው ኃላፊ ያልተፈረመ፤ በጀት ስለመፈቀዱ የበጀት ሰራተኛ፤ ሂሣቡን ባረጋገጠው ሰው ያልተፈረሙና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተለያዩ ግለሰቦች ራሳቸው ክፍያውን አረጋግጠው ብር 108,870.00 አበል ወስደው ተገኝተዋል፡፡

4.8. <u>ከተሰጣቸው ውክልና በላይ ወጪ አፅድቀው ስለመገኘታቸው</u>

የንግድ ሚኒስቴር	ብር	14,206,808.89
የፍትሕ ሚኒስቴር		3,364,334.91
የግል ድ/ ሠ/ ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ		<u>26,220.00</u>
በድምሩ	ብር	17,597,363.80

ከተሰጣቸው ውክልና ገደብ በላይ ወጪ ማፅደቅ እንደማይገባቸው አሳስበናል፡፡

4.9. የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ

የወጪ ሂሳብ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ለመመዝገቡ ኦዲት ሲደረግ በ6 መ/ቤቶች ብር 1,020,775.61 የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ ተመዝግቦ ተገኘቷል። (አባሪ 22) ከዚህ ውስጥ በከፍተኛው ፍ/ቤቱ የተከፈሉ የተከፋይ ሂሳቦች በአግባቡ መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ 24/07/06 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 047609 ከተለያዩ ገቢዎች የተሰበሰበው ገቢ ብር 252,308.02 ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ፈሰስ ሲደረግ፣ በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ላይ በሌሎች የገንዘብ ዝውውር /4009/ ዴቢት የተያዘ ሆኖ እያለ በሂሳብ እንቅሰቃሴ መዝገብ ላይ ግን በ5052 /የፍርድ ቤት የዋስትና መያዣዎች/ዴቢት ተይዞ ተገኝቷል፡፡ ይህም በ5052 /የፍርድ ቤት የዋስትና መያዣዎች/ እንደተከፈለ ስለሚያስቆጥረው የሂሳብ ሚዛኑን ዝቅ ብሎ እንዲታይ አድርጎል፡፡

በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ አወቃቀር መሠረት ሂሳቦች በመደባቸው እንዲመዘገቡ ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ እና ለተጠቀሰውም ሂሳብ ማስተካከያ እንዲሰራለት አሳስበናል፡፡

4.10. በፎቶ ኮፒ ማስረጃ የተወራረደ ሂሳብ

በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ብር 24,458.00 ተገኝቷል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት በሶማሌ ክልል ለተወራረደው የውሎ አበል ክፍያዎች ብር 116,900.00 የቀረበው ማስረጃ ፎቶ-ኮፒ ሆኖ መገኘቱ፣ በፎቶ ኮፒ ማስረጃነት የተወራረደው ሂሳብ ከአንድ ጊዜ በላይ የመወራረድ እድል ስለሚኖረው የወጪው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲት እንዲጣራ አሳስበናል፡፡

4.11. በብልጫ የተከፈለ

የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ	ብር 27,549.57
የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	41,935.13

(ከተሰራው ስራ በላይ ለግንባታ በብላጫ የተከፈለ)

የግል ድርጅቶች ሠራተኞች አሸናፊው ድርጅት በዋጋ ማወዳደሪያው ከሰጠው በላይ እና ከውል ውጪ የተከፈለ ሲሆን፣ የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ከቀረበው የግንባታ የክፍያ ጥያቄ በላይ የከፈለው ተገቢው ክትትል እንዲደረግ አሳስበናል፡፡ ማረሚያቤቶች በቀጣይ ክፍያ መቀነሱን ቢገልጽም ያላግባብ ክፍያ በመፈጸም የመንግስት ገንዘብ ላላስፈላጊ ክፍያ እንዳይደረግ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5. ተከፋይ ሂሣቦች

5.1. ፈሰስ ሳይደረግ ለረጅም ጊዜ በባንክ የተቀመጠ ያልተከፈለ የሠራዊት ደመወዝ

በሀገር መከላከያ ሚ/ር በሰኔ 30/2005 የሂሳብ ሪፖርት በሂሳብ መደብ 5004 የደመወዝ ተከፋይ ብር 198,888,924.20 ደመወዛቸውን ባለመውሰዳቸው ለረጅም አመታት በተከፋይ የተያዘ መገኘቱንና የሂሳቡን ትክክለኛነ ለማረጋገጥ መ/ቤቱ ማስረጃዎቹን ለማቅረብ ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘቱ፡፡ ይህ ሂሣብ በመንግሥት የሂሣብ አሠራር መሠረት ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ፈሰስ ተደርጐ ጥያቄው ሲቀርብ የገ/ኢ/ል/ሚኒስቴርን በመጠየቅ መከፈል ሲገባው ሂሣቡ በወጪ ተመዝግቦ ለዓመታት ሳይከፈል መቀመጡ ገንዘቡም ለምን ያህል ጊዜ ሳይከፈል እንደተቀመጠ ለማወቅ የማያስችል በመሆኑና ለብክነት እንዲጋለጥ የሚያደርግ መሆኑን በመጥቀስ ሂሣቡ ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ፈሰስ እንዲደረግ፣ ጥያቄው ሲቀርብ ክፍያ እንዲፈጸም አሳስበናል፡፡

የመከላከያ ሚ/ር ከተሰጠው ተልዕኮና ግዳጅ መነሻነት የሰራዊት አባላቱ ከተሰጣቸው ግዳጅ ሲመለሱ ያለእንግልት ደመወዛቸውን እንዲወስዱ በማሰብ የመከላከያ ሚ/ር ከፍተኛ ኃላፊዎች ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር ጋር በመነጋገር ደመወዛቸውን በግዳጅና በተለያየ ምክንያት ያልወሰዱ የሰራዊት አባላት ደመወዝ ማስቀመጫ መደቡ <<D>> የሆነ የባንክ ሂሳብ ቁጥር እንዲከፈት በጠየቁት መሰረት በቀን 09/10/1995 ዓ.ም. በቁጥር ክሂመ1/7/47 ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተጻፈ ደብዳቤ የተፈቀደላቸው መሆኑን፣ በውስጡም የሚታየው ገንዘብ ፍቃዱ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን በተለያየ ምክንያት ደመወዛቸውን ያልወሰዱ የሰራዊት አባለት የደመወዝና አበል

ተመላሽ ሂሳብ መሆኑን፡ የዚህን ዝርዝር ማስረጃ ለማቅረብም የአባሉን ሙሉ መረጃና ገንዘቡ ተመላሽ የሚሆንበትን ምክንያት የሚይዙ በመሆኑ ሰነዱን ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት በአገር ደህንነት ላይ አደጋ ሊያስከትል ስለሚችል ማቅረብ እንደማይቻል፡ ወደፊት በመከላከያ ሚ/ር ማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት ሚስጥር የሆኑት ተለይተው ሲቀርቡ በዚያ መሰረት የሚፈጸም መሆኑን፡ እንዲሁም በዚህ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ያለው ገንዘብ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ ወደ ገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ ለማድረግ በደብዳቤ ጠይቀው ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር በቀን 1/5/2006 ዓ.ም. በቁጥር ክሂመ1/7/7 በተጻፈ ደብዳቤ በተሰጠው መልስ መሰረት ገንዘቡን ፈሰስ ለማድረግ ሰነዱን የማደራጀት ስራ እየሰሩ መሆኑን ገለጸዋል፡፡

5.2. ያልተከፈለ ውዝፍ ሂሳብ

በተከፋይ ሂሳብ የተመለከተው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በ13 መ/ቤቶች ብር 377,337,455.67 ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ መኖሩ ተረጋግጧል/ዝርዝሩ በአባሪ- 28 ተመልክቷል/

ከተገለጹት ተከፋይ ሂሳቦች ብር 8,075,301.81 በሀገር መከላከያ ሚ/ር ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት በወቅቱ ገቢ ያልሆነ ሲሆን ቀሪዎቹ ብዙ ዓመታትን ያስቆጠሩና አንዳንዶቹ ተከፋይ ሂሣቦች በሪፖርት ላይ ከመገለጽ ውጪ ማስረጃ የሌላቸውና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢውን ክትትልና ማጣራት በማድረግ ተከፋይ ሂሳቦቹ ላይ እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ ሌሎቹም መ/ቤቶች የተከፋይ ሂሳባቸው ላይ እርማጃ እንዲወስዱ፡በውጭ ጉዳይ ሚ/ር የተከፋይ ሂሣቦች ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ተመሳሳይ የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸውና ችግሮቹ ሊቀረፉ አለመቻላቸውን በመግለጽ መ/ቤቱ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት እርምጃዎች አጠናቅሮ ሊወሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 2,559,150.11 በአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ለረጅም ጊዜ በምዝገባ የታየ ሂሳብና ተከፋዩ ድርጅት ወይም ግለሰብ ማን እንደሆነ በግልጽ የማያሳይና ገንዘቡም በጠቅላይ መምሪያው የባንክ ሂሳብ ውስጥ የማይገኝ መሆኑን፣ ትክክለኛ የፌዴራል መንግስት የሂሳብ አወቃቀርን (Charts of Accounts) ባለመረዳት የተፈጠረ የምዝገባ

ስህተት መሆኑንና አስፈላጊውን ማጣራት እያደረገ መሆኑን፡ብር 1,689,020.90 በተለያየ ምክንያት የተሰዉ አባላት የሶስት ወይም የስድስት ወር ደመወዝ መሆኑንና የወራሽ ቤተሰብ (ተተኪ) ቀርቦ እስኪወስድ ድረስ በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ የሚታይ መሆኑን፡ ብር 10,451,616.94 ከልዩ ልዩ የመከላከያ ክፍሎች በተለያዩ ዓመታት በአደራ ወይም በተከፋይ ሂሳብ ወደ መከላከያ ፋይናንስ በጀታዊ ሂሳብ ገቢ ሆኖ የነበረና ወደ ገ/ኢ/ል/ሚ/ር ገንዘቡ ፈሰስ የሆነ ቢሆንም ለፈሰስ ሂሳቡ በወቅቱ አስፈላጊው የሂሳብ ምዝገባ ማስተካከያ ባለመደረጉና የፈሰስ ሂሳብ ምዝገባም የተከፋይ ሂሳብን የማያጠፉ በመሆኑ የተከፋይ ሂሳቡ ለረጅም ዓመታት በምዝገባ እንደሚታይና የተከፋይ ሂሳቡ የሚጠፋበትን አሰራር ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር በደብዳቤ ጠይቆ በተሰጠው ምላሽ መሰረት ከመዝገብ መሰረዝ እንዲቻል አስፈላጊውን ማስረጃዎች በማጠናቀር ስራ ላይ መሆኑን ገልጿል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ከ2 ዓመት በላይ የቆየ እና ምንም ማስረጃ የሌለው ብር 35,330,297.03 እና በነገቲቭ (ዴቢት) የተመዘገበ ሂሳብ ብር (3,098,228.89) የሚገኝበት ሲሆን በዋናው መ/ቤት እና በሚሲዮኖች መካካል ባለው የቦታ ርቀት ሂሳቡን ለማወራረድ ጫና መፈጠሩን እና በ2005 በጀት ዓመት የተከሰቱ ተከፋይ ሂሳቦችን በከፍተኛ ጥረት በ2006 በጀት ዓመት እተወራረደ እንደሚገኝ፣ በ2006 በጀት ዓመት ብር 44,030,007.57 መወራረዱን ቀሪው ማስረጃ የሌለውን ብር 35,305,065.36 በተመለከተ ረጅም ዓመታት የቆዩ ሰነዶች መሆናቸው፡ን በቀጣይ ሂሳቡን ለማወራረድ በቂ ማስረጃ መኖሩን ለማረጋገጥ መ/ቤቱ ባቋቋመው የተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ አጣሪ ግብረ ሃይል እየተሰራ መሆኑንና ሰነዶቹ ከተረጋገጡ በኋላ በግብረሃይሉ በቀረበው አስተያየት መሰረት እርምጃ እንደሚወሰድ ገልጿል፡፡

6. የበጀት አጠቃቀም

6.1. ከበጀት በላይ የወጣና ያልተሰራበት ከ10% በላይ የሆነ

በ2005 በጀት ዓመት የተመደበው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲገናዘብ ከ10% በላይ ያለውን ብቻ በመውሰድ በ17 መ/ቤቶች ብር 369,682,962.83 ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን በ4 መ/ቤቶች ደግሞ

ብር 16,623,555.55 ከተደለደለው ከበጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡/ ዝርዝሩ በአባሪ-29 ተመልክቷል/

ከዚህ ውስጥ ከፍተኛው የጨ/ጨ/ኢ/ል/ኢንስቲትዩት፤ ንግድ ሚኒስቴርና የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ሲሆን፣ መ/ቤቶቹም በጀት ሲጠይቁ የተመደበውን በጀት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ ሥራ ላይ የማይውል በጀት በመጠየቅ የሌላውን መ/ቤት መሠረታዊ መርሀ ግብር እንዳያደናቅፉ በዕቅድና በጥናት ላይ የተመሠረተ በጀት ሊዘጋጅ እንደሚገባ አሳስበናል::

ከካፒታል በጀትን በተመለከተ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከኮንትራክተሮችና ከአማካሪ ድርጅቶች ጋር የግንባታ ስራው በታቀደለት ጊዜ እንዲሰራ በፕሬዝደንቱ ጽ/ቤት በኩል በተደጋጋሚ ስብሰባ በመጥራት ከፍተኛ ጥረት ቢደረግም ለፍርድ ቤቱ በቀረቡ የተለያዩ ምክንያቶች ስራው ባለመሰራቱና ወይም የክፍያ ሰርተፍኬት በጊዜው ተዘጋጅቶ ባለመቅረቡ በጀቱ ሊመለስ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

7. ዕቃና የንብረት አስተዳደር

የንብረት አስተዳደር መንግሥት ባወጣው ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝቷል፡፡

ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	4 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱ ያላረጋገጡ	6 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	1 መ/ቤት
የቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም ምዝገባ ያላከናወኑ	3 መ/ቤቶች
ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	2 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	6 መ/ቤቶች
ተያያዥነት ያለቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	1 መ/ቤቶች

7.1. ሌሎች የንብረት አያያዝና ድክመቶች የታየባቸው

ሆቴልና ቱሪዝም

- የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ከ8 ጥራዞች ውስጥ 15 ገጾች 3ቱም ኮፒ ተቀዶ መጥፋቱ፤

የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት

- ዋጋቸው ብር 744,762.50 የሆኑ በቁጥር 50 ኮምፒውተሮች ገቢ ሲሆኑ እንዲሁም ዋጋቸው ብር 51,626.95 የሆኑ የ58 ኮምፒውተሮች እና ፎቶ-ኮፒ ማሽን እንዲሁም ላፕ ቶፕ (Laptop) ለሠራተኞች ለሥራ ከንብረት ክፍል በሞዴል 22 ወጪ ሲሆኑ የተመረተበት የፋብሪካ ቁጥር (ሴሪ ቁጥር) ሳይመዘገቡ ቋሚ ንብረቶች ገቢና ወጪ ሆነው መገኘቱ፣

የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

- የኢንስቲትዩቱ ቋሚ ንብረቶች በአግባቡ የተጠበቁና አግልግሎት እየሰጡ ለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ ዋጋቸው በዩኤስ ዶላር 1,306,105.00 የሚያወጡ የላቦራቶሪ እቃዎችና እና መለዋወጫዎች ያለአገልግሎት ከአራት አመት በላይ በመጋዘን ተቀምጠው መገኘታቸው፣
- የኢንስቲትዩቱ የንብረት አስተዳደር ስርአት መንግስት ባወጣው የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት መሆኑን ኦዲት ሲደረግ፤ በጋርሜንት ክፍል የሚገኙ ፕሎተር ፤ ዲጂታይዘሮችና ኮምፒውተሮች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣

የግ/ድ/ሠ/ማ/ዋ/ኤጀንሲ

- አንዳንድ ቋሚ ዕቃዎች በሞዴል 19 ገቢ ሲሆን እንዲሁም ከንብረት ክፍል በሞዴል 22 ቁጥር ወጪ ሲሆን የተመረተበት የፋብሪካ ቁጥር (ሴሪ ቁጥር) በሞዴል 19 እና በሞዴል 22 ላይ ሳይመዘገቡ መገኘቱ፣

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት

- HP ፕሪንተር 4531-03-01 በቋሚ ንብረት መዝገብ ዝርዝር ተመዝግቦ የተገኘ ቢሆንም ለፕሪንተሩ ቁጥር ወይም ኮድ የቦርድ ጽ/ቤት ዋና ኃላፊ ቢሮ ፀሐፊ ያለ ፍሪጅ በ.ን.መ.ቁ 4531-12-02 የተሰጠው ቢሆንም በቋሚ ንብረት መዝገብ ዝርዝር ውስጥ ተመዝግቦ አለመገኘቱ፣

- ንብረት ክፍል ውስጥ በቀን 10/06/2003 በሞዴል 19 ቁጥር 25624 ገቢ የሆነ የሬድዮ መገናኛ ከ Avicom Trading በብር 1,462,800.00 የተገዛ ንብረት ያለስራ ተቀምጦ መገኘቱ፣

- የተለያዩ የስብሰባ ጠረጴዛዎች፣ ወንበሮች፣ ኮምፒውተሮች፣ ዩፒየሶች፣ የካፍቴርያ የሻይ ማሽኖች እንዲሁም የተለያዩ ማሽኖች፣ በር፣ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ የመኪና የግጭት መከላከያ፣ ተለያዩ የመኪና ጎማዎች፣ ሶፋ ወንበሮች፣የዲፕ ዕቃዎች አገልግሎት የሚሰጡ 50 የእንግዳ ወንበር ፣ 2 የፀሀፊ ወንበር፣6 የፀሀፊ ጠረጴዛዎች፣1 የሬድዮ መገናኛ 1 የአቅጣጫ መስጫ ቦርድ፣ ከሠራተኛ ተመላሽ ንብረቶች፣የፀሀፊ ወንበር፣ፓንቸር የወረቀት ትሬዎች እስቴፕለር መምቻዎች ብዛት ያላቸው ፋይል ካቢኔቶች በአንድ ላይ በክፍል ውስጥ ተከማችተው መገኘታቸው፣

የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

- በተቋሙ ዕቃ ግምጃ ቤት የቋሚ ንብረት አቀማመጥ ለቁጥጥር አመቺ ባልሆነ መልኩ የተለያዩ ዕቃዎች በውስጡ እንደሚገኙ፣

የፌ/ጥ/አ/ኢ/ን/ል/ኤጀንሲ

- የኤጀንሲውን ንብረት አመዘጋገብ ሁኔታ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ከቁጥር 0074051-0074069 እና ሞዴል 22 ከቁጥር 108234-108241 በሞዴሎቹ ሠንጠረዦች ላይ መሠረዝ፣ መደለዝ ፣ አስቀድሞ ከተመዘገበው ቁጥር ሌላ ከፊቱ ቁጥር ጨምሮ መመዝገቡ ፣

ታውቋል፡፡

<u>የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ</u>

- በተጠቃሚዎች እጅ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (UC) በሁለት ቅጅ ተዘጋጅቶ አንዱ ለተጠቃሚው ሌላው በንብረት ክፍል ንብረት ክፍል በተሟላ ሁኔታ ያልተሠራበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- የተለያዩ ብረታ ብረትና የቧንቧ ዕቃዎች በንብረትነት በሞዴል /19 ገቢ ሳይደረጉ ተገኝቷል፡፡

<u>የፍትህና የህግ ሥርዓት ኢንስቲትዩት</u>

- ለተለያዩ የሥራ ክፍሎች አለቂ ጽሕፈት መሳሪያዎች ብዛት ያላቸው ዕቃዎች ባአንድ ጊዜ ወጪ ተደርገው ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም ለቋሚ ንብረት መለያ ቁጥር በመስጠት በዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ ማከናወንና ከስቶክ ካርድ ጋር እንዲገናዘቡ ማድረግ፣ የማያገለግሉ እቃዎች ተለይተው አገልግሎት እንዲሰጡ እና አገልግሎት የማይሰጡት ደግሞ በጨረታ ወይም በሌላ ዘዴ እንዲወገዱ ማድረግ እንደሚገባ በአጠቃላይ ንብረቶች በመንግሥት ንብረት አያያዝ መሠረት ሊያዙ እንደሚገባ አስገንዝበናል፡፡

7.2. <u>ነዳጅና የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የታዩ ችግሮች</u>

<u>የፋይናንስ ደኅንነት መረጃ ማዕከል</u>

- የማዕከሉ ተሽከርካሪ መኪናዎች ላልሆኑ በተለያዩ ቀናት ለሥራ አገልግሎት የዋለ የናፍጣና ቤንዝን ግዥ ተከናውኖ ተገኝቷል፡፡ ተሽከርካሪ መኪናዎቹም እንዴት እንደመጡና አገልግሎት ሊሰጡ እንደቻሉ ማስረጃ ሊቀርብ አለመቻሉ ታውቋል፡

የነዳጅ አጠቃቀምን ትክለኛነት ማረጋገጥ እንዲቻል የመንግሥት ተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያ ቅጅ መጠቀምና የነዳጅ ፍጆታ መቆጣጠር የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

7.3. የገቢ ደረሰኝና ሌሎች የህትመት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው መ/ቤቶች

የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ መገኘት የሚገባው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ (መ/ሂ1) እና የገቢ ደረሰኝ ማጠቃለያ (መ/ሂ 64) ቆጠራ በማድረግ ቀደም ብሎ ከተመዘገበው ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ተመዛዝኖ በወቅቱ ለሚመለከተው ኃላፊ ሪፖርት አለመደረጉ፣

- በገንዘብ ሰብሳቢዎች የተሰበሰበ ጥሬ ገንዘብ የገቢ መለያ ቁጥር የተለየ የገቢ ደረሰኝ ማጠቃለያ በመ/ሂ 65 ተጠቃሎ ለዋና ገንዘብ ያዥ በመ/ሂ 64 መተላለፍ እንዳለበት ቢያዝም ሣይሰራበት መገኘቱ፣

የግ/ድ/ሠ/ማ/ዋ/ኤጀንሲ

- ኤጀንሲው በተለያየ ጊዜ ለሥራ መገልገያ የገዛቸውን የገቢ መሰብሰቢ ደረሰኝ፣ የቋሚና አለቂ ንብረቶች ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) እንዲሁም ንብረቶች ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) ኤጀንሲው ሥራውን ሲጀምር የተገዛውም ሆነ የተጠቀመበትን ለኦዲት ሥራ እንዲቀርብ ተጠይቆ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ለኦዲት ሊቀርብልን አለመቻሉ፣

7.4. የተሽከርካሪ አያያዝና አጠባበቅ

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-31 ተመልክቷል/

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ2 መ/ቤቶች	8 ተሽከርካሪዎች
በብልሽት ምክንያት የቆመ	በ6 መ/ቤቶች	37 ተሽከርካሪዎች
በተለያዩ ድርጅቶች ስም ሊብሬ ያላቸው	በ2መ/ቤቶች	15 ተሽከርካሪዎች

የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት

- ጽ/ቤቱ ካሉት መኪናዎች ውስጥ ኢ.ት ፎርድ የሰሌዳ ቁጥር 4-05444 መኪና የግል ማህደር በመክፈት በማህደሩ ውስጥ ቢያንስ የተሽከርካሪውን ዓይነትና ሞዴል፣ የጭነቱ ልክ፣ የቻንሲ የሞተር ቁጥሮች ፣ የተገዛበት ወይም በመ/ቤቱ ባለቤትነት ሥር የዋለበት ቀንና ዓ.ም. የተሽከርካሪው ዋጋ፣ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ቁጥር እና ሌሎችም ተመዝግበው መያዝ ሲገባ ስለ ሁኔታው የሚገልፅ ፋይል አለመገኘቱ፣

የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

- ኤጀንሲው ካሉት መኪናዎች Toyota land cruiser የሰሌዳ ቁጥር 4-02133 እና Toyota per ado የሰሌዳ ቁጥር 4-13247 ሁለት ተሽከርካሪዎች የህይወት ታሪክ የግል ማህደር የሚገልፅ ፋይል ሳይዘጋጅ መገኘቱ፣

የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ማዕከል

- አንድ ተሽከርካሪ የሰሌዳ ቁጥር (ኢ.ት 4-00521) ከአገልግሎት ውጭ ሆኖ አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፤

- አንድ ተሽከርካሪ (አዲስ) ከገ/ኢ/ል/ሚ ከውጭ አገር ሲመጣ ግጭት ስለደረሰበት አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፤

በመሆኑም መታወቂያ ደብተር የሌላቸው ተሽከርካሪዎች እንዲወጣላቸው፣ በጊዜያዊነት ሊብሬ ያላቸውም ቋሚ ደብተር ሊወጣላቸው እንደሚገባ፣ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑት ተጠግነው ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉት እንዲጠገኑ፣ ሊጠገኑ የማይችሉትን ደግሞ በመንግስት መመሪያ መሠረት መመቻቸች ያለበት መሆኑን በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

8. የውስጥ ኦዲትን በተመለከተ፤

8.1 የውስጥ ኦዲት አገልግሎት ክፍል በተፈቀደው መዋቅር መሰረት የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ብዛት መሠራቱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- ለንግድ አሠራርና የሸማቾች በመዋቅሩ 11 አሁን ያለው 2 መሆኑ፣

- የፌ/ጥ/አ/ኢ.ን/ል/ኤጀንሲ በሰው ማነስ ሪፖርት በወቅቱ አለመቅረቡ ፣
- የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በሰው ማነስ ሪፖርት በወቅቱ አለመቅረቡ፣
- የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ስድስት የሰው ሀይል ቢሆንም አሁን በስራ ላይ ያሉት ሁለት መሆኑ፣
- የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በመዋቅሩ መሰረት ሁለት ቢሆንም በአንድ ሰው መሆኑና በተለያየ ክፍል ውስጥ 38 ክፍት የሥራ መደብ መኖሩ፣

9. የውስጥ ቁጥጥር ስርአትን በተመለከተ

9.1 የውስጥ ቁጥጥር ስርአት ድክመቶች

የፌ/ጥ/አ/ኢ.ን/ል/ኤጀንሲ

- የኤጀንሲው የንብረት አመዘጋገብ ሲጣራ በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) በሞዴሎቹ ሠንጠረዦች ላይ መሠረዝ፣ መደለዝ ፣ አስቀድሞ ከተመዘገበው ቁጥር ሌላ ከፊቱ ቁጥር ጨምሮ በመመዝገብ በአብዛኛው ሞዴል 19 በየማህላቸውና እና 22 ሞዴሎቹ በትክክለኛው ያለመመዝገባቸው፣

- ክፍያ ለመፈፀም የባንክ ቼክ በሚዘጋጅበት ጊዜ የባንክ ቼክ ቁጥሮች በ8 ጥራዞች በእያንዳንዱ ጥራዝ ከ10 እስከ 22 ቅጠሎች ተሰረዘው/Void/ የተደረገ በራሪ ቼኮቹ ከጥራዙ ጉርድ ጋር ተያይዘው ተገኝተዋል፡፡ ይህ አሰራር ቼኮችን ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የማያስችል ከመሆኑም በላይ ለምዝበራ መንገድ የሚከፍት ሆኖ መገኘቱ፣

ከላይ የተጠቀሱት የአፈጻጸም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ ጉዳዩ ለሚመለከተው መ/ቤት እና ተቆጣጣሪ መ/በት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የበጎ አድጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ

የኤጀንሲዉ ኦዲት ክፍል ሃላፊ ሆነዉ አጠቃላይ ወጭዎችን መቆጣጠር ሲገባቸው የጸረ HIV-ኤድስ ግብረ ሃይል ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆነዉ ገንዘብ አንቀሳቃሽ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

በፌዴራል የመንግሰት የውሰጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ መሠረት የዉስጥ ኦዲት ክፍል የመስሪያ ቤቱ ሥራ አመራርና ሠራተኞች ኃላፊነታቸዉን በብቃት መወጣት እንዲችሉ በተዘረጋዉ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በሥራ ላይ ባሉት ህጎችና የአሰራር ሥርዓቶች መሰረት ስራዎች መከናወናቸዉን ኦዲት እያደረገ በመመሪያዉ ላይ በተቀመጡት ግዜ ዉስጥ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊና ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ማድረግ እንዳለበት በተገልጸው መሠረት እንዲፈጸም አሳስበናል፡፡

10. የክትትል ኦዲት

10.1 የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር

የሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖረት ላይ በተሰጡት አስተያየቶች መሰረት እርምጃ መውሰዱ ሲጣራ ከታች በተገለጹት ግኝቶች ላይ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

- የምዕራብ ዕዝ የቢሮ ሕንፃ ግንባታ በመሃንዲስ ግምት (bill of quantity) መሰረት በብር 32,158,416.64 በመገንባት ላይ እና እስከ ሰኔ 30 ቀን 2004 ብር 15,545,738.30 ወጪ የሆነ ሲሆን፣ ግንባታው በጀት ያልተፈቀደለት እና ግንባታው እንዲከናወን በሚ/ር መ/ቤቱ ያልተፈቀደ ተገኝቷል፡፡

- በ4201 የሂሣብ መደብ በጥቅል ከተመለከተው ብር 18,500,490.05 ውስጥ ብር 6,907,391.59 ከ1984 ጀምሮ ከ19 ዓመታት በላይ የቆየ እና ብር 11,593,098.46 በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ከ2000 በጀት ዓመት ጀምሮ ለ4 ዓመታት በተሰብሳቢ የተያዘ ተገኝቷል፡፡

- በሂሳብ መደብ 4253 ቅድሚያ ክፍያ ብር 2,235,989.71 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 4201 ብር18,704,522.41፣ በድምሩ ብር

20,940,512.12 በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት፣ በምስራቅ ዕዝ፣ በምዕራብ ዕዝ፣ እና በተለያዩ መምሪያዎች እና እዞች በጠፋ እና በወደመ ሂሳብ ከ1998 ጀምሮ ተይዞ የተገኘ እና በማስረጃ ያልተደገፈ ተገኝቷል፡፡

- በሂሣብ መደብ 4210 በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት በተሰብሳቢ የተያዘው ብር 48,000,000.00 ሲጣራ ከሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ ተብሎ ከተያዘው ገንዘብ በሚ/ር መ/ቤቱ ሥር ለሚገኙ ለዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ፋብሪካ ብር 45,000,000.00 እና ለብራና ማተሚያ ቤት ብር 3,000,000.00 በብድር ተሰጥቶ በተሰብሳቢ የተያዘ ሲሆን፣ ይህ ብድር ከሕግና መመሪያ ውጭ የተሰጠ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

- በአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት በሂሣብ መደብ 4211 ብር 4,813,048.67 ለረጅም ዓመታት በተሰብሳቢ የተያዘ ለውጭ ጉዞና ለልዩ ልዩ ወጪዎች ተከፍሎ ያልተወራረደ ተገኝቷል፡፡

- በሂሣብ መደበ 4251 ለኖሪንኮ ላሊበላ ብር 3,113,746.82 እና በኢትዮጵያ አየር ኃይል ለደጀን አቪዬሽን ብር 2,970,000.00 በድምሩ ብር 6,083,746.82 ለአመታት ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

- በሰኔ 30/2004 የተከፋይ ሂሣብ ሪፖርት በሂሣብ መደብ 5004 ከሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ ብር 163,504,599.94 ለረጅም ዓመታት ደመወዛቸውን ባለመውሰዳቸው በተከፋይ የተያዘ ሲሆን ይህ ሂሣብ በመንግሥት የሂሣብ አሠራር መሠረት የየወሩ ደመወዝ ተከፍሎ እንዳበቃ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ መደረግ ሲገባው ከመመሪያ ውጭ በተከፋይ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

በሂሳብ መደብ 5054 በተከፋይ ከተያዘው. ውስጥ ብር 10,319,949.16 በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት በተለያዩ የሚ/ር መ/ቤቱ ክፍሎች ስም ለረጅም አመታት በተከፋይ የተያዘ ተገኝቷል፡፡ መ/ቤቱ ገልጸዋል፡፡

የኦዲቱ ዋና ዓላማ በመ/ቤቱ ውስጥ ያሉትን የቁጥጥርና የሂሳብ አሰራር ችግሮችን በመለየት የሥራ አመራሩ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድና በቀጣይ እነዚህ ችግሮች የሚወገዱበትን ሁኔታ ለመፍጠር ነው፡፡ ስለዚህ መ/ቤቱ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ችግሮቹ በቀጣይነት በየዓመቱ ሊታዩ ይችላሉ፡፡

10.2 የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት

ከጽ/ቤቱ ኦዲት መምሪያ በሰኔ 2 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በድልድልና ክምችት ክፍል በተደረገ ኦዲት በክምችት ክፍል ብር 881,842.17 በድልድል ክፍል ብር 692,288.71 የሚገመቱ ቁሣቁሶች በድምሩ የብር 1,574,134.88 ንብረት በጉድለት የተገኘ መሆኑን በ2002 ኦዲቱ ወቅት ለማወቅ መቻሉን በመግለጽ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በመ/ቤታችን አስተያየት ተሰጥቶአል፡፡ ይሁን እንጂ እስከ አሁን የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ታውቋል፡፡ በሁለት የኦዲት በጀት አመት የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እስከ አሁን ውሳኔ አለመገኘቱ ታውቋል። ስለዚህ ጽ/ቤቱ ጉዳዩ ውሳኔ እንዲያገኝ ተገቢውን ክትትል እንዲያደርግ በድጋሚ ባሳሰብነው መሰረት ጽህፈት ቤቱ ለፌዴራል ሥነምግባር እና ፀረ-ሙሰና ኮሚሽን አፋጣኝ ውሳኔ እንዲሰጥበት ክትትል እየተደረገ ቢሆንም በኮሚሽኑ በኩል የሚታይ አጥጋቢ እንቅስቃሴ እንደሌለና በክምችትና ድልድል ክፍል የነበሩ ኃላፊ አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶ ከምድብ ቦታቸው እንዲነሱ መደረጉን በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅት እና በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

10.3 የፌዴ.ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር

- በልዩ ልዩ የአደራ ተከፋይ ሂሳቦች ብር 3,379,252.40 በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2003 ተዘጋጅቶ በቀረበው የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት ሣይካተት መገኘቱ በ2003 የአስተዳደሩ ኦዲት ሪፖርት የተገለፀ ቢሆንም ከዚሁ ሂሳብ ውስጥ በ2004 በጀት ዓመት ብር 643,514.42 ብቻ በሂሳብ መደብ 5054 የተመዘገበ ሲሆን ቀሪው ብር 2,735,737.98 በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30/2005 ተዘጋጅቶ በቀረበው የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል።
- ከአቅም ግንባታ ሚኒስቴር የሚተካ በሚል በ2002 በጀት ዓመት ከአደራ ሂሳብ በብድር ብር 700,360.43 ወጪ መደረጉንና ሂሳቡ እስኪተካ በሰኔ 30/2003 ሪፖርት ላይ በተሰብሳቢ ሂሳብ ያልተያዘ መሆኑን በ2003 ኦዲት ሪፖርት ወቅት ለማወቅ መቻሉን በመግለፅ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በመ/ቤታችን አስተያየት ተሰጥቷል። ይሁን እንጂ እስከ አሁን የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፡፡

10.4 የውጭ ጉዳይ ሚኒሰቴር

በ2003 በጀት አመት ሂሳብ ኦዲት በብራስልስ የኢትዮጲያ ኤምባሲ ምንም ደጋፊ ማስረጃ ሳይቀረብ ብር 105,334.88 በወጪ በመመዝገቡ ማስረጃ እንዲቀረብ ወይም ከሚመለከታቸው ሠራተኛ ተመላሽ እንዲደረግ፡ ብር 2,599.27 ከቀረበው ማስረጃ በላይ ክፍያ በመፈጸሙ ተመላሽ እንዲደረግ ባለፉት ኦዲት ሪፖርቶች አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል፡፡

10.5 የበጎ አድጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ

በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ ልዩ ልዩ ዕቃዎች እንዲወገዱ አስተያየት ቢሰጥም በ2005 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል፡፡

10.6 ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር

- 2004 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት መሠረት ብር 314,585.01ለረጅም ዓመታት መቆየቱ አግባብ አለመሆኑ ተጠቅሶ እንዲሰበሰብ ወይም በመመሪያው መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዝ አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል::

- በ2004 በጀት ዓመት የመ/ቤቱ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በሂሳብ መደብ 5054 በተከፋይ የተያዘው ብር 8,226,089.00 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለመ/ቤቱ በድጋሚ ገቢ ባደረገው ስህተት ምክንያት ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር ጋር በመነጋገር በተከፋይ ሂሳብ እና በፈሰስ ሲመዘገብ ሂሣቡ የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት እና በገቢ አለመመዝገቡን በመግለጽ ሂሳብ የገቢ ደረሰኝ እንዲቆረጥለት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም መ/ቤቱ በ2005 ለባንኩ ክፍያ ለመፈጸሙ ማስረጃ ሳይቀርብ እና ከሂሳብ አሠራር ውጪ በጆቪ ቁጥር 0025461 በ30/10/05 5054 ተከፋይን ዴቢት በማድረግ 5061 ኢኩቲ (ካፒታል) ክሬዲት ተደርጐ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የተከፋይ ሂሳቡ ሲቀነስ ካፒታል በተመሳሳይ የገንዘብ መጠን ከፍ እንዲል አድርጐታል፡፡ ይህም በማስረጃ ያልተደገፈና በባዶ ከፍ የተደረገ ኢኩቲ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሥራ አመራር ምለሽ ይህም የተደረገበት ምክንያት ገንዘቡ በቀጥታ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ብሎክ ተደረጎ መንግስት ግምጃ ቤት ስላስገባውና መ/ቤታችንን ስለማይመለከት በሌላ ገንዘብ ላይ እዳ ተብሎ መያዝ የሌለበት መሆኑን ከመንግስት ሂሳብ አስተዳደር ጋር ስለተማመንን የሂሰብ ማስተካከያው የተሠራ መሆኑ ተገልጿል፡፡

አሠራሩ የሂሳብ አያያዝ መሠረት የሌለውና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ዕዳውን ከመዝገብ ለመሰረዝ የተደረገ ምዝገባ ሲሆን ባንኩ ያልተከፈለውን ገንዘብ ከመ/ቤቱ እንደሚፈለግ ሂሳቡንም በተሰብሳቢ እንደሚያዝ ሊታወቅ ይገባል፡፡ስለዚህ ለሂሳቡ ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል።

10.7 <u>ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን</u>

- በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በኮሚሽኑ ባለቤትነት ሥር ካሉት ተሽከርካሪዎች ውስጥ፤ ታርጋ ለማውጣት በሂደት ላይ ያሉ 2፣ የባሌበትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው 255፤ ጊዜያዊ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ያላቸው 41 መገኘታቸው፣ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ 113 እና ከዚህ ቀደም ከ1998 ዓ.ም በፊት በጨረታ እንዲሸጡ ተወስኖ ሳይሸጡ የቀሩ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ መኪናዎች እርምጃ ሳይወሰዱ ተገኝቷል፡፡

- የፌደራል ፖሊስ ወንጀል መከላከል ዘርፍ ከብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን የጋፋት አርማመንት ኢንዱስትሪ ጋር በገባው ውል መሠረት ያልተሰበሰበ ብር 604,056.11 ቨቀት ሂሳብ እንዲሰበሰብ በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል።

በ2004 ኦዲት ሪፖርት አስተያየት የተሰጠበትን ጉዳይ እሰከ አሁን እልባት አለማግኘቱ የክትትል ማነስ መኖሩን ገልጸን በተሰጠው አስተያየት መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ አሳስበናል።

የ2005/2006 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች ዝርዝር

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ በጀት/ሥራ ላይ የዋለ		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	04/03/06	163,900,219.75	00.00	
2	የንግድ ሚኒስቴር	21/04/06	41,254300.00	213,447,500.00	
3	የሰነዶችማረጋገጫናምዝገባጽ/ቤት	20/02/06	34,641,350.00	00.00	
4	የፍትህ ሚኒስቴር	15/01/06	55,374,313.00	124,324,230.00	
5	የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ	26/02/06	27,718,330.00	00.00	
6	የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል	20/12/05	12,450,700.00	00.00	
7	የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም	02/05/06	19,949,740.00		
8	የንግድ አሰራርና የሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን	16/11/05	9,653,330.00	00.00	
9	ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	23/01/06	12,291,780.00	00.00	
10	የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	14/02/06	21,530,100.00	70,400,000.00	
11	የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ	14/02/06	10,724,580.00	00.00	
12	የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ	16/01/06	18,940,000.00	00.00	
13	የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል	26/02/06	17,309,550	5,000,000.00	

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ በጀት/ሥራ ላይ የዋለ		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
14	የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	23/03/06	254,878,277.96	356,705796.88	611,584,074.64
15	የፍትህና የሕግ ሥርኣት ኢንስቲትዩት	20/2/06	7,22,459.50	-	7,22,459.50
16	ጠቅላይ ፍ/ቤት	23/12/05	25,379,400.00	24,511,430.00	49,890,830.00
17	ብሔራዊ መረጃ ደህንነት	04/2/06 የተጠቃለለ 02/4/06	175,561,240.00	3,773,271.00	179,334,511.00
18	የኢትዮጵያ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንስቲትዩት	ጳጉሜ 4/2005	58,790,066.28	-	58,790,066.28
19	የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ	14/4/06	16,950,810.00	-	16,950,810.00
20	ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት	22/01/06	260,569,245.41		260,569,245.41
21	የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ማስልጠኛ ማዕከል	05/03/06	11,463,340.00		11,463,340.00
22	የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን	11/2/06	21,530,511.10	-	21,530,511.10
23	የፌደራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ	17/03/06	9,888,550.00	,	9,888 ,550.00
24	ፌዴራል ፖሊስ ኮምሽን	26/3/2006	157,778,085.00	149,364,399.00	307,142,484.00
	ወንጀል መከላከል ዘርፍ		701,894,386.00		701,894,386.00
25	ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር	3/4/2006	35,358,070.00		35,358,070.00
26	የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት	25/3/06	43,392,087.00	98,010,872.00	141,402,959.00
27	ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት	15/5/06	22,063,488.42	10,372,312.5	32,435,800.92
28	ፌዴራል ፀረ ሙስና ኮምሽን	23/12/05	38,108,729.00		38,108,729.00
29	ኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት	20/12/05	18,885,265.00		18,885,265.00
30	የታለቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ምክር ቤት ጽ/ቤት	19/2/06	3,483,920.00		3,483,920.00
31	ፕራይቬይታይዜሽንና የመንግስት ልማት	16/12/05	18,476,460.00		18,476,460.00

ተ. ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈኑ በጀት/ሥራ ላይ የዋለ		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
	ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ				
32	የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህራት ኤጀንሲ	13/01/06	8,126,410.00		8,126,410.00
33	የኢትየጵያ አእምሯዊ ጽ/ቤት	29/11/05	8,092,063.00	5,300,000.00	13,392,063.00
34	ብሔራዊ አክርዲቴሽን ጽ/ቤት	5/03/2006	6,501450.00		6,501450.00
35	የሀገር መከላከያ ሚ/ር	26/02/2006	6,576,446,043.0		6,576,446,043.0
35	የውጭ ጉዳይ ሚ/ር	5/02/2006	854,539,968.09		854,539,968.09

በበጀት አመቱ ኦዲት ለማድረግ የታቀደው የኦዲት ሥራ በሙሉ ተከናውኗል፡፡